Contents

ሰላምታ ቅኝት 1
በጌቴ ሴማኒ 1
በመስቀል ተሰቅሎ (ዘማሪ ታደለ) 1
አባታችን (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ) 1
ሰላም ለማርያም (ዘማሪት ሶስና) 2
ዋኔን/ትዝታ ቅኝት 2
ርግብና ዋኔን (አቶ ታፈሰ) 2
አቤቱ ደግ ሰው አልቋልና (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 3
ኢትዮጵያ ሆይ ተነሽ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 3
የአብርሃም አምላክ 4
ኑ እንቅረብ (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ) 4
ገብረ መንፈስቅዱስ (አቶ ታፈሰ) 4
አየሁኝ በህልሜ (አቶ ታፈሰ) 5
ስለ ቸርነትህ/አንቺሆዬ ቅኝት 5
ስለ ቸርነትህ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 5
በህይወቴ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 5
መጸሙን ይጸማል 6
ለእኔስ ልዩ ነች (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 6
ጽኑ ክርስቲያኖች (ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ) 6
መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ 7
አባታችን (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ) 7
ወንድሜ ጠፍቶ(መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ) 8
ተው ስማኝ ሀገሬ(መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ) 8
ሰላም ለኪ (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ) 8
ከቶ አይቀርም ሞቱ (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ) 9
ስለ ሥነ-ስቅለት (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ) 9
አባ ግራኝ ሞተ (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ) 9
ስለ ሥነ ፍጥረት (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ) 10
ስለ ዳግም ምፅዓት (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ) 10
ስለ ልደት (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ) 11
ማን ይመራመር (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ) 11
ማን ይመራመር (አቶ አለሙ አጋ አጋ) 11
ስለ ምሥጢረ ሆሣዕና(መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ) 12
ዋኔን (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ) 12
ይበላሃለ (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ) 12
ዓለም ማረፊያ ናት(መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ) 13
አላየንም በሉ (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ) 13
የበገና አካላት (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ) 14
ዘማሪ አቶ ታፈሰ 14
በስመ አብ/እስመ አንተ(አቶ ታፈሰ) 14
ርግብና ዋኔን (አቶ ታፈሰ) 15
ማን ይመራመር(አቶ ታፈሰ) 15
አየሁኝ በህልሜ (አቶ ታፈሰ) 16
ገብረ መንፈስቅዱስ (አቶ ታፈሰ) 17
በስመ አብ/አባታችን(አቶ ታፈሰ) 17
ስለ ስነ ፍጥረት(አቶ ታፈሰ) 17
ስለ ልደት/ስደት(አቶ ታፈሰ) 18
ስለ ጥምቀት/ሆሳዕና(አቶ ታፈሰ) 18
ስለ ሥነ-ስቅለት(አቶ ታፈሰ) 19
ስለ ትንሳኤ/ዳግም ትንሳኤ(አቶ ታፈሰ) 20
ወዳጄ ወዳጄ(አቶ ታፈሰ) 20
ወዳጄ ወዳጄ(አቶ ታፈሰ) 20
ከደጇ ይፈልቃል (አቶ ታፈሰ) 21
ዘማሪት ሶስና 22
በስመ ልዑል (ዘማሪት ሶስና) 22
ዋኔን (ዘማሪት ሶስና) 23
በመስቀል ተሰቅሎ (ዘማሪት ሶስና) 23
ቸሩ መድኃኔዓለም (ዘማሪት ሶስና) 23
እመቤቴ(ዘማሪት ሶስና) 24
ሰላም ለማርያም (ዘማሪት ሶስና) 24
አድነኝ ከሞት (ዘማሪት ሶስና) 25
አስቀድሞ (ዘማሪት ሶስና) 25
ድንግል ስልሽ (ዘማሪት ሶስና) 26
ስቀለው ስቀለው (ዘማሪት ሶስና) 26
አሥር አውታር ባለው በበገና (ዘማሪት ሶስና) 26
አንገቴን አልሰብርም (ዘማሪት ሶስና) 27
ዘማሪት የትምወርቅ 27
ሰማይና ምድርን (የትምወርቅ በገና) 27
በገናዬን ላንሳ (የትምወርቅ በገና) 28
ልቤን ላንሳ (ዘማሪት የትምወርቅ) 28
እሰይ ጌታ ተወለደ(ዘማሪት የትምወርቅ) 28
ሰቀሉህ(ዘማሪት የትምወርቅ) 28
የሳምራዊው ደግነቱ(ዘማሪት የትምወርቅ) 29
ይህን ሁሉ ፍቅር(ዘማሪት የትምወርቅ) 29
በድንኪንህ(ዘማሪት የትምወርቅ) 29
በልዑል መጠጊያ(ዘማሪት የትምወርቅ) 29
እጆቿን ዘርግታ(ዘማሪት የትምወርቅ) 30
ከምንጭ ውሃ(ዘማሪት የትምወርቅ) 30
ስደት(ዘማሪት የትምወርቅ) 30
ዘማሪ ዘርፉ ደምሴ 31
ዓርብ እሮብ (ዘርፉ ደምሴ በገና) 31

መልካም ቤተልሄም (ዘርፉ ደምሴ በገና)....31
ጲላጦስም (ዘርፉ ደምሴ በገና)....31
ይበላሃላ (ዘርፉ ደምሴ በገና)....32
በጌቴ ሴማኔ (ዘርፉ ደምሴ በገና)....32
ኧረ ስማኝ ሀገሬ (ዘርፉ ደምሴ በገና)....33
ድንግልም (ዘርፉ ደምሴ በገና)....33
የእመቤታችን ምሥጋና (ዘርፉ ደምሴ በገና)....33
ስለ አዳም መፈጠር (ዘርፉ ደምሴ በገና)....34
እስመ አንተ (ዘርፉ ደምሴ በገና)....34
ዳግም ስትመጣ (ዘርፉ ደምሴ በገና)....34
ዐርብ የታረደውን (ዘርፉ ደምሴ በገና)....35
አዲስ ቤት ስትሠሩ (ዘርፉ ደምሴ በገና)....35
እንመን በስሙ (ዘርፉ ደምሴ በገና)....35
ተወለደልን (ዘርፉ ደምሴ በገና)....36
ማዘን ጨምሩበት (ዘርፉ ደምሴ በገና)....36
በአዳም በደል (ዘርፉ ደምሴ በገና)....36
የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት (ዘርፉ ደምሴ በገና)....37
አሐዱ ብሎ ቅዱስ (ዘርፉ ደምሴ በገና)....37
እፎይ ታገስከኝ (ዘርፉ ደምሴ በገና)....38
ሞት እንዴት ሰነበትክ (ዘርፉ ደምሴ በገና)....38
ኪዳነ ምህረት (ዘርፉ ደምሴ በገና)....38
ዘማሪ ይልማ ኃይሉ....39
በይስሐቅ ፈንታ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....39
የብርሃን እናት ነሽና (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....39
አዝላው ወረደች (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....39
ሥላሴን ከሰማይ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....40
ኃይልህ ሲገለጥ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....40
ውሃ አጠጪኝ አላት (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....41
አቤቱ ደግ ሰው (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....41
አልዓዛር ይነሳ(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....41
እግዚአብሔር ለዳዊት (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....42
ይበላሃላ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....42
ብስራተ ገብርኤል (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....42
አምላኬ አምላኬ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....43
በማዳኔ ቀን ጠራሁህ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....44
የእኛ ጌታ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....44
ማን ይመራመር (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....45
ዋ እኔን (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....45
አላየንም በሉ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....45
እስመ አንተ(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....45
በማዳኔ ቀን ጠራሁህ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....46
ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ....46
ውለታህ ብዙ (ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ)....46
ሰላም ተዋህዶ (ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ)....46
ጽኑ ክርስቲያኖች (ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ)....47
የቅዱሳን አምባ (ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ)....48
በምን በምን እንመስልሽ(ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ)....48
ሰዓሊለነ ማርያም (ሲሳይ ደምሴ በገና)....48
አምላከ ዳዊት(ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ)....49
ከመንፈስህ (ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ)....49
ዋ እኔን (ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ)....49
ዘማሪ ዲ.ታደለ....50
ኧረ ስማኝ ፈጣሪ (ዲ.ታደለ በገና)....50
ኧረ አንቺ ዓለም(ዲ.ታደለ በገና)....50
እግዚአብሔርም (ዲ.ታደለ በገና)....51
እማዬን አባዬን (ዲ.ታደለ በገና)....51
ሰቀሉህ (ዲ.ታደለ በገና)....51
አርባ ሌሊት መዓልት (ዲ.ታደለ በገና)....52
ድንግል (ዲ.ታደለ በገና)....52
እንደ ክቡር ዳዊት(ዲ.ታደለ በገና)....53
አርባ ሌሊት መዓልት(ዲ.ታደለ በገና)....53
በጌቴ ሴማኒ(ዲ.ታደለ በገና)....54
ሰው አፉ አላርፍ ብሎ(ዲ.ታደለ በገና)....54
አለ ወይ(ዘማሪ ታደለ)....54
አንተ አልቅሰህ(ዘማሪ ታደለ)....55
ችግር በርትቶ(ዘማሪ ታደለ)....55
ድሃ ነሽ ሐገሬ(ዘማሪ ታደለ)....56
ኧረ ምነው(ዘማሪ ታደለ)....56
ሞቴን አየሁት(ዘማሪ ታደለ)....56
ነይ ድንግል(ዘማሪ ታደለ)....57
ሸክም ከብዶ(ዘማሪ ታደለ)....57
የሴቱ አለባበስ(ዘማሪ ታደለ)....57
ሲገፉኝ(ዘማሪ ታደለ)....58
ዘማሪ አቤል ተስፋዬ....58
በኪሩቤል ላይ ተቀመጠ (አቤል ተስፋዬ በገና)....58
ስምሽ ጉልበት ሆኖኝ (አቤል ተስፋዬ በገና)....59
ሞትን በሞት ገድለህ (አቤል ተስፋዬ በገና)....59
መቸ ይረሳል (አቤል ተስፋዬ በገና)....59
የዛሬ ዘመን መከንን (አቤል ተስፋዬ በገና)....59
በደም ሊታጠብ ኃጢአቴ (አቤል ተስፋዬ በገና)....60
ሠላምህ ይብዛላት (አቤል ተስፋዬ በገና)....60
ስሜ ዳዊት (አቤል ተስፋዬ በገና)....60

በደላችንን የተውክልን (አቤል ተስፋዬ በገና)....61
ሥላሴ (አቤል ተስፋዬ በገና)....61
ጥሩልኝ ዳዊትን/አቤል ቁ2/....61
ሦስትነት ባለው /አቤል ተስፋዬ በገና ቁ2/....61
የቃል ማደሪያ ነሽ/አቤል ተስፋዬ በገና ቁ2/....62
በጸም /አቤል ተስፋዬ በገና ቁ2/....62
ስለኔ ለሞተ /አቤል ተስፋዬ በገና ቁ፪/....62
ደጁ ሲመላለስ/አቤል ተስፋዬ በገና ቁ፪/....62
በፈጣን ደመና/አቤል ተስፋዬ በገና ቁ፪/....63
እስከ መቼ ነው /አቤል ተስፋዬ በገና ቁ፪/....63
ቅዱስ/አቤል ተስፋዬ በገና ቁ፪/....63
በርበን ነኝ/አቤል ተስፋዬ በገና ቁ፪/....63
ሞት ሆይ/አቤል ተስፋዬ በገና ቁ፪/....64
ዘማሪ አለማየሁ ፈንታ....64
ከእንግዲህ አልደግምም /ዘማሪ አለማየሁ ፈንታ/....64
እናት አባትሽ /ዘማሪ አለማየሁ ፈንታ/....64
ዘማሪ ዘውዱ....65
ቅድመ ዓለም ንጉስ(ዘማሪ ዘውዱ)....65
ቤተ ስብሐት(ዘማሪ ዘውዱ)....65
ከሰገነት ወጥተህ(ዘማሪ ዘውዱ)....65
በዘሩ የነበረች(ዘማሪ ዘውዱ)....65
ሀዘን መከራ(ዘማሪ ዘውዱ)....66
የአባ ሕርያቆስ(ዘማሪ ዘውዱ)....66
ሰላም ልበልሽ (ዘማሪ ዘውዱ)....66
አስተርዮ ኮነ (ዘማሪ ዘውዱ)....66
የንስሐ መዝሙር....67
ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ....67
ኑ እንቅረብ (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)....67
ድንግል (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)....67
የዓለም መድኃኒት (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)....67
እወርዳለሁ ቆላ (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)....68
ይህ ቁርባን(ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)....68
አልፋና ኦሜጋ(ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)....68
ድንግል ሆይ ስለአንቺ(ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)....68
እኔስ በምግባሬ (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)....69
እንደቸርነትህ(ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)....69
ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ....69
ኖኅተ አንቲ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)....69
በባዕድ ሀገር (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)....69
ቢፈልግባትም (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)....69
ከካራን ስወጣ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)....70
ሕሙም ስለአዳነ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)....70
ልቦና የሚመስጥ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)....70
ያቺን የተስፋ ምድር (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)....70
ወንጌሉን ያመኑ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)....71
የመድኃኒት እናት (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)....71
በደለኞች ሳለን (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)....71
ዘማሪት ማርታ....71
ድንግል የዚያን ጊዜ(ዘማሪት ማርታ)....71
ከፈጣሪ በታች(ዘማሪት ማርታ)....72
ጥንታዊቷ (ዘማሪት ማርታ)....72
ይፍቱኝ አባቴ(ዘማሪት ማርታ)....72
ምስጋና ጀመረ(ዘማሪት ማርታ)....72
እንዲህ አለው ጴጥሮስ(ዘማሪት ማርታ)....73
ኦ ድንግል ደስ ይበልሽ(ዘማሪት ማርታ)....73
የሰው ልጅ በኃይልህ(ዘማሪት ማርታ)....73
ለእኛ ብሎ(ዘማሪት ማርታ)....73
አምላካችን (ዘማሪት ማርታ)....74
ነፍሴ ሆይ (ዘማሪት ማርታ)....74
ዘማሪ ይልማ ኃይሉ....74
ኪዳነ ምህረት እናቴ(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....74
ለመዳኑ ህይወት(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....74
ኦ ጌታ ሆይ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....75
ስራህ ብዙ(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....75
በብርሃን ጸዳል (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....75
የአብ ቃል አክብሮሽ(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....75
እስራኤል ሠለቸው (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....76
ተስፋ አለኝ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....76
ማነው እርሱ(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....76
ኢትዮጵያ ሆይ(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....77
ከወገኔ ጋራ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....77
በየገዳማቱ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....77
በርጠሜዎስ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....77
በእጸ መስቀሉ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....77
ደም ግባት የለውም (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....78
ነፍሴ ሆይ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....78
ክበር ተመስገን ጌታችን (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....78
ውለታው ብዙ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....79
እጅግ ብዙ ነው ቸርነቱ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....79
አቤቱ እንማልዳለን (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....79
የሚጠብቀኝ አይተኛም (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....80
ተወዳጅ ልጅሽን(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....80

ያድነናል ብለው (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....80
እግዚአብሔር ጽዮንን (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....81
ለዚህ ለኃጢአት ህግ(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 81
ከዳዊት አብራክ ዘርን (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 81
እንተ በህሊና (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....81
ከንቱ ነኝ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 82
ሕማሙን ልናገር (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....82
አቤቱ ማረን (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 83
እንዴት እንዲያጠፉት (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 83
ዘመኑ ሲደርስ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 83
የአባቶች አለቃ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 84
ጻድቃን ስለጌታ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 84
እግዚአብሔር ምስክር (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....84
ስምህ ለዘለአለም (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 85
አልፈርድም እኔ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 85
ማኔቴቄልፋሬስ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....85
ኢየሱስም አለ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....85
ኑ ተመልከቱልኝ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 86
ተዋህዶ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....86
የጴጥሮስን እንባ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 86
ያ ድሀ ተጣራ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....87
እውነት ስለሆነ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 87
በኃይልና ጥበብ (ይልማ ኃይሉ በገና) 87
ወንበዴ የነበርኩኝ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....87
የተወደደ ስምሽ ማርያም (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....88
ወዳንቺ የመጣው (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....88
ልዑለ ባህርይ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....88
ስራህ ብዙ(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 88
ኢትዮጵያ ሆይ ተነሽ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 89
ስለ ቸርነትህ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 89
ለእኔስ ልዩ ነች (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 89
በህይወቴ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ) 90
እግዚአብሔር ሆይ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)....90
የሰርግ መዝሙሮች 90
ሙሽራው ሙሽራ (የሠርግ)....90
የሀብከ ዮም (የሠርግ ይልማ ኃይሉ)....90
እጹብ ድንቅ ስራ 91
ትዌድሶ 91

ሰላምታ ቅኝት

በጌቴ ሴማኒ

ቅኝት - ሠላምታ
423 224 542 222 /2/
423 115 113 224 542 222
በጌቴ ሴማኒ በአትክልቱ ቦታ /2/
ለእኛ ሲል ጌታችን በዓለም ተንገላታ በዓለም ተንገላታ
አዳምና ሄዋን ባጠፉት ጥፋት /2/
በእኛም ነበረብን የዘላለም ሞት የዘላለም ሞት
መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ /2/
ይገርፉት ነበረ ሁሉም በየተራ ሁሉም በየተራ
ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ /2/
እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ ልጇ ሲንገላታ
በአምላክነቱ ሳይፈርድባቸው /2/
እንዲህ ሲል ጸለየ አባት ሆይ ማራቸው አባት ሆይ ማራቸው
በረቂቅ ስልጣኑ ሁሉን የፈጠረ /2/
በሰዎች ተገርፎ ሞተ ተቀበረ ሞተ ተቀበረ
ፍቅሩን የገለፀው ተወልዶ በሥጋ /2/
ኢየሱስ ጌታ ነው አልፋና ኦሜጋ አልፋና ኦሜጋ
ክርስቶስ

በመስቀል ተሰቅሎ

ቅኝት - ሠላምታ
423 224 /542 222 በበገና/(2X)
423 115 113 224 542 222

በመስቀል ተሰቅሎ እንዲያ እየቃተተ
ዓለምን ለማዳን የማይሞተው ሞተ
ከሞት ሊታደገን በመጣልን ፈጥኖ
መስቀል አሸከሙት ውለታው ይህ ሆኖ
መከራውን ሳስብ ሳስታውስ ቀኑን
ይቆስላል ይደማል ልቤ በሐዘን
መች ለራሱ ነበር ይህ ሁሉ መከራ
መስቀል ተሸክሞ የወጣው ተራራ
ሲያጎርሱት ሚናከስ ሰው ክፉ ነውና
እውሩን ቢያበራ ጎባጣን ቢያቀና
ጌታዬን ሰቀሉን አይሁድ ጨከኑና
ምነው አያሳዝን የአይሁድ ክፋት
የዝናቡን ጌታ ውሃ ሲነፍጉት
በተንኮል በታጢያት ቀሩ እንደሰከሩ
ሙታን ከመቃብር ተነስተው ሲያስተምሩ
እናታችን ሔዋን ወዮ በይ አልቅሺ
ያንቺን ሕመም ታሞ ከሞት ሊያድንሽ
የሀያዋን ጌታ ተሰቀለልሽ
አዬ ጉድ አዬ ጉድ አለም የኋላሽ
መድኃኒት ክርስቶስ በግፍ ሞተብሽ
በመስቀል ተሰቅሎ ስጋውን ሲቆርስ
በችንካር ተወግቶ ደሙንም ሲያፈስ
ዋለች በመከራ ድንግል ስታለቅስ
ሰውነትሽ ራደ ሐዘን ከበበሽ
ስቃይ መከራውም ዳግም ፀናብሽ
ተሰቅሎ ስታይው አንድ አምላክ ልጅሽ
ቢፈስም እንባዬ ሆኖ መንታ መንታ
መች ዋጋ ይሆናል ለአንዲቱ ጡብታ
ላለቀሽው ለቅሶ ድንግል የዛን ለታ
ባለቀሽው ለቅሶ በልጅሽ ህመም
ከሃጢያት ነፃሁኝ ዳንኩኝ ከገሃነም

አባታችን (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ)

ቅኝት - ሰላምታ
4245 313 15423 312 45
4245 313 15442 222

አባታችን በሰማያት ላይ ያለህ
ተለይቶ ይመስገን ክቡር ስምህ
መንግሥትህን የምንፈልጋት ከጥንቱ
በልጅነት ትምጣ ትሰጠን አቤቱ
ፈቃድህም ይህ እንዲደረግ ይሁን
በሰማይ ሞተን ተነስተን ከደይን
እንድንኖር ምስጋናህ ምግብ ሆኖን
ዛሬም በምድር በሥጋ ሕይወት ሳለን
ምግባችንን በየዕለቱ አውቀህ ስጠን
ይቅር በለን የበደልንህም ቢኖር
ወንድማችን የበደለንን ነገር
እንደአቅማችን እኛም እንድንል ይቅር
በገሃነም በክፉ ሁሉ መዓት
አትጣለን አድነን እንጂ ከሞት
ይህቺን መንግስት የማያገኛት ህልፈት
ጌትነትም ከሀሊነትም ክብርም
ናቸውና የአንተ ገንዘቦች ሁሉም
ለዓለም ወለዓለም ዓለም አሜን።
የተላከው ቅዱስ ገብርኤል ከጌታ
ሰላም ለኪ ብሎ በሰጠሽ ሰላምታ
እኔ ባሪያሽ ልብሴን ስታጠቅ ስፈታ
ሰላም ልልሽ ይገባኛል ጠዋት ማታ
ማርያም ሆይ እመቤቴ ሆይ ድንግል
በሥጋሽም በህሊናሽም ድንግል
የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ድንግል
እንዳለሽ ቅዱስ ገብርኤል ሰላም
ሰላም ለኪ እንደርሱ ሁሉ እኔም
የሌለብሽ የነፍስ የሥጋ መርገም
ብሩክ ነው የማሕፀንሽ ፍሬም
እንደቀድሞው ብሩክ አምላክ ነው ዛሬም
እግዚአብሔር ወልድ በመጣ ጊዜ ለካሳ
እንበለ ዘር እንደ ንብና እንደ ዓሣ
ከነፍስሽ ነፍስ ከስጋፍ ሥጋ ቢነሳ
ደስ ያለሽ ሆይ ጸጋን አግኝተሽ ከጌታ
ደስ ይበልሽ በማቀርብልሽ ሰላምታ
ለምኚልን ሳትሰለቺ ጠዋት ማታ
ውድ ልጅሽ እንዲያደርግልን ይቅርታ
ይቅር ብሎ ታጢአታችንን ሁሉን
እንዲያድነን በአንቺ ተማፅነን አለን
ለዓለም ወለዓለም ዓለም አሜን።

ሰላም ለማርያም (ዘማሪት ሶስና)

ቅኝት - ሠላምታ
23 1555 1555 11 31132
23 15 31 113 242 45
423-1 113-1 113 242

ሰላም ለማርያም የአምላክ እናት
የአቤል የዋህት የአዳም ህይወት
እመቤቴ በምልጃሽ መድኃኒቴ ነሽ
የአብ ቃል መቅረጫ ጽላቱ የሙሴ
የመንፈስ ቅዱስ ቤት እመቃል ሞገሴ
የርኅራኄ መዝገብ እህተ መላእክት
የጻድቃን ተስፋቸው ጽላተ መለኮት
ትናንት ተጨንቀን በጨለማው ዓለም
ዛሬ ብርሃን አየን በድንግል ማርያም
የኢያቄም እንቁ የሃና ንብረቷ
ሥጋ ነፍሴን እርጂያት ይቅርላት ቅጣቷ
በወንጌል ሰማነው ድንግል የአንቺን ዜና
አማላጅነትሽ ሲገለጽ በቃና
ከዳዊትም ሰማን ድንግል ስለአንቺ ክብር
ወትቀውም ንግሥት እያለ ሲዘምር
በላዔሰብ ከሞት ከሲኦል የዳነው
በምልጃሽ ነው እንጂ ሞች በጥርኝ ውሃ ነው
ሊውጡኝ ቢነሱ አጋንንት በሞሉ
ስምሽን ስጠራ ትቢያ ይሆናሉ
ጽዮን እመብርሃን ጽላተ ሥላሴ
የበረከት ካዝና ደመወዜና ዋሴ
ሲጨንቀኝ ሲጠበኝ ሲከፋኝ ኦሮዬ
ድንግል አንቺ እኮ ነሽ አጽናኝ አለኝታዬ
ስምሽን ስጠራ ሲታወክ ህይወቴ
አለሁልህ/ሽ በይኝ ድንግል እመቤቴ
ድንግል ሆይ አትርሺኝ የዘላለም ልብሴ
ምልጃሽ ያውጣኝ ከሞት ከከፋ ድምሳሴ
የቅዱሳን ካባ የቅዱሳን ኩታ
ጸጋ ሰማዕታት የድሆች አለኝታ
ሹመተ መሰፍንት ቅብዐ ነገሥታት
የሰሎሞን ዕውቀት የዳዊት መዝሙራት
ዓለም የዳነብሽ ከሞት ከሲኦል
ለእኔስ እናቴ ነሽ ማርያም ድንግል
አድኚኝ እናቴ ከሥጋ ፈተና
እኔማ ያለአንቺ አልችልም ልጸና
ሸክም የከበደኝ እንግልት ሆኛለሁ
ከእኔ እንዳትለይ አደራ እልሻለሁ
አደራ እልሻለሁ ከጎኔ አትራቂ
ወዳጅ ዘመድ የለኝ ያለአንቺ ጠባቂ
ተሰክቶልኝ ባየው ሀሳቤ ምኞቴ
ድንግል ያላንቺማ መች ይፀናል ቤቴ
ልጅሽ እንዳይነሳኝ መንግሥተ ሰማያት
ከታጡአት ጠብቆ እንዲያኖረኝ ገነት
አንቺ ንገሪልኝ ለዓለም መድኃኒት
ተስፋዬ ነሽና አትርሺኝ የኔ እናት

ዋኔን/ትዝታ ቅኝት

ርግብና ዋኔን (አቶ ታፈሰ)

ቅኝት- ዋኔን (ትዝታ)
4444 55-3 115 42
44452-5-3 115 42
33 11 33 42-3-1 42
33 11 33 42-2 42

ርግብና ዋኔን ዋኔን አብረው ዘመቱና ዋኔን
ርግብ ደህና ገባች ዋኔን ዋኔን ገደሉና ዋኔን
እስቲ በስመአብ ብዬ ዋኔን ልቀኝ ለእመቤቴ ዋኔን
ማርያም በመሆኗ ዋኔን ክብሬና ህይወቴ ዋኔን
ሰላም እልሻለሁ ዋኔን ጽላተ ጽዮን ዋኔን
ደጅ እጠናሻለሁ ዋኔን አምኜ አንቺን ዋኔን
አዛኝቷ እመቤት ዋኔን ኪዳነ ምህረት ዋኔን
አለሁልህ/ሽ/ ብለሽ ዋኔን አውጪኝ ከመአት ዋኔን
እስቲ ሁላችሁም ዋኔን ኪዳነ ምህረት በሉ ዋኔን
መድኃኒት ናትና ዋኔን ለሰው ልጆች ሁሉ ዋኔን
ሁሌ እጠራሻለሁ ዋኔን በቃል ኪዳንሽ ዋኔን
የምህረት አማላጅ ዋኔን ድንግል አንቺ ነሽ ዋኔን
የዓለም ፈርጥ አንቺ ነሽ ዋኔን ማርያም እመቤቴ ዋኔን
እመካብሻለሁ ዋኔን እስከ ጊዜ ሞቴ ዋኔን
ያንን የእሳት ባህር ዋኔን አሻግሪኝ ድንግል ዋኔን
እንዳወድቅ አደራ ዋኔን ከሲኦል ገደል ዋኔን
የነቢያት ትንቢት ዋኔን የሰማዕታት አክሊል ዋኔን
ያላንቺ ማን አለኝ ዋኔን እመቤቴ ድንግል ዋኔን
በአማላጅነትሽ ዋኔን እንኮራለን እኛ ዋኔን
የጽድቅ መሰላል ነሽ ዋኔን የተሰጠሽ ለኛ ዋኔን
ያዕቆብ በህልሙ ዋኔን ያያት መሰላል ዋኔን
የዓለም አስታራቂ ዋኔን አንቺ ነሽ ድንግል ዋኔን
ታማልደናለች ዋኔን እጆቿን ዘርግታ ዋኔን
ከቶ እረፍት የላትም ዋኔን ከጧት እስከ ማታ ዋኔን
ኪዳነ ምህረት ነሽ ዋኔን አንቺ የኛ ተስፋ ዋኔን
መርቆ የሰጠን ዋኔን ኦሜጋና አልፋ ዋኔን
የዓለም ሁሉ መቅረዝ ዋኔን መንበረ ሥላሴ ዋኔን
መድኃኒቴ እሷ ነች ዋኔን ለሥጋም ለነፍሴ ዋኔን
ሁሌ ላመስግናት ዋኔን ተፈታ ምላሴ ዋኔን
የምህረት ቃል ኪዳን ዋኔን የሰው ልጅ መዳኛ ዋኔን
እንድታማልደን ዋኔን የተሰጠች ለኛ ዋኔን
ምላሴ ተናገር ዋኔን የማርያምን ዝና ዋኔን
ለኛ መሰጠቷን ዋኔን ሳትፈጠር ገና ዋኔን
ታስባ ስትኖር ዋኔን በእግዚአብሔር ሕሊና ዋኔን
ተወልዳ አደገች ዋኔን ጊዜው ደረሰና ዋኔን
ዘመን የማይሽረው ዋኔን ስላላት ቃል ኪዳን ዋኔን
ታማልደናለች ዋኔን መድኃኒት በመሆን ዋኔን
ምን ቃላት ይገኛል ዋኔን እርሷን ማመስገኛ ዋኔን
እነ ሕርያቆስ ዋኔን ያልቻሉት እነኛ ዋኔን
ከዓይኗ እያዘነበች ዋኔን የእንባዋን ዘለላ ዋኔን
ወደ ግብፅ በረረች ዋኔን አንድ ልጇን አዝላ ዋኔን
ፅጌ ፀዐዳ ነች ዋኔን እመቤቴ ድንግል ዋኔን
ድረሺልን ሲሏት ዋኔን ከተፍ ነው የምትል ዋኔን

የፃድቃን እመቤት ዋኔን የኃጥኣን ተስፋ ዋኔን
ወዳንቺ እጮሀለሁ ዋኔን ሳዝንና ስከፋ ዋኔን
የበላኤ ሰብን ዋኔን ያዳንሽው ድንግል ዋኔን
ለእኔም አትንፈጊኝ ዋኔን ይህንን እድል ዋኔን
ስንቅ የለኝ ለነፍሴ ዋኔን እንዴት ልሆን ነው ዋኔን
ድንግል እመቤቴ ዋኔን መግቢኝ አንቺው ዋኔን
ጥላሽን ጣይብኝ ዋኔን ኪዳነ ምህረት ዋኔን
ስጨነቅ ስጠበብ ዋኔን ስጋለጥ ያን ዕለት ዋኔን
ድንግል መድኃኒት ነሽ ዋኔን ለሰው ልጆች ተስፋ ዋኔን
ከጐኔ ቁሚልኝ ዋኔን ሳዝንና ስከፋ ዋኔን
የዓለም መድኃኒት ነሽ ዋኔን ማርያም እመቤቴ ዋኔን
በረድኤት ግቢልኝ ዋኔን ነይልኝ ከቤቴ ዋኔን
አደራሽን ማርያም ዋኔን ኪዳነ ምህረት ዋኔን
ፀጋሽን አልብሽኝ ዋኔን ኋላ ስራቆት ዋኔን
ዕርቃኔን መሆኔን ዋኔን አውቀዋለሁና ዋኔን
አልብሽኝ ፀጋሽን ዋኔን በኢያቄም በሃና ዋኔን
እስቲ ሁላችሁም ዋኔን ኪዳነ ምህረት በሉ ዋኔን
መድኃኒት ናትና ዋኔን ለሰው ልጆች ሁሉ ዋኔን
አፍሮ አይመለስም ዋኔን የቆመ ከደጇ ዋኔን
እመቤቴ ማርያም ዋኔን የጭንቅ አማላጇ ዋኔን
የአዳም መድኃኒቱ ዋኔን አንቺ ነሽ ድንግል ዋኔን
በኢያቄም በሃና ዋኔን አውጪኝ ከሲኦል ዋኔን
አንቺ የኤዶም ገነት ዋኔን የሰው ልጆች ተስፋ ዋኔን
መድኃኒት ነሽና ዋኔን አዝኖ ለተከፋ ዋኔን
የዓለምን መድኃኒት ዋኔን በጀርባሽ አዝለሽ ዋኔን
ኧረ ልምን ይሆን ዋኔን ቁራሽ የለመንሽ ዋኔን
ፍግም ብዬ ልስገድ ዋኔን ለእመቤቴ ድንግል ዋኔን
እርሷ በመሆኗ ዋኔን የሰው ልጆች እድል ዋኔን

አቤቱ ደግ ሰው አልቋልና (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት - ዋኔን
52-1 115 1113 4222 42
52-1 115 1113 4223 23
35-2-4453 1113 4222 42(2x)

35-2-4453 1113 4222 42(በበገና)

አቤቱ ደግ ሰው አልቋልና
ከምድርም ፍቅር ጠፍቷልና
እንደ ቸርነትህ አድነን
በደላችንንም አትቁጠር
በበገና...
የረድኤት አምላክ ፍቅር ስጠን
እንደ አህዛቡ አታድርገን
ክርስቲያን ነንና እንዋደድ
እባክህ አንውጣ ካንተ መንገድ
በበገና...
አቤቱ ንፁህ ልብ ፍጠርልን
ሰውን የሚያስወድድ ካለ እንከን
አንደበታችንም እንዲናገር
ስለ ሰላም ቋንቋ ስለ ፍቅር
አዝ.....
በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚመራ 2
ትሩፋት ደግነት የሚሠራ
አንደበቱ ሁሉ የታረመ
ለቃለ ወንጌሉ የደከመ
በበገና...
ምግባርና እውነት የተሰጠው
እባክህን ስጠን ሁነኛ ሰው
አንተን የሚመስል በሕይወቱ
ፍቅርና ትህትና የግል ሀብቱ
አዝ.....
የማስመሰል ፍቅር እየበዛ
ሰው ረክሷልና እንደዋዛ
ፍፁም መዋደድን ስጠንና
አዲስ ሰው እንሁን እንደገና
በበገና...
ደገኛ ሰው ማግኘት አስቸግሯል
እስከ መጨረሻ ማን ይፀናል
ምግባሩ ትክክል እውነተኛ
ልቡ የሚፀየፍ ከዳተኛ
አዝ.....

ኢትዮጵያ ሆይ ተነሽ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት - ዋኔን
213 24552 42421-11553 23
213 24552 42342 22-2 42
213 24552 42421-11553 23
213 24552 42342 22-2 42

213 24552 42342 22-2 42(በበገና)

15-113 42 42421-11553 23
15-113 42 42452-22-2 42
15-113 42 42421-11553 23
15-113 42 42452-22-2 42

ኢትዮጵያ ሆይ ተነሽ ክብርንም ልበሽ
በአዲስ ምሥጋና ይመላ ልብሽ
የተወደደ ነው በእግዚአብሔር ህዝብሽ/2/
በበገና...
ንብረቱ ጠፊ ነው ከንቱ የማይረባ
በግፍና ቅሚያ በአመፅ ሲገነባ
ሲሳይሽ ብዙ ነው ከአምላክ የተሰጠሽ
በረከት ለማግኘት መሥራት ነው ጠንክረሽ
አዝ...
የአህዛብ ብልጽግና አያስቀናሽ ፍፁም
ኃላፊ ጠፊ ነው ምኞቱም ዓለሙም
ደመና ነውና ይበናል በቅጽበት
በግፍ የተገኘ የተከማቸ ሀብት
አዝ...
ይልቅ በቅንነት በሰላም ለሰራ
ሲሳዩ ብዙ ነው ክብሩም አያባራ
ጉቦና ፍትህን ማጣመም እንዳንለምድ
ከወንጌሉ ጋራ አለብን መዛመድ

አዝ...
እግዚአብሔር ያለው ሰው በእርሱ የታመነ
ከግፍ ሥራ ሕመም አካላቱ ዳነ
ክርስቲያነኝ ብሎ ጉቦ የሚበላ
የሚያቃጥል እሳት ያገኘዋል ኋላ
አዝ...
በመታመን ፀጋ ይጠራ ስማችን
እውነተኛ እንሁን ለውድ ሀገራችን
የራሱን ሳይሻ ለሀገር የሚያስብ ሰው
በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ነው
አዝ...

የአብርሃም አምላክ

ቅኝት- ዋኔን (ትዝታ)
5-2-2-234-2 51-53545 5 /2x/
25231-513-1 24-2-5232 2 /2x/

የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም ቤዛ/2/
ወገኖቹን ሁሉ በራሱ ደም ገዛ/2/
የሐሰት ምስክር አቁመው ከሰሱት/2/
በሞት እንዲቀጣ ሁሉም ፈረዱበት/2/
ጲላጦስ ገረፈው በሰንሰለት አስሮ/2/
ከሮማዊው መንግሥት እንዲኖር ተባብሮ/2/
ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ/2/
እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ/2/
በብርሃን ዙፋን ላይ የቆሙት እግሮቹ/2/
በችንካር ላይ ቆሙ ምንም ሳይሰለቹ/2/
የብርሃን አክሊልን ለሰማዕት ያደለ/2/
የእሾህ አክሊል ደፍቶ ቀራንዮ ዋለ/2/

ኑ እንቅረብ (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)

ቅኝት - ዋኔን
1-123-4 3-42 355 5
1-123-4 3-42 222 2
211 513-2 2 211 513 3 3
211 513 3-42 222 2

211 513 3-42 222 2(በበገና)

1-1-1-321 1 4-4-4 515 5
3-3-3 242-4 234222 2
ኑ እንቅረብ መጠራት ሳይመጣ /2/
ሥጋውን እንብላ ደሙንም እንጠጣ
በበገና...
የቀራንዮ በግ የአምላክ ሥጋው
ተሰውቶልናል እንመገበው
እድፋን ኃጢአታችንን በንስሓ አንፅተን
እንቀበል አምነን በልጅነታችን
መቅረብ ወደ ጌታ በእምነት የሚገባው
በስተርጅና አይደለም በወጣትነት ነው
አዝ...
ጨረቃና ፀሐይ ደም የለበሱለት
ከዋክብት ከሰማይ የተነጠፉለት
ይኸው ተፈተተ እሳተ መለኮት
አዝ...
ቅድስት እናታችን ቤተክርስቲያን
ትጋብዘናለች ሥጋና ደሙን
የአማኑኤል ሥጋ ይኸው ተዘጋጀ
ከግብዣው ተጠራን አዋጁም ታወጀ
አዝ...
መጥቁ ተደወለ እንቅረብ በእልልታ
በኋላ አይረባንም ዋይታና ጫጫታ
ይህችን እድል ፈጥነን እንጠቀምባት
ዓለምን አልያዝንም ብዙ ልንቆይባት
አዝ...
ካሁኑ ቅረቡ ታውጇል አዋጁ
የይለፍ ደብዳቤ ስንቅን አዘጋጁ
ይህ ዓለም ጠፊ ነው በሀብት አትመኩ
ብሏል አምላካችን ተስፋችሁን እንኩ
አዝ...

ገብረ መንፈስቅዱስ (አቶ ታፈሰ)

ቅኝት-ዋኔን
231111 11315
113 115 113 242

ገብረ መንፈስቅዱስ አቦዬ ጻድቁ
ኧረ እንዴት ነህ አባቴ ኧረ እንዴት ነህ መድኃኒቴ
ገደል እንደ አከርማ የሚሰነጥቁ (ኧረ ...)
ገብረ መንፈስቅዱስ ተክለሃይማኖት (ኧረ ...)
ታላቅ ክብር ያገኙ በክርስቶስ ፊት (ኧረ ...)
ለጌታቸው ታዛዥ ለዓለም አማላጅ (ኧረ ...)
በፈጣሪያቸው ዘንድ በሥላሴ ደጅ (ኧረ ...)
ጻድቃን ሰማዕታት ደናግል በሙሉ (ኧረ ...)
ሌት ከቀን ሳያርፉ ሰው ያማልዳሉ (ኧረ ..)
ድንጋይ ተንተርሰው ዳዋ እየጣሱ (ኧረ...)
በጸሎት ተጠምደው ጤዛ እየላሱ (ኧረ ...)
ገብረ መንፈስ ቅዱስ አቡነ ተክልዬ (ኧረ...)
በእናንተ ጋሻነት ልኑር ተከልዬ (ኧረ...)
የዘልዳው ኮከብ ቅዱስ ጊዮርጊስ (ኧረ...)
ተጨንቀው ሲጠሩህ ፈጥነህ የምትደርስ (ኧረ...)
አቡነ አረጋዊ ታላቁ አባት (ኧረ ...)
ጸጋ ክብር ያገኙ በሥላሴ ፊት (ኧረ ...)
ሙሽራው ሰማዕት ገብረ ክርስቶስ (ኧረ...)
መንኖ የሄደ ጽድቅ ለመልበስ (ኧረ...)
ደራጐንን በጦር ወግቶ የገደለ (ኧረ...)
ፈረሰኛው ጊዮርጊስ የልዳው ኮከብ ነው(ኧረ...)
ገብረ መንፈስቅዱስ ታላቁ መናኝ (ኧረ...)
ከዚህ ዓለም መቅሰፍት ፈጥነው ያድኑኝ (ኧረ...)
ፃድቃን ሰማዕታት አባቶች ሁላችሁ (ኧረ...)
ኢትዮጵያን ጠብቋት አደራ ተግታችሁ(ኧረ...)

አየሁኝ በህልሜ (አቶ ታፈሰ)

ቅኝት-ዋኔን
33 22 3-5 33 22 3-1
544445 1111 33 4222 22

አየሁኝ በህልሜ /2/
ሞት የተባለውን እዳ ተሸክሜ
ሰማሁኝ በዝና /2/
ቀጠሮ አክባሪ ነው ሞት አይረሳም እና ሞት አይቀርም እና
ሞት ይቅር ይላሉ ሞት ቢቀር አልወድም
አፈሩም ድንጋዩም ከሰው ፊት አይከብድም
አጠረ ቁመቴ ወዳጆቼን ባይ
እያደሩ ማነስ ለካ እንዲህ ነው ወይ
እኔ አልገዛም ሱሪ ይቅርብኝ ለራሴ
አፈር ስለሆነ የዘላለም ልብሴ
ቤት አልሠራም ይቅር ጣራና ግድግዳ
መቃብር ነውና የኔ ሳሎን ጓዳ
እባክህ አምላኬ ስማ ጸሎቴን
በእንባ ዓለም እጄ የምበላውን
እራሴን አንገቴ አልችለው ብለህ
ሁል ጊዜ ከሰው ፊት ትጥለኛለህ
አየሁኝ በህልሜ አየሁኝ በህልሜ
ሞት የተባለውን እዳ ተሸክሜ
ሰማሁኝ በዝና ሰማሁኝ በዝና
ቀጠሮ አክባሪ ነው ሞት አይቀርም እና ሞት አይረሳም እና
አይጣል አይጣል እያልን ስንለምነው
ሳናስበው ድንገት ጣለብን ምነው
ግድግዳው ቢረዝም ምንባጡ ቢያምር
የምድር ቤት ነውና መፍረሱም አይቀር
እንግዳው ሞት መጣ ኧረ ወየው ወየው
ለእግሩ ውሃ አሙቄ በርዤ ሳልቆየው
የሞትን ማዕረጉን ሁላችሁ እወቁ
ከእርሱ ቤት ይገኛል ብሩም ሆነ ወርቁ
ይኸው የዘራልን በየቀኑ ሰው
አንድም አልበቀለ የታል ቡቃያው
ከአቤል ጀምሮ ነበር የታመነ
አሁን ግን ስናየው ሞት ቀጣፊ ሆነ
አይቼ መጣሁኝ ዛሬስ በእሁድ
ሰው እንደአዝመራ በግፍ ሲታጨድ
በከንቱ ያሙታል እንዲሁ በሐሰት
ሰው በልቶ ጨረሰ እያሉ መሬት
ከምድር እስከ ሰማይ ሰው ቢያስብ ሁልጊዜ
ከሰው አልተለየም ሞትና ትካዜ
ደስታና ሐዘን ጐን ለጐን ሲሄዱ
ይጐራበቱናል ከሁለቱ አንዱ
ሁሉ በሸተኛ ሁሉ ራሴን ባይ
በቤታችን ደህና መጥፋቱ ነው ወይ
እሱን ሞት ሲጠራው በሩቁ ሰምቼ
እኔም ወይ አላልኩም ለራሴ ፈርቼ
ሰው ሁሉ በርስቱ ይጨርሳል ሀብቱን
የኋላ የኋላ ላያጣው መሬቱን
ቀኑን ባሸንፈው ሌት መቶ ታገለኝ
በቶሎ ሞት ናና እባክህ ገላግለኝ
እድሜዬ ዘልዛላ ነው አያልቅ በቶሎ
ከቶ መሞት ላይቀር እንደው ውልውሎ
ከፋኝ ሞቴን ስጠኝ ለማይቀረው እዳ
ደግሞ እንደ ሥጋዬ ነፍሴ እንዳትጐዳ
ወለም ዘለም እያልኩ አለቀ እድሜዬ
ሞት መምጣቱ ላይቀር ወየው መከራዬ

ስለ ቸርነትህ/አንቺሆዬ ቅኝት

ስለ ቸርነትህ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት - ስለቸርነትህ
231542-3 45-13-42 2 /2x/አዝማች

231542-3 45-13-42 2 (በበገና)

231542-3 231515 5 /ዘማች/

ስለ ቸርነትህ ጌታ ተመስገን
ስለ ፍፁም ፍቅርህ አምላክ ተመስገን
በበገና...
ማነው የገመተ ከዛሬ መድረስን
ልብሱ ሳይነካ በእሳቱ ወላፈን
ባህሩን አሻግሮ ማዕበል አቁሞ
እርሱ ያውቅልናል ለመጪው ቀን ደግሞ
አዝ...
ሃሌ ሃሌ ሉያ መስዋዕት እናቅርብ
ጌታ ይፈልጋል የተሰበረ ልብ
ክርስቶስ ከሌለው ፍቅር ላይኖረው
ሰላም ሰላም ይላል ፍጥረታዊው ሰው
ሰላም ሰላም ይላል የዘመኑ ሰው
አዝ...
የኢየሱስ ነገር ለሚጠፉት ሁሉ
የመስቀሉ ነገር ለሚጠፉት ሁሉ
ሞኝነት መስሏቸው ክህደት ተሞሉ
የስንፍና አመል እያናወዛቸው
መጸም መጸለዩ ይጎዳናል ብለው
አምላክን ቢክዱ ፍቅርን ነፈጋቸው
አዝ...

በህይወቴ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት - ስለቸርነትህ
23-42 2 14-15 5
15-11231 1 2223 42 2

2223 42 2 14-15-42 2
2223 42 2 2315-11 231 1

በህይወቴ በዘመኔ ደስ የሚለኝ ለኔ በወንጌል ማመኔ
ሕይወቴ ሲመራ ጌታ በቃልህ
ጣፋጭ ይሆን ነበር ሲያድሰኝ ፍቅርህ
ያንተ ጸጋ ጌታ ስለበዛልኝ
ጨለማው ተገፎ ብርሃንህ መራኝ

ወዴት እሄዳለሁ የእጅህ ጥበብ ሆኜ
ፍቅርህ እያደሰኝ ሞተህልኝ ድኜ
ምን አይነት መውደድ ነው ለኔ አንተ ያለህ
ምን ይከፈለዋል ለፍፁሙ ፍቅርህ
ምን አይነት መውደድ ነው አንተ ለኔ ያለህ
ምን ይከፈለዋል ለፍፁሙ ፍቅርህ
ደጅህ ላይ ተጥዬ ደጅህ ላይ ልሙት
ቃልህን ልጠብቅ በፍፁም ፍርሃት

መጸሙን ይጾማል

ቅኝት- ስለቸርነትህ
15-1515 151515 151551 42-መጸሙን ይጾማል
(15-1515 151515 52-45-11 42-ይደርሳል ሰዓቱ)
23-1551 1123-42 2
23 2325-4 13 544442
45131542/በበገና/

መጸሙን ይጾማል ሁሉም የአዳም ልጅ ሁሉም የአዳም ልጅ
የጊዜውን መድረስ የሚያውቅ የለም እንጂ
የሚያውቅ የለም እንጂ የሚያውቅ የለም እንጂ
ይደርሳል ሰዓቱ ሳስብ ሌላ ሌላ ሳስብ ሌላ ሌላ
የተሰቀለውን ሥጋውን ሳልበላ
ሥጋውን ሳልበላ ሥጋውን ሳልበላ
ድጓ ጾመ ድጓ ተሰቅሎ ከቤቴ ተሰቅሎ ከቤቴ
አወይ አለማወቅ ሳልማር መቅረቴ
ሳልማር መቅረቴ ሳልማር መቅረቴ
ደግሜ ደግሜ ቀረኝ አሌፋቱ ቀረኝ አሌፋቱ
አድኅነኒ ሣልል አትጥራኝ በከንቱ
አትጥራኝ በከንቱ አትጥራኝ በከንቱ
እኔስ እሄዳለሁ አጣቢ ፍለጋ አጣቢ ፍለጋ
በጣም አድፎብኛል የለበስኩት ሥጋ
የለበስኩት ሥጋ የለበስኩት ሥጋ
ዳዊት እንዴት ይሙት ሳልተዋወቀው ሳልተዋወቀው
የሚመጣውን ሁሉ በገና የሚያውቀው
በገና የሚያውቀው በገና የሚያውቀው
ዐርብ ረቡን ገደፈኩ በሥጋ በአዋዜ በሥጋ በአዋዜ
እንዲህ ለሚደርሰው ለማይቆየው ጊዜ
ለማይቆየው ጊዜ ለማይቆየው ጊዜ
ከሥጋው ሳልበላ ተጠይፌ ደሙን ተጠይፌ ደሙን
ማን ይችለው ይሆን የላይ ቤት ረሃቡን
የላይ ቤት ረሃቡን የላይ ቤት ረሃቡን
ከንብረቴ ሁሉ አልጋዬ ነው ሀብቴ አልጋዬ ነው ሀብቴ
አድርሶኝ ይመጣል ከዘላለም ቤቴ
ከዘላለም ቤቴ ከዘላለም ቤቴ
ብልህ ነው ስትሉኝ እዩት ሞኝነቴን እዩት ሞኝነቴን
በራሴ ላይ ሆኖ አላውቀውም ሞቴን
አላውቀውም ሞቴን አላውቀውም ሞቴን
መማሩንስ ዳዊት ተምሬ ነበረ ተምሬ ነበረ
ከአምላኪየ ሳልደርስ ልቤ ሰንፎ ቀረ
ልቤ ሰንፎ ቀረ ልቤ ሰንፎ ቀረ
እንኳን ነአኩተከ በስመ አብም ቸገረኝ በስመ አብም ቸገረኝ
ዳዊት እንዴት ተማርክ እባክህ ንገረኝ
እባክህ ንገረኝ እባክህ ንገረኝ

ለእኔስ ልዩ ነች (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት - ስለቸርነትህ
233-42 2-42423-15-13 31-31 (2x)
3-42 2-42423-15-13 31-31
233-42 2-42423-15-13 31-31
233-42233-42 2-42 (2x)

233-42 233-42 2-42(በበገና)

233-42 2-42423-15-13 31-31 (3x)
233-42233-42 2-42

ለእኔስ ልዩ ነች ድንግል ማርያም
ለእኔስ ልዩ ነች እመብርሃን
ፈልጌ /2/ ላንቺ ምሥጋና አላገኘሁም /2/
በበገና...
ልቤ ሲያበቅል የኃጢአት አረም
ውስጤ ሲሸፍት አልተወችኝም
ከቤተ መቅደስ እጇን ዘርግታ
ትጠራኛለች የእኔ መከታ
አዝ...
የሆዴን ሀዘን የልቤን ምሥጢር
እነግርሻለሁ አንድም ሳይቀር
የምትሸሸጊ የሕዝብን ኃጢአት
ለእኔስ ልዩ ነሽ ድንግል አዛኝት
አዝ...
ጣዕሙ ልዩ ነው ከእርሷ ጋር መኖር
ድንግልን ይዤ መቼም አላፍር
ወደ ጽድቅ ህይወት ትወስደኛለች
ድንግል ማርያም ለእኔ እናቴኮ ነች
አዝ...
በሀዘን ስሰበር ማንን እጠራለሁ
ውስጤ ሲደማ ለማን እነግራለሁ
ከኃጢአት እድፍ ንፁህ መሆኛዬ
አንቺ ነሽ ድንግል የኔስ መጽናኛዬ
አዝ...
የኃጢአት ቁስል ያለአንቺ አይጠግም
ልጅሽ ሳይፈቅድ በህይወት አልኖርም
ከልጅሽ ሌላ መድህን የለኝም
ከጸሎት በቀር ፍፁም አልድንም
አዝ...

ጽኑ ክርስቲያኖች (ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ)

ቅኝት - ስለቸርነትህ
423115-13 42 422-22-2 42
423115-13 42 423 33-3231
545-13 42 45 422-22-2 42

545-13 42 45 422-22-2 42(በበገና)

423115-13 42 422-22-2 42
423115-13 42 423-33-3231
545-13 42 45 423-33-3231
545-13 42 45 422-22-2 42

ጽኑ ክርስቲያኖች ልባችን አይውደቅ
የእግዚአብሔርን እቃ ጦሩን እንታጠቅ/2/
ማዕበሉን አይቶ ልባችን አይፍራ
ታማኙ ጌታችን አለ ከእኛ ጋራ /2/
በበገና...

ሰማዕታት ልጆቿ የዓለምን ጣዕም ንቀው
ያላውያንን ዛቻ ፈተናውን አልፈው
ረሃቡን ስደቱን መከራን ታግሰው
ለዚህ አድርሰዋታል ተዋሕዶን ጠብቀው
ክህደቱ ቅሰጣው ኑፋቄው ቢነዛ
ሰይፍ ስለቱ ቢያቈጭ ፉከራው ቢበዛ
በድንግል ቃል ኪዳን መሠረቷ ጠብቋል
በቅዱሳን ጸሎት ቅጽሯ በእሳት ታጥሯል
አዝ...

ጥንተ ጠላታችን ፈተና እያስነሳ
ዙሪያችንን ቢከብብ ተርቦ እያገሳ
መከራን ቢያበዛ ስደት ቢያደርስብን
እስከ ሞት የሚያደርስ ስቃይ ቢያበዛብን
ዓለም ላቆመችው ለጣኦት አንሰግድም
በመከራው ጽናት ሀይማኖት አንክድም
ከሚነደው እሳት አምላክ ያድነናል
ባያድነን እንኳን እሳቱን መርጠናል
አዝ...

እንደ ግያዝ አንሁን ታውሮ አይናችን
በእሳት ሰረገሎች ተከቢል ዙሪያችን
ሰይፍን የሚያነሱ በሰይፍ ይወድቃሉ
ከእኛ ጋራ ያሉት ከእነርሱ ይበልጣሉ።
የጠሉህን ውደድ በሚል ሀያው ቃሉ
ሲያሳድዱህ ጸልይ በሚል ክቡር ቃሉ
በመንፈሳዊው ፍቅር ይጠንክር ልባችን
ይህን ነው ያዘዘን ቅዱስ አምላካችን
አዝ...

ነቅተን ከታጠቅን የጽድቅን ጥሩር
በትጋት ከቆምን በእምነት በፍቅር
በጾምና ጸሎት ስግደት ምጽዋት
በንስሃ ጸድተን ከጸናን በእውነት
በሥጋ ወደሙ በጸጋው ከታተምን
በህይወትም በሞት ከእርሱ ጋር ሀያው ነን
በወደደን በእርሱ ከሁሉ እንበልጣለን
በወደደን በእርሱ አሸናፊዎች ነን
አዝ...

ንፋሱ ማዕበሉ የማይነቀንቀው
መሰረቷ ጽኑ ቅጽሯም ጠንካራ ነው
የገሀነም ደጆች አይችሏትምና
ጸንታ ትጓዛለች ተዋሕዶ ገና
ጽኑ ክርስቲያኖች ልባችን አይውደቅ
የእግዚአብሔርን እቃ ጦሩን እንታጠቅ/2/
ማዕበሉን አይቶ ልባችን አይፍራ
ታማኙ ጌታችን አለ ከእኛ ጋራ /2/
አዝ...

መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ

አባታችን (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ)

ቅኝት - ሰላምታ
4245 313 15423 312 45
4245 313 15442 222

አባታችን በሰማያት ላይ ያለህ
ተለይቶ ይመስገን ክቡር ስምህ
መንግሥትህን የምንፈልጋት ከጥንቱ
በልጅነት ትምጣ ትሰጠን አቤቱ
ፈቃድህም ይህ እንዲደረግ ይሁን
በሰማይ ሞተን ተነስተን ከደይን
እንድንኖር ምስጋናህ ምግብ ሆኖን
ዛሬም በምድር በሥጋ ሕይወት ሳለን
ምግባችንን በየዕለቱ አውቀህ ስጠን
ይቅር በለን የበደልንህም ቢኖር
ወንድማችን የበደለንን ነገር
እንደአቅማችን እኛም እንድንል ይቅር
በገሃነም በክፉ ሁሉ መዓት
አትጣለን አድነን እንጂ ከሞት
ይህቺን መንግስት የማያገኛት ሀልፈት
ጌትነትም ከሀሊነትም ክብርም
ናቸውና የአንተ ገንዘቦች ሁሉም
ለዓለም ወለዓለም ዓለም አሜን።
የተላከው ቅዱስ ገብርኤል ከጌታ
ሰላም ለኪ ብሎ በሰጠሽ ሰላምታ
እኔ ባሪያሽ ልብሴን ስታጠቅ ስፈታ
ሰላም ልልሽ ይገባኛል ጠዋት ማታ
ማርያም ሆይ እመቤቴ ሆይ ድንግል
በሥጋሽም በሀሊናሽም ድንግል
የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ድንግል
እንዳለሽ ቅዱስ ገብርኤል ሰላም
ሰላም ለኪ እንደርሱ ሁሉ እኔም
የሌለብሽ የነፍስ የሥጋ መርገም
ብሩክ ነው የማሕፀንሽ ፍሬም
እንደቀድሞው ብሩክ አምላክ ነው ዛሬም
እግዚአብሔር ወልድ በመጣ ጊዜ ለካሳ
እንበለ ዘር እንደ ንብና እንደ ዓሣ
ከነፍስሽ ነፍስ ከስጋፍ ሥጋ ቢነሳ
ደስ ያለሽ ሆይ ጸጋን አግኝተሽ ከጌታ
ደስ ይበልሽ በማቀርብልሽ ሰላምታ
ለምኚልን ሳትሰለቺ ጠዋት ማታ
ውድ ልጅሽ እንዲያደርግልን ይቅርታ
ይቅር ብሎ ታጢአታችንን ሁሉን
እንዲያድነን በአንቺ ተማፅነን አለን
ለዓለም ወለዓለም ዓለም አሜን።

ወንድሜ ጠፍቶ(መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ)

ቅኝት- ሰላምታ

ወንድሜ ጠፍቶኝ ስሄድ ነብር አግኝቶኝ ከመንገድ
አልተመለስኩም ወዲያው ሄድኩኝ እኔን ይብላኝ እያልኩኝ/2/
የቀድሞ ዘመን ስህተት በፆም ቀን አሳ መብላት
ያሁን ዘመን ሰው አያውቅ መላ በፆም ሽሮ ነው የሚበላ/2/
የኛ መድኃኒት አይነቶች በብዙ አሉ ቅመሞች
ነገር ግን እኔ ሳስበው ስራስሩ መልካም ነው/2/
ያባቶቻችን ውሃ ዋና ላይ ላዩን ነበር በጤና
የዛሬ ልጆች ይበልጣሉ ውስጥ ለውስጥም ይሄዳሉ/2/
ኮሶ ተጣብቶኝ ትላንትና መድኃኒት ስሻ ዋልኩና
ድንገት ሰማሁኝ አንድ ዜና የወዲያ ሰዎች ህግ ደንብ አይከለክልም ምግብ
የኛ ስርዓቱ ከባድ እንዲያው በባዶ ሆድ/2/
የጌታችንን ፀባይ ያለኔ የሚያውቅ አለ ወይ
ማታ ለግብር መልካም ሰው ቀን ሲቆጣ ክፉ ሰው/2/
አያሳስትም ሰዓት ቀጠሮ ያከብራል ሞት
ሽማግሌ አይል ህፃን ሞት ጠያቂ ነው ሁሉን
አሁን ይመጣል በእውነት ሙት ብሎ አይቀርም ሞት/2/
እሁድ ቅዳሜ ቢሆን እበላ ነበር ምሳዬን
እንዲህ በፆም ቀን የምዞረው ለጊዜ ማድረሻ ነው/2/
ትንሽ ቤት ሰራሁ እንደአቅመኛ ሁለት ሶስት ሰው የምታስተኛ
አላስገባ አለች እርሷው ጠባ ሰው በሰው ላይ እየገባ/2/
ከታች ጉርጓዱ የጠለቀ ከላይ ጉበኑን የጠበቀ
እንዲህም አድርገው ቢሰሩት መፍረሱ አይቀርም ቤት/2/
የዛሬ ዘመን ሰው ስራ ሳሩም ቅጠሉም አያኮራ
እውቀቱስ ያንተ መሰለኝ በአብነትህ አድነኝ/2/
አባቶቻችን ካህናት ሲጠመጥሙ ከጥንት
ለስልጣናቸው ለክህነት መለያ ነበር ምልክት
አሁንማ ጠምጣሚዎቹ ሹሞቹና ጠበቆቹ/2/
ይህቺ በቅሎዬ ምን ሆነች አጉል መጥፎ አመል ለመደች
የጎረቤቷን እያየች ጭነት መገልበጥ አመጣች/2/
የሰሞኑ ጋብቻ ድንቅነቱ ከቀድሞ እጅጉን መለየቱ
መሆኑ ቀርቶ እስከ ሞት ተጀመረ ተጧሪ ፈቶ ወጣት ማግባት/2

ተው ስማኝ ሀገሬ(መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ)

ቅኝት-

ተው ስማኝ ሀገሬ ኧረ ስማኝ ሀገሬ/2/
ተው ስማኝ ሀገሬ ሲከፋኝ ነው መኖሬ ኧረ ስማኝ ሀገሬ
የገዳይ አጋዳይ ሆነህ ከመመለስ
እልም ጥርግ በል እስከወዲያው ድረስ ኧረ ስማኝ ሀገሬ /2/
ለፍጥረቱ ሁሉ ባያል ቸረፍ ቸረህ
እኔስ በሀገሬ ብኖር ምን ችገረህ ኧረ ስማኝ ሀገሬ /2/
መካሪዬ በዛ ቤት ስራ የሚለው
ምን ያታክተኛል አሁን ላፈርሰው ኧረ ስማኝ ሀገሬ /2/
አሉባልታ ሰምተው እውነት ነው ያሉ
ያሳባቂ ወሬ እየተቀበሉ
መግባባት ቀረና ከረረ ነገሩ
እናትና ልጁ ተቆራርጠው ቀሩ
አባትና ልጁ ተቆራርጠው ቀሩ
ጆሮ ያለው ይስማ የወንጌሉን ቃል
ራሱን ያዋረደ ከፍ ከፍ ይላል ኧረ ስማኝ ሀገሬ /2/
ቁጠባ ሳናደርግ ተሻምተን በልተን
እነኛ ወጥ አጡ እኛ እንጀራ አጣን ኧረ ስማኝ ሀገሬ /2/
ሽምብራውን ዘርተን እሸቱን ስንበላ
አወይ የእኛ ነገር ሁልጊዜ ጥርጠራ ኧረ ስማኝ ሀገሬ /2/
ለሊት ከጮቃ ላይ ፈረስ ቢጥልህ
ወንድሜ አትናደድ ማንም አላየህ
ይልቁን ተጠንቀቅ ቀን እንዳይጥልህ ኧረ ስማኝ ሀገሬ/2/
ቀለምና ቀለም ተጣልተው በቦታ
ጊዜ ተሰቷቸው የቀጠሮ ተርታ
ነገሩን ብንጠይቅ አግድሞ ካለፈ
ብለው ገለፁልን ወገን አሸነፈ ኧረ ስማኝ ሀገሬ/2/
ለፈረስ ለበቅሎ ይተርፍ ተነበረ
ዛሬስ ለሰው ያ እህል ይቸግር ጀመረ ኧረ ስማኝ ሀገሬ/2/
ሳጥናኤል ከሚስቱ ተጣልቶ ሲፋታ
ዲያቢሎስ ከሚስቱ ተጣልቶ ሲፋታ
ለሷ የደረሳት ቀሚስና ኩታ
ቀሚስና ኩታ ለሷ ቢደርሳትም
ምን ያሳዝንህል ብዙ ልባም አለ ላንተም ይተርፍሃል
ብዙ ልባም አለ ላንተም ይደርስሀል
ግራ አዝማች ሙቀጫ ደጃዝማች ጀበና
ፊት አውራሪ ስኒ ቀኝ አዝማቹ ቁርስ
እኚህ በሀገር ሳሉ አትማርም ነፍስ ኧረ ስማኝ ሀገሬ/2/

ሰላም ለኪ (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ)

ቅኝት - ሠላምታ
4245 313 15423 312 45
4245 313 15442 222

ሰላም ለኪ ማርያም ድንግል ንጽሕት /3/
ያቺን ርግብ ያቺን ወለላ ፍጥረት
በበገና እስኪ ላመስግን ጥቂት
የአምላክ እናት የሰማይ የምድር ፈጣሪ
የእርሷ አዝማሪ ዕዝራና ዳዊት በባህሪ
ቃል ኪዳኗ የማይፈርስባት ነዋሪ
እልፍ አዕላፍ መላእክት አሉዋት ነባሪ
ያገልግሉሽ ብሎ የሰጣት ፈጣሪ
እኒያን ይዛ ፍጥረት ዓለሙን መካሪ
ወለላዊት ቤዛዊት ዓለም ብፅዕት
ከወተት ውዳሴሽ ጥዑም በእውነት
ከወለላ ተዓምርሽ ጥዑም ሲበላ
የብርሃን ዘውድ የብርሃን አክሊል ደፍተሽ
ድረሺልን በሠረገላ ሆነሽ
ይሸሻሉ አጋንንት አንቺን ሲያዩሽ
ስታገለግል በቤተ መቅደስ ስትሠራ
ነይ ውጭ አሏት ሊቃውንት መክረው በሴራ
ተመቅኝተው ምናምን ታጢአት ሳትሰራ
እንደ ፀሐይ ገላዋ እንደ እሳት ሲያበራ
ትሙት ብለው ማየ ዘለፋን ቢያጠጧት
እንደገና ብርሃን መሆኑ ባሰባት
ያንን ግሩም ያንን ደስ የሚል መዐዛ

በንጽሕና ያለ ሩካቤ /ፀንሳ/ አርግዛ
ወለደችው በቤተልሔም ተጉዛ
ምጥ የለባት በመልአክ እጅ ተይዛ
የታደለች የተባረከች ፍጥረት
የበላውን ሰባ ስምንቱን ነፍሳት
አስገባችው በጥርኝ ውሃ ገነት
ከአድማስ አድማስ ወረቀት ቢሆን መሬት
ቀለም ቢሆን የሦስት ወር ውሃ ክረምት
ብዕር ቢሆን የዚህ ዓለም ሁሉ ዕፅዋት
ቢጻፍ አያልቅም የተአምርሽ ብዛት
ንግበር ብሎ ገና ሲፈጥረን ከጥንት
ፈጥሮ ሰጠን ድንግል ሕሊና ትሁት
በእርስዋ ሰበብ እንገባለን ገነት
ተመልከቱ የእግዚአብሔርን ምህረት
ብንወርድበት መቼ ይወዳል ከእሳት
እኛ ግና በኃጢአታችን ብዛት
እንወድቃለን ከዚያ ጨለማ ክርፋት
አደራሽን ቤዛዊት ዓለም ብፅዕት
በማልቀስሽ በመጨነቅሽ ብዛት
ሑሩ ሲለን እንድታወጪን ከእሳት
ቃል ኪዳንሽ እጅግ ታላቅ ነው ከጥንት
አንቺን አምኖ እንዴት ይጎዳል ፍጥረት
ማኅደሩ የአምላከ ሰማይ እናት
ታይቶ አይጠገብ ሁልጊዜ የልጅሽ ምሕረት
እኛን በቀኝ እንድታቆሚን ያን ዕለት
ለዓለም እስከ ዘለአለም ድረስ።።

ከቶ አይቀርም ሞቱ (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ)

ቅኝት -

ከቶ አይቀርም ሞቱ ምንም ቢታክቱ/2/
ምን ቢሰነብቱ
ሞት ፈደል ተምሮ ያነባል ስንል/2/
እንኪን ሊያነብና ገና ያግዛል
እህል ታሟል አሉ በእግሬ ልገስግስ/2/
እሞት የለሁም ወይ በቅሎማ እስኪደርስ
እኔን መስሎኝ ነበር ደሃ ነው ደካሚ
ለካስ ሁሉም ኖሯል አፈር ተሸካሚ
በሉ እናንተም ሂዱ እኛም ወደዚያው ነው/2/
ወትሮም መንገደኛ ፊትና ኋላ ነው
ለሠሪው ለመስጠት አፈሩን ይዣለሁ/2/
ገል አፈር መሆኑን ተረድቼዋለሁ
እኔስ ፍረድ ቢሉኝ ሞት በደለኛ ነው/2/
አንድ ሰው ለምስል ቀምሶ ቢቀር ምነው
ሞት ይቅር ይላሉ ሞት ቢቀር አልወድም
ድንጋዩም አፈሩም ከሰው ፊት አይከብድም
ሂያጅ ተሳፋሪ ሰዎች ከሆናችሁ/2/
ኧረ ለመቼው ቀን ቤት ትሠራላችሁ
እረገጡኝ ብለህ ምድር አትቆጣ/2/
ይህ ሁሉ ያንተ ነው ሸማውን ቢያነጣ
ዲያቆናት ቀሳውስት ደብተሮች በሙሉ/2/
ለመቀደስ ሲሉ መካን ይወልዳሉ።።

ስለ ሥነ-ስቅለት (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ)

ቅኝት- ሰላምታ

እውብ ድንቅ እንጂ ነው የጌታ ስቅለቱ/2/
እንዲህ በአርምሞ በእንዲህ ያለ ምክንያት አልቀው ህፃናቱ
ዮሴፍ ሰሎሜ ጌታ ከነእናቱ
ሆረ ደብረ ቁስቋም ምድረ ግብፅ ሰደቱ
በዚያ በበረሃ በመንከራቱ
ውሃ እየለመነች እመቤት እናቱ
የሄሮድስም ጥፋት ተሰማና ሞቱ
ምድረ ናዝሬት ገባች ከህይወት እርስቱ ከቶ አይቀርም ሞቱ
ወዲያውም ደረሰ ለመምህርነቱ
አርባ ሌሊት መዓልት/2/ ፆመ ወፀሎቱ
በእደ ዮሃንስ በባህረ ዮርዳኖስ የጌታ ጥምቀቱ
ተፅእኖ ገባ በነዓስ እድገቱ
ሆሳእና ዳዊት ለአለም መድኃኒቱ
ክሪያላይሶን ብለው ሰግደዋል ካህናቱ
ደቂቀ ሰራዊት አልቀሩም አበይቱ
ጌታችን ተይዞ በጊዜ ሠለስቱ
ወድቆ ተገረፈ ለምለም አካላቱ
ሰቀሉከ እየሱስ ግፍአሙ ዝንቱ
ዘለፌ ወለፌ አዕባን ተማቱ
ፀሀይም ጠለቀች ሆነ እንደሌሊቱ
ጨረቃም ደም ሆነ ሸሸ ብርሀናቱ
ከዋክብት ረግፈው ታጡ ካሉበቱ
ሲገርፉት ሲያዳፉት ሲወድቅ በደረቱ ከቶ አይቀርም ሞቱ
በስተኋላ ቆመው ስበው ወደአንገቱ
በስተፊቱ ቆመው ስበው በደረቱ
ስቅሉ ስቅሎ አሉት ሲዛበቱ
ሲገርፉት ሲያዳፉት ሲወድቅ በደረቱ
በከየት ማርያም አዘነች እናቱ
ከቶ አይቀርም ሞቱ ምንም ቢታክቱ
ምድረ ቀራንዮ መስቀል መሰረቱ
ጌታችን ተነሳ በእለተ ሰንበቱ
መጎስቆሉ ቀረ መጣ ጌትነቱ
ፅኑ ሽብር ሆነ አይሁድ ተፀፀቱ
ዲያቢሎስ ድል ሆነ ከነ ሰራዊቱ
ቁልቁለት ወረደ በመትህት ርስቱ
አዳምን አወጣው ምስለ ብእሲቱ
ወዲያው ገነት መራው ከቀደምት እርስቱ
እውብ ድንቅ እንጂ ነው የጌታ ስቅለቱ
ከቶ አይቀርም ሞቱ ምንም ቢታክቱ
ምን ቢሰነብቱ ከቶ አይቀርም ሞቱ

አባ ግራኝ ሞተ (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ)

ቅኝት - ሠላምታ

አባ ግራኝ ሞተ የሆዴ ወዳጅ /2/
የሚያበላኝ ጮማ የሚያጠጣኝ ጠጅ
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሳ ብሎ ስም
ዐርብ ዐርብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ

ሺህ ገመር ሺህ ጎራች የሸዋ ፈረስ
አንድ ጥርኝ ሆነ ቢዘልቅ ቴዎድሮስ
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
ፈረሱ አባ ታጠቅ ስሙ ቴዎድሮስ
ጠላትን የሚበትን እንደ ዓውሎ ንፋስ
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
መቅደላ አፋፉ ላይ ጩኸት በረከተ
የሴቱን አናውቅም ወንድ አንድ ሰው ሞተ
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
መቅደላ መቅደላ አንቺ ክፉ ጎራ
ሴቱን ሁሉ ንቆ ሲኮራ ሲኮራ
ወንዱ አንቺን ወደደ ተኛ ካንቺ ጋራ
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
አያችሁት ወይ ያንበሳውን ሞት
በሰው እጅ መሞትን ነውር አድርጎት
እርሳሱን እንደጠጅ ጎርሶ ሲጠጣት
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
አውሮፖም ያውቁሃል አፍሪካም ያውቁሃል እስያም ያውቁሃል
እንኪን የሰው ንጉሥ ውሃ እንኪን ፈርዶሃል
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
አባትና እናቱ ያለ አንድ አልወለዱ
አባ ታጠቅ ካሳ ያ ወንዱ ያ ወንዱ
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
የትግሬንም ንጉሥ ሲንቁ ሲንቁ
የሸዋንም ንጉሥ ሲንቁ ሲንቁ
ወንድ ያለ ራስዎ ገድለውም አያውቁ
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
ገደልን እንዳይሉ ሞተው አገኙዋቸው
ማረክን እንዳይሉ ሰው የለ በእጃቸው
ምን አሉ እንግሊዞች ሲገቡ ሀገራቸው
መቼም ለወሬ አይመቹም ተንኮለኞች ናቸው
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ
እንደ አፄ ቴዎድሮስ አላየሁም ኩሩ
ቢመጡ እንግሊዞች ምክር ሊማከሩ
በአርምሞ ሸኙዋቸው ሳያነጋግሩ
እኔ መዩ ቱርክን ባይ የምሸሽ ነኝ ወይ

ስለ ሥነ ፍጥረት (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ)

ቅኝት - ሰላምታ
4245 313 15423 312 45
4245 313 15442 222

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
አሐዱ እምላክ ብዬ ሰላምታ ላድርስ
ለፈጠርከኝ ላንተ የላይኛው ንጉሥ
እንዴት አለህ መጥቼ እስካይህ ድረስ
ያስደንቃል ያፏፏራቸው የጥንቱ
የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ የሦስቱ
ሦስት ናቸው በአካል በገጽ በስም
አንድ ናቸው በትእዛዝ በክብር ፍፁም
ስላሤም እምቅድመ ዓለም ሲኖሩ
ዓለም መፍጠር እሁድ በሠርክ ጀመሩ
ያን ጊዜውን ሰባት ፈጠሩ ቅጽበት
አስቀድመው ሰማይና ምድርን በፊት
አራተኛ መላዕክትና ጽልመት
ሰባተኛ ማይና ነፋስ እሳት
በአርምሞ ይህንን ሁሉ ፈጥረው
ተናገሩ ለይኩን ብርሃን ብለው
ሰኞ ጠዋት ውሃን ከፈሉት ከሦስት
አንደኛውን አዘቅት አረጉት ከምድር
ሁለቱን ሰማይ አረጉት ጠፈር
ማክሰኞም አብቅይ አሏት ምድርን
አበቀለች ሳር ቅጠሉን እህሉን
ረቡዕም ረቂቅ ሥራን ሲሰሩ
ከዋክብትን ፀሐይ ጨረቃን ፈጠሩ
ሐሙስም አልተውምና መፍጠር
የሚበሩ ክንፍ ያላቸውን ነገር
የማይበሩ የሚሄዱትን በእግር
በባህርም ዓሣ ጉማሬ ሳይቀር
ዓርብ ጠዋት አዳምን የኛን አባት
ንግበር ብለው በነሱ አምሳል ሠሩት
በሠልስት ሔዋንን ፈጥረው ሰጡት
ትርዳህ ብለው ብቻውን ሆኖ ቢያዩት
የሥላሴ የፍጥረታቸው ፍፃሜ
በሰባት ቀን ዳርቻ ሆነ ቅዳሜ
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ።።

ስለ ዳግም ምፅዓት (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ)

ቅኝት - ሰላምታ
4245 313 15423 312 45
4245 313 15442 222

እንዲህ አርገን ሥራውን ሁሉ አምነን
እናምናለን ዳግም ይመጣል ብለን
ነገር ግን ዳግም ይመጣል ስላልን
ከፃድቃን ከመላእክትም ቢሆን
የሚያውቅ የለም የሚመጣበት ቀኑን
ባላወቅነው ባልመረመርነው ሰዓት
ግሩም ሆኖ ይመጣል እንጂ ድንገት
መጀመሪያ የአዋጅ ነጋሪት ሲመታ
ከያለበት ይሰበሰባል በአንድ አፍታ
አጥንታችን ትቢያ የሆነው አፈር
ጅብ የበላው የተበተነው ከዱር
የራስ ፀጉር የእግር ጥፍራችን ሳይቀር
ተሳስቶ የአንዱ ወደ አንዱ ሳይዞር
በየራሱ ይሰበሰባል ሁሉም
ይመታል የአዋጅ ነጋሪት ዳግም
ነፍስ የሌለው በድን ይሆናል ፍፁም
በሶስተኛው የአዋጅ ነጋሪት ሲመታ
ይነሳሉ መልካም የሠሩ በእልልታ
የብርሃን ልብስ የብርሃን ቀሚስ ለብሰው
እንደ ፀሐይ እንደ ጨረቃ ደምቀው
እግዚአብሔርን ፈጣሪያቸውን መስለው
ይሰሙና በቀኙ ቆመው ፍርዱን
ከማያልፈው ተድላ ደስታ በቀር
ጠግቦ ቁንጣን ተርቦ ስስት ሳይኖር

ገብቶ መውጣት አግኝቶ ማጣት ችጋር
የሌለባት ደገኛይቱን ሀገር
ይወርሳሉ መልካም የሠሩ በምድር
ኃጥአንም እጅግ ከጭራ ቀጥነው
መልካቸውም እጅግ ከቁራ ጠቁረው
ከላይ ከታች የጨለማ ልብስ ለብሰው
ዲያብሎስን አለቃቸውን መስለው
ይሰሙና በግራ በኩል ቆመው
በመንቀጥቀጥ የሚፈርደውን ሰምተው
ከለቅሶና ጥርስ ማፋጨት በቀር
ተድላ ደስታ የሌለባትን ሀገር
ይወርሳሉ ክፉ የሠሩ በምድር
እንዲህ አርገው መጻሕፍት ሁሉ እንዳሉ
በየሥራው ይከፍለዋል ለሁሉ
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ

ስለ ልደት (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ)

ቅኝት - ሠላምታ
4245 313 15423 312 45
4245 313 15442 222
ድንግልም በምትወልድበት ወራት
በሮም ንጉሥ በአውግስጦስ ቄሳር መንግስት
ሰው ሁሉ ግብር ሊቆጠር ታዘዘ
ዮሴፍም ድንግልን ይዞ ተጓዘ
ከገሊላ ከነበረበት መንደር
ቤተልሔም ወደምትባል ሀገር
ከኤፍራታ ይወጣል ብሎ ንጉሥ
ሚክያስ የተናገረው ሊደርስ
ሳታፋልስ የወላዶችን ሥርዓት
በታኅሣሥ ሃያ ዘጠኝ ዕለት
ከዚያው ሳሉ የምትወልድበት ቢደርስ
ተወለደ ድንግልናዋን ሳይጥስ
ቤት ባይኖራት መጥታለችና ከሩቅ
ከበረት ጠቀለለችው በጨርቅ
ሊፈጸም የኢሳይያስ ነገሩ
እንስሳትም ትንፋሻቸውን ገበሩ
ከዚያ ቦታ ከብት ጠባቂዎች ነበሩ
ያዩ ነበር ካሉበት ቦታ ድረስ
የብርሃን ጎርፍ ከቤተልሔም ሲፈስ
እረኞቹም የብርሃኑን ጎርፍ አይተው
እጅግ ፈሩ ምን ነገር ነው ብለው
መልአኩም ፍርሐታቸውን አርቆ
ነገራቸው ተድላ ደስታሉን አድንቆ
ልዑል አምላክ ለአዳም ብሎ ተዋርዶ
ከድንግል በዳዊት ባሕርይ ተወልዶ
ጨርቅ ለብሶ ከበረት መሐል ተጥሎ
አለላችሁ ሄዳችሁ እዩት በቶሎ
እንዲህ ብሎ ሲናገራቸው በዜና
ከእርሱ ጋራ ብዙ መላእክት መጡና
አቀረቡ ከእረኞች ጋር ምስጋና
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ

ማን ይመራመር (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ)

ቅኝት - ሠላምታ

ማን ይመራመር
ያንተን ሥራ ያንተን ግብር
ማን ይመራመር
ጎጃም ተሸምቶ ይቀናል በጌምድር/2/
እየከዳ እምቢ አለ ወዳጅ እና ምድር
አለህም እንዳልል እንዲህ ይደረጋል
የለህም እንዳልል ይመሻል ይነጋል
እባክህ አምላኬ ስጠኝ መስታወት/2/
የሰው ስራ ጥዬ የኔን አይበት
እግዚአብሄር ምን ይበል እኛ ቅጥ ብናጣ/2/
በስምንተኛው ሺህ በቀጠሮው መጣ
እባክህ አምላኬ አትመራመረኝ/2/
እንደ በላኤሰብ በጥቂት ነገር ማረኝ
አንተ ነህ ይላሉ የዓለም ሁሉ ጌታ
ሰማይና ምድርን ያቆምክ ያለዋልታ
ወዴት እንዴት ይሆን ያለህበት ቦታ
እነግርህ ነበረ እኔ በቆይታ
የሰራችልኝን የእናትህን ወሮታ
ያንጊዜ አትለይም እሷ ከእኔ እርዳታ
ምግብና መጠጤን በውል አጋጅታ
እግሬን አሳጥባ ዙፋን አዘርግታ
ትከተለኛለች ለእርሷ ልዕልና
ለሷ ልዕንና የለውም ቅሬታ
ልጇ ፍፁም ንጉስ የለው ባለ ፋንታ
እኔስ ይገርመኛል ከጠዋት እስከ ማታ
ካለሁበት ሀገር አለመለየቷ
ለሁሉ ነው እርሷ ይህ ሩህሩህነቷ
አይበዛም እንደኔ ይህ መልካምነቷ
አንቺ አማልጂን እንጂ መድኃኒት ለዓለሙ
ወልደ አብ ሲለምን አባ ስረይ ሎሙ
እመቤት እመቤት የዓለም መድኃኒት
እንድታማልጂን በዕለተ ምፅአት
ምንም ክፉ ብንሆን አውቀን ብናጠፋ
አዛኝቷ አስምሪን እናት አትገፋ
ንኡ ና ሑሩ ሲል ሲያደራጅ ልጅሽ
እንደበላኤሰብእ ያድነን ጥላሽ
እባክህ አምላኬ አትመራመረኝ/2/
እንደበላኤ ሰብ በጥቂት ነገር ማረኝ
ያንተን ሥራ ያንተን ክብር
ማን ይመራመር

ማን ይመራመር (አቶ አለሙ አጋ አጋ)

ቅኝት - ሠላምታ
ማን ይመራመር
ያንተን ሥራ ያንተን ክብር ማን ይመራመር
አዳምና ሔዋን ጠፍቷቸው መንገዱ /2/
ለሰው ልጅ መከራን ትተውለት ሄዱ
እስከዚያው ድረስ ነው ሲሶ ማረሳችን
እንገባው የለም ወይ በየመሬታችን

አለህም እንዳልል እንዲህ ይደረጋል /2/
የለህም እንዳልል ይመሻል ይነጋል
እባክህ አምላኬ የምለምንህ /2/
ያጣ ሰው ሳያገኝ አይሙት አደራህን
የታመመ ሳይድን አይሙት አደራህን
አንተ ነህ ይላሉ የዓለም ሁሉ ጌታ
ሰማይና ምድርን ያቆምክ ያለዋልታ
ወዴት እንዴት ይሆን ያለህበት ቦታ
እነግርህ ነበረ እኔ በቆይታ
የሰራችልኝን የእናትህን ወሮታ
ሁልጊዜ አትለይም እሷ ከእኔ እርዳታ
ምግብና መጠጤን በውል አጋጅታ
እግሬን አሳጥባ ዙፋን አዘርግታ
እኔስ ይገርመኛል ከጡዋት እስከ ማታ
ካለሁበት ሀገር አለመለየቷ
ለሁሉ ነው እርሷ ይህ ሩህሩህነቷ
አንቺ አማልጂኝ እንጂ መድኃኒት ለዓለሙ
ወልደ አብ ሲለምን አባ ስረይ ሎሙ
እመቤት እመቤት የዓለም መድኃኒት
እንድታማልጂን በዕለተ ምፅአት
ምንም ክፉ ብንሆን አውቀን ብናጠፋ
አዛኝቷ አስምሪን እናት አትገፋ
ንኡ ና ሑሩ ሲል ሲያደራጅ ለጅሽ
እንደበላኤሰብእ ያድነን ጥላሽ
ያንተን ሥራ ያንተን ክብር
ማን ይመራመር
አለህም እንዳልል እንዲህ ይደረጋል/2/
የለህም እንዳልል ይመሻል ይነጋል

ስለ ምሥጢረ ሆሣዕና(መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ)

ቅኝት- ሰላምታ
4245 313 15423 312 45
4245 313 15442 222

በስመ አብ ብለን እስኪ ሠላምታ እናድርስ
ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ
እስኪ እናስታውስ የሆሣዕናን ትዕይንት
የሆነውን የነበረውን ያን ዕለት
ፋሲካቸው በስምንት ቀን ሲሆን
ከፋሲካ በሚቀድመው ሰሞን
ዘካርያስ የሚባል ነቢይ ካህን
ደስ ይበልሽ ኢየሩሣሌም ጽዮን
ንጉሥሽ ይመጣልና አሁን
በአህያ ላይ እንደ አንድ ደሃ ምስኪን
እንዲህ ብሎ የተናገረው ቃሉን
ለመፈፀም በአህያ ሆኖ መድኅን
ሲመጣ አይታ እርሱ መሆኑን ለይታ
ሀገሪቱ ተቀበለችው በእልልታ
በመንገዱም ቅጠሉን ቆርጠው በእርጥቡ
ልብሳቸውን ያነጠፉ አሉ ከሕዝቡ
ሁለተኛም ዳዊት ልበ አምላክ ነውና
ሲዘመር እያስማማ በበገና
አስቀድሞ ይህችን ዕለት አየና
ሲሰብክልን የዚህች ዕለትን ዜና
አዘጋጀህ ከህፃናት አፍ ምስጋና
ላለው ትንቢት መፈፀሚያ ቀን ናትና
እንዲህ ሆኖ ከቤተ መቅደስ ሲገባ
ሕፃናቱ እየወረዱ ከጀርባ
በጣታቸው እየጨበጡ ዘንባባ
በእግዚአብሔር ስም የምትመጣው አምላክ
ብሩክ ነህ ለዘለዓለም ብሩክ
የዳዊት ልጅ መድኃኒት የሆንክ ለሁሉ
ሆሣዕና መባል ተገባህ እያሉ
በደስታ በፊት በፊቱ ዘለሉ
ይህን ሰምተው ፈሪሣውያን ጸሐፍት
ቢናደዱ ቢመላባቸው ቅንዓት
ሕፃናቱን ተው በላቸው አሉት
እንዲህ አለ ሲመልስላቸው ጌታ
ከጡላችሁ የሕፃናቱን ዕልልታ
ድንጋዮቹ የሚገባቸው ዝምታ
ያመስግኑ በእናንተ በሰዎች ፈንታ
በዚህ ጊዜ አምላክነቱን ሊገልጡ
ድንጋዮቹ በፊት በፊቱ እየሮጡ
እንደ ሰዎች የምሥጋና ድምጽ ሰጡ
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ

ዋኔን (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ)

ቅኝት-

ምን ያጣላችኋል ዋኔን በመሬት ጉዳይ ዋኔን
አሁን ዘር ሲጠፋ ዋኔን ይቀር የለም ወይ ዋኔን/2/
ምድርን ጠላ መጥመቅ ዋኔን ማን አስተማረው ዋኔን
እየጠራ አጠጣው ዋኔን ያንን ሁሉ ሰው ዋኔን/2/
በል እደር ጆሮዬ ዋኔን ነገ እቆርጥሀለው ዋኔን
ባንተም ክፉ ነገር ዋኔን ሰምቼብሀለው ዋኔን/2/
ወይ አላሳጨድነው ዋኔን ወይ ከብት አልበላው ዋኔን
ከቶ መቼ ይሆን ያ ሳር ማለቂያው/2/
ብላጩው አመመኝ ዋኔን ብሰራው ከፋኝ ዋኔን
አንድ ራሴ እኮ ነው የሚያስጨንቀኝ/2/
የሁዳዴውስ ጾም ዋኔን ምንም አላለው ዋኔን
ሰው ሁሉ ያለቀው ዋኔን በህማማቱ ነው ዋኔን/2/
በባላገር ነበር ዋኔን ኑሮስ የሚሻል ዋኔን
ከተማ ሰው ገብቶ ዋኔን ምን ምን ሰው ይሆናል ዋኔን

ይበላሃላ (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ)

ቅኝት-

ይበላሃላ/4/
አንተንም አፈር ይበላሃላ እንደሞኝ ሰው እንደተላላ
አሊ ሲሞት ያለብኝ አሳር
በአንድ እጇ ዶማ በአንድ እጇ ምሳር
አሊ ሲሞት መብሌ ጉበት
ከአሊ በፊት እኔ ልሙት
አሊ ሲሞት መጠጤ አተላ
አንተንም አፈር ይበላሃላ
እኔንም ጎንደር ይሸጡኛላ

በላው አፈር በላው አፈር
ያንን አንገት ያንን እግር
አንቺንም አፈር ይበላሻላ
እንደሞኝ ሰው እንደተላላ
በላው አፈር በላው አፈር
ያስተማረህን ያንን ምሁር
በላው መረፊ በላው መረፊ
ያንን የዋህ ሰው ያንን ገበሬ
አንተንም አፈር ይበላሃላ
እንደሞኝ ሰው እንደተላላ
በላው አፈር በላው አፈር
ያንን ታሪክ ያንን ዘመን
ያንን ባህል ያንን ፍቅር
ያንን አንድነት ያንን ህብረት
በላው አፈር በላው አፈር
አንተንም አፈር ይበላሃላ
እንደሞኝ ሰው እንደተላላ

ዓለም ማረፊያ ናት(መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ)

ቅኝት-

ዓለም ማረፊያ ናት መኖሪያ ገነት/2/
ተነሱ እንከተል እኛም ከሄዱት
አፈር ከሸተተን ከያዘን በሽታ
ብንቆርብ አንድንም ይህን ጊዜ እንበርታ
መቁረብ በህይወት ነው ንስሐ መግባት/2/
ይህ ሁሉ አይገኝም ከገቡ መሬት
ቆዳ እየለበሱ ከገዳም ሲኖሩ
ከእነርሱ አይለይም የአምላካችን ፍቅሩ
ወርቅ የለበሰና ያጌጠ ፍጡር
ክብሩ ሁሉ ቀረ ደረቀ እንደሳር
ይህን ተመልክቶ ይጠንቀቅ ፍጡር/2/
በለስ ለመለመ መኸርም ደረሰ
የሰውም ዘመኑ ሄደ ገሰገሰ
ሁል ጊዜ ይሰማል ቃለ ዮሐንስ
አለሙን ለማዳን ስጋ በመልበስ
ምሳሌ ደረሰ አምላክ ምህረት
ገለባና ፍሬ የሚለይበት
ገለባው ይወድቃል ፈጠኖ ወደ እሳት/2/
ፍሬው ግን ይገባል ከቅዱሳን ቤት /2/
ለአብረሃም ለይስሐቅ የሰጠኸውን
ዛሬም ለህዝቦችህ ስጠን ህይወትን/2/
መጣጣር ከንቱ ነው ሁልጊዜ ለስጋ
ጾምን ካላወቅን አትገኝም ፀጋ/2/
ካለመጾም ሊያገኝ መንፈስ ቅዱስን
ፀጋ ብሎ ጠራው አንድ ሰው ልጁን
የኦሪት ቃል ዘሎ ወንጌል ካዘዘው
ዋ ጊዜ ደረሰ አንዱን ሳልሰራው/2/
ዋ ጊዜ ደረሰ ሳስብ ሌላ ሌላ
እጅግ ያታልላል የዚህ ዓለም ተድላ
ጥቂት ላይሰነብት ላይቆየን ለኋላ/2/

እስመ አንተ(መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ)

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
አሐዱ አምላክ ብዬ ሰላምታ ላድርስ
እስመ አንተ አምላከ ሰማይ ወምድር
እስመ አንተ ምሉአ ፀጋ ወክብር
ትባላለህ በነግህ በሰአት በቀትር
ኢየሱስ ደግ ባለፀጋ ንጉስ
ኢየሱስ በአፈ ኩሉ ውዱስ
ኢየሱስ ቅዳሴ ስጋ ወነፍስ
ወደላይ ልቤን ሰደድኩት እንዲያይ
ቢያየው እፁብ ድንቅ ነው ግሩም
መንጦላእቱ የተጋረደው በፊቱ
የሚጥለው የሚዘረጋው አሸከር
አልታዘዝ ጭራሽ አይልም ፍጡር
ካንተ ዘንድ አይኮራም አሉኝ ዘመድ
ካንተ ደጅ አይኮራም አሉኝ ወዳጅ
ካንተ ሲደርስ አይኮራም አሉኝ ንጉስ
ካንተ ሲደርስ አይኮራም አሉኝ ጳጳስ
አንተ እንጂ ነህ የማትዋረድ አታንስ
ብርቱ ዳኛ ያላንተ የለም ታይለኛ
አንተ ስትወድ ሁሉ ይሆናል ዘመድ
ብሉ ጠጡ ልበሱ ይላል በግድ
አንተ ስትጠላ የሚሆን የለን ከለላ
በቀኝ ያለው ዞሮ ይቆማል በግራ
ስትወድማ ስትመልስማ ፊትህን
በመጻጉ አይተነው የለ ጉድህን
ፈጣሪዬ በከንቱ አለቀች እድሜዬ
ሳልገዛ እያሸነፈኝ ስጋዬ
ዳሩ ግና አዛኝ ሩህሩህ ነህና
አደራህን የነፍሴን ነገር አትጥና
መበስበስ ደግሞ አለ ገና መፍረስ
መነሳት ደግሞ አለ ገና ፍርድ መስማት
ባህቲቱ እስመ ለዓለም ምህረቱ
መላዕክቱ አይሸፍቱበት ከቤቱ
ሌላ ጌታ ያላንተ የለም በከንቱ
ደህና ዋሉ ደህና ሰንብቱ አርፍዱ
የሚያውቅበት አንድም ሰው የለም በፍርዱ
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ

አላየንም በሉ (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ)

አላየንም በሉ ኧረ አልሰማንም በሉ
ያ ሞት ሲፈልገን ሲሻን ውሏል አሉ
እንዴት እሆናለሁ ኧረ እንዴት እሆናለሁ
አሁንም ከፍቶኛል ኋላም እሞታለሁ
ማረፊያዬን አላውቅ ተጉዤ ተጉዤ
እስከመቼ ድረስ እንዲህ ተወዝውዤ
አዝ...
አስከሬን አጓዥ አንተ ጥቁር መኪና
ለምን አትሰለችም ማለት ደፋ ቀና
መውሰድ እንጂ መመለስ አታውቅበትም ከቶ
መንጠቅ ልማድህ ነው ጎትቶ ጎትቶ

እኔማ ጠጅህን ምን አደርገዋለሁ
እኔማ ጮማህን ምን አደርገዋለሁ
በራሴ አዘንብዬ በአይኔ እቀዳዋለሁ
አዝ...
ሞት በደጇ መጣ መንገዱ አደረገኝ
ዳግመኛ ቢመጣ ካለኔ አያውቀኝ
አዝ...

<u>የበገና አካላት (መጋቤ ስብሐት አለሙ አጋ)</u>

ቅኝት - ሰላምታ
4245 313 15423 312 45
4245 313 15442 222

ሰላም ለኪ እንዘ ንሰግድ ንብለኪ
ማርያም እምነ በእንተ ሃና እምኪ
ወኢያቄም ዘምስለ ዳዊት አቡኪ
ሰአሊ ለነ ሀበ ክርስቶስ ወልድኪ
ተዓብዮ ለእግዚእየ ነፍስየ
ያፀግዋ ወያለብሳ ፀሐየ
ውዳሴሽን እናገራለሁ በዜና
ላመነሽ ለወደደሽ ሰው በበገና
በበገና ይገኛል አሉ ትምህርት
አስሩ ጅማት አስርቱ ቃላተ ኦሪት
ድምፀ ቃሉ ደስ የሚያሰኘው ለሁሉ
ተመራምሮ ለደረሰበት ሰው ሁሉ
ጣቶቹ ግን የዚህ የአስሩ ጅማት
የኤርሚያስ የአስርቱ ነቢያት አይነት
ጋድሙ ግን ከሁሉ በላይ ያለው
እግዚአብሄር አብ አሃዜ ኩሉ ዓለም ነው
ምሰሶው በስተቀኝ በኩል ያለው
መልአከ ምክሩ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ነው
ምሰሶውም በስተግራ በኩል ያለው
ብስራታዊው ገብርኤል ሊቀ መላእክት ነው
ማፈኛው ግን የአስሩ አውታር በሚል
መስሎታል በብሂሞትና በሊዮታን
ገበታው ግን ከልብሱ ጋራ ያለው
የድንግል ማርያም ቅድስናዋ ነው
በርኩማው ግን የዚህ የአስሩ አውታር
ደብረ ሲና የሙሴ የአሮን ሀገር
እንዚራውም የዚህ የአስሩ ጅማት
መስሎታል በአስርቱ ቃላተ ኦሪት
ድህንፃውም የዚህ የአስሩ አውታር
ቅዱስ ቅዱስ የሰማይ ጌታ የምድር
የታሪኩ የድህንፃው ጠፈር
መስሎታል በሂታቸው ወርቅ አምሳል
እፁብ ድንቅ ነው ማንም ለማየት አይችል
አውታሩ ግና የያዘውን እንጨት
መስሎታል በድንግል መሰረተ ህይወት
የዚህን የመያዣውን ጠፈር
መስሎታል በኪሩቤል አምሳል
በገናውም ከኋላ የተበሳው
ዳዊትን ለመግደል ሳኦል የወጋው ጦር ነው
ሚካኤል ነግሮት በገናው መከተው
መታሰቢያ ነው ቀዳዳው የኋላው
መቺው ግን የዚህ የአስሩ አውታር
ባለሟል ነው ከሰማይ ጌታ ከምድር
የሚሰማው የሚያዳምጠው ፍጡረት
ጉባኤ ነው የሙሴ የአሮን ትምህርት
ግሩም እንበል ወደ ላይኛው አባት
ሚስጥሩ ይህ ነው የበገናው መሰረት
አይገባም ለሳቅ ለዘፈን መምታት
እናመስግነው የዘላለምን አባት
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከዘለዓለም ድረስ

<u>ዘማሪ አቶ ታፈሰ</u>

<u>በስመ አብ/እስመ አንተ(አቶ ታፈሰ)</u>

ቅኝት-

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
አሐዱ አምላክ ብዬ ሰላምታ ላድርስ
እስመ አንተ አምላከ ሰማይ ወምድር
ስብሐት ለከ ምሉኀ ፀጋ ወክብር
ትባላለህ ቀንና ሌሊት ዘውትር
ክርስቶስ የዓለማት ሁሉ ንጉስ
ዘለዓለም ክብርህ ገናና አይቀንስ
ብርቱ ዳኛ ያላንተ የለም ኃይለኛ
ትገድላለህ ምንም ሳያመው ሳይተኛ
ስታፈቅር ሁሉ ይሆናል ዘመድ
ብሉ ጠጡ ልበሱ ይላል የግድ
አንተ ስትጠላ ወዳጅ ይሆናል ጠላት
ይንቁታል ከውጪም ሆነ ከቤት
ትገድላለህ ጠዋትና ማታ ሳትል
ሳይታመም ጤና ሳያጣ ሳይዝል
ስታድን ስትመልስማ ፊትህን
በመፃጉ ሰምተነው የለ ልኩን
ከመቃብር አልዓዛር ውጣ ብለህ
ስላዘዝከው በመለኮቱ ቃልህ
ከሙታን በአራተኛው ቀን ተነስቶ
ህያው ሆነ መሞቱን እንኳን ረስቶ
እንደዚህ ነው የመድኃኒዓለም ምህረቱ
እንዲጎዳ አይወድምና ፍጥረቱ
ቀንና ሌት ከቶ ሳይኖረን እረፍት
እየሰራን እንደዚህ ሁሉ ሀጥያት
ተመልከቱ የጌታችንን ምህረት
መቼ ይወዳል ብንወርድበት ከእሳት
እኛ ግን ከሀጢያታችን ብዛት
እንወርዳለን ከዚያ ጨለማ ክርፋት
ፈጣሪዬ በከንቱ አለቀች እድሜዬ
ሳልገዛ እያሸነፈኝ ስጋዬ
ጌታ ሆይ አዛኝ ሩህሩህ ነህና
አደራህን በነፍሴ ነገር አትጽና
መበስበስ አለብን እና መፍረስ
መራራው ሞት በድንገት ፈጥኖ ሲደርስ
መነሳት አለብን ፍርዱን መስማት

የዚያን እለት ድንልቅልቅ ሲሆን ጭንቀት
አደራህን ነፍሴን አድርጋት ወዳንተ
በሀዲቱ እስመ ለአለም ምህረቱ
ማን አለና ያላንተ ጌታ በብርቱ
ይሄይስ እምነ ኩሉ ንጉስ
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ
ለአለም እስከዘለአለም ድረስ

ርግብና ዋኔን (አቶ ታፈሰ)

ቅኝት- ዋኔን (ትዝታ)
4444 55-3 115 42
44452-5-3 115 42
33 11 33 42-3-1 42
33 11 33 42-2 42

ርግብና ዋኔን ዋኔን አብረው ዘመቱና ዋኔን
ርግብ ደህና ገባች ዋኔን ዋኔን ገደሉና ዋኔን
እስቲ በስመአብ ብዬ ዋኔን ልቀኝ ለእመቤቴ ዋኔን
ማርያም በመሆኗ ዋኔን ክብሬና ሀይወቴ ዋኔን
ሰላም እልሻለሁ ዋኔን ጽላተ ጽዮን ዋኔን
ደጅ እጠናሻለሁ ዋኔን አምኜ አንቺን ዋኔን
አዛኝቷ እመቤት ዋኔን ኪዳነ ምህረት ዋኔን
አለሁልህ/ሽ/ ብለሽ ዋኔን አውጪኝ ከመአት ዋኔን
እስቲ ሁላችሁም ዋኔን ኪዳነ ምህረት በሉ ዋኔን
መድኃኒት ናትና ዋኔን ለሰው ልጆች ሁሉ ዋኔን
ሁሌ እጠራሻለሁ ዋኔን በቃል ኪዳንሽ ዋኔን
የምህረት አማላጅ ዋኔን ድንግል አንቺ ነሽ ዋኔን
የዓለም ፈርጥ አንቺ ነሽ ዋኔን ማርያም እመቤቴ ዋኔን
እመካብሻለሁ ዋኔን እስከ ጊዜ ሞቴ ዋኔን
ያንን የእሳት ባህር ዋኔን አሻግሪኝ ድንግል ዋኔን
እንዳወድቅ አደራ ዋኔን ከሲኦል ገደል ዋኔን
የነቢያት ትንቢት ዋኔን የሰማዕታት አክሊል ዋኔን
ያላንቺ ማን አለኝ ዋኔን እመቤቴ ድንግል ዋኔን
በአማላጅነትሽ ዋኔን እንኮራለን እኛ ዋኔን
የጽድቅ መሰላል ነሽ ዋኔን የተሰጠሽ ለኛ ዋኔን
ያዕቆብ በህልሙ ዋኔን ያያት መሰላል ዋኔን
የዓለም አስታራቂ ዋኔን አንቺ ነሽ ድንግል ዋኔን
ታማልደናለች ዋኔን እጆቿን ዘርግታ ዋኔን
ከቶ እረፍት የላትም ዋኔን ከጧት እስከ ማታ ዋኔን
ኪዳነ ምህረት ነሽ ዋኔን አንቺ የኛ ተስፋ ዋኔን
መርቆ የሰጠን ዋኔን አሜጋና አልፋ ዋኔን
የዓለም ሁሉ መቅረዝ ዋኔን መንበረ ሥላሴ ዋኔን
መድኃኒቴ እሷ ነች ዋኔን ለሥጋም ለነፍሴ ዋኔን
ሁሌ ላመስግናት ዋኔን ተፈታ ምላሴ ዋኔን
የምህረት ቃል ኪዳን ዋኔን የሰው ልጅ መዳኛ ዋኔን
እንድታማልደን ዋኔን የተሰጠች ለኛ ዋኔን
ምላሴ ተናገር ዋኔን የማርያምን ዝና ዋኔን
ለኛ መሰጠቷን ዋኔን ሳትፈጠር ገና ዋኔን
ታስባ ስትኖር ዋኔን በእግዚአብሔር ሕሊና ዋኔን
ተወልዳ አደገች ዋኔን ጊዜው ደረሰና ዋኔን
ዘመን የማይሽረው ዋኔን ስላላት ቃል ኪዳን ዋኔን
ታማልደናለች ዋኔን መድኃኒት በመሆን ዋኔን
ምን ቃላት ይገኛል ዋኔን እርሷን ማመስገኛ ዋኔን
እነ ሕርያቆስ ዋኔን ያልቻሉት እነኛ ዋኔን
ከዓይኗ እያዘነበች ዋኔን የእንባዋን ዘለላ ዋኔን
ወደ ግብፅ በረረች ዋኔን አንድ ልጇን አዝላ ዋኔን
ፅጌ ፀዐዳ ነች ዋኔን እመቤቴ ድንግል ዋኔን
ድረሺልን ሲሏት ዋኔን ከተፍ ነው የምትል ዋኔን
የፃድቃን እመቤት ዋኔን የኃጥኣን ተስፋ ዋኔን
ወዳንቺ እጮሀለሁ ዋኔን ሳዝንና ስከፋ ዋኔን
የበላኤ ሰብን ዋኔን ያዳንሽው ድንግል ዋኔን
ለእኔም አትንፈጊኝ ዋኔን ይህንን እድል ዋኔን
ስንቅ የለኝ ለነፍሴ ዋኔን እንዴት ልሆን ነው ዋኔን
ድንግል እመቤቴ ዋኔን መግቢኝ አንቺው ዋኔን
ጥላሽን ጣይብኝ ዋኔን ኪዳነ ምህረት ዋኔን
ስጨነቅ ስጠበብ ዋኔን ስጋለጥ ያን ዕለት ዋኔን
ድንግል መድኃኒት ነሽ ዋኔን ለሰው ልጆች ተስፋ ዋኔን
ከጐኔ ቁሚልኝ ዋኔን ሳዝንና ስከፋ ዋኔን
የዓለም መድኃኒት ነሽ ዋኔን ማርያም እመቤቴ ዋኔን
በረድኤት ግቢልኝ ዋኔን ነይልኝ ከቤቴ ዋኔን
አደራሽን ማርያም ዋኔን ኪዳነ ምህረት ዋኔን
ፀጋሽን አልብሽኝ ዋኔን ኋላ ስራቆት ዋኔን
ዕርቃኔን መሆኔን ዋኔን አውቀዋለሁና ዋኔን
አልብሽኝ ፀጋሽን ዋኔን በኢያቄም በሃና ዋኔን
እስቲ ሁላችሁም ዋኔን ኪዳነ ምህረት በሉ ዋኔን
መድኃኒት ናትና ዋኔን ለሰው ልጆች ሁሉ ዋኔን
አፍሮ አይመለስም ዋኔን የቆመ ከደጇ ዋኔን
እመቤቴ ማርያም ዋኔን የጭንቅ አማላጇ ዋኔን
የአዳም መድኃኒቱ ዋኔን አንቺ ነሽ ድንግል ዋኔን
በኢያቄም በሃና ዋኔን አውጪኝ ከሲኦል ዋኔን
አንቺ የኤዶም ገነት ዋኔን የሰው ልጆች ተስፋ ዋኔን
መድኃኒት ነሽና ዋኔን አዝኖ ለተከፋ ዋኔን
የዓለምን መድኃኒት ዋኔን በጀርባሽ አዝለሽ ዋኔን
ኧረ ልምን ይሆን ዋኔን ቁራሽ የለመንሽ ዋኔን
ፍግም ብዬ ልስገድ ዋኔን ለእመቤቴ ድንግል ዋኔን
እርሷ በመሆኗ ዋኔን የሰው ልጆች እድል ዋኔን

ማን ይመራመር(አቶ ታፈሰ)

ቅኝት-ሠላምታ

ማን ይመራመር /4/
ያንተን ሥራ ያንተን ግብር ማን ይመራመር
እስቲ በስመ አብ ብዬ ሰላምታ ላድርስ
ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ
ደግሞም ላመስግንህ ብዬ ሃሌሉያ
አቤቱ አድነኝ ከዓለም ገበያ
አስረው ደበደቡት መድኃኔዓለምን
ሰማይና ምድርን ያስታረቀውን
ተይዞ ታሰረ እንደተራ ሽፍታ
እውር ስላበራ ሽባ ስለፈታ
ልብሱን ተገፈፈ ቆሞ በአደባባይ
ታስሮ ተገረፈ አጥንቱም እስኪታይ
የእሾህ አክሊል ደፍተው ተዘባበቱበት
እንደወንጀለኛ ጥፋት ሳይኖርበት
ደብድበው ሰቀሉት መድኃኒዓለምን
ምንድነው ጥፋቱ ከቶ ምን ይሆን
ያንተን ሥራ ያንተን ግብር ማን ይመራመር

የአለም መድኃኒት ክርስቶስ ስማን
ተጨንቀናልና ምህረት ላክልን
አንተ መድኃኔዓለም የሰው ልጆች ተስፋ
በምህረትህ ጐብኘን ከኖ እንዳንጠፋ
ቅዱሳት እጆቹ ተቸንክረው ዋሉ
ቅዱሳት እግሮቹ ተቸንክረው ዋሉ
በጣም አልቅሱለት ሰዎች ወዮ በሉ
እሥራኤልን መና የመገበ አውርዶ
በግፍ ተሰቀለ ለአዳም ሲል ተዋርዶ
መቃብር ቻለችው እንደ ተራ ሰው
አወይ መድኃኔዓለም ክርስቶስ ወየው
ቸሩ መድኃኔዓለም ታላቁ ባለአልጋ
ሰማይና ምድርን በቃሉ የዘረጋ
ጌታ አማኑኤል ኃያል ነው ንጉሥ
ለወደደው ሁሉ ጸጋ የሚያለብስ
ያንተን ሥራ ያንተን ግብር ማን ይመራመር
የሕይወትን እስትንፋስ እፍ ያለው በአዳም ላይ
ምድረ ቀራንዮ ዋለ በመስቀል ላይ
የተመላለሱ በገነት እግሮቹ
በሞት ተወሰደ ተጨፈኑ ዐይኖቹ
እንደ ወንጀለኛ ጥፋት ሳይኖርበት
የእሾህ አክሊል ደፍተው ተዘባበቱበት
ሰማይና ምድርን በእጁ የፈጠረ
ዓለምን ለማዳን ሞቶ ተቀበረ
በሦስተኛውም ቀን ብርሃንን ተላብሶ
በኃይሉ ተነሣ መቃብር አፍርሶ
ያንተን ሥራ ያንተን ግብር ማን ይመራመር
ወደ ሰማይ ወጣ ዓረገ በኃይሉ
ብርሃንን ላከልን ሰዎች እልል በሉ
ቸሩ መድኃኔዓለም የዓለም ሁሉ ተስፋ
በቀኝህ አቁመን መለከት ሲነፋ
ነጋሪት ሲጐሰም ለፍርድ ስትመጣ
አቤቱ ክርስቶስ በጉድ እንዳንወጣ
ያንተን ሥራ ያንተን ግብር ማን ይመራመር
በጐልጐታ ምድር መድኃኒት ተቀብሮ
ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊቶች አድሮ
በኃይል በሥልጣኑ ከሙታን ተነሣ
አበቃ ተሻረ የሰው ልጅ አበሳ
ምድረ ቀራንዮ ምድረ ጐልጐታ
የጌታን ትንሣኤ መስክሩ በተርታ
ለዓለም ግለጹ ሞቱን ትንሣኤውን
ኋላም በክብር ሆኖ ለፍርድ መመለሱን
ያንተን ሥራ ያንተን ግብር ማን ይመራመር
በክብረ መንግሥቱ ሲገለጥ በሰማይ
የሰው ልጆች ሁሉ ይሉለታል ዋይ ዋይ
አማኑኤል መጥቶ ሊያድን ዓለምን
እርቃኑን ተሰቅሎ መድኃኒት ሆነን
ያንተን ሥራ ያንተን ግብር ማን ይመራመር

አየሁኝ በህልሜ (አቶ ታፈሰ)

ቅኝት- ዋኔን
33 22 3-5 33 22 3-1
544445 1111 33 4222 22

አየሁኝ በህልሜ /2/
ሞት የተባለውን እዳ ተሸክሜ
ሰማሁኝ በዝና /2/
ቀጠሮ አክባሪ ነው ሞት አይረሳም እና ሞት አይቀርም እና
ሞት ይቅር ይላሉ ሞት ቢቀር አልወድም
አፈሩም ድንጋዩም ከሰው ፊት አይከብድም
አጠረ ቁመቴ ወዳጆቼን ባይ
እያደሩ ማነስ ለካ እንዲህ ነው ወይ
እኔ አልገዛም ሱሪ ይቅርብኝ ለራሴ
አፈር ስለሆነ የዘላለም ልብሴ
ቤት አልሠራም ይቅር ጣራና ግድግዳ
መቃብር ነውና የኔ ሳሎን ጓዳ
እባክህ አምላኬ ስማ ጸሎቴን
በእንባ ዓለም እጄ የምበላውን
እራሴን አንገቴ አልችለው ብለህ
ሁል ጊዜ ከሰው ፊት ትጥለኛለህ
አየሁኝ በህልሜ አየሁኝ በህልሜ
ሞት የተባለውን እዳ ተሸክሜ
ሰማሁኝ በዝና ሰማሁኝ በዝና
ቀጠሮ አክባሪ ነው ሞት አይቀርም እና ሞት አይረሳም እና
አይጣል አይጣል እያልን ስንለምነው
ሳናስበው ድንገት ጣለብን ምነው
ግድግዳው ቢረዝም ምንባጡ ቢያምር
የምድር ቤት ነውና መፍረሱም አይቀር
እንግዳው ሞት መጣ ኧረ ወየው ወየው
ለእግሩ ውሃ አሙቄ በርዤ ሳልቆየው
የሞትን ማዕረጉን ሁላችሁ እወቁ
ከእርሱ ቤት ይገኛል ብሩም ሆነ ወርቁ
ይኸው የዘራልን በየቀኑ ሰው
አንድም አልበቀለ የታል ቡቃያው
ከአቤል ጀምሮ ነበር የታመነ
አሁን ግን ስናየው ሞት ቀጣፊ ሆነ
አይቼ መጣሁኝ ዛሬስ በእሁድ
ሰው እንደአዝመራ በግፍ ሲታጨድ
በከንቱ ያሙታል እንዲሁ በሐሰት
ሰው በልቶ ጨረሰ እያሉ መሬት
ከምድር እስከ ሰማይ ሰው ቢያስብ ሁልጊዜ
ከሰው አልተለየም ሞትና ትካዜ
ደስታና ሐዘን ጐን ለጐን ሲሄዱ
ይጐራበቱናል ከሁለቱ አንዱ
ሁሉ በሽተኛ ሁሉ ራሴን ባይ
በቤታችን ደህና መጥፋቱ ነው ወይ
እሱን ሞት ሲጠራው በሩቁ ሰምቼ
እኔም ወይ አላልኩም ለራሴ ፈርቼ
ሰው ሁሉ በርስቱ ይጨርሳል ሀብቱን
የኋላ የኋላ ላያጣው መሬቱን
ቀኑን ባሸንፈው ሌት ሞቶ ታገለኝ
በቶሎ ሞት ናና እባክህ ገላግለኝ

እድሜዬ ዘልዛላ ነው አያልቅ በቶሎ
ከቶ መሞት ላይቀር እንደው ውልውሎ
ከፋኝ ሞቴን ስጠኝ ለማይቀረው እዳ
ደግሞ እንደ ሥጋዬ ነፍሴ እንዳትጐዳ
ወለም ዘለም እያልኩ አለቀ እድሜዬ
ሞት መምጣቱ ላይቀር ወየው መከራዬ

ገብረ መንፈስቅዱስ (አቶ ታፈሰ)

ቅኝት-ዋኔን
231111 11315
113 115 113 242

ገብረ መንፈስቅዱስ አቦዬ ጻድቁ
ኧረ እንዴት ነህ አባቴ ኧረ እንዴት ነህ መድኃኒቴ
ገደል እንደ አክርማ የሚሰነጥቁ (ኧረ ...)
ገብረ መንፈስቅዱስ ተክለሃይማኖት (ኧረ ...)
ታላቅ ክብር ያገኙ በክርስቶስ ፊት (ኧረ ...)
ለጌታቸው ታዛዥ ለዓለም አማላጅ (ኧረ ...)
በፈጣሪያቸው ዘንድ በሥላሴ ደጅ (ኧረ ...)
ጻድቃን ሰማዕታት ደናግል በሙሉ (ኧረ ...)
ሌት ከቀን ሳያርፉ ሰው ያማልዳሉ (ኧረ ..)
ድንጋይ ተንተርሰው ዳዋ እየጣሱ (ኧረ...)
በጸሎት ተጠምደው ጤዛ እየላሱ (ኧረ ...)
ገብረ መንፈስ ቅዱስ አቡነ ተክልዬ (ኧረ...)
በእናንተ ጋሻነት ልኑር ተከልዬ (ኧረ...)
የዘልዳው ኮከብ ቅዱስ ጊዮርጊስ (ኧረ...)
ተጨንቀው ሲጠሩህ ፈጥነህ የምትደርስ (ኧረ...)
አቡነ አረጋዊ ታላቁ አባት (ኧረ ...)
ጸጋ ክብር ያገኙ በሥላሴ ፊት (ኧረ ...)
ሙሽራው ሰማዕት ገብረ ክርስቶስ (ኧረ...)
መንኖ የሄደ ጽድቅ ለመልበስ (ኧረ...)
ደራጐንን በጦር ወግቶ የገደለ (ኧረ...)
ፈረሰኛው ጊዮርጊስ የልዳው ኮከብ ነው(ኧረ...)
ገብረ መንፈስቅዱስ ታላቁ መናኝ (ኧረ...)
ከዚህ ዓለም መቅሰፍት ፈጥነው ያድኑኝ (ኧረ...)
ፃድቃን ሰማዕታት አባቶች ሁላችሁ (ኧረ...)
ኢትዮጵያን ጠብቋት አደራ ተግታችሁ(ኧረ...)

በስመ አብ/አባታችን(አቶ ታፈሰ)

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
አሐዱ አምላክ ብዬ ሰላምታ ላድርስ
አባታችን በሰማይ ዙፋን ያለህ
ዘለዓለም ፀጋህ ይብዛልን ክብርህ
ለምድራችን ምህረትህ ይምጣ በተስፋ
አዘውትረህ በረከት ስጠን በይፋ
ሁሌም ጎብኘን በይቅርታ መንፈስ ሆነህ
አይጓደል እስከ ዘላለም ፀጋህ
እንዳንጠፋ በሀጢያት ቀንበር ወድቀን
አደራህን ሀይልና ብርታት ስጠን
ጠብቀን ከሚፈታተን ጠላት
እንድንወርስ ያንተን ደገኛ መንግስት
ይሁን ብለህ ይቅርታን ስጠን ምህረት
አድለን የዘላለምን ህይወት
ሰፍረህ ስጠን የመንፈስህን ስጦታ
ደስ እንዲለን ለቀንም ሆነ ለማታ
አረጋግተህ ሁልጊዜ ሰላም ስጠን
በመንፈስህ ዛሬም በደስታ ባርከን
ኃይልን ስጠን እንድናመልክህ በይፋ
እምነትንም አሳድርብን በተስፋ
ምግባችንን አንተው አስበህ ስጠን
ጠብቀን ከፈተናና ሀዘን
ሠላም ሰጥተህ ሁሌ በተስፋ ጎብኘን
ይህ እንዲሆን መልካም ፈቃድህ ይሁን
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ

ስለ ስነ ፍጥረት(አቶ ታፈሰ)

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
አሐዱ አምላክ ብዬ ሰላምታ ላድርስ
ለዓለም ጌታ ለምድር ለሰማይ ንጉስ
ሥላሴም ሰውን እንፍጠር ብለው
ተነሳሱ አልቀረምና ወዲያው
በመልካችን እንደአምሳላችን አድርገን
እንፍጠር በአንድነት ሆነን ሰውን
ወዲያውንም አዳም ሄዋንን ፈጠሩ
በህግ ሆነው ትዕዛዝ ጠብቀው ሊኖሩ
በዚህ አይነት በተድላ ገነት ሲኖሩ
ተሳሳቱ ተለወጠና ነገሩ
ነገር ግን ከጥቂት አመታት በኋላ
ተታለው ሞኞች ሆኑና ተላላ
በእባብ ተንኮል በኃጥያት ቀንበር ወድቀው
ተዋረዱ እፀ በለስን በልተው
እንዳትበሉ የተባሉትን እንጨት
ቆርጠው በሉ የጥፋት ፍሬ ቅንጣት
ሲፈጥራቸው አዳም ሄዋንን ከጥንት
እንዲያውቁለት ሰርቶ ነበረ ሥርዓት
እንዳትበሉ የእፀ በለሲቱን ፍሬ
ትዕዛዜን አስጠነቀኩኝ ነግሬ
እንዳትነኩ የእፀ በለስን ቅንጣት
ነገርኪችሁ ገና አስቀድሞ ከጥንት
እነርሱ ግን በእባብ ተንኮል ተታለው
ቀጥፈው በሉ የጌታን ትዕዛዝ አቃለው
እሷን በልተው አምላክ የሆኑ መስሏቸው
ተታለሉ ጥፋት ሆነና ስራቸው
በዚህ ጊዜ በኃጥያት ቀንበር ወድቀው
ተባረሩ ከገነት ተድላ ወዲያው
እየኖሩ እጅግ በጣም ተዋርደው
አሳለፉ ብዙ ዘመናት ተሰደው
/በበገና ብቻ/
ተገፈፉ ፀጋ እግዚአብሄርንም አጡ
ለዘመናት አይቀጡ ቅጣት ተቀጡ
ተፀጽተው እንባ አፈሰሱ ወድቀው
ዳግመኛም ደም አለቀሱ ወዲያው

በሶስተኛው እያለቀሱ ባክነው
ተጨነቁ እጅግ በጣሙን አዝነው
አዳምም ከገነት ተድላ ተባሮ
ይኖር ነበር እያለቀሰ አምርሮ
እግዚአብሄርም መራር እንባውን አየና
ተስፋ ሰጠው አድንሃለሁ አለና
አዳም አዳም አይዞህ ጠብቀኝ እመጣለሁ
ከልጅ ልጅህ መጥቼ ስጋ እለብሳለሁ
ተወልጄ ከድንግሊቱ ልጅህ
እመጣና አድንሃለሁ አይዞህ
ጀርባዬንም ለገራፊዎች ሰጥቼ
ጊዜው ሲደርስ አድንሃለሁ መጥቼ
ተሰቅዬ በቀራንዮ ተራራ
ተቀብዬ እጅግ አስፈሪ መከራ
ትድናለህ አይዞህ በተስፋ ተድናና
የአምላክህ ቃል ከቶ አይሻርምና
የሰው ልጆች በሀጥያት መርገም ሲኖሩ
ሲሰቃዩ ለብዙ ዘመን ነበሩ
በአዳም በደል ፍጥረቱ ሁሉ ተግዞ
ይኖር ነበር አንገቱን ደፍቶ ተክዞ
ጌታም አይቶ የአዳምን ሀዘን ጭንቀት
ተናገረ የህይወት ማዳን ትንቢት
አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን
ሲፈፀም ተወለደና መድሃን
በትንቢቱ የነገረውን አስታውሶ
በመስቀል ላይ መድኃኒት ደሙን አፍሶ
በችንካሩ ቅዱስ ስጋውንም ቆርሶ
የአዳምን ዘር ገነት አስገባው መልሶ
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
አሐዱ አምላክ እስከዘላለም ድረስ

ስለ ልደት/ስደት(አቶ ታፈሰ)

እንዲህ ነበር የመድኃኒዓለም ልደቱ
ከድንግል የተወለደው ከእናቱ
ተፀንሶ በቅዱስ ገብርኤል ብስራት
ተወለደ በተነገረው ትንቢት
በብስራቱ ጸነሰችና ድንግል
በበረት ወለደችልን በጎል
ሄሮድስም የጌታን መወለድ ሰማና
ተቃጠለ በቅናት መንገድ ሄደና
የእርሱን መንግስት የሚቀናቀን መስሎት
ተሸበረ ልቡን አወከው ቅናት
በዚህ ጊዜ በምቀኝነት ደበነ
ጌታን ሊገል አስቦ ተንኮል ወጠነ
በእርሱ ሰበብ ብዙ ህፃናት አረደ
ደማቸውም እንደጎርፍ ውሃ ወረደ
የቅድስት የድንግል ማርያም መከራ
አይረሳም ሁሌ ይኖራል ሲወራ
በሄሮድስም አዝና አልቅሳ ከፍቷት
ተንገላታች በምድረ ግብፅ ስደት
ልጇን አቅፋ በጎዳድ ቆላ በረሃ
ተሰደደች እንደ ምስኪኖቹ ደሃ
በበረሃው ተንከራተተች ተጨንቃ
የመከራው የጭንቋ ጊዜ እስኪያበቃ
በዚህ አለም በኖረችበት ዘመን
ተሳቀቀች እንዳይገሉባት ልጇን
ቁራሽንም ውሃ ለመነች ተርባ
ለአንድ ልጇ ሆዷ ተጨንቆ እየባባ
በቆላና በደጋው ምድር ሳይቀር
ተንገላታች በሸንተረሩ ምድር
በየዋሻው በየፍንኩታው አደረች
በመጨነቅ ልጇን ገደሉት እያለች
ረሃብና ሀዘን መከራ ጭንቀት
ደረሰባት በስደታቸው ወራት
ጊዜው አልፎ የተንከራተቱት ሲያበቃ
ለመመለስ ትመኝ ነበር አጥብቃ
ጌታን አቅፋ እንደባይተዋር ከርታታ
ደረሰባት ረሀብ ጥማት በተርታ
ተሰደደች ሶስት ዓመትና መንፈቅ
የስቃዩ የእንግልቱ ጊዜ እስኪያለቅ
ደረሰና መመለሻቸው ወራት
ተመለሱ ገቡ አገራቸው ናዝሬት
በልጇ ሞት በመድኃኒዓለም ስቅለት
ደርሶባታል ከባድ መከራ ጭንቀት
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
አሐዱ አምላክ እስከዘላለም ድረስ

ስለ ጥምቀት/ሆሳዕና(አቶ ታፈሰ)

ጌታችን ይታዘዝ ነበር በብርቱ
እንጨት ሰብሮ ውሃ እየቀዳ ለእናቱ
እስኪፈጸም የህፃንነት ወራቱ
እንዲህ ሆኖ ቀስ በቀስ ነበር እድገቱ
ኋላም አድጎ እድሜው ሲሞላ ሰላሳ
ለመጠመቅ አስቦ ሊሄድ ተነሳ
ዮሐንስን አጥምቀኝ አሁን አለው
እንዲያጠምቀው ሀይልና ብርታት ሰጠው
ተጠመቀ በዮርዳኖስ ወንዝ ጅረት
ለኛ ብሎ ሳይስፈልገው ጥምቀት
በመጥምቁ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ
ይፆም ጀመር እጅግ በጣሙን ተጨንቆ
ገዳም ገብቶ አርባ ቀንና ሌሊት
ፆሞ አሳየን እንዲሆንልን ትምህርት
ጊዜው ሲደርስ የመምህርነት ወራቱ
አስተማረ በይሁዳ ምድር በብርቱ
ሙታንንም በየወገኑ አስነሳ
ሽባ ሳይቀር እውር ፈወሰ አንካሳ
ተዘዋውሮ አስተማረና ወንጌል
ሂዱ አምጡ የአህያይቱን ግልገል
በፍጥነት ሄዳችሁ አምጡ አሁን
ብሎ አዘዘ ከተማሪዎች ወገን
ተቀምጦበት በአህያይቱ ግልገል
ይጓዝ ጀመር በከተማይቱ መሐል
ህዝቡ ሁሉ በመንገዱ ዳር ቆመው
ተቀበሉት ተሰምቷልና ዝናው

በውርንጭላ ተቀምጦ መቅደስ ሲገባ
እልል አሉ እያስተጋቡ ጭብጨባ
ብዙዎቹ ልብስ አነጠፉ ጎዳና
ስለ ክብሩ የአለም መድኃኒት ነውና
ህፃናቱም በእናቶች ጀርባ ታዝለው
በደስታ ይጮሁ ነበር አይተው
ገሚሶቹም በእጃቸው ይዘው ዘንባባ
እልል አሉ ከቤተ መቅደስ ሲገባ
ሆሳእና ለዳዊት ልጅ ይሁን እያሉ
ዘመሩለት ህፃን አዋቂ በሙሉ
የዘንባባ ዝንጣፊውን ይዘው
ለዳዊት ልጅ ክብር ይሁንለት ብለው
ዘመሩለት የምድር ድንጋዮች ሳይቀሩ
አሸብሽበው በደስታ ሆነው ጨፈሩ
ህፃናቱም ጡት የሚጠቡት ሳይቀሩ
እየጮሁ ለፈጣሪያቸው ዘመሩ
ጌታችንም በአህያ ጀርባ ተቀምጦ
ተክዘና በሀዘን ማእበል ተውጦ
ሲቃረብ ወደ ሀገሪቱ ሊገባ
አፈሰሰ እጅግ የመረረ እንባ
በጣሙን ልቡ አዘነ ተነክቶ
ተናገረ ትንቢት ከሀሳቡ አንቅቶ
በትዝብት የሀገሪቷን ጥፋት አየና
ትጠፊያለሽ አይቀርልሽም አለና
ወዮልሽ የኢየሩሳሌም ምድር
ተብተሻል መጥፋትሽ እንደሆን አይቀር
ወዮልሽ የኢየሩሳሌም ከተማ
ቢመክሩሽም ሆነሻልና የማይሰማ
ስለዚህም ቅጣት መምጣቱም አይቀር
እግዚአብሄርም ብዙ ታግሶሽ ነበር
ነገር ግን ቃሉን አልሰማ ብለሽ
ፈጣሪሽን አሳዘንሽና በደልሽ
በሀጥያትሽ አዘቅት ቁልቁለት ወርደሻል
የማይቀር ነው የጥፋት ቀንሽ ይመጣል
በትንቢቱ የወደፊቱን አስታውሶ
ተናገረ መራሩን እንባ አፍስሶ
የኋላውን የሀገሪቷን ጥፋት አየና
አለቀሰ ወዮልሽ አንቺ አለና
በጣም አዝኖ አንገቱን ቁልቁል ደፋና
አለቀሰ ሩህሩህ አባት ነውና
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
አሐዱ አምላክ እስከዘላለም ድረስ

ስለ ሥነ-ስቅለት(አቶ ታፈሰ)

በስመ አብ ብዬ እስቲ ሰላምታ ላድርስ
ለአብና ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
እስቲ ላስታውስ የህማማቱን ሳምንት
የጌታዬን የክርስቶስን ስቅለት
እንደዚህ ነው የመድኃኒዓለም መከራ
ያሰቅቃል በሰው አንደበት ሲወራ
አይሁድም በምቀኝነት ተነስተው
መከሩበት ጌታን ለመግደል አሲረው
ከሐዋርያት አንዱን ይሁዳን ጠርተው
ከሱ ጋራ በሚስጥር መሐላ ምለው
ፈጣሪውን በመሳም ሊያሲዝ ጠቁሞ
ሊመራቸው የጌታን ጉንጮቹን ስሞ
ሰላሳ ብር የእጅ መንሻውን ሰጠው
ሊያሳያቸው ጌታውን ሄዶ ሳመው
ጌታም አውቆ ምነው ነከስከኝ አለው
ወይ ይሁዳ እንደምን ያለ ሰው ነው
ፈጣሪውን በሰላሳ ብር ሸጠው
እንዲህ ነበር የህማማቱ ስቃይ
የሚያሰቅቅ በሰው አእምሮ ሲታይ
ሰኞ መክረው ማክሰኞም ዋሉ ሲያሴሩ
እሮብም አፅንተው በጣም መከሩ
ሀሙስ ሌሊት ይዘው የፊጥኝ አስረው
አቀረቡት ፍርድ አደባባይ ወስደው
አስፈረዱ ሞት ይገባዋል ብለው
እየመቱ በትልቅ በትር መትሮት
አቀዳጁት የአክሊለ እሾክን ብረት
የአይሁድ ንጉስ አንተ ነህ እንዴ እያሉ
አፌዙበት ተሳለቁበት በሙሉ
ተረባርበው በግፍ ገረፉት ወስደው
ሳይበድል ወንጀለኛ ነህ ብለው
ሲያንገላቱት ሲደበድቡ በተራ
አደረሱት ከቀራንዮ ተራራ
አሸክመው ከባዱን መስቀል በግፍ
አሰቃዩት ፈጣሪያቸውን በግርፍ
በእለተ አርብ ስድስት ሰአት ሲሆን
ሰቀሉት የዓለም ብርሃን ጌታን
ነፍሱን ሰጠ ዘጠኝ ሰአት ሲሆን
ተናወጠ ምድርና ሰማይ በእውን
እርቃኑን መሆኑን አይታ ፀሐይ
ጨለመች ብርሃኗ ታጣ ከላይ
ከዋክብትም ከሰማይ ረግፈው አለቁ
በቦታቸው አንድም ሳይተርፉ ወደቁ
ጨረቃዋ ብርሃኗን ነፍጋ ጨለመች
ፈጣሪዋ እርቃኑን ሆና ስላየች
መጋረጃው ከቤተ መቅደስ ያለው
ተቀደደ ከታች እስከላይ ወዲያው
ተሰቅሎም ዘጠኝ ሰአት ሲሆን
ተፈፀመ ብሎ አሰምቶ ቃሉን
ይህን ነግሮ ሞትን ቀመሰ መድኅን
ወደ ማታ ለንጊኖስ የሚባለው ሰው
የጌታን ጎን በተሳለ ጦር ወጋው
ቢወጋው ደምና ውሃ ፈሰሰ
የአዳምን ዘር በደሙ ፈሳሽ ቀደሰ
ውሃውም ለጥምቀታችን ሆነን
ስጋ ደሙን መዳኛ ብሎ ሰጠን
ብሉ ጠጡ ስጋዬንና ደሜን
ይህን ብሎ አንድነት አድርጎ ቸረን
ሁለት ሰዎች አረጋውያን ነበሩ
አወረዱ የጌታን ስጋ ሊቀብሩ
ገንዘው በሀዘንና በለቅሶ

እስኪነሳ መቃብር በሀይል አፍርሶ
ቀበሩት እጅግ በመራር ሐዘን
ስለሞተ የአለም መድኃኒት መድኅን
ቅዳሜም ተቀብሮ ዋለ ጌታም
በመሞቱ ሳይንቀሳቀስ ምንም
እሁድ ሌሊት መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል
ከሙታን እርሱ ተነሳ በኃይል
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከዘላለም ድረስ

ስለ ትንሳኤ/ዳግም ትንሳኤ(አቶ ታፈሰ)

በአዳም በደል አቅርቦ ራሱን ለካሳ
ደመሰሰ የሰውን ልጆች አበሳ
በሲኦል ተግዞ ላለ ነፍሳት
አበሰረ የዘላለምን ህይወት
በአርባ ቀኑ ወደ ሰማያት አረገ
የዓለምን ህዝብ በሙሉ ነፃ አደረገ
በፈቃዱ ነፍሱን ከስጋው ለይቶ
የአዳምን ዘር ከርስቱ አኖረ አግብቶ
የሚያስለቅስ እጅግ አስፈሪ መከራ
ተቀበለ በቀራንዮ ተራራ
እናፍስስ መራራ እንባ ለጌታ
ለሞተልን እንዲሆንልን ውለታ
ብናስብም መከራውንም ሁልጊዜ
በመጨነቅ በሀዘንና ትካዜ
አባታችን የምድር የሰማይ ንጉስ
አይተህ ማረን ሞተን ከፊትህ ስንደርስ
ይቅር በለን እንደሀጥያታችን ሳትፈርድ
በፍፃሜው ወደዚህ አለም ስትወርድ
በዚያን እለት ለፍርድ ስትመጣ ጌታችን
ፈጥነህ ማረን ክፋት ነውና ስራችን
ይቅር በለን ምህረት ልማድህ ነውና
አንተው ባርከን ቅዱስ እጅህን ዘርጋና
አትንፈገን ስጋና ደምህን በእውነት
እንድንወርስ ያንተን ደገኛ መንግስት
ጌታ ሆይ የምድር የሰማይ ንጉስ
እንዳናፍር ሞተን ከፊትህ ስንደርስ
ክርስቶስም የዓለም መድኃኒት ነህና
አደራህን በበደላችን አትፅና
በፍርድ ቀን በአስፈሪ ግርማህ ክብርህ
ስትመጣ በእሳት ዙፋን ላይ ሆነህ
ፃድቃንም የብርሃን ቀሚስ ለብሰው
በመደሰት በቀኝህ በኩል ቆመው
ተስፋ አድርገው የምትመጣውን መንግስት
የሌለባት ረሀብ ጥማት ውድቀት
ሀጥአንም በግራ በኩል በመሆን
ሲጠብቁ የማያዳግም ፍርድህን
በዚያን እለት አደራ ጌታ ማረን
ተፀይፈህ አትመልስብን ፊትህን
አይተህ ማረን አዛኝ ሩህሩህ አባት
ተማፅነናል በድንግል ማርያም ንጽሕት
አንተ ምራን ወደ ዘላለም ህይወት
እንድንወርስ የማያልፈውን መንግስት
ተማፅነናል በወለደችህ ድንግል
አትንፈገን የቅዱሳንን እድል
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከዘላለም ድረስ

ወዳጄ ወዳጄ(አቶ ታፈሰ)

ወዳጄ ወዳጄ ወዳጄ ወዳጄ
ወዳጅ ያዝናል እንጂ መቼ አብሮ ይሞታል
ኧከደከድዬ በዚህ ይካተታል በዚህ ይካተታል

እስቲ በስመአብ ብዬ ሰላምታ ላድርስ
ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ለመንፈስቅዱስ
ደግሞም ላመስግንህ ብዬ ሃሌሉያ
አቤቱ አድነኝ ከዓለም ገበያ ከዓለም ገበያ
አስረው ደበደቡት መድኃኒዓለምን
ሰማይና ምድርን ያስታረቀውን ያስታረቀውን
ተይዞ ታሰረ እንደ ተራ ሽፍታ
እውር ስላበራ ሽባ ስለፈታ ሽባ ስለፈታ
ልብሱን ተገፈፈ ቆሞ በአደባባይ
ታስሮ ተገረፈ አጥንቱም እስኪታይ አጥንቱም እስኪታይ
የእሾህ አክሊል ደፍተው ተዘባበቱበት
እንደወንጀለኛ ጥፋት ሳይኖርበት ጥፋት ሳይኖርበት
ደብድበው ሰቀሉት መድኃኒዓለምን
ምንድነው ጥፋቱ ከኖ ምን ይሆን ከኖ ምን ይሆን
ቅዱሳት እጆቹ ተቸንክረው ዋሉ
ቅዱሳት እግሮቹ ተቸንክረው ዋሉ
በጣም አልቅሱለት ሰዎች ወዮ በሉ ሰዎች ወዮ በሉ
እስራኤልን መና የመገበ አውርዶ
በግፍ ተሰቀለ ለአዳም ሲል ተዋርዶ ለአዳም ሲል ተዋርዶ
መቃብር ቻለችው እንደ ተራ ሰው
አወይ መድኃኒዓለም ክርስቶስ ወየው ክርስቶስ ወየው
የህይወትን እስትንፋስ እፍ ያለው በአዳም ላይ
ምድረ ቀራንዮ ዋለ በመስቀል ላይ ዋለ በመስቀል ላይ
የተመላለሱ በገነት እግሮቹ
በሞት ተወሰደ ተጨፍኖ አይኖቹ ተጨፍኖ አይኖቹ
ሰማይና ምድርን በእጁ የፈጠረ
አለምን ለማዳን ሞተ ተቀበረ ሞተ ተቀበረ
በሶስተኛውም ቀን ብርሃንን ተላብሶ
በኃይል ተነሳ መቃብር አፍርሶ መቃብር አፍርሶ

ወዳጄ ወዳጄ(አቶ ታፈሰ)

ወዳጄ ወዳጄ ወዳጄ ወዳጄ
ወዳጅ ያዝናል እንጂ መቼ አብሮ ይሞታል
ኧከደከድዬ በዚህ ይካተታል በዚህ ይካተታል

እስቲ በስመአብ ብዬ ሰላምታ ላድርስ
ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ
ደግሞም ላመስግንህ ብዬ ሃሌሉያ
አቤቱ አድነኝ ከዓለም ገበያ

በስምንተኛው ሺህ አለም ሲፈራርስ
በፅድቅህ አስበን አቤቱ ክርስቶስ
በዳግመኛ ልደት ሙታኖች ሲነሱ
በቃልህ ሲገፈፍ የሰማያት ልብሱ
ምድርና ሰማይ ከቦታው ሲጠፋ
አድነን ጌታ ሆይ መለከት ሲነፋ
ያኔ ስትገለጥ በታላቁ ክብርህ
አድነን ክርስቶስ ጌታ ሆይ አደራ
በመንግስተ ሰማይ በማያልፈው ስፍራ
በክብር በደስታ አስቀምጠን አደራ
ሰማያት ሲናጋ ምድሩ ሲፈራርስ
አቤቱ አድነን ጌታ ሆይ ክርስቶስ
ውጡ ግቡ ብለህ ሁሉን ስታደራጅ
ቸር አምላክ ነህና አታስቀረን ከደጅ
ያለ ነው ከጥንትም ዛሬም ቸርነትህ
አታሳጣን ስፍራ ከሰፊው መንግስትህ
ዋጋ ስትከፍል እንደየሥራችን
በግራ አታቁመን አደራ አባታችን
ነጋሪት ሲነሰም መለከት ሲነፋ
ሁሉን ቻይ ነህና በከንቱ እንዳንጠፋ
ሰማይ ምድር ፈርሶ መድረሻ ሲጠፋን
ቸር አምላክ ነህና ጨክነህ አታጥፋን
ከገሃነም ቦታ እጅግ ከሚያስፈራ
አድነን ጌታ ሆይ ከእንዲህ ያለ ስፍራ
ተማፅነን ወድቀናል በቆረስከው ስጋህ
ተማፅነን ወድቀናል ባፈሰስከው ደምህ
ተማፅነን ወድቀናል በማያሻር ቃልህ
በቀኝህ አቁመን ክርስቶስ አደራ
መከራው ሲወሳ የመድኃኒዓለም
እጅግ ያስለቅሳል እስከዘላለም
ግንድ ታሸክሞ አሸርጦ ጨርቅ
መከራው በዝቶበት ሲነሳ ሲወድቅ
ወጣ ቀራንዮ ከተራራው ላይ
መከራ ሊቀበል ለሰው ልጅ ሲሳይ
እርቃኑን ሳያፍር በጀርባው ተንጋሎ
ዋለ ተቸንክሮ ፍፁም ምስኪን መስሎ
ሰማያት ተናጉ ተናወጸ ምድር
አይሁድ ያልጠበቁት ብዙ ታየ ተአምር
በጣም ተንቀጥቅጣ ግዑዟ መሬት
የኢየሱስን መስቀል መያዝ አቃታት
ጨረቃና ፀሀይ ደግሞም ከዋክብት
መስክሩ በተርታ የጌታን ስቅለት
ሰማይና ምድር እናንተም መስክሩ
የጌታን ትንሳኤ ለዓለም ሁሉ አውሩ
አምላክ ለኛ ብሎ በመስቀል ላይ ሞቶ
ፀሃይ በማየቷ ጌታዋ ተራቁቶ
ብርሃኗን ነፈገች ተሳቃና ፈርታ
ተራቁቶ ስላየች ጌታ በአዳም ፋንታ
ጨረቃም ደም ሆነች ከዋክብት ረገፉ
ሀሞት ስለጋቱት በከበረ አፉ
የከበረ ስጋው በችንካር ተቆርሶ
ዓለምን አዳነ ደሙንም አፍስሶ
ዋለ ቀራንዮ ክርስቶስ ተሰቅሎ
እኛኑ ለማዳን ለሰው ልጆች ብሎ
ቀራንዮ ዋለ ተሰቅሎ እንደዋዛ
ከሀጢያት አላቆ ነፍሳትን ሊገዛ
ግንድ ተሸክሞ ሲወድቅ ሲነሳ
ዓለምን አዳነ ከሀጢያት አበሳ
ለፍርድ መመለሱን ሰማያት መስክሩ
አስጠንቅቁ ለዓለም ለህዝቡም ንገሩ
ህዝቦች ተጠንቀቁ እንዳትታለሉ
ለፍርድ መምጣቱንም ንገሩ ለሁሉ
በግራ እንዳንቆም ተራቁተን ከፀጋ
በንስሐ ታጥበን በፀሎት እንትጋ
የአዋጅ ድምፅ ሲነገር ፍርድ ሲያስተጋባ
በቀኝህ አቁመን በጭንቅ እንዳንገባ
ወዮ በዚያን እለት በክብር ሲገለጥ
የት እንገባ ይሆን ወዴትስ ለማምለጥ
ይህን ጊዜ እንበርታ ሳለን በህይወት
ጉድ እንዳያደርገን መቶ በድንገት
እውራንን ዳሰው ያበሩ ጣቶቹ
በደም ተለወሱ ቅዱሳት እጆቹ
ሁሉን ማድረግ ሲችል ለአዳም ሲል ተዋርዶ
ተቀበለ ስጋው ከሰማያት ወርዶ
ከደጅሽ ቆሚያለሁ ኪዳነምህረት
ታማልጂኝ ብዬ ደጅ በመጽናት
ለፍርድ ሲገለጥ ልጅሽ በዚያን እለት
እንድታማልጂን አደራሽን እመቤት
ኪዳነምህረት ነሽ የዓለም ሁሉ ቤዛ/2/
ሰማይና ምድርን ልጅሽ የሚገዛ
በምድራዊም ሆነ በፈተና ቦታ
ማርያም ትጠብቀን እጆቿን ዘርግታ
እንዴት እድናለሁ በየቱ ብልሃቴ
አንቺ ካልጠበቅሽኝ ማርያም እመቤቴ
እመቤቴ ማርያም ሚስጥሬ ነሽና
ከስጋዬ አድኚኝ በረድኤት ነይና
ክርስቶስ አምላኬ የአለም ብርሃን
በረድኤት ናና ሁልጊዜ ባርከን
በመስቀልህ ብርሃን ባርከህ ቀድሰን
በስጋ በደምህ ዘውትር አድሰን
በወንጌልህ ፀጋ ሁሌ እንድናበራ
መትጋቱን አድለን ጌታ ሆይ አደራ

ከደጇ ይፈልቃል (አቶ ታፈሰ)

ቅኝት- ሠላምታ
423 224 542 222
423 115 113 224 542 222

ከደጇ ይፈልቃል ማርና ወተት
አዛኝቷ ድንግል ኪዳነ ምህረት /2/
እስቲ ልናገረው የእመአምላክን ዝና
የኪሩቤል መቅደስ የሱራፌል ጽና /2/
ኤልያስ የጠራት የበራች ደመና
የኢሳይያስ ትንቢት የገብርኤል ዜና /2/

የቅዱሳን ምግብ የእስራኤል ደመና
ለፍጥረቱ አዛኝ ርህሩህ ነኾና /ናትና/ /2/
ዘካርያስ ያያት የተቋም ላይ ፋና
መድኃኒት ላለሙ የጽድቅ ጐዳና
የረሃብ መድኃኒት የድውያን ጤና
ስሟ ስንቅ እኮ ነው ተብሎ ተነግሯል
በእንተ ማርያም ብሎ ማን ሳይበላ ያድራል/2/
ስሟ እንቅ እኮ ነው ለሚኼድ ተከፍቶ
ጠግቦ ያድራልና የእርሷኑ ስም ጠርቶ /2/
የረሃብተኞች ምግብ የድኩማን ጽናት
የርህራሄ ምንጭ ነይ ኪዳነ ምህረት
ከደጇ ይፈልቃል ማርና ወተት
አዛኝቷ ድንግል ኪዳነ ምህረት
ስለ ማርያም ብሎ ስሟን ለሚጠራ
የትም ቦታ ኼዶ ይጠግባል እንጀራ
የቅዱሳን ምስጢር ጽላተ ጽዮን
ምስጋና ይድረስን ለሰጠን አንቺን /2/
ስለ ክብሯ ላቅርብ ምስጋና ውዳሴ
በጸሎት በስግደት በመጨነቅ ነፍሴ /2/
የማማለድ ሥልጣን አላት ኪዳነ ምህረት
እራሱን ዝቅ አድርጐ አዝኖ ለለመናት /2/
እሳት ተዋህዷት ሳትቃጠል ደህና
የእግዚአብሔር አብ ቃሉን ወልዳዋለችና/2/
ስሟ ስንቅ እኮ ነው ለሚሄድ ተከፍቶ
ጠግቦ ያድራል እና የእርሷኑ ስም ጠርቶ /2/

ዘማሪት ሶስና

በስመ ልዑል (ዘማሪት ሶስና)

(ሰላምታ ቅኝት - ይበላ ሀላ)

በስመ ልዑል በስመ አብ
በመንፈስ ቅዱስ ቅኔ ላቅርብ
ፈጣሪ በሰው ትዳኛለህ
ደህ ፊት ቆመህ ሲከስህ ደህ
አባቴ ሞኙ አዳም ተላላ
በጠላት ምክር በለስ ትበላ
አባቴ ምነው አዳም አጅሬ
ህግን አስጥሶ ከሰሰህ አውሬ
እንደምትነግስ ነግሮህ ቀጣፊ
ሽሮ አለበሰህ ቅጠል ረጋፊ
ጠላት ሲመክር ተደግፎ ዛፍ
ለካ አለ ቅጣት ጸጋ መገፈፍ
የብርሃን ጸጋ የብርሃን ካባ
በለስ ስትበሉ ወዴት ገባ
ትዕዛዝ መጣስ ህግን መድፈር
ሞትን ያመጣል ያገባል ከአፈር
ሄዋን እናቴ አታላይ ሰምታ
እርቃኗን ቆመች ጨለማ ገብታ
ማልቀስ ደግ ነው ያሰጣል ዋጋ
ንስሀ መግባት ያስገኛል ፀጋ
ፈጣሪያችን ሆይ ህግን ሰርተህ
እኛ ብንሸረው ምን አመጣህ
ላትጨክን ትራራለህ
ማን ያከብርሃል ሆነህል ደህ
አዳም ዘንግተህ ሄዋን ስተሽ
እባብን አምነሽ አውሬ ሰምተሽ
እንዴት ከጠላት ትመክሪያለሽ
አዳም ሳይሰማ ትቀጥፊያለሽ
እኔ አላማህም አዳም ንጉስ
ንስህ እኮ ነው የሔዋን ፈውስ
ንስህ ገብቶ በትህትና
ልጆችን ማዳን ሙያ ነውና
አዳም ልጆችህ ህጉን ሰርዘው
ሄዋን ልጆችሽ ፈጣሪን ረስተው
አውሬውን ወደው ጠፍተዋልና
ቆመዋል ይኸው በሞት ጐዳና
አዳምም ጮኸህ ሄዋን ለምነሽ
አንተ አማልደህ አንቺም አግዘሽ
ያንተ ልመና ይረዳልና
ሄዋን አልቅሰሽ ድነናልና
እንደለመነህ እዝራ ሱቱኤል
እንዳሳሰበህ ቅዱስ ሚካኤል
ራራልን ማረን ያንተ ነንና
ለምን ዲያብሎስ ኮርቶ ይፅናና
ፈቃደ ሥጋ እያታለለን
ዲያብሎስ መክሮ አንተን አስጠላን
ታውቃለህና ድካማችንን
ደምስሰህ ፋቀው በደላችንን
አምላክ አቅርበህ ልጆቼ በለን
በእመ ልዑል በድንግል ማርያም
በህያው ስምህ በመድኃኒዓለም
ሥጋ ነፍሳችን እንዳትደክም
መድኃኒታችን በአንተ እንታከም
ከላይ ዙፋንህ ጽርሐ አርያም
እዚህ የመጣህ እንዲድን ዓለም
ወዲህ ነውና ቢጠራህ አዳም
ባርከን ቀድሰን በድንግል ማርያም
በቀራንዮ ኤሎሄ ያልከው
ሰይጣንን መተህ ሀይል ያሳጣኸው
ለኛ ነውና ወደህ የሞትከው
ዲያብሎስ ይሻር ሰውን አይፍጀው
ስለነበረው አሁን ስላለው
የምታውቅ አንተ ስለሚመጣው
አትርሳን አንተ በፍርድ ሰዓት
ሲኦል ይቅርልን ገሀነም እሳት
የነበርክ ያለህ የምትኖር
ምሥጋና ይግባህ እግዚአብሔር
አሜን ይገባል ለመድኃኒዓለም
ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለም

ዋኔን (ዘማሪት ሶስና)

(በሰላምታ ቅኝት)

እስኪ ሰላም ብዬ ዋኔን ልጀምር ውዳሴ ዋኔን
አንተ አይደለህም ወይ ዋኔን ቤዛዋ ለነፍሴ ዋኔን
ምነው ከጠቢቦች ዋኔን ዝምድና ቢኖረኝ ዋኔን
ሥጋው ሞልቶ ሳለ ዋኔን መቁረጫው ቸገረኝ ዋኔን
እኔ እየመሰለኝ ዋኔን ሳላስበው ድንገት ዋኔን
ያንን ልብ ሥጋ ዋኔን ለውሻ ሰጠሁት ዋኔን
የጠቢቦች አባት ዋኔን አንተ መሰልከኝ ዋኔን
መልካም አይነት ጥበብ ዋኔን እንድትሰራልኝ ዋኔን
ጃኖማ ሁልጊዜ ዋኔን እለብስ የለም ወይ ዋኔን
ብርቅ ይሆንብኛል ዋኔን ጥበብ ለብሰው ሳይ ዋኔን
ወዳንተ ስመጣ ዋኔን መንገዱ ጠፍቶኝ ዋኔን
መልሶ መላልሶ ዋኔን እንቅፋት መታኝ ዋኔን
አዝግሜ መጥቼ ዋኔን ካንተ እንዳልገናኝ ዋኔን
ውስጥ እግሬን ሆነና ዋኔን አላስኬድሽ አለኝ ዋኔን
ሥጋዬ በአመሉ ዋኔን ሜዳ ሲል ተራራ ዋኔን
ውሃ ጠምቶት ቆሟል ዋኔን ቢመጣ መከራ ዋኔን
አምላኬ በሰማይ ዋኔን በምድርም ያለኸው ዋኔን
ሊጠፋ ነውና ዋኔን ዓለምን ታደገው ዋኔን
ብር ብር ብላ ዋኔን ሄዳ ካጠገቤ ዋኔን
ሳትመለስ ቀረች ዋኔን ተቅበዝባዧ ልቤ ዋኔን
ምርቃቱንማ ዋኔን ችዬበት ነበረ ዋኔን
አለማመኔ ግን ዋኔን ሲያዋርደኝ ኖረ ዋኔን
በልቼ እንዳላድር ዋኔን ቆርጥሜ ከጥሬው ዋኔን
መምህሩ አይደሉም ዋኔን የጐዳኝ ረዱ ነው ዋኔን
እሜቴ መቃብር ዋኔን መጥታ እንደንግዳ ዋኔን
ጥሬ አልበላም አለች ዋኔን ሥጋ ብቻ ለምዳ ዋኔን
ጫጩት ከበዛበት ዋኔን አደርኩኝ ገብቼ ዋኔን
አዬ ልብ ማጣት ዋኔን ቅንቅኑን ረስቼ ዋኔን
ሜዳውን ቢኖጡ ዋኔን አይድክሙ አይለፉ ዋኔን
የሰው ሁሉ ዕዳ ዋኔን አፋፉ ነው ክፉ ዋኔን
ወደ ኢየሩሳሌም ዋኔን ልሄድ ዅሌ ስመኝ ዋኔን
እንጃልኝ አሁንስ ዋኔን ዝቋላም እራቀኝ ዋኔን
ዛሬስ ታርቀሽ ኑሪ ዋኔን ሥጋ ከነፍስሽ ዋኔን
ጾምና ጸሎትን ዋኔን አማላጅ ይዘሽ ዋኔን
እመቤቴ ማርያም ዋኔን ሳንኪኪ ደጅሽን ዋኔን
ማርማር ብለሽ ለኔ ዋኔን ጠይቂው ልጅሽን ዋኔን

በመስቀል ተሰቅሎ (ዘማሪት ሶስና)

ቅኝት - ሠላምታ

423 224 /542 222 በበገና/(2X)
423 115 113 224 542 222

በመስቀል ተሰቅሎ እንዲያ እየቃተተ
ዓለምን ለማዳን የማይሞተው ሞተ
ከሞት ሊታደገን በመጣልን ፈጥኖ
መስቀል አሸከሙት ውለታው ይህ ሆኖ
መከራውን ሳስብ ሳስታውስ ቀኑን
ይቆስላል ይደማል ልቤ በሀዘን
መች ለእርሱ ነበረ ይህ ሁሉ መከራ
መስቀል ተሸክሞ የወጣው ተራራ
ሲያጎርሱት የሚነክስ ሰው ክፉ ነውና
እውሩን ቢያበራ ጎባጣን ቢያቃና
ጌታዬን ሰቀሉት አይሁድ ጨከኑና
ምነው አያሳዝን የአይሁድ ክፋት
የዝናቡን ጌታ ውሃ ሲነፍጉት
በተንኮል በታጢአት ቀሩ እንደሰከሩ
ሙታን ከመቃብር ተነስተው ሲያስተምሩ
እናታችን ሄዋን ወዮ በይ አልቅሺ
ያንቺን ህማም ታሞ ከሞት ሊያድንሽ
የሕያዋን ጌታ ተሰቀለልሽ
አየጉድ አየጉድ ዓለም የኋላሽ
መድኃኒት ክርስቶስ በግፍ ሞተብሽ
በመስቀል ተሰቅሎ ሥጋውን ሲቆርስ
በችንካር ተወግቶ ደሙንም ሲያፈስ
ዋለች በመከራ ድንግል ስታለቅስ
ሰውነትሽ ራደ ሀዘን ከበበሽ
ስቃይ መከራውም ዳግም ፀናብሽ
ተሰቅሎ ሥታይ አንድዬ ልጅሽ
ቢፈስም እንባዬ ሆኖ መንታ መንታ
መች ዋጋ ይሆናል ለአንዲቱ ጡብታ
ላለቀሽው ለቅሶ ድንግል የዛን ለታ
ምነው ባፅናናቻት ነፍሴ ከሷ ደርሳ
ወይ ልጄ እያለች ስትወድቅ ስትነሳ
ባለቀሽው ለቅሶ በልጅሽ ህማም
ከታጢአት ነጻሁኝ ዳንኩኝ ከገሃነም

ቸሩ መድኃኔዓለም (ዘማሪት ሶስና)

ቸሩ መድኃኔዓለም ቸሩ እግዚአብሔር
በምን ቃል አንደበት ሥራህ ይነገር
ከአርያም ክብርህ ከዙፋን ወርደህ
ከእጅህ ሥራ ጋር ከኛ ተዋህደህ
እጅግ ያሰደንቃል ያንተ ትህትና
ለአዳም ልጅ ስትሆን ህያው ምግብ ጤና
ፈጣሪ ሰው ሲሆን ሰው ሲሆን ፈጣሪ
የአዳም ታጢያት ዕዳ ሲሻር ሲሆን ቀሪ
ያንተ ስራ . . .
ሰይጣን በተንኮሉ አዳምን ቢጥለው
ከሰማያት ወርዶ ክርስቶስ አነሳው
ድሮም ከአርያም እዚህ የመጣኸው
ለማዳን ነውና ከሰይጣን ሰውረህ
ድንግል ማርያም ጌጤ የአዳም ልጅ ሲሳይ
ማደሪያ ሆነች ለአምላክ አዶናይ
ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷም የነሳ
ወልድ ዋህድ ጌታ ሞቶ የተነሳ
ያንተ ስራ . . .
አንተ ይቅር በለን ስለ በደላችን
ሁሉ አልቆብናል አይሞላም ስራችን
ሁሉ ጎዶሎ ነወ አይሞላም ስራችን
ጥንት የሌለህ አንተ ህፃን ሆነህ አንተ
አለም ናቀህ ቆሞ ዳግም እየሳተ
ያስደንቃል እንጂ ክርስቶስ ሲወለድ
ሁሉን ቻይ ፈጣሪ ለሰው ልጅ ሲዋረድ

ያንተ ስራ . . .
አልቀበል ካሉት አይሁድ በጥላቻ
መጣባቸው ስደት ሆኖ መተረቻ
በቃና ገሊላ ውሃ ወይን ሲሆን
አይሁድ ሳይረዱ የጎላ ምስጢሩን
ታውረው ደንቁረው ተመቅኝተው ትላንት
ዛሬም በጨለማ አሉ በሞት ሥርዓት
ያንተ ስራ . . .
ዲያብሎስ ተለቀ በተንኮል ብዛት
አዳምና ሔዋን ቢፈርሙለት
አምስት ሺ ዘመን አምስት መቶ ዓመት
በሲኦል ከረሙ ውሉ ጠፍቶ ከቤት
ወልደ አብ ፈጣሪ ከላይ ተመልክቶት
በዮርዳኖስ ሻረው ዶሴውን አግኝቶት
ለሲኦሉ ዶሴ እጅግ ርቆ በፊት
አርብ እለት ተገኘ በመስቀሉ መብራት
ያንተ ስራ . . .
ሰይጣን አፍሮ ጮኸ ምስጢር ቢወጣበት
በዮርዳኖስ ሲኦል ያኖረው ታይቶበት
በቀራንዮ ላይ በመስቀል ከረብታ
አምላክ ተሰቅሎ ዲያብሎስ ሲመታ
እኔ ዳንኩኝ ይኸው የታለ የሞት ካርታ
ተወግሯል በመስቀል ክብሩን ያጣ ሽፍታ
እንዲህ ከመታኸው በመስቀል በትር
እንጦሮጦስ ጣለው ከላይ አታስቀረው
እሱ ከታሰረ በእሳት ሰንሰለት
የአዳም ልጅ ይድናል ከዳግመኛ ሞት
ያንተ ስራ . . .
በዲያብሎስ ተንኮል ዓለም እየሳተ
መሬት ሲኦል ሆነች ሰው እያሟረተ
በኖህ ዘመን ጊዜ እንደሆነው ሁሉ
ዓለም ተበላሽታ እየበዛ ጥሉ
አውሬ ሰለጠነ ሰው እየመሰለ
ሁሉ አልቆብናል የሰው ሰው የታለ
እግዚአብሔር ፈጣሪ ቸር አባት ነህና
ሰውን ልብ ስጠው ልባም ጠፍቷልና
ስለ እመአምላክ ብለህ ስለ ድንግል ማርያም
ይቅር በለን አንተ እሳት ሞት አይበጅም
ያንተ ስራ . . . . . /፪/

እመቤቴ(ዘማሪት ሶስና)

እመቤቴ የፍጠረት ሁሉ አለኝታ
ክብር ለስምሽ ይገባል ላንቺ ሰላምታ
እናታችን አማላጃችን ድንግል
ተስፋችን ነሽ የጽድቅ የብርሃን አክሊል
ማርያም ሆይ አንቺ የገነት መውረሻ
እንኳን ለሰው የምትራሪ ነሽ ለውሻ
ባንቺ አምነው በቃልኪዳንሽ ተማጽነው
ገነት ገቡ ኃጥአን ስርየት አግኝተው
ባንቺ ምልጃ ባንቺ ልመና ያመኑ
በኪዳንሽ በልጅሽ አምነው የጸኑ
ለክብር በቁ ከዳግመኛ ሞትም ዳኑ
ኦሮ ከፍቶት ደሃ ሲጨነቅ በቤቱ
አይዞህ ብለሽ ተምታጽናኚው እናቱ
ሲራብ ጉርሱ ሲዝል ሲደክም ብርታቱ
አንቺ እኮ ነሽ ለችግረኛ ህይወቱ
ምጽዋት ሰጥተው ስለቅዱሱ ስምሽ
ሲደሰቱ ምእመናን በእውን ምልጃሽ
ተለይቼ እንዳልቀር ምስኪን ልጅሽ
ከጌታዬ አማልጂኝ ድንግል እባክሽ
ታውካብኝ በዓለም ጣጣ ህይወቴ
ስፍገመገም እጅግ ፀንቶብኝ ጉዳቴ
ታድኚኝ ዘንድ ከስጋ ወጥመድ ጭንቀቴ
ድረሺልኝ ድንግል ማርያም እናቴ
ሃይማኖቴ ቢታይ ቢመዘን ምግባሬ
ስለሚበልጥ ከክብሬ ይልቅ ነውሬ
በሰንሰለት እጅና እግሬን ታስሬ
በገሃነም ይበዛልና ሀሳሬ
በምልጃሽ አሁን አድኚኝ ዛሬ

ሰላም ለማርያም (ዘማሪት ሶስና)

ቅኝት - ሠላምታ
23 1555 1555 11 31132
23 15 31 113 242 45
423-1 113-1 113 242

ሰላም ለማርያም የአምላክ እናት
የአቤል የዋህት የአዳም ህይወት
እመቤቴ በምልጃሽ መድኃኒቴ ነሽ
የአብ ቃል መቅረጫ ጽላቱ የሙሴ
የመንፈስ ቅዱስ ቤት እመቃል ሞገሴ
የርኅራኄ መዝገብ እህተ መላእክት
የጻድቃን ተስፋቸው ጽላተ መለኮት
ትናንት ተጨንቀን በጨለማው ዓለም
ዛሬ ብርሃን አየን በድንግል ማርያም
የኢያቄም እንቁ የሃና ንብረቷ
ሥጋ ነፍሴን እርጂያት ይቅርላት ቅጣቷ
በወንጌል ሰማነው ድንግል የአንቺን ዜና
አማላጅነትሽ ሲገለጽ በቃና
ከዳዊትም ሰማን ድንግል ስለአንቺ ክብር
ወትቀውም ንግሥት እያለ ሲዘምር
በላዔሰብ ከሞት ከሲኦል የዳነው
በምልጃሽ ነው እንጂ መች በጥርኝ ውሃ ነው
ሊውጡኝ ቢነሱ አጋንንት በመሉ
ስምሽን ስጠራ ትቢያ ይሆናሉ
ጽዮን እመብርሃን ጽላተ ሥላሴ
የበረከት ካዝና ደመወዜና ዋሴ
ሲጨንቀኝ ሲጠበኝ ሲከፋኝ ኑሮዬ
ድንግል አንቺ እኮ ነሽ አጽናኝ አለኝታዬ
ስምሽን ስጠራ ሲታወክ ህይወቴ
አለሁልህ/ሽ በይኝ ድንግል እመቤቴ
ድንግል ሆይ አትርሺኝ የዘላለም ልብሴ
ምልጃሽ ያውጣኝ ከሞት ከከፋ ድምሳሴ

የቅዱሳን ካባ የቅዱሳን ኩታ
ጸጋ ሰማዕታት የድሆች አለኝታ
ሹመተ መሰፍንት ቅብዐ ነገሥታት
የሰሎሞን ጥበብ/ዕውቀት/ የዳዊት መዝሙራት
ዓለም የዳነብሽ ከሞት ከሲኦል
ለእኔስ እናቴ ነሽ ማርያም ድንግል
አድኚኝ እናቴ ከሥጋ ፈተና
እኔማ ያለአንቺ አልችልም ልጸና
ሸክም የከበደኝ እንግልት ሆኛለሁ
ከእኔ እንዳትለይ አደራ እልሻለሁ
አደራ እልሻለሁ ከጎኔ አትራቂ
ወዳጅ ዘመድ የለኝ ያለአንቺ ጠባቂ
ተሳክቶልኝ ባየው ሀሳቤ ምኞቴ
ድንግል ያላንቺማ መች ይፀናል ቤቴ
ልጅሽ እንዳይነሳኝ መንግሥተ ሰማያት
ከኃጢአት ጠብቆ እንዲያኖረኝ ገነት
አንቺ ንገሪልኝ ለዓለም መድኃኒት
ተስፋዬ ነሽና አትርሺኝ የኔ እናት

አድነኝ ከሞት (ዘማሪት ሶስና)

ቅኝት -

አንተ ሠርተህ ነበር ትልቅ አዳራሽ አድነኝ ከሞት
አውሬ አስገብቼ አረኩት ብላሽ " "
አንተማ ሰጠኸኝ የተከበረ ዕንቁ " "
እኔ ግን ተሳነኝ ዋጋውን ማወቁ " "
አንተ ለኔ ታማኝ እኔ አደራ በላ " "
በቤትህ አስገባሁ ጅብ ቀበሮ ተኩላ " "
አንተ ሰፍተህ ነበር መልካም አገልግል " "
እኔ ግን አጋጥሞኝ ልክስክስ እድል " "
ማፈሻ አደረኩት የአመድ የከሰል " "
በፈቃደ ሥጋ ሰይጣን ሲያገብረኝ " "
አንተ አስረህ ያዘኝ ለጠላት አትስጠኝ " "
አሁን ግን ፈለኩህ ጮልጥ ሳትል ነፍሴ " "
ከጅብ አፍ አስጥለኝ የአብርሃሙ ሥላሴ " "
ለሰው የሚሻውን መሻቱን አውቀህ " "
በፈቃድህ ሁሉን ትሰጠዋለህ " "
ለጽድቅ የሚያበቃ ግብርም ባይኖረኝ " "
በምህረትህ አንተ ከሞት አድነኝ " "
ደካሞች በረቱ ብርቱዎች ደክመው " "
አንተን አምነው ዳኑ አንተን ተማፅነው " "
ያመሰግኑሃል መናንያን ሁሉ " "
ድንጋይ ተንተርሰው ቅጠል እየበሉ " "
በፍጹም ልብ ሆነው ጌታ ላመኑህ " "
አምባና መጠጊያ ጋሻም አንተ ነህ " "
በምህረት አስበህ ችግረኛውን " "
ታብስለታለህ መሪር እንባውን " "
ሁሉን ስታሳልፍ በጌትነትህ " "
አንተ አታልፍም ከቶ ሁሌም ሕያው ነህ " "
ባህር ውቅያኖስ ሳይሆኑህ ወሰን " "
ትገዛለህና አንተ ዓለምን " "
ዓለምን ለመምሰል እኔስ አልጥርም " "
በአንተ አምኛለሁ ከቶ አላፍርም " "
ለሰው ልጅ በሙሉ ሰጠህ ሕይወትን " "
በልተው እንዲድኑ ሥጋና ደምህን " "
ንስሐ የገባ በደለኛውን ሰው " "
ከበደሉ አንፅተህ ለጽድቅ አበቃኸው " "
እንደ ቸርነትህ ካልሆነ ጌታዬ " "
እኔ አልድንምና በዚህ በሥራዬ " "
እየኝ ተመልከተኝ በምህረት ዐይንህ " "
ምስጋና እንዳቀርብ ለቅዱስ ስምህ " "
ስለ ቸርነትህ ጌታ መድኃኔዓለም " "
ምስጋና ይድረስህ ዛሬም ዘለዓለም " "
አድነኝ ከሞት

አስቀድሞ (ዘማሪት ሶስና)

አስቀድሞ ነፍሱ ሳትወጣ በፊት
እናቱን ቆማ ስታለቅስ ቢያያት
ለዮሐንስ አደራ ብሎ ሰጣት
ይርዳሽ ያፅናሽ ይህ ልጅሽ ነው አላት
እሱንም ቆሞ ሲያለቅስ ቢያየው
ቢወደው ለእናቱ አደራ ሰጠው
ዮሐንስም እያለቀሰ በሞቱ
እናቱን ወስዶ አኖራት ከቤቱ
ሊፈፀም የተናገረው ዳዊት
አይሁድ ጌታን ውሃ ጠማኝ ሲል ሰሙት
መጻጻውን ውሃ ቀላቅለው ሰጡት
ቀመሰልን ያን የሰጡትን ሃሞት
ተፈፀመ ትንቢቱ ሁሉ አሁን
ይህን ብሎ ዘለፍ አድርጎ ራሱን
በስልጣኑ ከስጋው ለያት ነፍሱን
በነፍስ ወርዶ ነፍሳት ካሉበት አዘቅት
ነፍሳትን የወረዱትን ከጥንት
ከዛ አውጥቶ ወስዶ አስገባቸው ገነት
ተጠራጥሮ አንዱ ሀራዊ ሞቱን
ሞተ ብሎ በጦር ቢወጋው ጎኑን
አፈሰሰ ከውሃ ጋራ ደምን
አይሁድም እርግጥ መሞቱን አውቀው
ሳያዝኑለት ነገ ሰንበት ነው ብለው
አይደር አሉ ከመስቀል ይውረድ ስጋው
ኒቆዲሞስ ቀድሞ በሌሊት ያየው
ዮሴፍም በአርማትያስ ያለው
ሞት ሳይፈሩ ከጲላጦስ ፊት ቀርበው
ተካሰሱ በድኑን እናውርድ ብለው
ጲላጦስም ጠዋት ስላየው ታግሶ
ትዕግስቱ ፃድቅነቱን አስታውሶ
እንዴት ሞተ ብሎ ጠየቀ መላልሶ
ሞተ ቢሉት እጅግ አዘነ ተከዘ
በድኑን ስጡ ብሎ ጭፍሮቹን አዘዘ
ከመስቀሉ አወረዱና ሁለቱ
ገነዙት በድርብ በፍታ በሽቱ
ከተክል ውስጥ ከአዲስ መቃብር ቀብረውት

መቃብሩን በታላቅ ድንጋይ ገጠሙት
ወልድ ጌታ በተናገረው መሰረት
ተነሳና ህቱም መቃብር ሳይከፍት
ለማርያም ወዶ ተገልጦ ታያት
ረቢ ብትል አይዞሽ ጠንክሪ አላት
እንዲህ ሆኖ ሞቶ ተነስቶ በፍጥነት
አዳምን አስገባው ተድላ ገነት
የአዳም ልጆች አሁን ያላችሁ በመሬት
አመስግኑት ስላወጣችሁ ከእሳት
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዘላለም ምስጋናህ ይብዛ ክርስቶስ
/በበገና/

ድንግል ስልሽ (ዘማሪት ሶስና)

ቅኝት - ሠላምታ

ድንግል ስልሽ ማርያም ስልሽ
እንደ በላኤ ሰብ ይጋርደኝ ጥላሽ ድንግል ስልሽ
በጭንቅ ውስጥ ሆኜ ከብዶኝ መከራ
የአምላክ እናት ስምሽን ስጠራ
ታማልጂኝ ዘንድ ልቦናሽ ይራራ
አዝ...
ጭንቄ በረታ ሀዘን ከበበኝ
ኃጢአቴ በዛ ተስፋ ቢስ ሆንኩኝ
ድንግል እመቤቴ ምልጃሽ አይለየኝ
አዝ...
ልጅሽ በሰጠሽ ቃል ኪዳንሽ
ተግተሽ ዘወትር እያማለድሽ
የሰውን ልጅ ሁሉ ታስምሪዋለሽ
አዝ...
ስምሽ እንደ ማር እየጣፈጠኝ
ደግነትሽም እየመሰጠኝ
ሁሌ እዘምራለሁ ልቤን ደስ እያለኝ
አዝ...
እምነቴ ሳስቶ ጽድቅም ባልሠራ
እመቤቴ ሆይ ነፍሴን አደራ
አስታርቀሽ አኑሪያት ከቅዱሳን ጋራ
አዝ...
ድንግል በሃና በእናትሽ
በኢያቄምም በአባትሽ
ተማጽኜሻለሁ ልቁም በፊትሽ
አዝ...
አንቺን ስጠራ ልቤ ይረካል
ሀዘኔ ርቆ ሰላም ይተካል
ለሀዘንተኞች ተስፋ ከኖ እንዳንቺ የታል
አዝ...

ስቀለው ስቀለው (ዘማሪት ሶስና)

ቅኝት - ዋኔን

ስቀለው ስቀለው እያሉ
አይሁድ ባንተ ላይ ተማማሉ
እውነተኛው ዳኛ አንተ ሆነህ ሳለ
የጲላጦስን ፍርድ ፍቅርህ ተቀበለ
ጌታ ይቅር በለን /2/
ምንም ብንበድልህ የእጆችህ ሥራ ነን/2/
ተጠማሁ ተጠማሁ እያለ
በቀራንዮ ላይ መስቀል ላይ ሆነህ
የአፍላጋት ጌታ አንተ ሆነህ ሳለህ
ሆምጣጤ አጠጡህ ሳለህ ተቸግረህ
ጌታ ይቅር በለን /2/
ምንም ብንበድልህ የእጆችህ ሥራ ነን/2/
ማን መታህ ንገረን እያሉ
ፊቱን እየጸፉት ሲሳደቡ ዋሉ
ምንም አልመለሰ ምነውም አላለ
ህማሙን በትዕግስት አውቆ ተቀበለ
ጌታ ይቅር በለን /2/
ምንም ብንበድልህ የእጆችህ ሥራ ነን/2/
ምራቅ እየተፉ ፊትህ ላይ
ሲመቱህ ሲሰድቡህ ስትሰቃይ
ምንም ሳትመልስ በፍቅር አየሃቸው
በመስቀል ሰቀሉህ ወደህ ሞትክላቸው
ጌታ ይቅር በለን /2/
ምንም ብንበድልህ የእጆችህ ሥራ ነን/2/
ይቅር ባይ ነህና መሀሪ
ትህትና ፍቅርን አስተማሪ
ጠልተው ለሰቀሉት ለተፉት በፊቱ
ምህረትን ጠየቀ ከአብ ከአባቱ
ጌታ ይቅር በለን /2/
ምንም ብንበድልህ የእጆችህ ሥራ ነን/2/
መከራህን ሳስብ ስቃይህን
መስቀል ላይ እንደዋልክ እርቃንህን
ነፍሴ ተጨነቀች እጅጉን አዘነች
ፍዳና በደሏን እያሰላሰለች
ጌታ ይቅር በለን /2/
ምንም ብንበድልህ የእጆችህ ሥራ ነን/2/

አሥር አውታር ባለው በበገና (ዘማሪት ሶስና)

ቅኝት -

አስር አውታር ባለው በበገና
ስለ ቅዱስ ስምህ ልቀኝና
ስምህን ላወድስ በዝማሬ
እኔም ከአባቶቼ ተምሬ
ዳዊት ስለ ክብርህ እጅግ ቀንቶ
በሰው ፊት መክበርን ሁሉን ትቶ
ሲዘምር የዋለው ስምህን ጠርቶ
መች ሆነና እርሱ ሹመት ሽቶ
አዝ...

በእስር ቤት ሳሉ እነ ጳውሎስ
የእጃቸው ሠንሰለት እስኪበጠስ
የወህኒውን ደጆች ያስከፈቱት
ባንተ ምስጋና ነው የበረቱት
አዝ...
ባንደበቴ ልጩህ ላመስግንህ
በቀንና በሌት ልቀኝልህ
ልዋረድ ከፊትህ ሰው ይናቀኝ
ምስጋናዬን አንተ ተቀበለኝ
አዝ...
በምስጋና ልምሰል አባቶቼን
ለዘወትር ስምህን በማመስገን
ታጢአቴን አታስብ መበደሌን
ምስጋናዬን ስማ ዝማሬዬን
አዝ...
ፍቅርህ የጎደለኝ ስሆንብህ
ለምስጋና አቆመኝ ቸርነትህ
አወድስሀለሁ በበገና
ምስጋናህ ይብዛልኝ እንደገና
አዝ...

አንገቴን አልሰብርም (ዘማሪት ሶስና)

አንገቴን አልሰብርም ድንግል ባንቺ አፍሬ
ስምሽ ሞገሴ ነው ምስጋናሽም ክብሬ
አንቺን ተስፋ አድርጌ ስምሽን እጠራለሁ
በስጋም በነፍስም ድኅነት አገኛለሁ
የአማኑኤል እናት የመድኃኔአለም
የፍጥረት አማላጅ ድንግል ማርያም
ስምሽን እየጠራሁ ስዘምርልሽ
አድዪኝ እናቴ ከበረከትሽ
አዝ...
የመላዕክት እህት የፃድቃን እናት
የነቢያት ትንቢት የሐዋርያት ስብከት
ባንቺ አማላጅነት እየተማፀኑ
ታጥአን ከሲኦል ከገሃነም ዳኑ
አዝ...
አጣሁ ነጣሁ ብዬ መቼ እከፋለሁ
ሀብቴ ነሽ ድንግል ሆይ እመካብሻለሁ
በሰማያት ያለው ፈጣሪሽ ነውና
ዓለማትን ሁሉ በእጁ ይዟልና
ምልጃ ልመናሽን ይቀበላልና
ምህረትን አሰጪን ያውጣን ከፈተና
አዝ...
አለም ብትነፍገኝስ ልቤ መቼ ያዝናል
ከወርቅ ከብር ይልቅ ስምሽ ያደምቀኛል
በአማላጅነትሽ ደሃ ጠግቦ ያድራል
በስምሽ ሲማፀን ጎዶሎው ይሞላል
አዝ...
ያለዋጋ እንዳይቀር በከንቱ ድካሜ
ድንግል ሆይ አሰጪኝ የንስሐን እድሜ
ከኪሩቤል ይልቅ የምትወደጂ
ተግተሽ ከልጅሽ ዘንድ ህዝብሽን አማልጂ
አዝ...

ዘማሪት የትምወርቅ

ሰማይና ምድርን (የትምወርቅ በገና)

ሠማይና ምድርን ያቀናህ
የሰውን ልጅ ፈጥረህ በአምሳያህ
የሐጥያት ቀንበር ለመስበር
ገብተህ ከፍጡራኑ መንደር
የሐጥያት ቀንበር ለመስበር
ገብተህ ከፍጡራኑ መንደር
ከድንግል ማርያም ተወልደህ
ከሠማያት ሠማያት ወርደህ
አምላካችን ወደህ ሰው ሆነህ
ህዝብህን በደምህ የዋጀህ
አምላካችን ወደህ ሰው ሆነህ
ህዝብህን በደምህ የዋጀህ
ሐሙስ በሌሊቱ ፀለይክና
አርዓያ ምሳሌ ሆንከንና
ጭፍሮች ተሰብስበው ጅራፍ ይዘው
ሊይዙህ ቀረቡ ሠይፍን መዘው
ጭፍሮች ተሰብስበው ጅራፍ ይዘው
ሊይዙህ ቀረቡ ሠይፍን መዘው
ጅራፍና በትር አዘጋጁ
የሞትህን አዋጅ ሊያሳወጁ
ስቀለው እያሉ ተነሳሱ
ባንተ ሞትን ነሱ ተፈወሱ
ስቀለው እያሉ ተነሳሱ
ባንተ ሞትን ነሱ ተፈወሱ
በቀራኒዮ ራስ አደባባይ
ተሰቅለህ ጌታዬ በመስቀል ላይ
ውሃ ስትጠማ ሐሞት ጠጣህ
ሰውን ከመከራ እያወጣህ
ውሃ ስትጠማ ሐሞት ጠጣህ
ሰውን ከመከራ እያወጣህ
መቃብሩን አልፈህ ከፈኑን
ሳትገብ ሳትነቅል ማይተሙን
የድንግል ማርያም ልጅ ተነሳህ
በሞትህ ሰይጣንን ድል ነሳህ
የድንግል ማርያም ልጅ ተነሳህ
በሞትህ ሰይጣንን ድል ነሳህ
ሲዖል ተሸነፈ በሞትህ
ገነት ተከፈተ በደምህ
ያመኑብህ ሁሉ እንዲድኑ
ተስፋ ተሰጣቸው በወንጌሉ
ያመኑብህ ሁሉ እንዲድኑ
ተስፋ ተሰጣቸው በወንጌሉ
ያመኑብህ ሁሉ እንዲድኑ
ተስፋ ተሰጣቸው በወንጌሉ

በገናዬን ላንሳ (የትምወርቅ በገና)

በገናዬን ላንሳ ሁሌም ልቀኝልህ
ንጉሴና አምላኬ ባሪያህ ላገልግልህ
ከእረኝነት ግብር ጠርተህ አነገስከኝ
ከበጐች ጥበቃ በህዝብህ ላይ ሾምከኝ
የኤልያብ ክብር በፊትህ ምንድነው
ከፊት አስቀደምከኝ ታላቆቼ ቀርተው
ሸሽጐኝ አባቴ ሆኜ ብላቴና
አንተ ግን መረጥከኝ ሳትንቅ ለንግስና
ጠጠሬን ሳነሳ ቀኝህ እረዳችኝ
ጋሻ ጦሩ ከድቶት ጠላት ወደቀልኝ
ጐልያድም የለም ከነኃይሉ ተዋርዷል
ፍልስጤም በእስራኤል ተሸንፎ ሸሽቷል
ከኋላዬ ቀረ ሳኦል ከነ ጦሩ
ገዳዬን ጣልክልኝ ከነ ክፉ ምክሩ
ቀብተህ አቆመከኝ በርሱው አደባባይ
ከእጁ ቀስት ድኜ ወጣሁ ሰገነት ላይ
አቤሴሎም ልጄ ጨክኗል በአባቱ
ከላይ ባልተሰጠው መንግስቴን መሻቱ
በዮርዳኖስ አሸዋ በልቤ ተኝቼ
ታሪክ እስኪለወጥ አነባሁ አብዝቼ
እንደቸርነትህ መጠን ምረኽኝ
ስንቱን በደል ሸረሀ በፍቅር አደስከኝ
በማለዳ በሰርክ ይብዛ ዝማሬዬ
ሌሊት መኝታዬን ልጠብ በእንባዬ

ልቤን ላንሳ (ዘማሪት የትምወርቅ)

ልቤን ላንሳ ወደ ሰማይ ፣ እረዳቴን ዓይኔ እንዲያይ
የሚረዳኝ ከእርሱ በቀር፣ ማንም የለም በዚህ ምድር
ባህር ከፍሎ ያሻገረኝ፣ እስከ መቃብር ያፈቀረኝ
ለኔ ዋጋ የከፈለ፣ እንደ እግዚአብሔር ማንም የለ
ለእርሱ ብቻ ነው ለአምላኬ፣ የምኖረው ተንበርክኬ
ነግሶ የሚኖር በሕይወቴ፣ የድንግል ልጅ ነው ውበቴ
የምቆመው ለምስጋና፣ በመሰንቆ በበገና
አይቼ ነው አምላኬን፣ ሲቀይረው ታሪኬን
ስጠራ ቅዱስ ስሙን፣ አበሰልኝ እንባዬን
በፍቅር ዓይኑ ስላየኝ፣ ሠላም ደስታ በዛልኝ
እኖራለው በሠላም፣ እርሱን ይዤ አልወድቅም
ጽኑ ሸክሜን አቅሎልኝ፣ እስከ ሞቱ አፈቀረኝ
ሠላሜ ነው ረዳቴ፣ ጌታዋ ነው ለሕይወቴ
የቤቴ ራስ ነው አባቴ፣ አምላኬ ነው ጉልበቴ
ልቤን ላንሳ ወደ ሰማይ ፣ እረዳቴን ዓይኔ እንዲያይ
የሚረዳኝ ከእርሱ በቀር፣ ማንም የለም በዚህ ምድር

እሰይ ጌታ ተወለደ(ዘማሪት የትምወርቅ)

እሰይ ጌታ ተወለደ እሰይ በቤቴልሄም
እሰይ ለሰው ልጅ ቀን ወጣ ለምድርም ሠላም
ኧኸ በበረት አየነው ኧኸ ሆኖ እንደ ሕፃን
ኧኸ ፍጥረትን የሰራ ፈጣሪ ሲሆን
ድንግል ታናሽ ሙሽራ፣ ሆነች ቤተ እንጀራ
ጌታን ታቅፋ ታየች፣ ፈጣሪዋን ወለደች
ተ-ወ-ለ-ደ
እሰይ ጌታ ተወለደ እሰይ በቤቴልሄም
እሰይ ለሰው ልጅ ቀን ወጣ ለምድርም ሠላም
ኧኸ የዓለም ጌታ ሲሆን ኧኸ ሁሉን ያዘጋጀ
ኧኸ የኛን ስጋ ሲለብስ ዓለሙ ተዋጀ
ዝማሬ ምድርን ሞላ፣ ተሰማ እስከ ገሊላ
ሰባሰገል ሰገዱ፣ መልአክት ወጡ ወረዱ
ተ-ወ-ለ-ደ
እሰይ ጌታ ተወለደ እሰይ በቤቴልሄም
እሰይ ለሰው ልጅ ቀን ወጣ ለምድርም ሠላም
ኧኸ በኮከብ ተመርተው ኧኸ ሰባሰገል መጡ
ኧኸ ወርቅ ዕጣን ከርቤውን ለክብሩ ሊሰጡ
ተወለደ ከድንግል፣ ሊሸር የአዳምን በደል
ሊመልስ የኛን ፀጋ፣ አየነው ከከብቶችጋ
ተ-ወ-ለ-ደ
እሰይ ጌታ ተወለደ እሰይ በቤቴልሄም
እሰይ ለሰው ልጅ ቀን ወጣ ለምድርም ሠላም
ኧኸ ይህ ምስጢር ታላቅ ነው ኧኸ እጅግ የገነነ
ኧኸ አምላክ ሰው ሰው አምላክ በተዋህዶ ሆነ
መልአክት ከሰው ታረቁ፣ አዲስ ቅኔን ታጡቁ
ዘመሩ ሠማይ ምድር፣ ስብሃት ለእግዚአብሔር
ተ-ወ-ለ-ደ
እሰይ ጌታ ተወለደ እሰይ በቤቴልሄም
እሰይ ለሰው ልጅ ቀን ወጣ ለምድርም ሠላም
እሰይ ጌታ ተወለደ እሰይ በቤቴልሄም
እሰይ ለሰው ልጅ ቀን ወጣ ለምድርም ሠላም
እሰይ ጌታ ተወለደ እሰይ በቤቴልሄም
እሰይ ለሰው ልጅ ቀን ወጣ ለምድርም ሠላም
እሰይ ጌታ ተወለደ እሰይ በቤቴልሄም
እሰይ ለሰው ልጅ ቀን ወጣ ለምድርም ሠላም

ሰቀሉህ(ዘማሪት የትምወርቅ)

ባለጸጋው ተራቆተ፣ ንፁሁ በግ ተጎተተ
በወደደን ባፈቀረ፣ ከወንበዴ ተቆጠረ
ኦኦኦ ጌታዬ ሰቀሉህ ወይ አለኝታዬ(2x)
ያንን ንጉስ ያንን ጌታ፣ ሲፈርዱበት ሲንገላታ
ፍቅሩን አየሁ የወዳጄን፣ ሲያሻግረኝ ይዞት እጄን
ኦኦኦ ጌታዬ ሰቀሉህ ወይ አለኝታዬ(2x)
የመስቀሉ ታላቅ ጉዞ፣ ለእኛ መዳን ለሞት ታዞ
ያን አቀበት ያን ተራራ፣ በድል ወጣው ታሪክ ሰራ
ኦኦኦ ጌታዬ ሰቀሉህ ወይ አለኝታዬ(2x)
በራስ ቅል ላይ በጎለጎታ፣ ተሰቀለ የኛ ጌታ
ደሙን በእኛ ስላተመ፣ መከራችን ተፈፀመ
ኦኦኦ ጌታዬ ሰቀሉህ ወይ አለኝታዬ(2x)
ጠላቶቹ ሆነን ሳለን፣ በልጁ ሞት ከታረቀን
አሜን አሜን አሜን ይሁን፣ ገና ክብሩን እንወርሳለን(2x)

የሳምራዊው ደግነቱ(ዘማሪት የትምወርቅ)

የሳምራዊው ደግነቱ፣ የወደቀን ሰው ማንሳቱ
ምህረት ፍቅሩ የገነነ፣ ዛሬም ለእኔ እውነት ሆነ
በመንገድ ላይ ተጎድቼ፣ ደም ሲያነቡ ቁስሎቼ
ገለል ሲል ሌዋዊው፣ አዘነልኝ ሳምራዊው
ዘይት ይዞ የደረሰ፣ የሞትን መርዝ ያረከሰ
የታደገኝ ከውድቀቴ ኢየሱስ ነው ደግ አባቴ
አብሮኝ አድሮ ጠብቆኛል፣ ሁለት ዲናር ከፍሎልኛል
የስቃይ ጦር ተሸነፈ፣ በሳምራዊው ልቤ አረፈ
በወንበዴ እጅ ወድቄ፣ ልጅነቴን ተነጥቄ
ሁሉም ሲርቅ ቀርቦኝ እርሱ፣ ፈውስን ለበስኩ በንጉሱ
በሕያው ቃሉ መከረኝ፣ ምህረትን አስተማረኝ
እኔም በፍቅር እንዳየሁህ፣ አንተም አድርግ ለወንድምህ
በሕያው ቃሉ መከረኝ፣ ምህረትን አስተማረኝ
እኔም በፍቅር እንዳየሁህ፣ አንተም አድርግ ለወንድምህ

ይህን ሁሉ ፍቅር(ዘማሪት የትምወርቅ)

በዕፀ ሞስቀሉ በቀራኒዮ፣ ለሰው ተሰቅለህ ዓይኖቼ አዩ
ይህን ሁሉ ፍቅር እፁብ አልን፣ አንተ ስትሰቀል እኛ ከበርን (2x)
ዓለም የዳነበት ፍቅር በመስቀል ተሰቅሎ
በሞቱ ሊያሳየን ቀረበ ከሁሉ አስበልጦ
አዳም ቢያመጣብን መርገምን እርሱ ካሳ ሆኖ
በደሙ ሊገዛን ወደደ ከሁሉ አስበልጦ
ይህን ሁሉ ፍቅር እፁብ አልን፣ አንተ ስትሰቀል እኛ ከበርን (2x)
እረኛ ነውና የሚያዝን፣ ለበጉ የሚራራ
የተቅበዘበዝን በጎቼን፣ ዋጀን ከመከራ
እራቁቱን ሆኖ አየነው፣ በራስ ቅል ኮረብታ
ፀጋን አለበሰን በሞቱ፣ የነፍሳችን ጌታ
ይህን ሁሉ ፍቅር እፁብ አልን፣ አንተ ስትሰቀል እኛ ከበርን (2x)
እግሩን ምስማር በሳው እጆቹም በችንካር ቆሰሉ
የፍቅር ዓዋጅ ወጣ ለሰዎች በዕፀ መስቀሉ
ቤዛችን የሆነው ክርስቶስ የሕይወት ራስ
እርሱ ሞትን ሞተ በመስቀል እኛን ሊፈውስ
ይህን ሁሉ ፍቅር እፁብ አልን፣ አንተ ስትሰቀል እኛ ከበርን (2x)
የሞት ስልጣን ሲሻር ተሰማ አርብ ከሰአት
ሰማይ እና ምድር በአንድነት ተገረሙበት
እኛም ሕያው ሆነን ተራመድን በሞቱ ተዋጅተን
ዛሬም ተሰልፈን ቆመናል ስሙን ለማመስገን
ይህን ሁሉ ፍቅር እፁብ አልን፣ አንተ ስትሰቀል እኛ ከበርን (4x)

በድንኪንህ(ዘማሪት የትምወርቅ)

መልካም በተባለች በመቅደስህ በር
ሲቀደስ ሲነገር የመንግስትህ ክብር
ጌታዬ እሰማለሁ ጣፋጭ ድምፅህን
ትጠግባለች ነፍሴ ስታይ ክብርህን
በድንኪንህ ማን ያድራል? ማንስ ይኖራል?(2x)
ኦኦኦ.... ክብር ይገባል ለቤትህ
በሐዋሪያት መሰረት በጴጥሮስ ዓለት
በደምህ አፅንተህ በመሰረትካት
መዝሙር እና ቅኔ ምስጋና ውዳሴ
እንሰዋለን ለአንተ ታላቁን ቅዳሴ
በድንኪንህ ማን ያድራል? ማንስ ይኖራል?(2x)
ኦኦኦ.... ክብር ይገባል ለቤትህ
እንባ ከፊታችን የሚታፈስባት
ከሐዘን ከመከራ የምንፅናናባት
ሁሌ የምናይባት የእግዚአብሔር ፊቱን
ቅድስት እናታችን ቤተክርስቲያን
በድንኪንህ ማን ያድራል? ማንስ ይኖራል?(2x)
ኦኦኦ.... ክብር ይገባል ለቤትህ
ለታላቁ ንጉስ የሆንሽው ማደሪያ
ከእግዚአብሔርም አፍ ሕይወትን መማሪያ
ተክሎ ያፀደቀሽ ጌታ ኢየሱስ
የአትናቲዮስ ሐውልት የዲዎስቆሮስ
በድንኪንህ ማን ያድራል? ማንስ ይኖራል?(2x)
ኦኦኦ.... ክብር ይገባል ለቤትህ
የሥጋ እና የደም ጥበብ የሌለብሽ
በአምላክሽ ክንዶች ተደግፈሽ የቆምሽ
ኢየሱስ ክርስቶስ ራስ ሆኖልሻል
ከአንቺ ጋር ተጣልቶ ማን ያሸንፍሻል
በድንኪንህ ማን ያድራል? ማንስ ይኖራል?(2x)
ኦኦኦ.... ክብር ይገባል ለቤትህ
የሲያልም ደጆች የማያናውፁሽ
የአህዛብም ክንድ የማይቋቋሙሽ
እስከ ዓለም ፍፃሜ ፀንተሽ የምትኖሪ
ንሴብሆ ብለሽ ለአምላክሽ ዘምሪ
እስከ ዓለም ፍፃሜ ፀንተሽ የምትኖሪ
ንሴብሆ ብለሽ ለአምላክሽ ዘምሪ
በድንኪንህ ማን ያድራል? ማንስ ይኖራል?(4x)

በልዑል መጠጊያ(ዘማሪት የትምወርቅ)

ሁላችን እንግባ በልዑል መጠጊያ
ከእቅፉ ሰገባ በልዑል መጠጊያ
አለ ሠላማችን በልዑል መጠጊያ
ዓለም የማይሰጠን በልዑል መጠጊያ
በመሸሸጊያችን በልዑል መጠጊያ
እንኑር ተከበን በልዑል መጠጊያ
በልዑል መጠጊያ የሚኖር የሚኖር
እርሱን የሚጠራ ዘወትር ዘወትር
እውነት እንደ ጋሻ ይከበዋል
አምላክ ከስብራት ያድነዋል ያድነዋል
በክንፎቹ በታች በልዑል መጠጊያ
እንጠለል ሰዎች በልዑል መጠጊያ
አይነካንም ክፉ በልዑል መጠጊያ
አይከድነንም ሰልፉ በልዑል መጠጊያ
እንጋረዳለን በልዑል መጠጊያ
ስሙን ጋሻ አድርገን በልዑል መጠጊያ

በልዑል መጠጊያ የሚኖር የሚኖር
እርሱን የሚጠራ ዘወትር ዘወትር
እውነት እንደ ጋሻ ይከበዋል
አምላክ ከስብራት ያድነዋል ያድነዋል
ምስጋና እና ውበት በልዑል መጠጊያ
ሠላም እና እረፍት በልዑል መጠጊያ
ብርሃን ለፃድቃን በልዑል መጠጊያ
ተስፋ ለቅቡፃን በልዑል መጠጊያ
መሸለም ማሸነፍ በልዑል መጠጊያ
ክብርን መጎናፀፍ በልዑል መጠጊያ
በልዑል መጠጊያ የሚኖር የሚኖር
እርሱን የሚጠራ ዘወትር ዘወትር
እውነት እንደ ጋሻ ይከበዋል
አምላክ ከስብራት ያድነዋል ያድነዋል
በልዑል መጠጊያ የሚኖር የሚኖር
እርሱን የሚጠራ ዘወትር ዘወትር
እውነት እንደ ጋሻ ይከበዋል
አምላክ ከስብራት ያድነዋል ያድነዋል

እጆቿን ዘርግታ(ዘማሪት የትምወርቅ)

እጆቿን ዘርግታ ኢትዮጵያ ወደ እግዚአብሔር ሐገሬ
ምህረት ስትለምን ኢትዮጵያ ሠላምና ፍቅር ሐገሬ
ሁሌም ይሰማታል ኢትዮጵያ የስቃይዋን ጣር ሐገሬ
ውቅር መቅደሶቿ ኢትዮጵያ የጥበብ መለያ ሐገሬ
ደብር ገዳሞቿ ኢትዮጵያ ለዓለም መታያ ሐገሬ
ታመሰግናለች ኢትዮጵያ ብላ ሃሌ ሉያ ሐገሬ
የደመራው እሳት ኢትዮጵያ ወጥቷል ወደ ሰማይ ሐገሬ
የእምነት ፅናቷ ኢትዮጵያ ከፍ ብሎ እንዲታይ ሐገሬ
ጨለማዋ ገፏል ኢትዮጵያ በዓማናዊው ፀሃይ ሐገሬ
ነብር ተፈጥሮውን ኢትዮጵያ ኢትዮጵያዊ መልኩን ሐገሬ
አይለውጥም እና ኢትዮጵያ የእምነት መድረኩን ሐገሬ
በቃ በላት እና ኢትዮጵያ ይቅርላት ስደቱ ሐገሬ
የንግስተ ሳባ ኢትዮጵያ የእምነት ምስክር ሐገሬ
ግዮን የከበበሽ ኢትዮጵያ ሐገረ እግዚአብሔር ሐገሬ
የታቦተ ጽዮን ፍፃሜ ተራራ
ሕያው ታሪክ አለሽ ልብን የሚያኮራ ሐገሬ

ከምንጭ ውሃ(ዘማሪት የትምወርቅ)

ከምንጭ ውሃ ስትቀዳ ቢያያት
እስቲ አንቺ ሴት አጠጭኝ አላት
ዝናባትን ያስገኘ አባት
እስራኤልን ያጠጣ ከዓለት
ተጠማና ወደ ምንጭ ዳር
ገሰገሰ ከሳምር መንደር
ሊያስተሳስር ሕዝብን ከ አህዛብ
ቆሞ ታየ ከውሃ ወደብ
የሚለመን እርሱ ለመነ
ሁሉ እያለው ባዶ ሰው ሆነ
ትሁት ጌታ ጅረት ወረደ
የልዩነትን ግድግዳ ናደ
ሳትረዳ መሲህነቱን
የአባቶች አምላክ ጌታ መሆኑን
መዘነችው ከፍጡር ጋራ
እርሱስ አምላክ ነው ሁሉን የሰራ
ሰማይ ምድሩን የሰራውን
ፍጡር አለችው ሳታውቅ ክብሩን
ሕይወት ጓዳዋን ገልጦ ቢነግራት
ጌትነት ክብሩ ተገለፀላት
ጠርታው መጥታ እርሱን ከቤቱ
እንዲለወጥ በርሱ ሕይወቱ
ሸክሟን ጥላ አዲስ ሰው ሆነች
ሕይወት ትዳሯን ለእግዚአብሔር ሰጠች
ጠርታው መጥታ እርሱን ከቤቱ
እንዲለወጥ በርሱ ሕይወቱ
ሸክሟን ጥላ አዲስ ሰው ሆነች
ሕይወት ትዳሯን ለእግዚአብሔር ሰጠች

ስደት(ዘማሪት የትምወርቅ)

የማደግ ተስፋችን ስደት ሆኖ ስደት ሆኖ
ህዝብህ በሰው ሐገር ተበትኖ ሐገር ተበትኖ
እረኛ የሌለው መንጋ ሆኗል መንጋ ሆኗል
ማንነቱን ሸጦ ክብሩን ጥሏል ክብሩን ጥሏል
መሰንቋችንን ሰቅለነዋል ሰቅለነዋል
ከባቢሎን ሆነን ተክዘናል ተክዘናል
ለብሰን ተመግበን የምንረካው የምንረካው
ሁሉም የሚያምርብን በሐገር ነው በሐገር ነው
ሲረግጡን ሲገዙን የማይራሩ የማይራሩ
ሕዝብን እና አምላክን የማይፈሩ የማይፈሩ
ግፋቸው ሲመዘን ከላባችን ከላባችን
አንድ ቀን ይፈርዳል አምላካችን አምላካችን
የእግዚአብሔር ልጆች እያነቡ እያነቡ
የእነርሱን ፒራሚድ ሲገነቡ ሲገነቡ
አይቶ ዝም አይልም ይፋረዳል ይፋረዳል
ምናመልከው አምላክ ያውቅልናል ያድነናል
ነፃነት እና እረፍት በግብፅ የለም በግብፅ የለም
በስደት በሽሽት አልደላንም አልደላንም
ባሕሩን አሻግረህ መልሰን መልሰን
ለሞት ለባርነት አትስጠን አትስጠን
የዳንኤል አዳኝ መከታው መከታው
የዮሴፍ እረዳት እረኛው እረኛው
ጉድጓዱ ውህኒው አይረታንም አይረታንም
ከጎናችን ስትሆን መድኃኒዓለም መድኃኒዓለም
አንተ ነህ ተስፋችን ሕይወታችን ሕይወታችን
ፈጥረህ የማትጥለን አባታችን አባታችን
ሰውን ማየት ትተን ጠርተንሃል ጠርተንሃል
ምድረ ርስትን ስጠን ይቻልሃል ይቻልሃል

ዘማሪ ዘርፉ ደምሴ

ዓርብ እሮብ (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ዓርብ እሮብ ሁዳዴን እንግደፍ ያላችሁ/2/
ጊዜ እንዲህ ይደርሳል ስሙኝ ልንገራችሁ
እኛ ሀገር ተቀምጦ በክርስቲያን ስም/2/
አሳ ማን ይበላል በሁዳዴ ጾም
እዝራ በመሰንቆ ዳዊት በበገና/2/
አምላክም እንደሰው ይወዳል ምስጋና
እዩልኝ ያንን ጌጥ አልጠገብ ባይ/2/
መርገፍ ጨመረበት በጥበቡ ላይ
ታጥቦ ተገንዘ መጣሁ ሳይቀበር/2/
ትናንትና ሰንበት በዓለ እግዚአብሄር ነበር
ሞጣ ቀራንዮ ሁሉም ደብር ነው/2/
በኢየሱስ ንገረኝ ያለቀውን ሰው
ሞት ደግ ሰው መስሎ ባህታዊ ምዕመናን/2/
ወጣኒ ይዞ ሄደ ወደ ቤተ-ክርስቲያን
የሁዳዴውስ ጾም ምንም አላለው/2/
ሰው ሁሉ ያለቀው በህማማቱ ነው
አሊፍ ብሄድ ብዬ እታው ድረስ ሳውቀው/2/
ቤት በመሃል ገብቶ ልቤን አስጨነቀው

መልካም ቤተልሄም (ዘርፉ ደምሴ በገና)

መልካም ቤተልሄም መልካም ደጀ ሰላም
እኔ አምላክን ብሆን በጉልበቴ አልኮራም
ላላሰነብተው ላፈርሰው አልሰራም
በጣም ተደነኩኝ ስትሰራው ባይ
ለካ ይህ ገላችን አፈር ኖሯል ወይ
አፈር ኖሯል ወይ
ሰው ሁሉ በሆዱ ጠጅ እያማረው
እግዚአብሄር ጠላና እንጀራ ነሳው
እንጀራ ነሳው
ሰው ሁሉ በርስቱ ይጨርሳል ሀብቱን
የኋላ የኋላ ላያጣው መሬቱን
ላያጣው መሬቱን
የዛሬ ዘመን ሰው ሁሌ አትርሱኝ ባይ
ካዘንኩማ እራሴን አላድንም ወይ
አላድንም ወይ
ይሉኛል አረጀህ መች ምድርን ይዣለሁ
የኮራሁ መስዬ መሬት ለቅቄአለሁ
መሬት ለቅቄአለሁ
እንግዲህ ረዳት የት ሀገር አግኝቼ
እኖራለሁ እንጂ ካቡን ተጠግቼ
ካቡን ተጠግቼ
መጾሙን ይጾማል ሁሉም የአዳም ልጅ
የጊዜውን መድረስ የሚያውቅ የለም እንጂ
የሚያውቅ የለም እንጂ
እዝራ መሰንቆውን ዳዊት በገናውን የሰጠን ለምን ነው
ማርያም ያረገችው በቶማስ በኩል ነው
በቶማስ በኩል ነው
አለህም እንዳልል እንዲህ ይደረጋል
የለህም እንዳልል ይመሻል ይነጋል
ይመሻል ይነጋል
እስቲ መከራዋን ልሁን ተናጋሪ
በበረት ወለደች ሆና መሸአዳሪ
ሆና መሸአዳሪ
ላሞች አመጡላት ትንፋሽ የአራስ ጥሪ
መሆኑን አውቀውት የእነርሱ ፈጣሪ
የእነርሱ ፈጣሪ

ጲላጦስም (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት - ሰላምታ
4245 313 15423 312 45
4245 313 15442 222

ጲላጦስም ባይቃወመው ቅናት
ጠይቆት ባያገኝበት ሐሰት
እንደነሱ ይሙት ማለቱ ጨንቆት
የለም ብሎ ከተገረፈ ስቅለት
ያዝኑለታል ይራሩለታል መስሎት
አስገረፈው እስኪታይ ድረስ አጥንት
ገርፎ መስቀል አይደለም እና ስርዓት
ከገረፍነው ልቀቁት ይሂድ ፍቱት
ቢላቸው እነሱም እንዲህ አሉት
ይህንን ሰው ካላራቅክልን በሞት
አይደለህም የቄሳር ወዳጅ ከጥንት
ካንተም በቀር የለውም ሌላ ጠላት
ጲላጦስም ከፀብ ክርክር በቀር
ቢያጣባቸው አንድ የሚጠቅም ነገር
እንዲጠበቅ ሚስቱን ልኮባት ነበር
ውሃ አምጥቶ እጁን ይታጠብ ጀመር
ከዚህ ሰው ደሜ ንፁህ ነው እያለ
በህዝቡ ዘንድ ነገሩ ቀላል መሰለ
እንዲህ አሉ እኛ እንፍራው ደሙን
ፍዳው በኛ በልጆቻችን ይሁን
እንዲህ ብለው የተናገሩት ቢከፋ
ትንፋሻቸው አንደበታቸው ከረፋ
ተወለዱ የአይሁድ ልጆች ሁሉም
ደም ጨብጠው ፍፁም ደም ጎርሰው ወንዶች
ሴቲቱም በማህፀን ውስጥ ሳለች
በተፈጠሮ የምትወለድ ሆነች
ጲላጦስም እኔ ንፁህ ነኝ ብሏቸው
እናንተ ግን ስቀሉት ብሎ ሰጣቸው
ተቀብለው ጭፍሮች ይዘውት ሲደርሱ
በአደባባይ ይዘብቱበት ተነሡ
የእሾህ አክሊል ታተው ደፉበት በራሱ
ልብሱን ገፈው ሃር አለበሱት እነርሱ
በቀኝ እጁ አስያዙትና እ'ለት
እንዴት አለህ የአይሁድ ንጉሥ አሉት
ከፊቱ ላይ እየሰገዱ ዘበቱ
ብድግ ብለው ምራቅ ተፉበት በፊቱ
የሰጡትን ያቀበሉትን እ'ለት
ተቀብለው እራስ እራሱን መቱት

ገፈፉና ያለበሱትን ሜላት
አለበሱት የለበሰውን ከጥንት
ርህራሄ ጥቂት የላቸው ለሁሉ
ከገረፍነው እንዴት ይሰቀል ሳይሉ
ሊሰቅሉት በሮማውያን ልማድ
ወሰዱት ግንድ አሸክመው አይሁድ
ለትዕግስቱ የለውምና አምሳል
በአንዲት ሰዓት እነርሱን ማጥፋት ሲችል
የምትሰቅሉኝ በምን ነገር ነው ሳይል
ሄደላቸው ተሸከመና መስቀል
ቀራንዮ እንዲህ አድርገው ወስደው
ሊፈጸም ዳዊት በመዝሙር ያለው
እጁን እግሩን ከመስቀሉ ጋር አብረው
ቸነከሩት እንደ ብራና ወጥረው
ሠልስት አልፎ ድብ ድንበር ቀትር ሲሆን
ሊሰውር የፈጠሪውን እርቃን
ፀሃይ ነሳ የለበሰውን ብርሀን
ላያትም ሰው አምላክነቱን አስታውቃ
ተለወጠች በደም ጠለቀች ጨረቃ
ከዋክብትም ፈጠሪያቸውን አውቁ
እንደ ቅጠል ከመስቀሉ ስር ወደቁ
መጋረጃው ያለው ከይሁዳ መቅደስ
ተቀደደ ከላይ እስከታች ድረስ
ድንጋዮችም የሚነካቸው ሳይኖር
እንደ ዳቦ ይቆራረሱ ጀመር
መቃብሮች በቀራንዮ ያሉት
ተገለጡ አፋቸውንም ከፈቱ
ሙታንም ከስድስት መቶ ያነሱ
አምስት መቶ ከመስቀሉ እግር ተነሱ
ስብሀት ለአብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ

ይበላሃላ (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ይበላሃላ/6/
አንተንም መሬት ይበላሃላ
በላው አፈር/6/
ያንን አንገት ያንን ከንፈር
በላው መረሬ/3/በላው አፈር
ያንን የዋህ ሰው ያንን ገጠሬ
በላው መረሬ/2/
ይበላሃላ/4/
አንተንም መሬት ይበላሃላ
በላው አፈር/4/
ያንን አንገት ያንን ከንፈር
በላው አፈር/4/
ያስተማረህን ያን መምህር
ያንን አዋቂ ያንን ጠቢብ
በላው አፈር/4/
ሀገር ተረካቢ ያን ተማሪ
በላው መረሬ በላው አፈር/2/
ሀገር ጠባቂ ያን ወታደር
በላው አፈር/2/
ይበላሃላ/2/
አንተንም መሬት ይበላሃላ/2/
በላው መረሬ/4/
ያንን ፈጣሪ ያንን ከያኔ
በላው መረሬ በላው አፈር
በላው አፈር/4/
ያንን አደራ ያን ቃልኪዳን
በላው አፈር/2/
በላው አፈር/2/
ያንን አላማ ያንን ሀሳብ
በላው አፈር/2/
ይበላሃላ/4/
አንተንም መሬት ይበላሃላ/2/
ይበላሃላ/4/
አንተንም መሬት ይበላሃላ/2/
በላው አፈር/2/
ያንን ታሪክ ያንን ዘመን
ያንን ባህል ያንን ፍቅር
በላው አፈር/2/
ያንን አንድነት ያንን ህብረት
በላው አፈር/2/
ይበላሃላ/4/
አንተንም መሬት ይበላሃላ/2/

በጌቴ ሴማኔ (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት - ሠላምታ
423 224 542 222
423 115 113 224 542 222

በጌቴ ሴማኒ በአትክልቱ ቦታ
ለእኛ ሲል ጌታችን በዓለም ተንገላታ/2/
አዳምና ሔዋን ባጠፉት ጥፋት
እኛም ነበረብን የዘለዓለም ሞት/2/
መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ
ይገርፉት ነበረ ሁሉም በየተራ /2/
ዓሣ አትብሉ ብሎ ቄሱ ሲራገም
ዓሣማ ይበላል በኩዳዴ ጾም /2/
የተጠበሰ ዓሣ ይሸታል እጃችሁ
ኧረ እናንተ ሰዎች ዓሣማ በላችሁ /2/
መለስ ቀለስ ብላ አየችሁ ቀሚሷን
እረሳችው እና ከአፈር መለወሷን /2/
በስምንተኛው ሺ በተልከሰከሰው
ቤተክርስቲያን ይስሟል አይጣሉም ከሰው /2/
ሠርቼ ሠርቼ አዳራሽ ከልፍኝ
በማለቂያው ጊዜ ላፈር ሰው ሆንኩኝ/2/
እስከዛው ድረስ ነው ሲሶ ማረሳችን
እንገባው የለም ወይ በየመሬታችን /2/
ጐድን ከዳዊት ተብትበህ ጥበሰው
እስኪበላ ሞቱን አይውቅምና ሰው /2/
ሰው ከሶኛል አሉ ቆሞ አደባባይ
እውነት ነውር ሆኖ ሊያስቀጣኝ ነው ወይ /2/

ሸንበቆ ግድግዳ ማገር ከመቁረጥ
ማዘን ቤት ይሠራል የማይናወጥ /2/
ሸማኔው ሰውዬ ችግር ሳይገባው
አንድ አርብ ቢኖረው ለሥጋ ሸጠው /2/

እረ ስማኝ ሀገሬ (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት - ሰላምታ
423 224 542 222
423 115 113 224 542 222

እረ ስማኝ አገሬ ተው ስማኝ አገሬ እረ ስማኝ ሀገሬ /2/
በጌቴ ሴማኔ በአትክልቱ ቦታ
ለኛ ሲል ጌታችን በዓለም ተንገላታ /2/
አዳምና ሔዋን ባጠፉት ጥፋት
እኛም ነበረብን የዘላለም ሞት/2/
መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ
ይገርፉት ነበረ ሁሉም በየተራ2/
አሳ አትብሉ ብሎ ቄሱ ሲራገም
አሳማ ይበላል በሁዳዴ ጾም /2/
የተጠበሰ አሳ ይሸታል እጃችሁ
እረ እናንተ ሰዎች አሳማ በላችሁ/2/
መለስ ቀለስ ብላ አየችው ቀሚሷን
እረሳችው እና ከአፈር መለወሷን/2/
በስምንተኛው ሺ በተልከሰከሰው
ቤተክርስቲያን ይስሟል አይጣሉም ከሰው/2/
ሰርቼ ሰርቼ አዳራሽ ከእልፍኜ
በማለቂያው ጊዜ ላፈር ሰው ሆንኩኝ/2/
እስከዚያው ድረስ ነው ሲሶ ማረሳችን
እንገባ የለም ወይ በየመሬታችን/2/
በበገና . . . . . .
ጐድን ከዳዊቱ ፈትፍተህ ጥበሰው
እስኪበላ ሞቱን አያውቅም እና ሰው/2/
ሰው ከሶኛል አሉ ቆሞ አደባባይ
እውነት ነውር ሆኖ ሊያስቀጣኝ ነው ወይ /2/
ሸምበቆ ግድግዳ ማገር ከመቁረጥ
ማዘን ቤት ይሠራል የማይናወጥ/2/
ሸማኔው ሰውዬ ችግር ሳይገባው
አንድ አርብ ቢኖረው ለሥጋ ሸጠው/2/
እረ ስማኝ . . . . . .
ጣናን በታንኳ ላይ ሲጓዙ ብታይ
እረ አባይን በግር ትጓዛለህ ወይ /2/

ድንግልም (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት - ሠላምታ
4245 313 15423 312 45
4245 313 15442 222

ድንግልም በምትወልድበት ወራት
በሮም መንግሥት ባውግስጦስ ቄሳር መንግሥት
ሰው ሁሉ ግብር ሊቆጠር ታዘዘ
ዮሴፍም ድንግልን ይዞ ተጓዘ
ከገሊላ ከነበረበት መንደር
ቤተልሔም ወደምትባል አገር
ከኤፍራታ ይወጣል ብሎ ንጉሥ
ሚኪያስ የተናገረው ሲደርስ
ሳታፋልስ የወላዶችን ሥርዓት
ከሱጋር ብዙ መላእክት መጡና
አቀረቡ ከጸሎት ጋር ምስጋና
ሊገርዙት እንደ አሪቱ ሥርዓት
ወሰዱት በ8ኛው ዕለት
ስሙን ኢየሱስ ብለው ጠሩት
ደሙ እንዳይፈስ ከዕለተ ዓርብ በፊት
ገረዙ በእጁ የያዘው ስለት . . .
አደረገ በተአምራት ግዝረት
በአርባ ቀኑ ዋኖስ ርግብ ይዘው
በአገር ስምአን የሚባል ነበር
ተጠራጥሮ የድንግሊቱን ነገር
እንደ ትሉ ካልታ ተጣብቆ ሲኖር
ያን ዕለት ከተኛበት ተነስቶ
በድካሙ በመንፈስቅዱስ ተጽናንቶ
ምኩራብ ገብቶ ከምኩራብ ገብቶ ሕፃኑ
ተቀብሎ ጌታን ቢይዘው ከጭኑ
ታደሰና በዐምስት መቶ ዘመኑ
ወደ ፊት የሚሆነውን ነገር
ተናገረ እጅግ በሚያምር ምስጢር
እንዲደረግ የሰው ሁሉ ድህነት
ተናገረ ነቢያት ሐናም ትንቢት

የእመቤታችን ምሥጋና (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -
ሰላም ብዬ እስቲ ልጀምር ምሥጋና
በይባቤ ደስ በሚያሰኘው በገና
ለኣምላክ እናት ለሰማይ ለምድር ፈጣሪ
ለእሷ አዝማሪ እዝራና ዳዊት በባህርይ
ቃል ኪዳኗ የማይፈርስባት ነዋሪ
እኛን ይዛ ፍጥረት ዓለምን መካሪ
ወለላዊት ቤዛዊት ዓለም ብፅህት
ከወተት ታምርሽ ጥዑም ትሁት
ከወለላ ታምርሽ ሲበላ
የብርሃን ዘውድ የብርሃን አክሊል ደፍተሽ
ድረሽልኝ በሠረገላ ሆነሽ
ይሸሻሉ ሰይጣናት አንቺን ሲያዩሽ
ያንን ግሩም ያንን ደስ የሚል መአዛ
ወለደቸው በቤተልሔም ተጉዛ
ምጥ የለባት በመላእክት እጅ ተይዛ
የታደለች እንደሷ ያለች ብጽህት
የበላውን ሰባ ስምንቱን ነፍሳት
አገባችው በጥርኝ ውሃ ገነት
ከአድማስ አድማስ ወረቀት ቢሆን መሬት
ቀለም ቢሆን የ3ወር ዝናም ክረምት
ቢጻፍ አያልቅ የተአምርሽ ብዛት
ስብሃት ለአብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ
የበላኤ ሰብ እመቤት
ነፍሴን አድኛት እባክሽ

ለተራበ ሰው ያላበላ
ለተጠማ ሰው ያላጠጣ
ለታረዘ ሰው ያላለበሰ
6ቱ ቃላት ያልፈፀመ ሰው ወየው
በዚያች ቀን የፍርዱ ለታ
እስኪ ልናገረው የርሱን ልዕልና
የኪሩቤል መቅደስ የሱራፌል ጽና /2/
የዘካርያስ አያት የተቋም ላይ ፋና
የሰሎሞን ሽቶ የዳዊት በገና /2/
የሩሁባን ምግብ የደውያን ጤና
የሙሴ ሐመልማል ያያት ደብረ ሲና
የዳንኤል ጉድጓድ የእንባቆብ ምግብና
የኢሳይያስ ፅንስ የገብርኤል ዜና

ስለ አዳም መፈጠር (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት - ሠላምታ
ዲያቢሎስን ከሁሉ በላይ አርጐት
በብልጠት አምላክ የሚሆን መስሎት
ፈጠርኩ አለ ይኽንን ሁሉ ፍጥረት
መላእክት ፈጥረህ አሳየን ቢሉት
ሊፈጥር እጁን ጨመረ ከእሳት
እሳት አውቃ የዲያቢሎስን ትዕቢት
አረገችው እሳት የበላው ጅማት
ተባበሩ መላእክት ሁሉ ሊክዱ
የሰገዱ አብረውት ሲአል ወረዱ
ጌታም አይቶ የእኩሌቶቹን ሀዘን
እሱ ክዶ ሳያስክዳቸው ሰይጣን
ለማመን ፈጠረላቸው ብርሃን
መላእክትም ይህንን ብርሃን አይተው
ሰገዱለት ቅዱስ እግዚአብሔር ብለው
በኹለት ቀን በተዝመረ ፍጥረት
ተናግረው ውሃውን ከሦስት
አንዱን ጠፈር አንዱንም ሐኖስ አሉት
አንዱን ብቻ ከናጌብ ወዲያ ዳርቻ
ሠፈሩበት ሌዋትንና ብሄሞት
በሦስት ቀን በተዝመረ ፍጥረት
ልታበቅል ምድር ሐመልማል ዘርፈ ቢላት
አበቀለች ከአዝርዕት ጋር አትክልት
በዐራት ቀን እንዳይሠለጥን ጽልመት
ከከዋክብትም ከጨረቃ ጋር ሌሊት
በመዓልትም ፀሐይ ደገኛው ፍጥረት
ተፈጠሩ ለኛ ሊያበሩ በውነት
የጎሙስ ፍጥረት ገና እንደሆነ አይተው
ለታውፅኑ ባህር ዘመድ ዓሣት ብለው
የሚበርን የሚኼደውን በእግሩ
ለአንክሮ ለተዘክሮ ፈጠሩ
ዐርብ ጠዋት አዳም የኛን አባት
ንግበር ሰብ በአርአያ ቢሉት
ተፈጠረ ከመኸለኛው መሬት
ሥራውን በ6 ቀን ፈጽሞ
ዐረፈበት በ7ኛው ዕለት ደግሞ
ሥራችንን በ6 ቀን ሠርተን
እናንተም ከሥራ እረፉ ሲለን
በፈጠሩት በስምንተኛው ዕለት
በሣልስት ብቻውን ሆኖ ቢያዩት
ንግበር ብለው ከጐኑ አንስተው አጥንት
ልትረዳው ሔዋንን ፈጥረው ሰጡት
በአርባ ቀኑ ወስዶ አግብቶታል ገነት
አግብቶትም ወስኖለታል ስርዓት
አትንካ ሲል ከዕፀ በለስ ቅንጣት
ብላ ጠጣ የቀረን ሁሉ ፍጥረት
ከምድር በላይ ከሰማይ በታች ያለው
ፍጥረት ሁሉ ላንተ ይገዛል አለው
ቢቀርብለት ዕፀ በለስን መብላት
ሳይታመም ከህመም በኋላም ሳይሞት
ሊያወርሰው የዲያቢሎስን ርስት

እስመ አንተ (ዘርፉ ደምሴ በገና)

እስመ አንተ አምላከ ሰማይ ወምድር
እስመ አንተ ምሉአ ፀጋ መክብር
ትባላለህ በነግ በሰልስት በቀትር
ኢየሱስ ደግ ባለ ጸጋ ንጉሥ
ኢየሱስ በአፈ ሁሉ ውዱስ
ኢየሱስ ቅዳሴ ሥራ ወነፍስ
አንተ እንጂ ነህ የማትዋረድ አታንስ
ብርቱ ዳኛ ያላንተ የለ ደገኛ
ፈጣሪዬ በከንቱ አለቀች እድሜዬ
ሳልገዛ እያሸነፈኝ ሥጋዬ
ዳሩ ግና አዛኝ እሩህሩህ ነህና
አደራህን የነፍሴን ነገር አትጽና
መበስበስ ደግሞ አለ ገና መፍረስ
መነሣት ደግሞ አለ ገና ፍርድ መስማት
በአንቲቱ እስመ ለዓለም ምህረቱ
መላእክቱ አይሸፍቱበት ከቤቱ ሌላ ጌታ
ያ ላንተ የለም በውነት
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ
ለዓለም እስክ ዘላለም ድረስ

ዳግም ስትመጣ (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት - ስለቸርነትህ

ዳግም ስትመጣ በዓለም ፍፃሜ
እንዴት አይህ ይሆን በየት በኩል ቆሜ /2/
ለነፍሴ ሳልሰንቅ አንዳች በጐ ነገር
እንዴት እወርሳለሁ የመንግሥቱን ሀገር/2/
እግሮቼ ካልቆሙ ከቅስት ተራራ
በረከት ካልያዙ የጽዮንን ሥፍራ
በቁጣው እሳት ፊት እንዴት ይድናሉ
በመቅረዙ በርተው በክብር ካልዋሉ/2/
ዓይኖችህ በፍቅር እንዲያዩኝ በምህረት
ልተከል በደጅህ ከድህነት ሰገነት /2/
ሳልል በላዬ ላይ ተራራን ተከዳን
በንስህ ልቁም በምጽአትህ ቀን/2/

አለቆች ሲሻሩ ከዙፋን ሲወድቁ
ጠቢባን ሲሰንፉ በኃይልህ ሲወድቁ
አቤቱ ባርያህን አትተው ብያለሁ
ትንሣኤህን ለክብር ለመንግሥትህ በለው/2/
ላንተ የማቀርበው አጣሁ በጐ ነገር
ከፍቶ የሚያስገባ የመንግሥትህን በር/2/
አለው ባዶ እጇን መብራት ሳላበራ
ኃጢኣቴ በዝቶ መቅረዜ ተሰብራ/2/
ኃያላን ሲፈቱ ሲሰበር ቀስታቸው
ትምክህታቸው ሲቀር ሲጠፋ ስማቸው
ታናሹን ባርያህን ጻፈኝ በመጽሐፍህ
ቅዱሳን ካሉበት የድህነት መዝገብህ/2/
ጣዖታት ሲናዱ ወድቀው ሲሰበሩ
ገፃቸው ሲጠቁር ወድቀው የነበሩ
ሀፍረት ሲከናነብ አንተን የበደለ
ዐየን በምህረት ጻድቅ እንደ በቀለ/2/

ዐርብ የታረደውን (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -

ዐርብ የታረደውን /2/ ምነው ባገኘሁት
ሥጋውን በልቼ ደሙን በጠጣሁት
አይቀርም ሞቱ
ሥጋውን በልቼ ደሙን በጠጣኹት
ሥጋዬና ነፍሴ ትግል ገጥመውብኝ
አዬ ጉድ ወየው ጉድ ወየው መከራዬ
ሞት አንተ ነህ አሉኝ መቼም ገላጋዬ
አይቀርም ሞቱ
ሞት አንተ ነህ አሉኝ መቼም ገላጋዬ
ሚ መጠን ሳይባል የመጣው ቀድሜ
ሥጋህና ደምህ አመለጠኝ ቆሜ
አይቀርም ሞቱ
ሥጋህና ደምህ አመለጠኝ ቆሜ
ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ ከእኔ ጋር ይኖራል ብለህ ተናግረህ
ተኮነን ብትለኝ ተኮነን ብትለኝ
እንወርዳለን አብረን እኔ ምን ቸገረኝ
የክብር መብራቱ እሳቱ ሲቃጠል
አዬ ጉድ ወይ ሰይጣን አጠፉት በቅጠል
ከዛ ከሞኝ ሰው ከዛ ከቂሉ ሰው ከዛ ከየዋህ ሰው ተወልጄ ከአዳም
አንዱ ትቶት ሲሄድ ስንቅ አያሳነዳም
አይቀርም ሞቱ
አንዱ ትቶት ሲሄድ ስንቅ አያሳነዳም
እስቲ ልናገረው የርሷን ልዕልና
የኪሩቤል መቅደስ የሱራፌል ጽንሐ የሱራፌል ጽንሐ /2/
ዘካርያስ ያያት የተቋም ላይ ፋና
የሰሎሞን ሽቶ የዳዊት በገና የዳዊት በገና /2/
የርሁባን ምግብ የድውያን ጤና
የሙሴ ሐመልማል ያያት ደብረሲና ያያት ደብረሲና /2/
የዳንኤል ጉድኳድ የእንባቆብ ምግብና
የኢሳይያስ ጽንስ የገብርኤል ዜና የገብርኤል ዜና /2/
አንተ ነህ ይሉኛል /2/ የዓለም ሁሉ ጌታ
ሰማይና ምድርን ያቆምክ ያለዋልታ
ያቆምክ ያለዋልታ ያቆምክ ያለዋልታ
አልታገልህም ግራ ካገባኸኝ
ደግሞም ማፈር አለ ከሰው ፊት ጥለኸኝ
አይቀርም ሞቱ
ደግሞም ማፈር አለ ከሰው ፊት ጥለኸኝ ከሰው ፊት ጥለኸኝ
ዲያቢሎስ ከሚስቱ ሳጥናኤል ከሚስቱ ተጣልቶ ሲፋታ
ለሷ የደረሳት ቀሚስና ኩታ
ለሷ የደረሳት ቀሚስና ኩታ ምን ያሳዝንህል
ብዙ ልብ አልባ ላንተም ይደርስህል
ምድርን ጠላ መጥመቅ /2/ ማን አስተማረው
እየጠራ አጠጣው ይኸን ሁሉ ሰው
አይቀርም ሞቱ
እየጠራ አጠጣው ይኸን ሁሉ ሰው
ሥራ ፈቶ ዋለ ትላንት ሸማኔው
ያ ቀለምሽ ነው ወይ የተበላሸው /2/

አዲስ ቤት ስትሠሩ (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -

አዲስ ቤት ስትሠሩ ባለ ጉልላት
ማዘን ጨምሩበት እንዲሰነብት
ተካፈሉት አሉኝ እቴ የኛን እጣ
የትም ሀገር ብንሄድ በይ መሬት አናጣ
ቤቴን መንገድ ዳር ሠርቼው ቅር አለኝ
አላፊው አግዳሚው ያፈርሰው መሰለኝ
መካሪዬ በዛ ቤት ሥራ የሚለው
ምን ያታክተኛል አሁን ላፈርሰው
ጣፍጦኝ እንዳልበላ ይምረረው ብለህ
ምነው በሥጋ ሀሞት ጨምረህ ሰጠኸኝ
ገበያ ወጥቼ ብመለከተው
በጣም በዝቶ አየሁት ሥጋ ፈላጊው
ዳዊቴን ወሰደው የማላውቀው ልጅ
የማይቀር ገንዘቤን ደግሞት ይስጠኝ እንጂ
ለምን ይዘሽዋል ዳዊቱን ለምስል
ከስብሐት ለአብ ወዲህ ይደገም ይመስል
ድጓውን ክተቱት አስተጋቡት በጣም
በቃ ተከተተ ከእንግዲህ አይወጣም
ይገኝ መስሎኝ ነበር የመጣን ከተማ
እንግባ አገራችን እውነት ከጠፋማ
የራበው ካልበላ እንደምን ይሆናል
ከዚያ ወዲያ ጾም ነው ህማማት ይጀምራል
ዐርብ ረቡን በላሁ እንጀራ በአዋዜ
እንዲህ ቶሎ ብሎ ለሚደርሰው ጊዜ

እንመን በስሙ (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -

እንመን በስሙ በፈጠረን ጌታ
እርሱ ነው በሞቱ አዳምን የፈታ /2/
ከመቃብር በላይ ስማችንን ጽፎ
ጠራን በትንሣኤ ሞትን አሸንፎ /2/
ሰዎች ተሰብሰቡ ከፍሪዳው መንደር
የመከሩ ዘመን ደርሶ ሳንሰበር /2/

አጫጆች ቆመዋል ከደጃችን በራፍ
ይነጠፍ ፊታችን የጽድቃችን ምንጣፍ/2/
ሃይማኖት አቅንተን ምግባር እየሠራን
ቤተል እንታደም አምልጠን ከካራን /2/
የደም ጣቶች ካሉን ይንጹ በንስሀ
እርሱ ይሰጠናል የሂሶጵን ውሃ /2/
የእግዚአብሔር ልጆች ነን የተሠራን በደም
ወድቋል ከላያችን የታቀፍነው መርገም/2/
ተሠርተናልና በእጅ ዳግም እንደገና
ለሕይወት ተከለን ሞትን ነቀለና /2/
የሞትን አቀበት አፍርሶ በደሙ
ሁላችን ከበርን በገናናው ስሙ /2/
የመቃብር ስሞች ፈርሰው ተዘነጉ
በመስቀል ተሰቅሎ ታርዷልና በጉ /2/
መድኃኒት ነውና ኢየሱስ ክርስቶስ
ሸሸ ከላያችን ያስጨነቀን መንፈስ /2/
ሞት የተጻፈበት መዝገቡ ተከደነ
የሌጊዮን ጭፍራ ፊታችን ተነነ /2/
በብርሃን መስቀል ጨለማን ገፈፈው
መቃችን ወለቀ ፊት ለፊት አየነው /2/
የፍቅር አይኖቹን ተክሏል በላያችን
ፍጹም የወደደን ያዳነን ጌታችን /2/
የሸጥነውን ሀገር በደሙ ገዛልን
እዳችንን ከፍሎ ሕይወት ታወጀልን
ኃይልን አስታጠቀን ከበበን ሞገሱ
ሸፈንን በደሙ ባማረ ቀሚሱ /2/

ተወለደልን (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -
እራቆቱን በዚያ በክረምት በብርድ
ወድቆ አደረ እኛን ለማዳን ቢወድ
በዚያ በክረምት በብርድ እኛን ለማዳን ቢወድ
እረኞቹም አቀረቡለት ማፈድ
አይተው ነበር መላክ ከሰማይ ሲወርድ
አቀረቡለት ማዕድ መላክ ከሰማይ ሲወርድ
ሰባ ሰገልም መጥተው በምሥራቅ
በአውድ ሰገዱለት እንደ አገራቸው ልማድ
መጥተው በምስራቅ በአውድ እንደ አገራቸው ልማድ
ሄሮድስም ሰማ ተንቀጠቀጠ
አይኑድ ወሬው በዛ በኢየሩሳሌም ተስፋፋ
ወሬው በዛ ተስፋፋ ተንቀጠቀጡ አይኑድ
ፈለገውና ሕፃኑን ሊገል
ሄሮድስ ሕፃናት መግደል ዝመረ ማረድ
ቅድስት ማርያም ልጇን ጠቅልላ
በዳባ ዮሴፍ ጋር ሸሸች ሆና ስንቅ አልባ /2/
በዚያ በረሃ በንዳድና በወባ
ስትሸሽ ተያዘች በወንበዴና በሌባ /2/
እያለቀሰች ልቧ ቢዋልል ቢባባ
ወንበዴው ምሯት ወደዱሩ ገባ
ልቧ ቢዋልል ቢባባ ወንበዴው ምሯት ዱር ገባ
ውሃ ቢጠማት ጡጥታ አደረች እንባዋን
ዮሴፍ አይቶ ጥሟን ወድረቁን ተርባ
ፍሬ ለቃቅሞ አምጥቶ ሰጣት ዘንባባ /2/
በመከራ ጭንቅ ልትሞት ተርባ
ዝላ ደረሰች ከቁስቋም አንባ
በመከራ ጭንቅ ተርባ ዝላ ደረሰች ቁስቋም
ዘንግተዋል የሰሎሞን ዘንግ እሴይ
ከንፈሮቿም መከኖ ያፈራው እንኮይ
ፀጉሯም ደግሞ የሊባኖስ ዱር መሳይ
ጡቆረች በዚያ በሀሩርና በፀሓይ
ጡቆረች በዚያ ፀሓይ ጡቆረች በዚያ ፀሓይ

ማዘን ጨምሩበት (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -
አዲስ ቤት ስትሠሩ ባለ ጉልላት
ማዘን ጨምሩበት እንዲሰነብት
ተካፈሉት አሉኝ እቴ የኛን እጣ
የትም ሀገር ብንኼድ በይ መሬት አናጣ
ቤቴን እመንገድ ዳር ሠርቼው ቅር አለኝ
አላፊው አግዳሚው ያፈር ሰው መሰለኝ /2/
መካሪዬ በዛ ቤት ሥራ የሚለው /2/
ምን ያታክተኛል አሁን ላፈርሰው /2/
ጣፍጦኝ እንዳልበላ ይምረረው ብለህ /2/
ምነው በሥጋ ሞት ጨምረህ ሰጠኸኝ /2/
ገበያ ወጥቼ ብመለከተው /2/
በጣም በዝቶ አየሁት ሥጋ ፈላጊው /2/
ዳዊቴን ወሰደው የማላውቀው ልጅ /2/
የማይቀር ገንዘቤን ደግሞት ይስጠኝ እንጂ/2/
ለምን ይዘሽዋል ዳዊቱን ለምስል
ከስብሃት ለአብ ወዲ ይደገም ይመስል
ድጓውን ክተቱት አስተጋቡት በጣም
በቃ ተከተተ ከእንግዲህ አይወጣም
ይገኝ መስሎኝ ነበር የመጣን ከተማ
እንግባ አገራችን እውነት ከጠፋማ
ድጓ ጸመ ድጓ ተሰቅሎ ከቤቴ
እኔስ የሚገርመኝ ሳልማር መቅረቴ
ሸክላ በሩቅ ሲያዩት ብረት ይስላል
ለመረመረው ሰው ገል አፈር ኖሯል
ሰው አይቸገርም ሌሊት ዝናብ ቢሆን
ጉዳት የሚበዛው ቀን የጣለ እንደሆነ

በአዳም በደል (ዘርፉ ደምሴ በገና)

እንዲህ ሲለው ተስፋውን ብቻ ሰማ እንጂ
አላገኘም ፈጥኖ የሚያድነው ወዳጅ
በአዳም ፍዳ የአዳም ልጅ ሁሉ ተጋዘ
እያንዳንዱ በቁራኝነት ተያዘ
ለሞትም በነፋስ በሥጋ ታዘዘ
ወደ ሲዖል ወደ ቃብር ተጓዘ
በአዳም በደል ባላጋራችን ሰይጣን
በሰው ላይ ተሰጠው እና ስልጣን
ኃጢአትን አንድ እንኳን ሳይቀር በሙሉ
በየዕለቱ ያስተምር ዝመረ ለሁሉ
ለቃየል ነፍስ መግደል ቢያሳየው
የናቱን ልጅ አቤል ወንድሙን ተጣላው

በድንጋዩ ራሱን ብሎ ገደለው
እንዲስፋፋ የመገዳደል ትምህርት
ለዛዛኤል ለተወለደው ለሴት
አስተማረው የጦር መሳሪያ መሥራት
በዓለም ላይ በዝቶ እንደሠራ
ዝሙት በወነዶች ላይ እንዲቀሰቀስ ፍትወት
ዐይንን መኳል መነቀስንም አንገት
በእንሾሽላ የእጅ የግር ጣት ማቅላት
አስተማረ እንዲያለ ተንከል ለሴት
10ኛው ኖኅ የሚባለው ፍጡር
እሱ ብቻ ከነልጆቹ ሲቀር
በየሥራው ሰው ሁሉ እሱን መሰለ
ተካከለ ዓለምም በአንድነት በደለ
እግዚአብሔርም ፍጥረት ሁሉ ፈተነ
አላገኘም በሕጉ በሥርዓቱ የሆነ
ተጠጠተ ሰው በመፍጠሩ አዘነ
ሰበሰበው ቁርጠኛ መዓት ፈረደ
እስከ 40 ቀን የጥፋት ውሃ ወረደ
አስቀርቶ 8 ራሱን የኖህ
ደመሰሰ በጥፋት ውሃ ሰውን
ኖኅም አይቶ የወረደውን መከራ
ውሃው ሲደርቅ ከመርከቧ መውጣት ቢፈራ
መሥዋት ሰዋ ጌታም ወደ ርሱ መጣና
በቀስት አምሳል 4 ሳብር ባላት ደመና
በፍል ውሃ አላጠፋም ሰውን
ብሎ ሰጠው እግዚአብሔር ለኖኅ ቃል ኪዳን
የሰው ልጅም እንዲህ ከሆነ በኋላ
እጅግ በዛ ብዛቱም ምድርን ሲመላ
ኹለተኛ ከግብር አባቱ ተማረ
እንደ ቀድሞ ኃጢኣት ይሠራ ዠመረ
በባቢሎን የኃጢኣት ግንብ . . .
ይልቁንም ኃጢኣት ሁሉ ከባድ
ጣዖት መሥራት ከወርቅ ከብር ከግንድ
የዠመረ ሴሩህ የሚባል ትውልድ
ሰው ሁሉ ጣዖት ማምለክ ወደደ
በጣዖት ፍቅር ልቡ እንደ እሳት ነደደ
ጣዖት ማምለክ በዓለሙ ላይ ተስፋፋ
የእግዚአብሔር ስም ጨርሶ ከምድር ሲጠፋ
ያልተሞኘ በጣዖት ባሕር ያልዋኘ
በዚያ ወራት አብርሃም ብቻ ተገኘ
የሚጠራ የእግዚአብሔርን ስም በምድር
በዚያ ወራት አብርሃም ብቻ ነበር

<u>የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት (ዘርፉ ደምሴ በገና)</u>

ቅኝት -
የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት አሉለት ዋይ ዋይ
የኃያላን ጌታ በግፍ ሲሰቃይ
እንደ ውሃ ሲፈስ በፊቱ ላይ ደሙ
አፋቸውን ያዙ እየተደመሙ
በአመፀኞች እጅ መውደቅ መገፋቱ
ሊያነሳን ሽቶ ነው መታመም መሞቱ
የግፈኛን ምራቅ ገጹ ተቀበለ
አላበቃም በነዚያ በእንጨት ተሰቀለ
የብርሃን ፊቱ በደም ተሸፈኖ
ሊያየው አልደፈረም ፍጥረት ዐይኑን ከድኖ
ድንቅ ነው ውለታው የበዛ ምህረቱ
ለገደሉት ሕይወት አንገቱን መስጠቱ
የአይኑድ ንጉሥ ብለው ቢዘብቱበት
ሊሸከም ወደደ የመውጊያውን ሸክም
አቁሳዮችን ቢያድን እርሱ እየቆሰለ
ያቀልጣል መውደዱ ፍቅሩን ላስተዋለ
አፏን ከፈተችው የኢየሩሳሌም ምድር
የፈጠራት ጌታ ከመቃብር ሲያድር
ሐውልቶች ተናዱ ሙታንም ተነሡ
ምስክር ሊሆኑ ለዚያ ለንጉሡ
የመከራው መንገድ በደም ተጠረገ
እርሱ ዝቅ እያለ ከፍ አደረገ
በችንካሩ ጥልቀት አይለካም ፍቅሩ
አርምሞ ይኖላል አለመናገሩ
ከሰማያት ወርዶ ዝቅ ዝቅ እያለ
ከከብቶች ማደሪያ ግርግሙ ላይ ዋለ
ከሐዋርያት ሀገር ቁጭ አለ ንጉሡ
እግራቸውን አጥቦ ጠረገ በልብሱ

<u>አሐዱ ብሎ ቅዱስ (ዘርፉ ደምሴ በገና)</u>

ቅኝት -

እዛ ላይ ያለች ሸክላ ሰሪ
ድሃ ነች አሉ ጾም አዳሪ
ማን አስተማራት ጥበቡን
ገል አፈር መሆኑን/2/
ከወጥ ቤት ገባሁ ድንገት
ቋንጣ ጠብሼ ለመብላት
ከወጥ ቤት ገባሁ ድንገት
ወድቄ ነበር ከእሳት ላይ
ሥጋ ሥጋ ሥጋዬን ሳይ
ሥጋ ሥጋዬን ሳይ
ከዚያ ታች ያለች ድውይ
ከቶ ምን ቀመሽ አልሻት ወይ
ከዚያ ታች ያለች ድውይ
ኋላ ፀፀቱ ባንቺ ይሆናል
ተይ ሥጋ ብላሽ ይሆናል/2/
የልጃገረድ አውታታ
ከአውራ መንገድ ላይ ተኝታ
ተነሺ በሏት ምነው
ይህ ሁሉ ዓለም አለም ዓፈር ነው/2/
ትንሽ ቤት ሠራሁ እንደ አቅመኛ
ሁለት ሦስት ሰው የሚያስተኛ
ትንሽ ቤት ሠራሁ እንደ አቅመኛ
አላስገባ አለች እሷው ጠባ
ሰው በሰው ላይ እየገባ/2/
የኢየሩሳሌም መንገድ
ቅርብ ነው አሉኝ የረፋድ
የኢየሩሳሌም መንገድ
ለቀደመኝ ነው የማዝነው
ወይኔ የማልቀረው/2/

የኢየሩሳሌም ሴት
ጐልጐታ ላይ ሠርታ ቤት
የኢየሩሳሌም ሴት
እግዚአብሔር ያፅናሽ አልናት ወይ
ወልዳ አልሞታትም ወይ
ከሰማየ ሰማይ ወርደህ
ከድንግል ማርያም ተወልደህ
ከሰማየ ሰማይ ወርደህ
አንተንም አሙህ እንደሰው
ምን እና ምን ምን እና ምን ብለው
ምን እና ምን ብለው
ከሰማየ ሰማይ ወርደህ
ከድንግል ማርያም ተወልደህ
ከሰማየ ሰማይ ወርደህ
ትጨክናለህ ምነው
አምላክ በእናትህ ሰው/2/
አሐዱ ብሎ ቅዱስ
እንዴት ይጠፋል ለቄስ
አሐዱ ብሎ ቅዱስ
በስመ አብን ሳያውቅ እንዴት ኖረ
እንደኔ ያልተማረ/2/
እኔ ተሠራው ፀጉሬን
አላርፍ ብዬ ነውሬን
እኔ ተሠራው ፀጉሬን
ሌሎች ሲላጩ እያየ ዐይኔ
ለምን ተሠራው እኔ/2/
ከብት ጠፍቶብኝ በሌሊት
ስፈልግ አደርኩ ስዋትት
ከብት ጠፍቶብኝ በሌሊት
እነግርሃለሁ ተጣርቼ
ይህን ቀን ወጥቼ አይቼ/2/

እፎይ ታገስከኝ (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር አምላክ
ሰማያት ወምድር የፈጠርክ አምላክ
አምላክ ሰማይ ወምድር
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር አምላክ
የፈጠርክ አንተ ነህ የሰማይ መላእክት
አምላክ የሰማይ መላእክት
ሰባቱ ሰማያት የፈጠርክ አምላክ
ስብሐት ለከ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ
ቅዱስ አምላክ ሰማያት
መዓልቱን ሌሊቱን የፈጠርክ አምላክ
ስብሐት ለከ ቅዱስ እግዚአብሔር
ኣምላክ አንተ ቅዱስ
እፎ ሰቀሉሰ አንተን አንተን ዲበ ዕፅ
ኢየሱስ ኣምላክ ለአይኑድ ለአሞፅ
ሰቀሉክ አይኑድ አሞፅ
መድኃኒቱም አንቲ ለመበልት
መዝገበ ምህረት ሰአሊለነ ማርያም
እፎ አልበሱከ አንተን ከለሜዳ
ኢየሱስ አምላክ ለአሞፅ ለይኑዳ
አለበሱክ አሞፅ አይኑዳ
እፎ ተአገስክ አንተ መለኮት
ጊዜ ሰቀሉከ አይኑድ ካህናት
ተአገስክ አንተ መለኮት

ሞት እንዴት ሰነበትክ (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -
ባንዳንዱ ቀን መልእክት
ባንዳንዱ ቀን
መልእክት ሰው ያማርራል
የኔስ ወንድም ታዞ አባይ
ዳር ይኖራል
ቤታችው ቢሳወር ከእንግዳ ይተርፋል
ቢመሽ ከእኛ አደረ ነገም በእናንተ ያልፋል
ወይ አጭደን አልጣልነው ወይ ከብት አልበላው
ከቶ መቼ ይሆን ያሣር ማለቂያው
ዘመዶቼ ሁሉ አልቃችሁ አልቃችሁ
ወገኖቼ ሁሉ አልቃችሁ
ይኼ መግቢያ የለው ታሰኙኛላችኹ
የኔማ ዘመዶች ምን አጡ በሙሉ
መልካም በቅሎ ነበር ፈረስ ፈረስ አሉ
ምንም በቅሎ ቢያምር ኮርቻው ቢመች
መቀመጥ አይወዱም የኔ ዘመዶች
እጄ አመድ አፋሽ ነው ሞት ይመኛል አሉ
ጨርሼ ሰጥቼው ዘመዶቼን ሁሉ
ሞት እንዴት ሰነበትክ እንዴት ሰንብተሀል
እግዚአብሔር ይመስገን ወዴት ታውቀኛለህ
ለምን አላውቅህም አውቅሀለሁ እንጂ
የእህቴን የወንድሜን ስትዘጋ ደጅ አንተ
ሁል ጊዜ እንግዳ ሰው አጥፊ ነህ እንጂ
ሞት አገኘሁት እንደምን ዋልክ ብለው
አለኝ ደና ሰንብት
ሸኝቼው ተመለስኩ እኔም አላመንኩት

ኪዳነ ምህረት (ዘርፉ ደምሴ በገና)

ቅኝት -

ንኢ ንኢ ንኢ ኪዳነ ምህረት
ሰዓሊ ለነ ማርያም መዝገበ ምህረት
ነአ ነአ ነአ ቅዱስ ሚካኤል
ታወጣለህ አሉኝ ከሞት ከሲኦል
ነአ ነአ ነአ ቅዱስ ገብርኤል
አይደለህም ወይ ዜናዊ ሐዲስ
ነአ ነአ ነአ ቅዱስ ጊዮርጊስ
ትደርሳለህ አሉኝ ፈጥነህ በፈረስ
አዳምን ከሲኦል እሌኒን ከባህር
አልዓዛርን ከሞት ያወጣህ አምላክ
እኛንም አድነኝ ከዲያቢሎስ ፊት
ሰዓሊ ለነ ቅድስት ነይ ከደማስቆ
እዝራ ወደሰኪ አንቲን በመሰንቆ
ማርያም ሰዓሊ ለነ ድረሽ ፅጌ ሃና
ዳዊት ወደሰኪ አንቺን በበገና

ስጠራሽ ስሚን አፀደ ገነት
ትንቢቶሙ አንቲ ለአምላክ ነቢያት
ፈጥነሽ ድረሺልኝ ዘመና መሰብ
መድኃኒት እኮ ነሽ አንቺ ለያዕቆብ
የአክሱም ጽዮን ድረሽ ኩሉ ገዳም
መድኃኒቱም አንቲ ለይስሐቅ ለአብረሃም
ንኢ ንኢ ንኢ ኪዳነ ምህረት
ሰዓሊ ለነ ማርያም መዝገበ ምህረት
ነአ ነአ ነአ ቅዱስ ሚካኤል
ታወጣለህ አሉኝ ከሞት ከሲኦል
ነአ ነአ ነአ ቅዱስ ገብርኤል
አይደለህም ወይ ዜናዊ ሐዲስ
ነአ ነአ ነአ ቅዱስ ጊዮርጊስ
ትደርሳለህ አሉኝ ፈጥነህ በፈረስ

ዘማሪ ይልማ ኃይሉ

በይስሐቅ ፈንታ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -

በይስሐቅ ፈንታ ኢየሱስ ታረደ
ደሙን ከፈለና አዳምን ታደገ
ተጨነቀ ጌታ ተሰቃየ ጌታ
የኔ መድኃኔዓለም የአዳም ልጅ አለኝታ
እንደሚታረድ በግ ተነዳ ወደ ሞት
ንፁሁ ኢየሱስ በደል የሌለበት
አዝ...
በማመን ሊሸከም የአዳምን መከራ
ስቃይ ተቀበለ ደሙ እየተዘራ
ለሚገርፉት ሁሉ ምህረትን ሲቸር
እርሱ ግን ሲገረፍ ብዙ ተቸገረ
አዝ...
የሰማነውንስ ማን ሰው እኮ አምኗል
የእግዚአብሔርስ ክንድ ለነማን ተገልጿል
ባየነውስ ጊዜ ህማም ተሸክሞ
ስለበደላችን ተገርፎና ታሞ
አዝ...
እጁ የታሰረው ይስሐቅ ተፈታ
ኢየሱስ ቀረበ በሰው ልጆች ፈንታ
ንፁህ በግ ቀረበ በደል የሌለበት በደለኛ ሆኖ
ሊሰቀል ሊገደል መስቀሉን ተጭኖ
አዝ...
ተቆጠረ እንጂ እንደተቸገረ
በደሜ በህማም ማቆ እንደኖረ
አምላክ ለኛ ብሎ ተናቀ በሰዎች
እየተፀየፉት ተፉበት ብዙዎች
አዝ...
በእውነት ደሜያችንን እርሱ ተቀበለ
በሰው ልጆች ፈንታ በእንጨት ተሰቀለ
እኛ ግን ከሰስነው እንደ ወንጀለኛ
ስለ እኛ ቢሰቀል ሰማያዊው ዳኛ
አዝ...

ለሰው ልጆች ህይወት የታሰበው ሰይፍ
አይተናል ሰምተናል በኢየሱስ አንገት ሲያልፍ
የመስቀሉ ስዕል ኧረ እንዴት ይገርማል
እዩት ንፁሁ በግ በአርምሞ ይነዳል
አዝ...

የብርሃን እናት ነሽና (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -

የብርሃን እናት ነሽና የብርሃን እናት/2/
ለምኚልን ድንግል ለምኚልን /2/
ጸጋንና ክብርን የተመላሽ
ከሴቶች መካከል የተመረጥሽ
ለቃሉ ማደሪያ ዙፋን ሆነሽ
በደመና መንበር የተመሰልሽ
አዝ...
የሸቶ ማኖሪያ የተቀደስሽ
መዓዛሽ ያማረ ሽቶ ያለሽ
ውዳሴሽ ብዙ ነው እናታችን
ስምሽን እያሰብን ነው መፅናኛችን
አዝ...
በሀሳብ በግብር ፍጹም ሆነሽ
ምንኛ ብሩህ ነው ድንግል ልብሽ
አንቺን የሚመስል የለምና
ይሰማል ምልጃሽ ያንቺ ልመና
አዝ...
የብርሃን መውጫ ምሥራቁ ነሽ
ሰውን ለለወጠ ለድል ልጀሽ
ምሥጋናሽ አያልቅም ለዘላለም
ማህሌት ነሽና በአርያም
አዝ...
መላዕክት ፍጥረትሽን ያደንቃሉ
ጌታን በመውለድሽ ይመካሉ
ሰማይና ምድር ሳይወስኑት
ባንቺ ተወሰነ እውብ በእውነት
አዝ...
የሸቶ ማደሪያ የተቀደስሽ
መዓዛሽ ያማረ ሽቶ ያለሽ
ውዳሴሽ ብዙ ነው እናታችን
ስምሽን እያሰብን ነው መጽናኛችን
አዝ...

አዝላው ወረደች (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -

አዝላው ወረደች ወደ ግብጽ /2/
ስደተኛዋ የአምላክ እናት
ይህ ዓለም ለእርሷ መች ተገባት
አዝ.....
ዓለም በምን ውሃ ታስተናግዳት
የፍቅር ምንጯ ተሟጦባት
እነ ኮቲባን እየላከች
የአምላክን እናት ተሳደበች
እነ ሄሮድስን እየላከች
ህፃኑን ልትገድል አሳደደች

አዝ.....
የክብርን ጌታ ተሸክማ
ውርደት ለበሰች እንደሸማ
የሀብቱን ጌታ በጀርባ አዝላ
ሰው ተዘከራት ተቸግራ
አዝ.....
በቃሉ ትዕዛዝ ምድርን ሰርቶ
ተንከራተተ ማደሪያ አጥቶ
ጌታ ሲወለድ የምስራች
በረት ሰጠችው ዓለም ታካች
አዝ.....
ግና መላእክት በሰማያት
ሃሌሉያ አሉ በፍርሃት
ወልድን በአብ ቀኝ ከላይ አይተው
ደግሞም በምድር ከድንግል ክንድ
ከላይም ሳይጎል ተመልክተው /2/
አዝ.....
ዓለም በምን ውሃ ታስተናግዳት
የፍቅር ምንጯ ተሟጦባት
እነ ኮቲባን እየላከች
የአምላክን እናት ተሳደበች
እነ ሄሮድስን እየላከች
ህፃኑን ልትገድል አሳደደች
አዝ.....
በቃሉ ትዕዛዝ ምድርን ሰርቶ
ተንከራተተ ማደሪያ አጥቶ
ጌታ ሲወለድ የምስራች
በረት ሰጠችው ዓለም ታካች
አዝ.....

<u>ሥላሴን ከሰማይ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)</u>

ቅኝት -

ሥላሴን ከሰማይ እስጢፋኖስ አይቶ
አይኑ በመገረም ቀረ ተሰክቶ
የድንጋዩ ናዳ ቢወርድበት እንኳ
ሥላሴን በማየት 'ረስቶታል ለካ
ስብሐት ለእግዚአብሔር
የሰው ልጅ በቀኙ ተቀምጦ ነበር
እስጢፋኖስ ሲያየው በሚያስፈራ ክብር
ካህናተ ሰማይ ዙፋኑን ከበውት
ቅዱስ ቅዱስ ሲሉ ስብሐት ስብሐት
ስብሐት ለእግዚአብሔር
ምስጢረ ሥጋዌ ተገልጾለት በአካል
ሥጋው ቢታመምም ሀዘኑን ሽሮታል
ነፍሱ ከፀባኦት ስታመሰጥር
ድንጋይ ይለቅማሉ ያልታደሉ ፍጡር
ስብሐት ለእግዚአብሔር
ለፈሪሳውያን ተሰውሮባቸው የሥላሴ ምሥጢር
ድንጋይ ሰበሰቡ ጻድቁን ለመውገር
እርሱ ግን ከሰማይ ፈጣሪውን አይቶ
ድንጋዩን እረሳው ሀሊናው ተነክቶ
ስብሐት ለእግዚአብሔር
የሰማዩ ሥርዓት ልዩ ስለነበር
ምንም አልመሰለው የድንጋዩ ክምር
የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ ተገልጠው
ስቃዩን አስረሱት ሀሊናውን ነጥቀው
ስብሐት ለእግዚአብሔር
ልባችሁ ጆሮአችሁ መቼ ተገረዘ
የጠነከረ ነው ለአምላክ ያልታዘዘ
መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ
እንደገዛ ፈቃድ እየተመራችሁ
ስብሐት ለእግዚአብሔር
አዝ.....

<u>ኃይልህ ሲገለጥ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)</u>

ቅኝት -

ኃይልህ ሰገለጥ በሰማይ /2/
አቤት ማን ይቆም ይሆን ከፊትህ ማን ይቆም ይሆን
ማን ይቆም ይሆን ከፊትህ ማን ይቆም ይሆን
አቤት ቀንደ መለከት ሲነፋ
አዋጅ ሲታወጅ በይፋ
ጻድቃን ሲጠሩ ለተድላ
ምን ይሆን የእኛ ተስፋ
አዝ.....
አቤት መላእክት ሰማዩን ሲያርሱት
ቀድመው ሲሰሙ መባርቅት
ያልታየና ያልተሰማ
ድምፅ ሲሰማ ከራማ
አዝ.....
አቤት ሰባቱ ነፋስ ተገልጠው
ምድርን ሲያውኳት ቀዝፈው
ሲታዘዝ የባህር ሞገድ
ምድሪቱን ሊከድናት ለፍርድ
አዝ.....
አቤት ሲጠሩ ጻድቃን ቅዱሳን
መልካም የሰሩ ብሩካን
በምድር የሰሩ ትሩፋት
ሲያቀርቡ ለአምላክ ስብሐት
አዝ.....
አቤት ኃጥአን ግን ለፍርድ ሲጠሩ
በጨለማ ዓለም ሊቀሩ
የማይጠቅም ዋይታ ሆኖ
መዋረድ ይሆናል አዝኖ
አዝ.....
አቤት ሲጠሩ ጻድቃን ቅዱሳን
መልካም የሰሩ ብሩካን
በምድር የሰሩ ትሩፋት
ሲያሰሙ ለአምላክ ስብሐት
አዝ.....

ውሃ አጠጪኝ አላት (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -

ውሃ አጠጪኝ አላት አፍላጋት የሰራው
እንደ ተቸገረ ውሃ እንደጠማው ሰው
አይሁዳዊ አለችው አወይ አለማወቅ
ሰማያዊው አምላክ እራሱን ቢደብቅ
የእግዚአብሔር ስጦታ ውሃ ብጠይቅሽ
የሚፈርሰውን ዘር ትልቅ ነገር አርገሽ
አንተ አይሁዳዊ እኔ ሳምራዊ ነኝ
እንዴት ይቻልሃል ውሃ ልትጠይቀኝ
አዝ.....
እያልሽ ካለ እውቀት ግንብ እየገነባሽ
ምነው መለያየት መፍረስንስ ፈለግሽ
ትለምኚኝ ነበር የህይወትን መጠጥ
የእኔ አምላክነት በፊትሽ ቢገለጥ
አዝ.....
ወልደ ጓለእምህያው ውሃ ቢጠይቃት
ዘሩን ጠየቀችው ለመፍጠር ልዩነት
የሁሉን ፈጣሪ መሆኑን ሳታስብ
ይሁዳዊ አለችው በሚፈርስ ገንዘብ
አዝ.....
ይህን የዓለም ውሃ የሚጠጣ ሁላ
ሳይጠማ አይቀርም ከእንግዲህ በኋላ
እኔ የምሰጠው አያስጠማም እና
ሰዎችን ጥሪያቸው ይርኩ ይጠጡና
አዝ.....
የመንደሩን ሰዎች ወደዚህ ጥሪያቸው
ውሃ እንዳይጠሙ እስከ መጨረሻው
ይህንን ስትሰማ ደነገጠችና
ህሊናዋን ገዛች አገኘች ጥሞና
አለችው ጌታ ሆይ ውሃ እንዳልጠማ ከእንግዲህ በኋላ
እስከ መጨረሻው በህይወት ልሞላ
የሚያስጠማ ውሃ ለዘላለም ቀርቶ
ቃልህ ፍፁም ያርካኝ ህሊናዬን ሞልቶ
አዝ.....

አቤቱ ደግ ሰው (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት - ዋኔን
52-1 115 1113 4222 42
52-1 115 1113 4223 23
35-2-4453 1113 4222 42(2x)

35-2-4453 1113 4222 42(በበገና)

አቤቱ ደግ ሰው አልቋልና
ከምድርም ፍቅር ጠፍቷልና
እንደ ቸርነትህ አድነን
በደላችንንም አትቁጠር
በበገና...
የረድኤት አምላክ ፍቅር ስጠን
እንደ አህዛቡ አታድርገን
ክርስቲያን ነንና እንዋደድ
እባክህ አንውጣ ካንተ መንገድ
በበገና...
አቤቱ ንፁህ ልብ ፍጠርልን
ሰውን የሚያስወድድ ካለ እንከን
አንደበታችንም እንዲናገር
ስለ ሰላም ቋንቋ ስለ ፍቅር
አዝ.....
በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚመራ
ትሩፋት ደግነት የሚሠራ
አንደበቱ ሁሉ የታረመ
ለቃለ ወንጌሉ የደከመ
በበገና...
ምግባርና እውነት የተሰጠው
እባክህን ስጠን ሁነኛ ሰው
አንተን የሚመስል በሕይወቱ
ፍቅርና ትህትና የግል ሀብቱ
አዝ.....
የማስመሰል ፍቅር እየበዛ
ሰው ረክሷልና እንደዋዛ
ፍፁም መዋደድን ስጠንና
አዲስ ሰው እንሁን እንደገና
በበገና...
ደገኛ ሰው ማግኘት አስቸግሯል
እስከ መጨረሻ ማን ይፀናል
ምግባሩ ትክክል እውነተኛ
ልቡ የሚፀየፍ ከዳተኛ
አዝ.....

አልዓዛር ይነሳ(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት-

አልዓዛር ይነሳ መግነዙን ፍቱለት
በፅድቅ አደባባይ ይመላለስበት
ተስፋ ላለው ህይወት ልቡ ይነቃቃ
ነፍሱ እንዳትወሰድ በአጋንንት ተሰርቃ
የበደል እስራት መግነዙን ፍቱለት
ህይወትን ያግኛት ጽድቅን ይኑርባት
ሞት መሻሩን አውቆ ከሞት በላይ ይሁን
በእግዚአብሄር ቸርነት ልቦናው ይታመን
አዝ.....
በደሉ ቢበዛ ልቦናው ቢከብድም
ከአምላኩ ቸርነት በሚዛን ይበልጥም
ሐጥያቱን ተናዞ ንስሐ እንዲገባ
መንፃትን አሳዩት የፍቅርን እንባ
አዝ.....
የሚያስደንቅ ብርሀን አይቶ ይመላለስ
አዲሲቷን ምድር በንስሐ ይውረስ
ካህናት አፅናኑ ህዝቡን በፍቅር ቃል
ሞት እውነት አይደለም በቃሉ ተሸሯል
አዝ.....
በአምላክ ብርሀን ይመላለስ አይቶ
ንስሐ ይጠበው እንዲታይ አብርቶ
ንፁህ ልብስ አልብሱት ነፍሱ ሀሴት ታድርግ
እርሱም ህያው ይሁን በሰዎች መዓረግ

አዝ.....
ከመቃብር ይውጣ ጌታ እየጠራው ነው
ከህይወት እንጀራ ማነው የሚያግደው
ብርሃን ክርስቶስ ለእርሱ ተሰውቷል
ስጋው ለእርሱ እኮ ነው ማን ይመገበዋል
አዝ.....
ብርሀን ክርስቶስ አልዓዛር ይለዋል
መቃብሩን ሽሮ አዲስ ፍጥረት ሆኗል
ማነው ሙት የሚለው ከእንግዲህ በኋላ
ተጠርቷል በጌታ ወደ ፍፁም ተድላ
አዝ.....

እግዚአብሔር ለዳዊት (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
እግዚአብሔር ለዳዊት ቃልኪዳን ገባለት
የባህርይህን ፍሬ በክቡር ዙፋንህ አኖራለሁ ብሎት
ዳዊት ያን ሲሰማ እጅግ ተደስቶ
አመነ በቃሉ በሀሴት ተሞልቶ
ስለዚህ እንለምን ዘወትር ድንግልን
እንድታማልደን ከቸሩ አምላካችን
ይህንን ራዕይ ይህን ታላቅ ጥበብ
ሲያወጣና ሲያወርድ በህሊናው ሲያስብ
በጾምና ጸሎት ተግቶ ሲጠይቀው
በመንፈስ ቅዱስ ተሞላና ዳዊት
ብሎ ተናገረ በኤፍራታ አየናት
ስለዚህ እንለምን .....
ጮኸ በታላቅ ድምጽ ድንግልን ስላየ
በእንባና በደስታ ሲያወድሳት ቆየ
በገናውን ነስቶ ምሥጋና ሲጀምር
ልደቱን ጥምቀቱን ስቅለቱንም ሳይቀር
በራዕይ አይቶታል አንድም ሳይቀነስ አንድም ሳይጨመር
ስለዚህ እንለምን .....
በጸፍጸፈ ሰማይ ድንግል ልጇን አቅፋ
እንደ ልዩ ሀብር በድምቀት ተጽፋ
የዳዊት ከተማ የአንድዬ እናት
ጽዮን እናታችን የነቢያት እህት
ስለዚህ እንለምን .....
በተሸፈነ ቃል ኤፍራታ ይላታል
ከነቢያት አንዱ ሚኪያስ አይቷታል
ስለዚህ እንለምን .....
ከነቢያት አንዱ ሚኪያስ ተነስቶ
የመጪውን ዘመን በራዕይ ተመልክቶ
የኤፍራታ ክፍል አንቺ ቤተልሔም
የሚወለድብሽ ቸሩ መድኃኔዓለም
ስለዚህ እንለምን .....
ተንቀሽ ብትኖሪም ለብዙ ዘመናት
አታንሺም በፍፁም ከብዙ ነገስታት
የነገስታት ንጉስ ከአንቺ ይወጣልና
ትወልጂዋለሽ በህቱም ድንግልና
ስለዚህ እንለምን .....
ከሦስቱ አካል አንዱ ሥጋሽን ይነሳል
ሲጠበቅ የኖረው በአንቺ ይፈጸማል
የህያዋን እናት አንቺ ትሆኛለሽ
ሞትን ስለሚሽር አማኑኤል ልጅሽ
ስለዚህ እንለምን .....

ይበላሃላ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ይበላሃላ/6/
አንተንም አፈር ይበላሃላ
እንደሞኝ ሰው እንተላላ
ሞኝ ተላሌ/4/
ይደላህ መስሎህ ነገ እንደዛሬ
ንስሐን ትተህ ተበላህ አውሬ
ሞኝ ተላሌ/2/
አዝ.....
በላው አፈር/4/
ያንን ወታደር ያንን ምሁር
በላው አፈር/2/
ንስሐ ግባ የእናቴ ልጅ/2/
የክተት ጥሪ ሳይታወጅ
ስራና ሰሪው ሳይቀናጅ
ንስሐ ግባ የእናቴ ልጅ
አዝ.....
ንስሐን ትተህ የት ትሄዳለህ/2/
ሲመለከቱህ ታሳዝናለህ
ንስሐን ትተህ የት ትሄዳለህ
በላው አፈር/4/
ያንን ገበሬ ያንን ወታደር
በላው አፈር/2/
ተሰብሰብ ዛሬ ወደአምላክህ/2/
እንድታመልጠው ሰይጣንን ፈጥነህ
ተሰብሰብ ዛሬ ወደአምላክህ
የሰላም አምላክ ሲጠራህ ስማ/2/
በጠላት ነፍስህ እንዳትቀማ
የሰላም አምላክ ሲጠራህ ስማ
ፆምና ፀሎት ምጽዋት ሆነ/2/
መድኃኒት ሆኖ አለም ያዳነ
ፆምና ፀሎት ምጽዋት ሆነ
አዝ.....

ብስራተ ገብርኤል (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

በአምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን
ጌታ መጥቶ እስኪለብስ ድረስ ስጋን
ነቢያትም ስንኪን በህጉ ሲኖሩ
ከአህዛብ እነ በለዓም ሳይቀሩ
የስጋዌ ተገልጦላቸው ሚስጠሩ
በብዙ አምሳል እየመሰሉ ሲነግሩ
በሱባኤም ዘመኑን ሁሉ ሲቆጥሩ
እንዲህ አድርገው ደጅ ሲጠኑ ነበሩ
በመጋቢት በሃያ ዘጠኝ እለት
አስቀድሞ በጀመረበት ፍጥረት

ከዘመኑ ለዕለት እንኪን ሳይተርፍ
ከሰዓቱም አንዲት ደቂቃ ሳያልፍ
ተስፋውንም አዳም ከሰማ በኋላ
አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ሲሞላ
ለመፈፀም የማንነትን መሐላ
ከድንግል ዘንድ መልአኩን ላከው ገሊላ
ድንግልም በልጃገረድ ስርዓት
በአጭር ታጥቃ ማድጋ ነጥቃ ከቤት
ወደ ወንዝ ውሃ ልትቀዳ ሄደች
ከዚያም ወርዳ የጠማው ውሻ አየች
ሲያባርሩት ና ሂድ እያሉ ሴቶች
ምነው ለእርሱስ አታዝኑለትም አለች
ቸር ነችና ከፈጣሪዋ በታች
መለሱላት እንዲህ እያሉ ሴቶች
የስራ ፈት ይመስላልና ትጥቅሽ
ይኸውልሽ አጠጪው አንቺ ቀድተሽ
ድንግልም የእነርሱን ነገር አድንቃ
ለፍጥረቱ ታዝናለችና አጥብቃ
ወርቅ ጫማ ከተረከዟ አውልቃ
አጠጣችው ከማድጋዋ ፈልቃ
እኒያም ሴቶች እንዲህ ስታደርግ ቢያዩዋት
እንዳትቀጂ ውሃው ጉድጓድ ነው አዘቅት
ማድጋሽን ምን ልትሞይው ነው አሏት
ሃይማኖቷ ፍፁም ነውና ከጥንት
አለቻቸው እነዚያን እናንት
አታስቡ ምን ትሞላው ነው ብላችሁ
ከወደታች ውሃ የሚገኝ መስሏችሁ
ይህን ውሻ ያጠጣው አምላክ የት ሄዶ
ይሞላዋል ከወደሰማይ አውርዶ
ስትጨርስ ይህን ተናግራ ወዲያው
ማድጋዋን በተዓምራት ሞላው
እኒያም ሴቶች እንዲህ ስታደርግ ቢያዩዋት
በዚያ ወራት ጉባኤ አድርገው ለሁሉ
ይወለዳል አምላክ ከድንግል እያሉ
ነቢያትም ይናገራሉ ትንቢት
የአምላክ እናት አንቺ ትሆኚ አሏት
እንዲህ ብለው ሲነጋገሯት ምጸት
ሳያውቁት ተናገሩላት ትንቢት
ድንግልም በሴቶች ሁሉ ልማድ
በጀርባዋ ውሃዋን አዝላ ስትሄድ
ትፀንሻለሽ በድንግልና የሚል
ድምፅ ሰማች ከወደኋላ ድንግል
ተሰወራት ምን ይሆን ብላ ልትለይ
ወደኋላ መለስ ብላ ብታይ
ይሆናል ያው ጡላታችን ሰይጣን
ያሳታቸው አባትና እናቴን
ይህን ብላ ዝም ብላ ሄደች ቤቷን
ከዚያም ሄዳ ሸክሟን ስታወርድ ከቤት
ትፀንሻለሽ በድንግልና አላት
ይሄ ነገር እውነት ነገረኝ መሰለኝ
ያንኑ ቃል አሁን ደግሞ እዚህ ደገመኝ
ይህን ብላ ከመቅደስ ሄደች ተነስታ
ከዚያም ሄዳ የወርቅ ወንበሯን ዘርግታ
ስትፈትል ወርቅና ሐሩን አስማምታ
መልአኩም ልብሱም ሲታጠቅ ሲፈታ
ደስ ይበልሽ ላንቺ ይገባል ደስታ
ብርክት ነሽ እያለ ሰጣት ሰላምታ
ድምፁን ሰምታ መልአኩን አይታ ለይታ
እንዲህ ብላ መለሰችለት ድንግል
ምድር ብትል ያለዘር እህል ላብቅል
ሴትም ልጅ ያለወንድ ልውለድ ብትል
ይቻላል ወይ መቼስ ተደርጎ ያውቃል
እኔ ድንግል ወንድ አጠገቤ አይደርስ
ይህን ነገር የት አገኘኸው አንተስ
መለሰላት እንዲህ እያለ ሳይዋሽ
ማርያም ሆይ አትፍሪ አንቺስ አይዞሽ
ያንቺማ ፅንስ እንደ ሴቶች ፅንስ መስሎሽ
ካንቺ ባህርይ አንዱ አካል ስጋን ሲለብስ
ያድርብሻል አንዱ አካል መንፈስ ቅዱስ
ያፀናሻል አንደኛው አካል አብም
በባህሪሽ እንዳያገኝሽ ድካም
እንዲህ አድርገሽ ሳትፈልጊ ወንድን
ትወልጃለሽ ከሶስቱ አካል አንዱን
እንኪን አንቺ ሙቀት ልምላሜ ያለሽ
ያረጀችው ኤልሳቤት እንኪን እህትሽ
በእርጅናዋ እግዚአብሄር ሰጥቷት ልጅን
ካረገዘች ስድስት ወር ሆኗት የለን
ትፀንሻለሽ በድንግልና አንቺም
ለእግዚአብሄር የሚሳን ነገር የለም
ስትመልስ እንዲህ እያለች እርሷም
እነሆ አለሁ የእግዚአብሄር ባርያው አሁን
እንደቃልህ ይደረግልኝ አሁን

<u>አምላኬ አምላኬ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)</u>

ቅኝት -

አምላኬ /3/ ፈጣሪ አምላኬ አምላኬ
ስለህ ደስ ይለኛል
በቸገረኝ ጊዜ ከተፍ ይልልኛል /2/
አይቀርም ሞቱ
በቸገረኝ ጊዜ ከተፍ ይልልኛል
እንባዬ ወረደ /2/ ሆዴን ምነው ከፋው
አምላክ እያለልኝ የችግሬ መፍቻው /2/
አይቀርም ሞቱ
አምላክ እያለልኝ የችግሬ መፍቻው
ሰማዩም መሬቱም ደጋውም ቆላውም
ባህሩም ጠፈሩም ሁሉም ያንተ ሀገር ነው
ልቤ ከወደደው ብሰነብት ምነው /2/
አይቀርም ሞቱ
ልቤ ከወደደው ብሰነብት ምነው
ከአዳም ልጆች መሀል ልቡናው የጠፋ ማሰብ የተሳነው
በሰው ግፍ ይሰራል ተዘጋጅቶ ጽዋው/2/
አይቀርም ሞቱ
በሰው ግፍ ይሰራል ተዘጋጅቶ ጽዋው

ይሄ ቂላቂሉ የዋህ ሞኛሞኙ ጥበብ የጐደለው
እህል ያከማቻል ስንቅ እየመሰለው/2/
አይቀርም ሞቱ
እህል ያከማቻል ስንቅ እየመሰለው
ታላቅ ባለሞያ ጉዳዩ የገባው የተመራመረ
የነፍስ ስንቅ አግዞ በሰማይ አኖረ /2/
አይቀርም ሞቱ
የነፍስ ስንቅ አግዞ በሰማይ አኖረ
ቤተክርስቲያን ጓሮ /2/ ሰው እየዘራችሁ
ሲበሰብስ እንጂ ሲበቅልን አያችሁ /2/
አይቀርም ሞቱ
ሲበሰብስ እንጂ ሲበቅልን አያችሁ
ካጣቢውም ይሁን ከሳሙናው ይሁን ከእንዶዱ ማነስ
አፈር መስሎ ታየኝ የሰው ሁሉ ልብስ /2/
አይቀርም ሞቱ
አፈር መስሎ ታየኝ የሰው ሁሉ ልብስ
ሥጋ ሥጋ ሽተትክ /2/ ለምን ትለኛለህ
ይህን እርጥብ ስጋ ለብሼው እያየህ /2/
አይቀርም ሞቱ
ይህን እርጥብ ስጋ ለብሼው እያየህ
እኔስ እሄዳለሁ ሳሙና ፍለጋ አጣቢ ፍለጋ
እጅግ አድፎብኛል የለበስኩት ሥጋ /2/
አይቀርም ሞቱ
በጣም አድፎብኛል የለበስኩት ሥጋ
ሰይጣን አታለለኝ/2/ ወርቅ እያፈለቀ
ከቶ ምን ሊበጀኝ ዘመኔ ካለቀ /2/
አይቀርም ሞቱ
ከቶ ምን ሊጠቅመኝ ዘመኔ ካለቀ
ሰው ሁሉ እያወቀው /2/ አልሞትም ማለቱ
ይረዳዋል በግድ ሲፈራርስ ቤቱ
አይቀርም ሞቱ
ይረዳዋል በግድ ሲፈራርስ ቤቱ
ታላቁን ገበያ ጸሎትን ገፍቼው
የጽድቁን መሰላል ምጽዋትን ትቼው
ሕሙማን መጠየቅ ከንቱ እየመሰለኝ
ሞት ይጠራኝ ጀመር ከቶ ምን ይዋጠኝ/2/
ስንቄን ሳላደራጅ ተጠራሁ መሠለኝ
አንተ መጠየቅ ወዳድ ምን ይመልስ ይሆን /2/
ነጣቂ ሳይወስደኝ ሌባ ሳይመጣብኝ
በሬን ልዘጋጋ የሰማይ መንገዴን /2/
አንቺ የፍቅር ድግስ ፍኖተ ሰላም
ወንጌል እናታችን እስከ ዘለዓለም /2/
የወልድ ገንዘቡ በሥጋ የገዛው
መከራ መስቀሉ መሞት መነሳት ነው/2/
ሥጋው ከመለኮት ሳይለይ የሠራው
በመቃብር ያሉን ማስነሳቱ እኮ ነው

በማዳኔ ቀን ጠራሁህ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -

በማዳኔ ቀን ጠራሁህ ይለናል ጌታ
ዛሬ እንመለስ በፍጥነት ሳናመነታ
ነገ ለራሱ አያውቅበት ለነገው ሰው ነው
የእኛ ቀን ዛሬ መሆኑን ሁሉም ይረዳ
ለንስሐ ነው የሰጠን ይህንን ጊዜ
ነገ ሳይመጣ ታጅቦ በሞት ትካዜ
በሞት መዳፍ ነን ሰዎች ሆይ እንዳንዘነጋ
እንሄዳለን ለፍርዱ 'ፈጣሪ ጋ
በማዳኔ ቀን ጠራሁህ ይለናል ጌታ...
የነገን ነገር ማን አውቆ ይተማመናል
ዛሬ ነው መዳን በእውነት ኑ ተብለናል
የእግዚአብሔር ጥሪ ካወቅነው እጅግ ኃያል ነው
በፍቅሩ ስቦ ለማዳን እጁ ሰፊ ነው
በማዳኔ ቀን ጠራሁህ ይለናል ጌታ...
ጌታ በረከት በእጁ ሞልቶ ተርፎታል
በእግዚአብሔር ታመን በጽድቁ ልብህ ይረካል
እንደ ወንዞቹ ሰላምህ ተርፎ ይፈሳል
የአምላክ በረከት ሁል ጊዜ ይከተልሀል
በማዳኔ ቀን ጠራሁህ ይለናል ጌታ...

የእኛ ጌታ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት - ስለቸርነትህ

የእኛ ጌታ የኛ መድኃን
በቸርነትህ ታደገን
እኛ እንደሆነ ኃይል የለን
ጠዋት ለምልማ ማታ ጠፋች
የሰው ህሊና እያባባች
ዓለም ምኗ ነው የጣፈጠን
እያሳሳቀ የወሰደን
አዝ...
ዛሬ አለች ሲኢት ትጠፋለች
ከነተንኮሏ ዓለም ሟች ነች
እሸህ በቅሎባት እሸህ ሆና
በመተላለፍ ሰው ሊያልቅ ነው
አዝ...
ከእኛ ጋር ያለው ኃያል ነው
በሥጋዊው ዓይን ባናየው
የጦሩ ብዛት መች አድኗት
የዓለምን ትምክህት ተዋህዷት
አዝ...
እንደ ሰው ጥበብ ጥበበኛ
እንደሰው ንብረት ወደረኛ
እንደ ዓለም ጉልበት ጉልበተኛ
በአምላክ ፊት ሲታይ ህመምተኛ
አዝ...

ማን ይመራመር (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ማን ይመራመር/4/
ያንተን ስራ ያንተን ግብር ማን ይመራመር

አምላክ ሆይ ድግስህን እንዳታሳንሰው
ጌታ ሆይ ድግስህን እንዳታሳንሰው
ቀርቶ አይቀርምና አንተ የጠራኸው ሰው
ያንተን ስራ...
እባክህ አምላኬ ስጠኝ መስታወት
እባክህ ጌታዬ ስጠኝ መስታወት
የሰው ስራን ትቼ የኔን አይበት
ያንተን ስራ...
ጎረቤት አይጥላህ መንደሩ አይክፋብህ/2/
ጎረቤት አይጥላህ ሀገር አይጠላህ
ለጠባቧ አለም ለሆድህ ብለህ
ያንተን ስራ...
ያሳጣህን ወገን ያሳቀልከው ያኔ
እርሱ አፈር በላው ላንተ ግና መጥኔ
ያንተን ስራ...
የማይለወጠው ስራችን ብቻ ነው/2/
ሲነገር የሚኖር ደጉ ወይ ጠማማው
ያንተን ስራ...
እግዚአብሄር ንፍርቱን ቢተወው ቢተወው/2/
ምነው ልክ አለፈ ዝርፊያው እና ቅሚያው
ያንተን ስራ...
ዝምታ ስንፍና እየመሰላቸው/2/
ግድየለም ይጨዱት ይከምሩት ደርሰው
ያንተን ስራ...

ዋ እኔን (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ዋ እኔን/7/ እኔን እኔን/3/
የብርሃን አምላክ የህይወት መገኛ
ፀጋን ልታድለን ብትመጣ ወደኛ እኔን እኔን...
በኛ የነበረን ጨለማን ልታርቅ
ከሞት ወደ ህይወት ልታሸጋግረን እኔን እኔን...
ነውር የሌለብህ ንፁህ ሆነህ ሳለ
በሞቱ አከበረን ስለኛ ታመመ
የሞት አበጋዝን ሰይጣንን ሊያጠፋ
የሲኦል ፍርሃት በኛ እንዳይስፋፋ እኔን እኔን...
ህይወት ያቀዳጀን ከሰማይ በታች
በስጋው መከራን ተቀበለ እንጂ እኔን እኔን...
እርሱ በባህሪው መቼ ይሞታል አምላክ
ይወደሳል እንጂ በሊቃነ መልአክት እኔን እኔን...
ነፍሴ እስከሞት ድረስ አዘነች እያለ
በጌቴ ሴማኒ ጌታ ተናገረ እኔን እኔን...
የመከራው ፅዋ ይለፍልኝ ብሎ
አባቱን ተጣራ በስጋው ተጨንቆ እኔን እኔን...
ጠላትን አያውል አያሳድር ብሎ እኔን እኔን...
ይሁዳ ጉንጮቹን ሳመው በክህደት
ከሁሉ አልቆ የሰጠውን ክህነት
ወዳጄ ሆይ አለው ጌታ በትህትና እኔን እኔን...
የይሁዳን ተንኮል ምክሩን ያውቃልና እኔን እኔን...
ትምህርተ ፍቅሩን የፀብ አደረከው
መጥተሃል ወይ ዛሬ አለና ነገረው እኔን እኔን...
ጌታ እንደበደለ ቆመ በአደባባይ እኔን እኔን...
ጲላጦስ አምላኩን ፈጣሪውን ሊዳኝ
ያሳጡት ይከሱት ይጮሁ ጀመረ እኔን እኔን...
እርሱ ግን ለዚህ ሁሉ መቼ ተናገረ እኔን እኔን...
እንደበግ ሊነዳ ስለተቆጠረ እኔን እኔን...
ጌታን ገረፉና ሊሰቅሉት አጋዙት
ከለሜዳ አልብሰው ዘበቱበት በእርሱ እኔን እኔን...
ከእሾህ አክሊል ሰርተው ደፉበት በራሱ
ሺህ ጥቃቅን እሾህ ሰባው ታላላቅ ነው እኔን እኔን...
በጌታችን ራስ ወየው የተሰካው
ፊቱንም በጡፊ ይመቱት ጀመረ እኔን እኔን...
ለመግረፊያ የሚሆን ጉጥና ስለት እኔን እኔን...
አብረው አስገመዱ ጌታን ሊገርፉት እኔን እኔን...
ስጋውን መተሩት ገረፉት በግፍ እኔን እኔን...
ደሙ እንደ ውሃ ፈሰሰ በመንገድ
ወደ ቀራንዮ አምላካችን ሲሄድ እኔን እኔን...
እኔን/7/ እኔን እኔን/3/

አላየንም በሉ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

አላየንም በሉ እስኪ አልሰማንም በሉ/2/
ያ ሞት ሲፈልገን ሲሻን ውሏል አሉ እስኪ አላየንም በሉ
እንዴት እሆናለሁ ኧረ እንዴት እሆናለሁ
ዛሬም እራት የለኝ ነገም እሞታለሁ ኧረ እንዴት እሆናለሁ
መንገድ ላይ ወድቄ እያየኝ ያለፈኝ/2/
ነገም የእርሱ ተራ መሆኑ መሰለኝ እስኪ አላየንም በሉ
ገንዘቡ ሳይጠፋ እንተዛዘን ስልጣን ሳይወገድ እንተዛዘን
ነገ ሁሉ ቀርቶ እኩያ ሳንሆን እኩያ ሳንሆን
አላየንም በሉ እስኪ አልሰማንም በሉ
አዋጁ ሲታወጅ ሲነገር ወንጌሉ እስኪ አልሰማንም በሉ
ምናልባት ምናልባት ነገሩ ያልገባው/2/
ንስሐ ግቡ ነው ዲያቆኑ የሚለው ካህኑ የሚለው
በግፍ የተገኘ ገንዘቡም አለቀ
ያጠለቅነው ካባ ስልጣኑም ወለቀ
ጀርባችን በትዝብት ቀረ እንደደቀቀ እስኪ አላየንም በሉ
እስኪ አላየንም በሉ እስኪ አልሰማንም በሉ
አዋጁ ሲታወጅ ሲነገር ወንጌሉ እስኪ አላየንም በሉ

እስመ አንተ(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

እስመ አንተ አምላከ ሰማይ ወምድር
እስመ አንተ ምሉአ ፀጋ ወክብር
በቅድስና መንግስትህም ንፁህ
በልዕልና ባህሪህም ምጡቅ
በሰው ሀገር የማትመረመር ፈጣሪ
ለዘላለም የማትነዋወፅ ነዋሪ
ትባላለህ በነግህ በሰአት በቀትር
ኢየሱስ ደግ ባለፀጋ ንጉስ
ወተሰቅለ በእንቲአነ ኢየሱስ
ኮነ ህይወትነ ፅንእነ ቤዛነ

አንተ እንጂ ነህ የማትነዋወፅ አታንስ
ብርቱ ዳኛ ያላንተ የለም ደገኛ
እስመ ልዑል ወግሩም አንተ ኢየሱስ
አንተ ብትወድ ሁሉ ይሆናል ዘመድ
ብሉ ጠጡ ልበሱ ይላል በግድ
አንተ ብትጠላ የሚሆን የለም ከለላ
ለዚህ አለም እየተገዛች ስጋዬ
ባከነብኝ የተሰፈረው ጊዜዬ
ምንም ምንም የነፍሴን ነገር ሳልሰራ
ተቃረብኩኝ ከላይኛው ቤት ልጠራ
ዳሩ ግና አዛኝ መሐሪ ነህና
አደራህን የነፍሴን ነገር አትጠና
ሞት አለና ሀብታሙን ፈርቶ ሳያፍር
ለደሃውም ጉስቁልናውን ሳይቆጥር
መበስበስ ደግሞ አለ ደግሞ መፍረስ
አፈር ሆኖ ከአዋራ ትቢያ መድረስ
መነሳት ደግሞ አለ ፍርድ መስማት
ባህቲቱ እስመ ለአለም ምህረቱ
መላእክቱ አይሸፍቱበት ከቤቱ
ሌላ ጌታ ያላንተ የለም በከንቱ
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከዘላለም ድረስ/2/

በማዳኔ ቀን ጠራሁህ (ዘማሪ ይልማ ታይሉ)

በማዳኔ ቀን ጠራሁህ ይለናል ጌታ
ዛሬ እንመለስ በፍጥነት ሳናመነታ
ነገ ለራሱ አውቆበት የነገው ሰው ነው
የእኛ ቀን ዛሬ መሆኑን ሁሉም ይረዳ
ለንስሀ ነው የሰጠን ይህንን ጊዜ
ነገ ሳይመጣ ታጅቦ በሞት ትካዜ
በሞት መዳፍ ነን ሰዎች ሆይ እንዳንዘነጋ
እንሄዳለን ለፍርዱ እፈጣሪ ጋ
በማዳኔ ቀን ጠራሁህ ይለናል ጌታ...
የነገን ነገር ማን አውቆ ይተማመናል
ዛሬ ነው መዳን በእውነት ኑ ተብለናል
የእግዚአብሔር ጥሪ ካወቅነው እጅግ ታያል ነው
በፍቅሩ ስቦ ለማዳን እጁ ሰፊ ነው
በማዳኔ ቀን ጠራሁህ ይለናል ጌታ...
ጌታ በረከት በእጁ ሞልቶ ተርፎታል
በእግዚአብሔር ታመን በጽድቁ ልብህ ይረካል
እንደ ወንዞቹ ሰላምህ ተርፎ ይፈሳል
የአምላክ በረከት ሁል ጊዜ ይከተልሀል
በማዳኔ ቀን ጠራሁህ ይለናል ጌታ...

ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ

ውለታህ ብዙ (ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ)

ውለታህ ብዙ እግዚአብሔር
ስንቱን ዘርዝሬ ልናገር
ስለማይነገር ስጦታህ
ክበር ተመስገን ልበልህ
ክበር ተመስገን ጌታችን/2/
ለዚህ ያደረስከን
በአምሳልህ ፈጥረህ አክብረህ
በፍፁም ፍቅርህ ጠብቀህ
የምትመግበን በችሮታ
ክበር ተመስገን የኛ ጌታ
ክቡር ገናና ታያል ነህ
ማንም በምንም አይመስልህ
የዓለማት ገዢ ኤልሻዳይ
የጌቶች ጌታ ሁሉን አዶናይ
ክበር ተመስገን ጌታችን/2/
ለዚህ ያደረስከን
መርገም ተጭኖን የሃጥያት እዳ
ሲኦል ስንጋዝ ስናይ ፍዳ
መጥተህ ፈለከን በፍቅር
ከእቅፍህ ወጥተን እንዳንቀር
ከድንግል ማርያም ተወልደህ
አርአያ ቤዛ ሆነህ
ፍፁም ፍቅርህን ገለፅክልን
ሰላማችንን አወጅክልን
ክበር ተመስገን ጌታችን/2/
ለዚህ ያደረስከን
አዝ...

ሰላም ተዋህዶ (ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ)

ሰላም ተዋህዶ ሰላም ኦርቶዶክስ
በደሙ ያጸናሽ መድኅን ኢየሱስ

የአዳም መመኪያ የሄዋን ሀገር
አንቺ አይደለሽም ወይ የቅዱሳን ክብር*
በከንቱ የሞተው የአቤል መስዋዕት
የሄኖክ ሃይማኖት ያዳንሽው ከሞት
አንቺ የኖህ መርከብ የሴም በረከት*
በአብረሃም ድንኳን ተወልደሽ ያደግሽ
የይስሐቅ መዓዛ ወደር የሌለሽ
ያዕቆብ በህልሙ በቤቴል ያየሽ
የዮሴፍ አጽናኙ ተዋህዶ ነሽ*
አዝ...
የሙሴ ጽላት ነሽ የአሮን በትር
የኢያሱ ሐውልት የጌዲዮን ጸምር
የሳሙኤል ሙዳይ የእሴይ ትውልድ
የዳዊት በገና የሰሎሞን ዘውድ
የታተመች ገነት የምስጢር ጉድጓድ*

ቡአዴና ህድረት የኬልቄዶን ዘር
ቱሳሄና ሚጠት ውላጤም ጭምር
ያልተቀላቀለሽ ንጽህቲቱ ምድር
ኢሳይያስም አይቶ በሩቅ መነጽር
ስለቅድስናሽ ሆነ ምስክር*
ሰላም ተዋህዶ ሰላም ኦርቶዶክስ
የአትናትዮስ ሐውልት የዲዮስቆሮስ*
አዝ...

በነኤልያስ ቤት የወርቅ መሶብ
ውስጥሽ የተሞላ በምሥጢር ምግብ
የኤልሳ ማሰሮ የህይወት መዝገብ
ፋራን የምትባል የእንባቆም ተራራ
ሁሉን የምታሳይ ከቀኝ ከግራ
የሕዝቅኤል እልፍኝ ባለአንድ በራፍ
የማትከፈቺው በኬልቄዶን ቁልፍ*
የህግ መፍለቂያ የነፃነት ቦታ
የሚኪያስ ሀገር አንቺ ነሽ ኤፍራታ
እፀህይወታችን የኤፌሶን ቅርስ
የተፈወሱብሽ እነ አቡን ቄርሎስ
ለተፈወስንብሽ ከኬልቄዶን ቁስል
ተዋሕዶ ላንቺ እልል እንበል*
አዝ...

አንቺን በማየቱ በብርሃን ተቋም
ደስ አለው ከልቡ ዘካርያስም
በውስጥም በውጪም የሌለሽ እንከን
የህይወት ምግብ ነሽ ተዋህዷችን*
ሐዋርያት ይምጡ ያውሩ ያንቺን ዜና
የሚያወቅ ሲናገር ደስ ያሰኛልና
ሰማዕታት ልጆችሽ የፃፉሽ በደም
የህይወት መጽሐፍ ነሽ የጽድቅ የሰላም*
አንቺን ለመጠበቅ እስከ ዓለም ፍፃሜ
ቃል እንገባለን ባለንበት እድሜ*
እናምናለንና በፈጣሪያችን
እናምናለንና በአምላካችን
ካንቺ እንደማንለይ ምን ጊዜም ቢሆን*
አዝ...

ጽኑ ክርስቲያኖች (ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ)

ቅኝት - ስለቸርነትህ
423115-13 42 422-22-2 42
423115-13 42 423 33-3231
545-13 42 45 422-22-2 42

545-13 42 45 422-22-2 42(በበገና)

423115-13 42 422-22-2 42
423115-13 42 423-33-3231
545-13 42 45 423-33-3231
545-13 42 45 422-22-2 42

ጽኑ ክርስቲያኖች ልባችን አይውደቅ
የእግዚአብሔርን እቃ ጦሩን እንታጠቅ/2/
ማዕበሉን አይቶ ልባችን አይፍራ
ታማኙ ጌታችን አለ ከእኛ ጋራ /2/
በበገና...

ሰማዕታት ልጆቿ የዓለምን ጣዕም ንቀው
ያላውያንን ዛቻ ፈተናውን አልፈው
ረሃቡን ስደቱን መከራን ታግሰው
ለዚህ አድርሰዋታል ተዋሕዶን ጠብቀው
ክህደቱ ቅሰጣው ኑፋቄው ቢነዛ
ሰይፍ ስለቱ ቢያፏጭ ፉከራው ቢበዛ
በድንግል ቃል ኪዳን መሠረቷ ጠብቋል
በቅዱሳን ጸሎት ቅጽሯ በእሳት ታጥሯል
አዝ...

ጥንተ ጠላታችን ፈተና እያስነሳ
ዙሪያችንን ቢከብብ ተርቦ እያገሳ
መከራን ቢያበዛ ስደት ቢያደርስብን
እስከ ሞት የሚያደርስ ስቃይ ቢያበዛብን
ዓለም ላቆመችው ለጣኦት አንሰግድም
በመከራው ጽናት ሀይማኖት አንክድም
ከሚነደው እሳት አምላክ ያድነናል
ባያድነን እንኳን እሳቱን መርጠናል
አዝ...

እንደ ግያዝ አንሁን ታውሮ አይናችን
በእሳት ሰረገሎች ተከቧል ዙሪያችን
ሰይፍን የሚያነሱ በሰይፍ ይወድቃሉ
ከእኛ ጋራ ያሉት ከእነርሱ ይበልጣሉ።።
የጠሉህን ውደድ በሚል ሀያው ቃሉ
ሲያሳድዱህ ጸልይ በሚል ክቡር ቃሉ
በመንፈሳዊው ፍቅር ይጠንክር ልባችን
ይህን ነው ያዘዘን ቅዱስ አምላካችን
አዝ...

ነቅተን ከታጠቅን የጽድቅን ጥሩር
በትጋት ከቆምን በእምነት በፍቅር
በጾምና ጸሎት ስግደት ምጽዋት
በንስሃ ጸድተን ከጸናን በእውነት
በሥጋ ወደሙ በጸጋው ከታተምን
በህይወትም በሞት ከእርሱ ጋር ሀያው ነን
በወደደን በእርሱ ከሁሉ እንበልጣለን
በወደደን በእርሱ አሸናፊዎች ነን
አዝ...

ንፋሱ ማዕበሉ የማይነቀንቀው
መሰረቷ ጽኑ ቅጽሯም ጠንካራ ነው
የገሀነም ደጆች አይችሏትምና
ጸንታ ትጓዛለች ተዋሕዶ ገና
ጽኑ ክርስቲያኖች ልባችን አይውደቅ
የእግዚአብሔርን እቃ ጦሩን እንታጠቅ/2/
ማዕበሉን አይቶ ልባችን አይፍራ
ታማኙ ጌታችን አለ ከእኛ ጋራ /2/
አዝ...

የቅዱሳን አምባ (ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ)

የቅዱሳን አምባ ሀገረ እግዚአብሔር
የስልጣኔ ምንጭ የታሪክ ማህደር
ክብርት ኢትዮጵያ ቅድስት እናታችን
አንቺን የመረጠ ይክበር አምላካችን
ይክበር አምላካችን
የሰሎሞን ጥበብ ምስጢሩ እና ፍቅሩ
በንግስተ ሳባ መጥቷል ወደ ሀገሩ
ንዋየ ቅድሳት ገዳማት አድባሩ
የጥበብ አሻራው ዛሬም አለ ክብሩ
አክሱም ላሊበላ ግማደ መስቀሉ
የዜማ የቅኔ የአቋቋም ባህሉ
የዕለት የዓመት የዘመን ቀመሩ
ምልክቶች ናቸው ላስተዋለው ሁሉ
ላስተዋለው ሁሉ
ተወስዶ የነበረው ሐውልት ተመልሷል
በቀደመ ቦታው በክብር ተተክሏል
ታሪኩን ተረድቶ ወቅቱን ላስተዋለው
ለኢትዮጵያ ትንሳኤ ይሄ ምልክት ነው
በፅዮን ቃልኪዳን ሁሉም ይመለሳል
እናታችን ብሎ ዙሪያዋን ይከባል
እንደተሰደድን መቼ እንቀራለን
ደሃ እንደተባልን መቼ እንኖራለን
ታሪክ ይለወጣል በዓለም እንገናለን
በዓለም እንገናለን
ኢትዮጵያውያን ሁሉ በስደት ያላችሁ
ግቡ ወደሀገር ቤት ለእድል ፈንታችሁ
እርም የሆነውን ግብር ሃጥያትን ትታችሁ
የአህዛብን ባህል ልማዱን ጥላችሁ
ወርቅ እንቁ አልማዙን ጥሩውን ይዛችሁ
ቶሎ ከግብፅ ውጡ እውቀቷን ዘርፋችሁ
ኢትዮጵያዊ መልኩን አይለውጥምና
እንደ አባቶቻችን ለሀገር እንቅና
በበለዓም ምክር ተታለን እንዳንወድቅ
ከአህዛብ ጣአታት ተንከል እንጠንቀቅ
ተታለን እንዳንወድቅ
ክብሯ ይመለሳል አትጠራጠሩ
ሁሉም በእጃችን ነው ጥበብ ነው ምስጢሩ
የአርባ ቀኑ መንገድ አርባ አመት እንዳይሆን
በጥበብ እንጓዝ እንደያዝን መንገዱን
እንደ ነህምያ በእምነት ተነስተን
----------ንቀን
የህዝባችንን ልብ ለስራ አስጨክነን
ጠላት እንዳይወረን ትጥቃችንን ታጠቀን
እኛ ባሪያዎቹ ተነስተን እንስራ
ጥበብን በፍቅር አርገን ከኛ ጋራ
በፍቅር እንስራ
ጥበብ እግዚአብሄር ነው ሁሉን ተፈጠረ
ሁሉን የመከረ ሁሉን ያስተማረ
የኃያላን ኃያል የጌቶች ጌታ ነው
ሁሉንም ይችላል የለም የሚሳነው
ሁሉን ቻይ አምላክ ነው አዝ...

በምን በምን እንመስልሽ(ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ)

በምን በምን እንመስልሽ ድንግል ማርያም
ኦ ድንግል ምሳሌ የለሽ አንቺን የሚመስል
አንቺን የሚመስል
በሔዋን ምክንያት የተዘጋው ገነት
በአንቺ ተከፈተ በልጅሽ ምህረት
የተዋሕዶ ምስጢር የተገለጠብሽ
የቃልኪዳኑ ውል ማሰሪያው አንቺ ነሽ
ማሰሪያው አንቺ ነሽ/2/
ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ
አንቺን የሚመስል ማን አለ በዓለም ላይ
ማን አለ እንዳንቺ ጌታን የወለደ ይዞ የተሰደደ
በሐዘን ፍላፃ ልቡ የተወጋ የተንሰፈሰፈ
ወላዲተ አምላክ ማርያም አንቺ እኮ ነሽ
ኪዳነ ምህረት ድንግል አንቺ እኮ ነሽ
በመኑ በአምሳለ መኑ ናስተማስለኪ
ኦ ድንግል ምልዕተ ውዳሴ ምልዕተ ውዳሴ
ምልዕተ ውዳሴ
ዳዊት በበገና በመንፈስ በትንቢት እንዳመሰገነሽ
አባ ሕርያቆስ በንፁህ ልቦናው እንደቀደሰልሽ
ሶሪያዊው ኤፍሬም ውዳሴሽን በፍቅር እንዳደረሰልሽ
ማሕሌታይ ያሬድ በአርያም ዜማ እንደዘመረልሽ
ድንግል እመቤቴ እኔም ላመስግንሽ
እንደ አባ ጊዮርጊስ ፅዋውን አጠጪኝ
ማርያም ሆይ እመቤቴ ሆይ ድንግል/3/
እልሻለሁ እስከ ዘለዓለም አለም
ቀምሻለሁ የእናትነት ፍቅርሽን
አይቻለሁ ፍፁም ጥበቃ ምልጃሽን
እናቴ ነሽ ዘውትር በህይወቴ የማልረሳሽ
በደስታዬ በሐዘኔ ጊዜ የማነሳሽ
እመቤቴ ስጦታዬ ነሽ ሽልማቴ
እመቤቴ መፅናኛዬ ነሽ ህይወቴ
እመቤቴ ምልክቴ ነሽ አርማዬ
እመቤቴ መጠጊያዬ ነሽ አምባዬ
እመቤቴ መመኪያ ነሽ ጋሻዬ
እመቤቴ ክብሬ ስሜ ነሽ መጠሪያዬ
የታደሉት በአንቺ ምስጋና ተመልተው
አወደሱሽ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው
እኔ ደሃው በምን አቅሜ ልቻለው
በምን ቋንቋ በምን አንደበት ልግለጸው
የዋልሽልኝ ድንግል ውለታሽ ብዙ ነው/2/

ሰዓሊለነ ማርያም (ሲሳይ ደምሴ በገና)

ቅኝት -

ሰዓሊለነ ማርያም /2/
ሐበ ወልድኪ ሔር መድኃኔዓለም
ለምኚልን ማርያም /2/
ከቸሩ ከልጅሽ ከመድኃኔዓለም
ለመኑ እነግር ሀዘነ ልብየ
እንበሌኪ ማርያም እግዝእትየ
ወፍጡነ ስምእኒ ጸሎትየ
ለምኚልን ማርያም .....

ለማን እነግራለሁ የልቤን ሀዘን
የጌታዬ እናት ከአንቺ በቀር
ፈጥነሽ ስሚኝ ጸሎቴን
ሰዓሊለነ ማርያም .....
ድንግል ሆይ አሳስቢ ሀዘን መከራሽን
በሄሮድስ ዘመን የደረሰብሽን /2/
ድንግል ሆይ አሳስቢ ረሃብ ጥምሽን
በግብፅ በረሃ የደረሰብሽን /2/
ለጻድቃን ያይደለ ለኃጥአን አሳስቢ
ለንጹሃን አይደል ለአደፉት አሳስቢ /2/
ለምኚልንማርያም .....
ክብሬ ተስፋዬነሽ እናቴ እልሻለሁ
ስምሽን ስጠራ ከጭንቀቴ አርፋለሁ/2/
ውዷ ስጦታዬ ድንግል ሆይ ነይልኝ
ባዶነቴን አይተሽ ጉድለቴን ሙይልኝ/2/
ሰዓሊለነ ማርያም .....
በእንተ ፍቅረ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ኬንያ
እስእለኪ ማርያም በሀሌሉያ
ታዘና ስምኢ ወብካያ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ
ሰዓሊለነ ማርያም.....

አምላከ ዳዊት(ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ)

አምላከ ዳዊት ሆይ ማረኝ
አምላከ ዳዊት ሆይ ይቅር በለኝ
አምላከ ዳዊት ሆይ ማረኝ ራራልኝ
ባለእውቀቴ ዘመን የበደልኩህን ኦ አምላኬ ሆይ
በልጅነት እድሜ ያሳዘንኩህን ኦ ጌታዬ ሆይ
የቀድሞ በደሌን አታስብብኝ ኦ አምላኬ ሆይ
እንደቸርነትህ ምህረት አርግልኝ ኦ ጌታዬ ሆይ
አዝ...
በጠላቴ ተንኮል በስጋዬ ምኞት ኦ አምላኬ ሆይ
በሀጥያት ሰጥሜአለሁ ደርሻለሁ ልሞት ኦ ጌታዬ ሆይ
እውቀቴ አስጨነቀኝ ሀብቴም ሰላም ነሳኝ ኦ አምላኬ ሆይ
ነፍሴ ተጨነቀች አጣሁ የሚያፅናናኝ ኦ ጌታዬ ሆይ
አዝ...
ከባህር አሸዋ ሀጥያቴ የበዛ ነው ኦ አምላኬ ሆይ
አምላኬ ፊትህን እንዴት ብዬ አያለሁ ኦ ጌታዬ ሆይ
የቀናውን መንገድ ትቼው ትዕዛዝህን ኦ አምላኬ ሆይ
አነሳስቻለሁ ቁጣ መዓትህን ኦ ጌታዬ ሆይ
አዝ...
ሀጥያቴን አምናለሁ ፍፁም በድያለሁ ኦ አምላኬ ሆይ
ይቅርታህን ሽቼ ፊትህ ወድቄአለሁ ኦ ጌታዬ ሆይ
አሳልፈህ አትስጠኝ ለክፉ ታጥያቴ ኦ አምላኬ ሆይ
ከበቀልህ ልትረፍ ማረኝ መድኃኒቴ ኦ ጌታዬ ሆይ
አዝ...
ከኔ ክፋት ይልቅ የበዛ ፍቅርህን ኦ አምላኬ ሆይ
ከቁጣ የራቅህ ቸር ይቅር ባይ ነህ ኦ ጌታዬ ሆይ
ፍጻሜ የሌለው ታላቅ ክብር ያለህ ኦ አምላኬ ሆይ
ገናና እግዚአብሔር አንተ ብቻ ነህ ኦ ጌታዬ ሆይ
አዝ...

ከመንፈስህ (ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ)

ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ
ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ
ወደ ሰማይ ብሄድ አንተ በዚያ ነህ
ወደ ሲኦል ብወርድ አንተ በዚያ አለህ

*ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ
ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ

እንደ ንስር ብበር በየብስ በባህር
ከእጅህ አላመልጥም በጥልቁም ብኖር
ጨለማ ባንተ ዘንድ አይጨልምምና
ሌሊትም እንደቀን ታበራለችና
*ከመንፈስህ...
አንተ መርምረኸኝ አይተኸኛል እኔን
ሁሉን ታውቀዋለህ ሀሳቤን መንገዴን
እጅህ እንደምትመራኝ አሁን አውቄአለሁ
ከአንተ ከህይወቴ ወዴት እሄዳለሁ
*ከመንፈስህ...
የፍቅር ባለቤት የሰላም ንጉሥ ነህ
ማዕበሉም ንፋሱም ሁሉ የሚገዛልህ
የዘላለም ህይወት ክብር የሚገኝብህ
መንገድም እውነትም ህይወትም አንተ ነህ
*ከመንፈስህ...

ዋ እኔን (ዘማሪ ሲሳይ ደምሴ)

ዋ እኔን/7/ ዋ እኔን እኔን
እኔን/3/ ዋ እኔን
በዓለም ፍቅር ታውሬ በክፉ ሃሳብ ታልፌ
ድርሻዬን ይዤ ተጓዝኩኝ ከአንተ ከአባቴ ከብልፌ
የሰጠኸኝን ሀብት ሁሉ በዓለም በትኜው ያለአግባብ
ሰላሜን አጣሁ ተጨነኩ አገኘኝ የጸናው ረሃብ
መግቢያው መድረሻው ጠፋብኝ ተገፋሁ ስቃዬ በዛ
ከሞላው ቤትህ ወጠቼ አጣሁኝ መጠጊያ ታዛ
አዝ...
እንጀራ የሚተርፋቸው ባሪያዎች በቤትህ ሞልተው
የምቀምሰውን አጥቼ የእሪያ ምግብ ተመኘሁ
አባት ሆይ አልኩኝ በእንባ የጸጸት እንባ ሲፈጀኝ
ከፍቅርህ እቅፍ ወጥቼ የቀን ጨለማ ሲውጠኝ
ልጅህ ልባል ባይገባኝ መመለስ ፈለኩ ከቤትህ
ጉዞ ጀመርኩኝ ወዳንተ በጸጸት ልቆም በፊትህ
አዝ...
ወደ ልቤ ተመልሼ በጸጸት ስጓዝ ብታየኝ
አባት ሆይ አንተ ሩህሩህ ነህ በፍቅርህ አቅፈህም ሳምከኝ
በሰማይና በፊትህ ብበድልህም ልጅህ
ፈጽማ አልተዘጋችም ክፍት ናት ለኔ ቤትህ
ካንተ ፊት በመኮብለሌ ጎድቶኝ ብታየኝ ሀዘኔ
አዲሱን ልብስ አልብሱት አልክ እንዲሸፈን እርቃኔ
ለጣቱም ቀለበት አድርጉ አልክ የቀድሞ ክብሬን እንዳገኝ
ለእግሩም ጫማ ስጡት አልክ ጋሬጣው እንዳያውከኝ
አዝ...

በኔ ጸጸት ሐዘን እንባ የእኔ ከጥፋት መመለስ
የሰባው ሙክት ታረደ ቤትህ ተሞላ በደስ ደስ
ክፉ ፀባዬን ታግሰህ ሀጥያቴን ሳትቆጥርብኝ
ሰው እንደናቀኝ ሳትንቀኝ እንደወጣህ ቅር ሳትለኝ
ዳግም ህይወትን አገኘሁ ሞቼ የነበርኩት ልጅህ
አባት ሆይ በኔ መመለስ ፍስሐ ሆነ ቤትህ
አዝ...

በፈቃዳችን አምጸን ከቤቱ ብንኮበልልም
አምላካችን ደግ አባት ነው ያለፈን በደል አይቆጥርም
በንስሐ ተመልሰን ቢሰበር በዕውነት ልባችን
በፍቅር እጆቹን ዘርግቶ ይቀበለናል ጌታችን
ከባለፀጋ አባትህ ቤት እያለ የህይወት እንጀራ
ስማኝ ወንድሜ ተመለስ አትብላ ከእሪያ ጋራ
በመመለስህ ቢያፌዙ አይግባህ በዚህ ቅሬታ
ያንተ መመለስ በሰማይ ይሆናል ታላቅ ደስታ
አዝ...

አባትህ እግዚአብሄር ቤቱ ቤተክርስቲያን ናት
ሀብትህ እምነት ሥርዓቷ እሪያው ምግብ ነው ጎጥያት
ወዳጆች ቅዱሳን ናቸው ባንተ መምጣት ደስ ያላቸው
አዲሱ ልብስህ ንስሐ አዲሱ ጫማ ወንጌል ነው
አዝ...

ዘማሪ ዲ.ታደለ

ኧረ ስማኝ ፈጣሪ (ዲ.ታደለ በገና)

ቅኝት - ሰላምታ
423 224 1542 222
423 115 113 224 542 222

ኧረ ስማኝ አምላኬ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ /2/
አላገኝምና ያለአንተ መሐሪ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ /2/

አድነኝ ጌታዬ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
ሁሉንም ትተህ " "
ይቅር በለኝ አምላክ " "
በደሌን ንቀህ " "
ዘወትር ነውና የማስቀይምህ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ

በደሌን አውቄ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
ወዳንተ ስጠይቅ " "
በሰራሁት ኃጢአት " "
መንፈሴ ሲጨነቅ " "
ይቅር በለኝ እንጂ ምህረትን አታርቅ ኧረ...

እያወቅሁ አጥፍቼ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
እኔም ብበድልህ " "
ከሥጋ ገበያ " "
ውዬ ባስቸግርህ " "
እስኪ አድነኝ አንተ የምህረት አምላክ ነህ ኧረ...

እስኪ ዛሬስ ይብቃኝ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
ልዙር ወደ ነፍሴ " "
መፈጠሬ የግባኝ " "
በአርአያ ሥላሴ " "
ተቀበለኝ አምላክ ልጅምር ውዳሴ ኧረ....

ለሥጋ እያደላሁ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
ብዙ አጠፋሁኝ " "
አውቄ እንዳላወቅሁ " "
ቃልህም ሻርኩኝ " "
አምላክ ይቅር በለኝ አሁን ፀፀተኝ ኧረ .....

እንድታማልደኝ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
ድንግልን ጠይቄ " "
አለቅሣለሁ እንጂ " "
ከፊትህ ወድቄ " "
የትስ እደርሳለሁ ከመንፈስህ ርቄ ኧረ .....

ይቅር በለኝ ብዬ ኧረ ስማኝ ፈጣሪ
ወዳንተ ሣለቅስ " "
የዕንባ ዘለላ " "
በጐንጮቼ ሲፈስ " "
ምህረትን ነው እንጂ " "
በደሌን አታስታውስ " "
ፊትህን ወደእኔ እባክህን መልስ ኧረ ስማኝ...

ኧረ አንቺ ዓለም(ዲ.ታደለ በገና)

ኧረ አንቺ ዓለም (4x)
አታታይኝ ተይ ግድ የለም
ማታለልሽ ከኖ ለምነው
ካንቺ ጋር ላልሆን እስከወዲያኛው
የእኔስ ሐገሬ በሰማይ ነው (2x)
አዝ----

ፍቀድልኝ ግድ የለም
ገብቼ ልኑር በገዳም
ኧረ አስቸገረኝ ይህ ዓለም (2x)
አዝ----

ማይጠቅመኝን ሳጠራቅም
ከማይረባኝ ስሸቀዳደም
በከንቱ ቀረሁ ከዚች ዓለም(2x)
የእለት ጉርሴን ካልነፈግከኝ
የዓመት ልብሴን ከሰጠኸኝ
ከዚህ በላይ ለእኔ ምን አስፈለገኝ (2x)
አዝ----

ዓለምን ላልጨርሳት ተስገብግቤ
አንዱን ነጥቄ አንዱን ደርቤ
ባስበደረስ ከንቱ ንብረት አሰባስቤ
ዳር ላያወጣኝ ከንቱ አስቤ
ይሻለኛል እኖራለሁ ንፁህ ቃልክን ተመግቤ
አዝ----

ከፍርድህ በፊት ሳልሞት ልዳን
ትወቅ ነፍሴ ሕያውነቷን
በስራዋ ትውረስ መንግስትህን
ስስቷን ትታ የዚህች ዓለምን
አዝ----

ነፍሴ አደራ ተጠንቀቂ
ሞትን ያህል አለ ነጣቂ
ከዚያች ሲዖል እንዳትወድቂ
የአምላክሽን ህጉን ጠብቂ

ንስሐ ግቢ ተፀፀቺ አይጠቅምሽም ይህ ዓለም ላንቺ
የሞትን ሞት ኋላ እንዳትሞቺ
የፅድቅን ጉዞ መንገድ ክፈቺ
አዝ----
እድሜ ጥላ ነው ፈጥኖ ያልፋል
ሃብት ንብረቱም ከዚህ ይቀራል
ጽድቁን አስቢ እርሱ ይበልጣል
ከጻድቃን ጎራ ይመድብሻል
አዝ----
ኮብልዬ ነበረ ትእዛዝህን ጥሼ
ለለፈው ጥፋት እኔን ወቅሼን
በንስሐ ዳኛ እራሴ ከስሼ
ተቀበለኝ በይቅርታ መጣሁ ተመልሼ
አዝ----

እግዚአብሔርም (ዲ.ታደለ በገና)

ቅኝት - ሰላምታ
4245 313 15423 312 45
4245 313 15442 222

እግዚአብሔርም አዳም ባጠፋው ጥፋት
በተስፋ ቃል አሰናበተው ያን ዕለት
ለአዳም በገባለት ቃልኪዳን
አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን
ሲፈፀም ያ የተስፋ ቀን ደረሰ
የአዳምም የስቃይ ዘመን ፈረሰ
አዳምንም በሲያል ሲኖር ተቀብሮ
አዳነው ሞቱን በሞቱ ቀይሮ
አምላክም ወደዚህ ዓለም ሲመጣ
ቆየችው እመቤታችን ተመርጣ
የሌለባት መርገመ ፍዳ ከጥንት
ፀነሰችው በመልኣኩ ቃል ብስራት
ፍቅር ስቦት ወደዚህ ዓለም መጣና
ለአዳም ምን ያልሆነለት አለና
ተወለደና ድንግልናዋን ሳይሸር
ለሰው ልጅ ሲል ተመላለሰ በምድር
በዮርዳኖስ በዮሃንስ እጅ ተጠምቆ
በዲያቢሎስ የተፃፈውን ተራቆ
አጠፋለት ያንን ደብዳቤ ደምስሶ
ከባርነት ያኔ አላቀቀው ጨርሶ
በመስቀል ላይ በዕለተ አርብ ተወግቶ
ከሲያል በደሙ አነፃው አውጥቶ
እንዲህ አርጎ ወደ ጥንት ቦታው መለሰው
በምህረቱ ዳግም ገነትን አሳየው
በአባታችን በአዳም ጥፋት በደል
ገብተን ነበር እኛም ሁላችን ሲያል
በስራችን በኃጥያታችን እኛማ
ሆነን ነበር ከመርገም ግዞት ጨለማ
ግን አዳነን የፍቅር አምላክ ነውና
በትህትና እናቅርብለት ምስጋና
ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ

እማዬን አባዬን (ዲ.ታደለ በገና)

ቅኝት -

እማዬን አባዬን ማለቱ ቀረና
አያቴ ቅድመ አያቴ ማለቱ ቀረና
ልጄ ልጄ ሆነ የልቅሶአችን ቃና
ባሳደጉ ፋንታ መጮርን ሲችሉ
ባስተማሩ ፈንታ መደገፍ ሲችሉ
አልቅሶ ቀባሪ እንዴት ይሆናሉ
ደረሰ እያለች እናት ስታይህ
ለወግ መረግ በቃ ብላ ስትገልጽህ
የመቃብር ጉዞ . . .
በልጅ ሊኮራ አባት ሲጠብቅሽ
ወልደሽ ልትስሚለት ለአቅመ ሔዋን በቅተሽ
ጨርሶ ስንብት ምን ይሆን ያሰኘሽ
በልጅ ሊጦሩ ነበር ምኞታቸው
ጧሪ ቀባሪ አጡ ባዶ አደረግናቸው
ፍቅርን ሳንጨርስ ታይተን ጠፍተናቸው
የወላድ መካኖች ሆኗል ዕድላቸው
የሀገር ባላደራ ተተኪው አንተ ነህ
ባባትህ ተተካህ አላማን ሰንቀህ
የዕቃቃ ጨዋታ እባክህ ይቅርብህ
ታቅፋ አሳድጋህ አዝላ በዝርባዋ
አጉርሳ አስተምራ በድሃ ኑሮዋ
ጥቁር መልበስ ሆነ የእናት ውለታዋ
ያለውን ኹኔታ ጠንቅቀን ስናውቀው
ወገን ተነጥሎ ሲኼድ እያየነው
ከቶ እንደምን ይሆን ልቦና ያጣነው
ተምሮ ጨርሶ ሥራ ያዘ ሲባል
ወዳጅ ዘመድ ሲለው ወገኑን ያኮራል
ሀገር ተረክቦ አደራን ይወጣል
አንድ ዓመት ሳይሞላው መሞቱ ይሰፋል
በራስ የሚመጣው በሽታ ይቅርና
ከፍቶ የመጣውን የጣልያንን ጀግና
መመለስ ተችሏል በራሱ ጐዳና
አንተም ወኔ ታጠቅ ጀግንነት ነውና
አምላክ ሳይፈርድብህ አንተው ባንተ ፈርደህ
ያንተን ሕይወት ባንተ እንዴት ታጠፋለህ
ፈጣሪ ያልሸሸህን አንተ ግን ኮበለልህ
አንተው በእጅህ ጭረህ በእሳት ተበላህ
ትሰማኝ እንደሆን ዘዴውን ልንገርህ
መጥፎውን ተውና ከፈጣሪ ታርቀህ
እስከ ወዲያኛው ኑር መልካም ሕይወት ፈጥረህ

ሰቀሉህ (ዲ.ታደለ በገና)

ቅኝት -

ሰቀሉህ ወገሩህ ምንም ሃጥያት ሳይኖርህ
ይስቀሉኝ ይውገሩኝ ሀሰት በቃልህ ላይገኝ
ቀራኒዮ እንዴት ዝም አልሽ ጎለጎታ እንዴት ጨከንሽ
አምላክ ሲሰቀል አስቻለሽ
ተሰቃየህ አምላክ ሆይ ተወጋህ ቸሩ ሆይ
እንደ ተራ ሰው በአደባባይ

አየተመታ በአይሁድ ወገን ጋራውን ወጣ ተራራውን
መስቀሉን ይዞ የጫኑትን
የዓለም ፈጣሪ የሁሉ ጌታ ላደረገልን ሳይል ውለታ
በፈጠረው ነው የተንገላታ
ሰቀሉህ ወገሩህ ምንም ሃጥያት ሳይኖርህ
ምድር ታልቅስ ወዮ ትበል በሰራችው በዛ በደል
ከፊቱ ወድቃ ከዛ መስቀል
ምድር ሆይ ስሚ ጆሮ ሰጥተሽ አትዘናጊ ግፉን ረስተሽ
በደም ያነፃሽ ከበደልሽ ከመስቀሉ ነው መድኃኒትሽ
በሰውነቱ ክፋት ሳይኖረው በቃሉም ሐሰት ጭራሽ ሳይወጣው
ጌታን ሰቀሉት አይሁድ ወንጅለው
ሰቀሉህ ወገሩህ ምንም ሃጥያት ሳይኖርህ
ይስቀሉኝ ይውገሩኝ ሀሰት በቃልህ ላይገኝ

አርባ ሌሊት መዓልት (ዲ.ታደለ በገና)

ቅኝት -

አርባ ሌሊት መዓልት ሳይቀመጥ ቆሞ
ጾምን አስተማረ በፈቃዱ ጾሞ
ስርዓትንም ሰጠ እራሱ ፈፅሞ
ይመስገን ከሁሉ አስቀድሞ
አምነዋለው የሚል የሚወድ ጌታውን
ይፁም የጾመውን ጾሞ ያሳየውን
ለሕጉ ይገዛ ከፍቶ ልቦናውን
በቃሉ ይከተል አምላኩን
እምነት ያለው ቢኖር ሥራ የሌለው
እንደማይድን ይወቅ ተስፋ እንደሌለው
ክብር አይሰጠውም ዘላለማዊው
በጸጋ አምላኩን ሊያየው
ቆሞ የጸለየው ታጢኣት ሳይኖርበት
ሥርዓትን ሊሰጥ ነው ለፈጠረው ፍጥረት
ጾሞና ጸልዮ መንግሥቱን . . .
በበረሀው ገብቶ በቆሮንቶስ ገዳም
40ሌሊት መዓልት ደከመኝ አላለም
ከቆመበት እግሩ ጭራሽ አልታጠፈም
ሲያዝን ነው በንፅህና እንድንጾም
በንጽህና ሆኖ ጾሞ የጸለየው
እርሱ ነው አምላከን በነፍስ ዐይኑ ያየው
በሥራው ለመዳን አምኖ ያልዘገየ
ተስፋውን ከፍቅሩ ያልለየ
ለሥጋችን እንድትሆን ምድርን ባረካት
ምግበ ነፍስ ሠጠ ጾምንና ጸሎት
ፍቅርና ትህትና እንዲሁም ስግደት
ሊሆነን ሰማያዊ ሀብት

ድንግል (ዲ.ታደለ በገና)

ድንግል እለምንሻለሁ በውዳሴሽ ዜማ
ድንግል ሰላም ለኪ ስልሽ ድምፄ እየተሰማ
የፈጣሪ እናት ሆና እያለች
ሄደች በበረሃው ውሃን ተጠማች
ወይ ልጄን እያለች እግሯ ሳይሰለች
አምላክን ታቅፈሽ ስትወርጂ በረሃ
ምንም እንደሌለው እንደ ምስኪን ደሃ
አንቺን ያለ እናት እንዴት ይጥማሽ ውሃ
አዝ.....
ፈጣሪ በእውነት ከሁሉም መርጦሻል
ፍፁም ሰው ለመሆን በማሕፀንሽ አድሯል
ከድንግልና ጋር እናቱ ሆነሻል
በነብያት ትንቢት የተነገረልሽ
እርይተ ልቦና ድንግል አንቺ እኮ ነሽ
እንኳን በሰው ፍጡር በውሻም ያልጨከንሽ
አዝ.....
ስምሽን እጠራለሁ እያልኩ ድንግል ማርያም
እመቤቴ ካላልኩ ውስጤ አይታደስም
ስምሽን ለጠራ እመቤቴ ብሎ
በልጅሽ ቃል ኪዳን ትደርሺያለሽ ቶሎ
አዝ.....
ከነፍስሽ ነፍስ ነስቶ ከስጋሽ ስጋን
እናቱ አደረገሽ ሰውን ለማዳን
በዚህ ገለፀልን ታላቅ ክብርሽን
ይሄ ነው ያሰጠሽ ማማለድ አንቺን
አዝ.....
ከብዙታን መርጦ አማላክ የሰጠን
የፃድቃን ክብራቸው እመብዙታን
ለእኛ ግን አንቺ ነሽ አማላጃችን
የንፁሃን አክሊል የሃጥአን መመኪያ
የፈጣሪሽ እናት ሆነሻል ማደሪያ
አዝ.....
ባዶ አርባዳ ይዤ ስምሽን ስጠራ
ይሔ መልካም ስምሽ ሆኖኛል እንጀራ
በአንቺ አልፈዋለሁ ያን ሁሉ መከራ
እመሰክራለሁ አማላጅነትሽን
በስምሽ አድጌ እንዴት ልርሳሽ አንቺን
ጎፈዳዬ ሞልቶ ያበላኝ ስምሽን
ሁሌ እጠራዋለሁ አይደክመውም አፌን
አዝ.....
ውሻው ሲያባርረኝ ያን ሁሉ ስደክም
ድንግል ካንቺ ሌላ ስንቅ አልነበረኝም
በልቼ አድር ነበር እያልኩ ስለ ማርያም
አይለየኝ ድንግል በረከትሽ ዛሬም
ዛሬም ደካሞቹ በስምሽ ነው ያሉ
ስለ ድንግል ማርያም አትርሱን እያሉ
የእለት ጉርሳቸውን በአንቺ ይበላሉ
አዝ.....
አለብኝ ውለታ ምከፍለው ለስምሽ
ንፁህ አገልግሎት ለእናትነትሽ
ወገቤን ታጥቄ እናቴ ልበልሽ አዝ.....

እንደ ክቡር ዳዊት(ዲ.ታደለ በገና)

ቅኝት -

እንደ ክቡር ዳዊት እኔም በበገና
ስማኝ ስማኝ እያልኩ አለቃሳለሁና
እባክህ ተቀበል የውስጤን ልመና (2x)
ዛሬን በምድር ላይ ነገን በሰማይ
እባክህ አምላኬ ስቃይ እንዳላይ
የፀባኦት ጌታ እርዳኝ አዶናይ (2x)
በገናዬ ድምጹን ወደ አንተ ሲያሰማ
ዓይኔም እያነባ ውስጤም እየደማ
ዝማሬዬን ቁጠር ከቅዱሳን ዜማ ከአባቶቼ ዜማ
ሰማይና ምድርን በቃልህ ያቆምክ
ባሕር ውቅያኖሱን በእጅክ የሰፈርክ
በእምነቴ አፅናኝ ልቦናን ሰጥተህ ጌታዬ ስልህ
ያላንተ የሆነ ምንም ነገር የለም
በጣም ያስገርማል ሲነጋ ሲጨልም
ወቅቱ ሲፈራረቅ በጋው አልፎ ሲዘንብ
ጥበብህን መርምሮ የደረሰው የለም
በጎልዳማው አፌ እንኪን በእኔ አቅም
ጠበብት ነን የሚሉ ተናግረው አልቻሉም መርምረው አልቻሉም
የበላይ የሌለህ የንጉሶች ንጉስ
እኛ ብንበድልህ ብንወድቅም በበለስ
ቀድመህ ያዘዝከንን ተዕዛዝህንም ብንጥስ
አንተ ነህ ያዳንከን ስጋችንን በመልበስ(2x)
ዘምሬ አወድሼ ከንቱም እንዳልሆን
ከመንፈስህ ርቄ እንዳልፈተን
እባክህ አድለኝ ንፁህ ህሊናን ንፁን ልቦናን
መቼም ልልህም አትፈትነኝ
ብቻ የዛን ግዜ ፀሎቴን ስማኝ
የለበስኩት ስጋ እንዳያስጥለኝ(2x)
ጨካኝ ሆነህ ሳይሆን እንዲህ የምልህ
አንተም አዘኸኛል አንኪኪ ብለህ
ከበርህ ቆሚያለሁ ፈውሰኝ ልልህ
አንደ ፃድቁ ኢዮብ ይዩኝ አይኖችህ(2x)
ብቸኝነት ከብዶኝ ውስጤ ተርበትብቷል
ጠላት በውድቀቴ ይሳለቅብኛል
የሚያፅናናኝ የለም ሐዘኑ ከብዶኛል
ከአንተ በቀር ለእኔ ማን ይደርስልኛል(2x)
ፀንቷል በሽታዬ ከአልጋ ወድቂያለሁ
ሰው እንደማይረዳኝ አረጋግጫለሁ
እንደ ራሔል እምባ ወዳንተ ልኪያለሁ(2x)
ልቦናዬ ከአንተ ብዙ ነገር ይሻል
የላንተ የሚሆን ምን ነገር ይገኛል
የእኔ መሻት በአንተ ሁሉም ይፈፀማል አዎ ይፈፀማል
እኔማ በራሴ ብዙ አስቤ ነበር
ከቁመቴ ስንዝር አንዳችም ላልጨምር
ይበቃኛል ገናስ በራሴ መፎከር
ስያዝ ተረዳሁኝ ጌታ ያንተን ነገር አምላክ የአንተን ነገር
ይበቃኛል ገናስ በራሴ መፎከር
ስያዝ ተረዳሁኝ ጌታ ያንተን ነገር
አምላክ ያንተን ነገር

አርባ ሌሊት መዓልት(ዲ.ታደለ በገና)

አርባ ሌሊት መዓልት ሳይቀመጥ ቆሞ
ፆምን አስተማረ በፈቃዱ ፆሞ
ስርዓትንም ሰጠ ራሱ ፈፅሞ
ይመስገን ከሁሉ አስቀድሞ
አምነዋለሁ የሚል የሚወድ ጌታውን
ይጾም የጾመውን ጾሞ ያሳየውን
ለሕጉ ይገዛ ከፍቶ ልቦናውን
በቃሉ ይከተል አምላኩን
እምነት ያለው ቢኖር ስራ የሌለው
እንደማይድን ሕይወት ተስፋ እንደሌለው
ክብር አይሰጠውም ዘለዓለማዊዉ
በፀጋ አምላኩን ሊያየው
ቆሞ የጸለየው ሃጥያት ሳይኖርበት
ስርዓትን ሊሰጥ ነው ለፈጠረው ፍጥረት
ጾሞ እና ፀልዮ መንግስቱን እንዲወርሳት
ዘለዓለም እንዲኖር በሕይወት
በበረሃው ገብቶ በቆሮንጦስ ገዳም
አርባ ሌሊት መዓልት ደከመኝ አላለም
ከቆመበት እግሩ ጭራሽ ያልታጠፈው
ሲያዘን ነው በንፅህና እንድንፆም
በንፅህና ሆኖ ፆሞ የፀለየ
እርሱ ነው አምላኩን በነፍስ ዓይኑ ያየ
በስራው ለመዳን አምኖ ያልዘገየ
ተስፋውን ከፍቅሩ ያልለየ
ለስጋችን እንድትሆን ምድርን ባረካት
ምግበ ነፍስም ሰጠ ጾምና ፀሎት
ፍቅርና ትህትና እንዲሁም ስግደት
ሊሆነን ሰማያዊ ሃብት
ፀባ አጋንንቱን ድምፀ አራዊቱን
መከራን ታግሶ ረሃብ እና ጽሙን
በለበሰው ስጋ ፈጣሪ ጾመልን
በጾሙም ድል ነሳው ሰይጣንን
ጥንተ ጠላታችን ዲያቢሎስ ሚያፍረው
በስግደት በፀሎት በጾም ብቻ ነው
ኢየሱስ በገዳም እንዳሸነፈው
እንጹም እጅ እንዳንሰጠው
በገዳም ውስጥ ገብቶ ቆሞ ሲጸልይ
ዲያቢሎስ ፈተነው በፍቅረ ነዋይ
ዳቦ አድርጎ አሳየው በምትሃት ድንጋይ
በተንኮል ማንነቱን እንዲያይ
ከድንግል ተወልዶ አለምን ያዳነው
በስስት በትዕቢት ስንቱን ተፈተነው
እናስታውስ ይህንን ለኛ እንደሆነ
ምስጋና ለእርሱ እያቀረብን
ዲያቢሎስ በገነት በእባብ ተመስሎ
አዳምን ቢጥለው በበለስ አታሎ
አምላክ ሰው ሆነና ለአዳም ልጆች ብሎ
ድል ነሳው ደካማ ሰው መስሎ
አርባ ሌሊት መዓልት ሳይቀመጥ ቆሞ
ፆምን አስተማረ በፈቃዱ ፆሞ
ስርዓትንም ሰጠ ራሱ ፈፅሞ
ይመስገን ከሁሉ አስቀድሞ

በጌቴ ሴማኒ(ዲ.ታደለ በገና)

በጌቴ ሴማኔ በአትክልቱ ቦታ(2x)
ለእኛ ሲል ጌታችን በዓለም ተንገላታ
አዳም እና ሔዋን ባጠፉት ጥፋት(2x)
እኛም ነበረብን የዘላለም ሞት
መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ(2x)
ይገርፉት ነበረ ሁሉም በየተራ
ድንግል አልቻለችም እምባዋን ልትገታ(2x)
እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ
በአምላክነቱ ሳይፈርድባቸው(2x)
እንዲህ ሲል ፀለየ አባት ሆይ ማራቸው
በረቂቅ ስልጣኑ ሁሉን የፈጠረ
በረቂቅ ጥበቡ ሁሉን የፈጠረ
በሰው እጅ ተገርፎ ሞቶ ተቀበረ
ፍቅሩን የገለፀው ተወልዶ በስጋ(2x)
ኢየሱስ ጌታ ነው አልፋና ኦሜጋ
በመስቀል ተሰቅሎ እንዲያ እየቃተተ(2x)
ዓለምን ለማዳን የማይሞተው ሞተ
ከሞት ሊታደገን በመጣልን ፈጥኖ(2x)
መስቀል አሸከሙት ውለታው ይህ ሆኖ
መከራውን ሳስብ ሳስታውስ ቀኑን(2x)
ይቆስላል ይደማል ልቤ በሐዘን
ሞች ለራሱ ነበር ይህ ሁሉ መከራ (2x)
መስቀል ተሸክሞ የወጣው ተራራ
ሲያጎርሱት ሚናከስ ሰው ክፉ ነውና
እውሩን ቢያበራ ጎባጣን ቢያቀና
ጌታዬን ሰቀሉን አይሁድ ጨከኑና
ምነው አያሳዝን የአይሁድ ክፋት(2x)
የዝናቡን ጌታ ውሃ ሲነፍጉት
በተንኮል በታጢያት ቀሩ እንደሰከሩ (2x)
ሙታን ከመቃብር ተነስተው ሲያስተምሩ
እናታችን ሔዋን ወዮ በይ አልቅሺ
ያንቺን ሕመም ታሞ ከሞት ሊያድንሽ
የህያዋን ጌታ ተሰቀለልሽ
አዬ ጉድ አዬ ጉድ አለም የኋላሽ (2x)
መድኃኒት ክርስቶስ በግፍ ሞተብሽ
በመስቀል ተሰቅሎ ስጋውን ሲቆርስ
በችንካር ተወግቶ ደሙንም ሲያፈስ
ዋለች በመከራ ድንግል ስታለቅስ
ሰውነትሽ ራደ ሐዘን ከበበሽ
ስቃይ መከራውም ዳግም ፀናብሽ
ተሰቅሎ ስታይው አንድ አምላክ ልጅሽ
ቢፈስም እንባዬ ሆኖ መንታ መንታ
ሞች ዋጋ ይሆናል ለአንዲቱ ጠብታ
ላለቀሽው ለቅሶ ድንግል የዛን ለታ
ባለቀሽው ለቅሶ በልጅሽ ህመም (2x)
ከሃጢያት ነፃሁኝ ዳንኩኝ ከገሃነም

ሰው አፉ አላርፍ ብሎ(ዲ.ታደለ በገና)

ሰው አፉ አላርፍ ብሎ ሐሜት ሲቀኝብኝ
የሐሜቱን ቅኔ አንተው ፈታህልኝ
በሀሴቱ ጉዞ በጽድቅህ መራኸኝ (2x)
ቃልህ የማይሻር ዘለዓለማዊ ነህ
አልፋና ኦሜጋ በፀባኦት ያለህ
አይራቁብኝ ከእኔ ምህረትህ እና ፍቅርህ (2x)
እንደ ሰዎች ሳይሆን እንደ አንተ ሆነና
አምላኬ ስልህ ሰምተከኛልና
በከንቱ አልቀረሁም ምኞቴ ተቃና(2x)
አልቀረሁም እና ያን ሁሉ ደክሜ
በምህረትህ ብዛት ተለውጧል ስሜ
ስምህን ላወድስ በአደባባይ ቆሜ(2x)
የፍጡራን ጌታ ተመስገን አምላኬ
የምፈልገውን ሰጠኸኝ በልኬ
በእጅክ ተፃፈልኝ አዲሱ ታሪኬ
እሰግዳለሁ ላንተ ሁሌም ተንበርክኬ(2x)
ሲሳለቁ በእኔ ባዶነት ሲሰማኝ
የሐዘን ሆድ ጭንቀት ማዕበል ሲውጠኝ
አይዞክ ልጄ ብለክ አንተ ነህ ያዳንከኝ (2x)
ሰዎች ልብሴን ሲያዩ አንተ ልቤን አየህ
እንደ ልብሴ ሳይሆን እንደ ልቤ ፈርደህ
ለዚህ አበቃኸኝ በበጎ ፈቃድህ
ላንኪት ክፍት ነው አይዘጋም በርህ(2x)
አንተን ለጠየቀ መልስህ አይዘገይም
ቀናትን ሳይጨርስ ደርሶልኛል ለእኔ
ተመስገን እላለሁ አንተን ለዘለዓለም
ለእኔ እንደ አንተ የለም ጌታ መድኃኒዓለም(2x)
ተመስገን ነው እንጂ ምን እመልሳለሁ
ስተኛም ስነሳም ስምህን እጠራለሁ
የስቃዩን ዘመን በአንተ አልፌዋለሁ(2x)
ብዙ አርገኅልኛል ለነፍስ ለስጋዬ
ውለታህን ልክፈል በፍቅር አገልግዬ
እንደ መላእክቱ ቅዱስ ቅዱስ ብዬ
እጆቹን ዘርግቶ አንተን ለጠየቀ
ንፁህ ልብን ይዞ ፊትህ ለወደቀ
ከአፀደ መቅደስህ ከቤትህ ላልራቀ
የፍቅር ስጦታህ መቼ ይሆን ያለቀ መቼም አላለቀ(2x)

አለ ወይ(ዘማሪ ታደለ)

አለ ወይ ለጌታ ሲሳይ (2x)
በምድረ-በዳው በበረሃው ላይ(2x)
ከሰማይ አውርዶ መናን የመገበ
እህል እና ውሃ ከቶ ሞች አሰበ
ሰውን ነበር እንጂ እሱ የተራበ(2x)
አዝ----
በስስታምነት በላው ሲል ለሞተው
አምላክነት ሽቶ አምላኩን ለካደው
እራሱን ሰውቶ ደሙን ካሳ ሰጠው(2x)
አዝ----

እሱን ዋጋ አድርጎ ሕይወቴን ለገዛ
ለዓለም መድኃኒት ለሆነላት ቤዛ
ረሃቡ ተጠራ እንጀራ እንደዋዛ
አዝ----
የላጪን ልጅ ቅማል እንዳይበላት ሲያውቁ
የአባይን ልጅ ውሃ እንዳይጠማት ሲያውቁ
የእንጀራን ባለቤት ረሃቡን ጠየቁ (2x)
አዝ----
መቃብር ቆፍሮ ሞትን ሳይቀብረው
እንዲያ ደም አልቅሶ ሙትን ሳይቀብረው
እህል መች ይቀምሳል ፈፅሞ ያ ሰው(2x)
አዝ----
እዚያ ቀራኒዮ መና እየዘነበ
እዚያ ቀራኒዮ ፍቅር እየዘነበ
ኧረ ምነው ጉዱ ዛሬም ሰው ተራበ(2x)
አዝ----
ከሰማይ አውርዶ መናን የመገበ
እህል እና ውሃ ከቶ መች አሰበ
ሰውን ነበር እንጂ እሱ የተራበ
እኔን ነበር እንጂ እሱ የተራበ
እሷን ነበር እንጂ እሱ የተራበ
አንተን ነበር እንጂ እሱ የተራበ
አዝ----

<u>አንተ አልቅሰህ(ዘማሪ ታደለ)</u>

አንተ አልቅሰህ እኛ ሳቅን
በሞትም ሕይወት አገኘን
ታዲያ ይህን ውለታ መች ከፈልን
ለፍቅርህ መልሱ ሃጥያት ሆነ (2x)
እርቃኑን ሆኖ የሚያለብስ
ደሙን ለዋጋ የሚለግስ
እርሱ ተዋርዶ የሚያነግስ
እንደ አንተ ያለ የታል ንጉስ(2x)
የጠዋት ጮራ የምሽት ጀምበር
የሔዋን ሞገስ የአዳም ክብር
የፍቅር አባት የሠላም መምህር
አንተ ነህ ጌታ በሠማይ በምድር
አንተ ነህ አምላክ በሠማይ በምድር
ገዳያችንን የገደለ የሞት መድኃኒት በእጁ ያለ
ሰውን ለማክበር የተሰቀለ
በፍቅሩ ፀዳል ዛሬም አለን
በፍቅሩ ፀዳል ሁሌም አለን
ፍቅር ነው መጥሪያው ለልጆቹ
በድምፅ ያውቁታል ወዳጆቹ
ሁሉም ተዘርቷል በእጆቹ
ጽድቅ ነው ምዕራፍ ለእግሮቹ(2x)
ጥለነው ስንሄድ የፈለገን
እኛ ሳንመርጠው የመረጠን
ቅርንጫፍ ልንሆን የወይን ግንድ ሆነ
ፍሬ ማፍራት ነው ሚጠበቅብን(2x)
ከጠላት በረት ታስረን በከንቱ
የእስራት ፍትሃት ሆኖን ሕይወቱ
ከራሱ ተክሎን በመስቀል ሞቱ
ምነው ተሳነን ፍሬ ማፍራቱ(2x)
ሀገር እያለን የዘለዓለም
ምነው ጨንቀቱ ለቀሪው ዓለም
አሁን ነው ጊዜው ሞትን ለመቅደም
ከሞት በኋላ ንስሃ የለም
ከሞት በኋላ ሩጫ የለም(2x)
በስጋ ሕይወት ስንኖር በምድር
ነፍሳችን ትራቅ ከከንቱ ነገር
ሰጥቶናል እና የልጅነት ክብር
ምርጫችን ይሁን ከርሱ ጋር መኖር(2x)

<u>ችግር በርትቶ(ዘማሪ ታደለ)</u>

ችግር በርትቶ ሲያሰቃየን
ለምን ተውከን ፈጣሪያችን እስኪ አስበን
የኑሮ ትርጉም አልገባን ብሎ
አስቸግሮናል ተመሰቃቅሎ እርዳን በቶሎ
እንዴት እንጠይቅ ከሰው እርዳታ
አንተ እያለህ የኛ ጌታ አንንገላታ
ያኔ ወላጅ እንደሌላቸው አልተዋቸሁም ብለኸን ነበር
እንዴት አየኸን ስንቸገር ስናማርር
በርግጥ አድርገኸናል የእምነት ሐብታም
ይሄን እናውቃለን እንደኛ የለም በመላው ዓለም
ነገር ግን ነፍስ ያለ ስጋ አትቆምም እና
ባርከህ አድለን የእጅህን መና እንኑር በጤና
አባት ሆይ ስንል ልጆቼ በለን
ሌላ ማን አለ እኛን ሚሰማን አቤት የሚለን
ለተወለደው ማደጊያ ጠፍቶ
እናት አዝናለች ሆዷ ተከፍቶ ችግር በርትቶ
ልጇ እየጮኸ ጎድሎባት ቤቷ
እንዴት ትቻለው በእናት አንጀቷ አሁን ነው ሞቷ
ችግር በርትቶ ሲያሰቃየን
ለምን ተውከን ፈጣሪያችን እስኪ አስበን
የኑሮው ትርጉም አልገባን ብሎ
አስቸግሮናል ተመሰቃቅሎ እርዳን በቶሎ
እንዴት እንጠይቅ ከሰው እርዳታ
አንተ እያለህ የኛ ጌታ አንንገላታ
ያኔ ወላጅ እንደሌላቸው አልተዋቸሁም ብለኸን ነበር
እንዴት አየኸን ስንቸገር ስናማርር
በርግጥ አድርገኸናል የእምነት ሐብታም
ይሄን እናውቃለን እንደኛ የለም በመላው ዓለም
ነገር ግን ነፍስ ያለ ስጋ አትቆምም እና
ባርከህ አድለን የእጅህን መና እንኑር በጤና
አባት ሆይ ስንል ልጆቼ በለን
ሌላ ማን አለ እኛን ሚሰማን አቤት የሚለን
ለተወለደው ማደጊያ ጠፍቶ
እናት አዝናለች ሆዷ ተከፍቶ ችግር በርትቶ
ልጇ እየጮኸ ጎድሎባት ቤቷ
እንዴት ትቻለው በእናት አንጀቷ አሁን ነው ሞቷ

ድሃ ነሽ ሐገሬ(ዘማሪ ታደለ)

ድሃ ነሽ ሐገሬ ኢትዮጵያ ይሄንን አውቃለሁ ሐገሬ
ስምሽ እንዲቀየር እማማ ሁሌም እመኛለሁ ሐገሬ
የዕድገትሽን ብርሃን ሐገሬ ማየት ናፍቄያለሁ እማማ
ድህነት ባይለቅሽ እናቴ ችግር ቢዋጋሽም ኢትዮጵያ
በታሪካዊነት እናቴ ሌሎቹ አይቀድሙሽም ሐገሬ
ቅርስሽ ምስክር ነው እማማ ላሊበላ አክሱም ሐገሬ
ቅርስሽ ምስክር ነው ሐገሬ የጎንደር የአክሱም እናቴ
ሕዝቦችሽም ኩሩ እናቴ እንከን የሌላቸው ሐገሬ
ውስጣቸው በእምነት እናቴ የተሞሉ ናቸው ሐገሬ
እማማዬ ልቀሽ ሐገሬ ብርታትን ስጪቸው እማማ
ከሐገር የበለጠ ሐገሬ ለሰው የለምና እናቴ
ያበልፅግሽ ብዬ ሐገሬ አልተውም ልመና ኢትዮጵያ
ያሰማኝ አምላኬ ሐገሬ የዕድገትሽን ዜና እማማ
ጨርሶ እንዲጠፋ ሐገሬ የድህነት ስምሽ እማማ
ሃብት ዕውቀት ጉልበቴን ሐገሬ በውል ልለግስሽ ኢትዮጵያ
ከጥንትም ያንቺው ነኝ ሐገሬ ዛሬም ቃል ልግባልሽ ሐገሬ
ሰባራው አካልሽ ኢትዮጵያ ጎንሽ ተጠግኖ ሐገሬ
ብልፅግናሽ ጎልቶ እማማ ሠላም ምግብሽ ሆኖ ሐገሬ
ውስጥሽ አገግሞ እናቴ የርሃብ ሆድሽ ድኖ ኢትዮጵያ
ያሳየኝ አምላኬ ሐገሬ ጊዜ ሳይፈጅ ፈጥኖ እማማ
እንጀራ ሆኖብኝ እናቴ ብሄድም እርቄ ሐገሬ
የእትብቴ መኖሪያ ኢትዮጵያ መሆንሽን አውቄ ሐገሬ
አስታውስሻለሁ እናቴ ባህልሽን ናፍቄ ሐገሬ
አስታውስሻለሁ እማማ እምነትሽን ናፍቄ ሐገሬ
ባንድ አልገኝ ብለው ኢትዮጵያ እንጀራና ኑሮ ኢትዮጵያ
ስደተኛው ልጅሽ ኢትዮጲያ ቢሄድም አምሮ ሐገሬ
ስምሽ አይጠፋውም ሐገሬ ይፈቅድሻል ዞሮ ሐገሬ

ኧረ ምነው(ዘማሪ ታደለ)

ኧረ ምነው (2x) ሆዴን ሆድ የባሰው
ውስጤ ተጨናንቆ ሠላሜን አሳጣኝ(2x)
የሠላም ባለቤት እስቲ ሠላም ስጠኝ (2x)
ሆዴ ሲጨናነቅ ውስጤ ሠላም ሲያጣ(2x)
ካንተ በቀር ለእኔ ሌላ ማን ሊመጣ
ካንተ በቀር ጌታ ሌላ ማን ሊመጣ
ካንተ በቀር አባት ለእኔ ማን ሊመጣ
ኧረ ምነው (2x) ሆዴን ሆድ የባሰው
ሁሌ እረፍት የለኝም እንቅልፍ ከዓይኔ ርቋል
የማስበው ሁሉ ከእኔነቴ ወጥቷል
አምላኬ ደግፈኝ መኖር ተስኖኛል
ጌታዬ ደግፈኝ መኖር ተስኖኛል
አባቴ ደግፈኝ መኖር ተስኖኛል
ኧረ ምነው (2x) ሆዴን ሆድ የባሰው
ሠላም እያጣሁኝ ውስጤ ተጨነቀ
ሁከት ከዙሪያዬ እንድም ቀን አልራቀ
በሃሳብ ውቅያኖስ ምናቤ ጠለቀ(2x)
ኧረ ምነው (2x) ሆዴን ሆድ የባሰው
እንዲህ ተጨንቄ ኑሮን እንዴት ልግፋው
ያልተፈታ ቅኔ ሁሉ እንቆቅልሽ ነው
የጭንቀቴን ምስጢር እስኪ አምላኬ ፍታው
የጭንቀቴን ምስጢር እስኪ አባቴ ፍታው
የጭንቀቴን ምስጢር እስኪ ጌታ ፍታው
ኧረ ምነው (2x) ሆዴን ሆድ የባሰው
ምንም አይሳካ ከንቱ ነው መሮጤ
ወጥመዴ ብዙ ነው ሁሉ ሆኗል ዳጤ
እኔስ ተሞላብኝ በከንቱ ሃሳብ ውስጤ(2x)
ኧረ ምነው (2x) ሆዴን ሆድ የባሰው
አንተ እንደሰራኸው ጥንት እንደፈጠርከው(2x)
እባክህ አምላኬ ውስጤን ሠላም ስጠው(2x)
እባክህ አባቴ ውስጤን ሠላም ስጠው(2x)
እባክህ ጌታዬ ውስጤን ሠላም ስጠው(2x)
ኧረ ምነው (2x) ሆዴን ሆድ የባሰው

ሞቴን አየሁት(ዘማሪ ታደለ)

ሞቴን አየሁት በሞቱት
ያኔ አይቼው ወንድሜን በአልጋ ሲወስዱት
እህቴን በአልጋ ሲወስዷት
ጽድቄንም ልየው በጌታዬ
አንተን ልከተል በጊዜዬ
እስኪ አነሳሳኝ አምላኪዬ
እስኪ አነሳሳኝ ፈጣሪዬ
አይ ሞኝነቴ (2x) ሞቴን መርሳቴ
አይ ሰው ከንቱ (2x) ሞቱን መርሳቱ
ሞቴንም ባየው አሻግሬ
አለቀቀኝም መጥፎ ግብሬ
አልተመለስኩም ተመክሬ(2x)
ሞቴንም ባየው አሻግሬ
አለቀቀኝም መጥፎ ግብሬ
አልተመለስኩም ተመክሬ(2x)
ቃሉ ይፈሳል በጆሮዬ
ግን አልያዘውም ልቦናዬ
ልቤን መልሰው ፈጣሪዬ(2x)
አይ ሞኝነቴ (2x) ሞቴን መርሳቴ
ምን ከባድ አለ ከሞት የላቀ
ሁሉን ደፋሪ ንጉስ የናቀ
ታዲያ ለምን ነው ሰው አላወቀ
ኧረ ለምን ነው ሰው አላወቀ
አይ ሰው ከንቱ (2x) ሞቱን መርሳቱ
ከአንተ የሚደበቅ ምንም የለም
ሁሉን ታውቃለህ መድኃኔዓለም
የሰጠኸኝ ልብ ላንተ አልሆነም(2x)
በቤተ-መቅደስህ ሳልቆርብበት
ሁሌ እንደሮጥኩኝ ከጠንቋይ ቤት
ዘመኔ አለቀ ሳላውቅበት(2x)
አይ ሞኝነቴ (2x) ሞቴን መርሳቴ
ያለፈው ዘመን ፀፀተኝ
ከአንተ ለይቶ ያቆየኝ
ባይሆን ለዛሬ ልብ ስጠኝ(2x)
አይ ሞኝነቴ (2x) ሞቴን መርሳቴ

አንደበት አለኝ ማወራበት
ብዙ እላለሁኝ በሰዎች ፊት
ልብ ነው ያጣሁ ምሰራበት (2x)
ምድር መግባቴ እጅ እግሬን ታስሬ
መሞቴ ላይቀር መቀበሬ
ታድያ ለምን ነው ሰነፍኩ ዛሬ
ኧረ ለምን ነው ሰነፍኩ ዛሬ
አይ ሞኝነቴ (2x) ሞቴን መርሳቴ
አይ ሰው ከንቱ (2x) ሞቱን መርሳቱ
ሁሌስ አያለሁ የሞት ቀኔን
በዓይነ-ስጋ መቃብሬን
በዓይነ-ህሊና ገሃነምን
ታድያ ማን ያውጣው ከዓለም ልቤን(2x)
አይ ሞኝነቴ (2x) ሞቴን መርሳቴ
የማንሞት መስሎን ስንንጠራራ
ለነፍስ የሚሆን ምንም ሳንሰራ
ሞት ስራ አይፈታም ፈጀን በተራ(2x)
አይ ሰው ከንቱ (2x) ሞቱን መርሳቱ
ዛሬስ አስጠላኝ ሰው መሆኔ
ምንም ሳልሰራ ሲያልቅ ዘመኔ
እኔ ወደ እሱ ሞት ወደ እኔ
እንጓዛለን እንጃልኝ እኔ(2x)
አይ ሞኝነቴ (2x) ሞቴን መርሳቴ
አይ ሞኝነቷ (2x) ሞቷን መርሳቷ
አይ ሞኝነቱ (2x) ሞቱን መርሳቱ
አይ ሰው ከንቱ (2x) ሞቱን መርሳቱ

ነይ ድንግል(ዘማሪ ታደለ)

ነይ ድንግል ነይ (8x) ነይ እናቴ ነይ
ነይ ድንግሌ ነይ ነይ ነይ
ነይ እናቴ ነይ ድንግል
አንቺ እኮ ነሽ መሰላል
የነፍሴ ስንቅ የጽድቅ ቃል ነይ ድንግል
እንደ ዶኪማስ ስጠራሽ
ለሰርግ ባርኮ ነይ ስልሽ
ቤቴ በረከት አጥቷልና
ልጅሽ ይባርከው እንደ ቃና (2x)
የመስቀሉ ስር ስጦታችን
የፈጣሪ እናት የአምላካችን
ወድቀን ሳለ እኛን ሊያነሳ
ነፍስና ስጋን ከአንቺ ነሳ(2x)
አዝ-----
አንቺን መርጦ ከአዳም ዘር
ከአብ ተላከ ወደ ምድር
ከአንቺ ህፀፅ የለምና
ጌታን ፀነስሽው በንፅሕና በድንግልና
አዝ-----
አልምሻለሁ ጠዋት ማታ
በእቅፍሽ አለ ፈቺው ጌታ
መክፈቻ ይዞ የዳዊትን
አወጣኝ ሰብሮ መቃብሬን የአንቺ ፍሬ
ወደ ሊባኖስ ልቤ አቅንቶ
ነይ ይልሻል እናት ሽቶ
ንጽሕት ፈሳሽ የታተምሽው
በፍቅርሽ ዝናብ እንድታጥቢው(2x)
አዝ-----
ተነሽ ወዳጄ ውበቴ ሆይ
ስቃዬ እንዲወድቅ ከእራሴ ላይ
ትበረቻለሽ ከሠልፈኛ
ታጥቀሻል ጥበብ ማያስተኛ(2x)
ንዒ ገሊላ ብዬሽ ነበር
ርስትሽ ሠላም እንድታድር
አለሽ አስራት ወደ ምስራቅ
ግቢ ኢትዮጲያ እንዲሆን እርቅ እንዲወርድ እርቅ
አዝ-----

ሸክም ከብዶ(ዘማሪ ታደለ)

ሸክም ከብዶ መቆም ሲያቅተን አቅም አጥተን
ፈጣሪያችን ይጠራናል ሊያቀልልን
በንስሃ ወደ ቤቱ ተመልሰን
እናምልከው እርሱ ብቻ ነው ሕይወታችን
በበገና...
በሃጢያት እድፍ የቆሸሸው ስብዕናችን
ይታጠባል እንደገና በአባታችን
ብቻ እንቅረብ ተፀፅተን ለይቅርታ
መሃሪ ነው ፍፁም ፍቅር የኛ ጌታ
ያቺ ሕይወት ጥንት የገዛት በደም ካሳ
ምነው ሄደች ወደ ጠላት ተመልሳ
በበገና...
በአንዱ ሃጢያት ሁላችንም ሞተን ነበር
ሞትን ገድሎ አንዱ አነሳን በፍፁም ፍቅር
ጨለማውን ተሸግረናል በይባቤ
ለዝማሬ ከእንግዲ እንቅረብ ይዘን ከርቤ
በበገና...
ላንመለስ እንደገና ወደ ኋላ
በክርስቶስ ሕይወታችን ሆኗል ሌላ
ከል ብቻ ነው ወደ ጠፋው የሚመለስ
እኛስ ለክብር በአምልኮ እንቀደስ
ለፈጠረን ለሚወደን ለጌታችን
ጠዋት ማታ ምስጋና ይሁን ስጦታችን
ስብሃት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ

የሴቱ አለባበስ(ዘማሪ ታደለ)

የሴቱ አለባበስ በእጅጉ ሲገርመን(2x)
ወንዱ ለወንድ ታጨ ለወንዱ ሚስት ሊሆን
እኛ ስንጫጫህ ሱሪያችን ወስዳችሁ(2x)
የእጃችሁ ነው ብለው አምባሩን ቀሟችሁ
ገና እንገረማለን አፋችንን ይዘን(2x)
ተፈጥሮውን ረስቶ ባላችሁ ሚስት ሲሆን
ይሰማል ጠብቁ ደግሞ ነገ ሌላ(2x)
አረገዝኩኝ ይላል ወንዱ በወንድ ገላ

የዘመኑ ትውልድ ሞኝነት አብዝቷል(2x)
በቅጡ ወንድ ሳይሆን ሴት መሆን ያምረዋል
ድሮ ሰው ሲያብድ ልብስ እየቀደደ(2x)
የዛሬማ ወጣት ከነጨርቁ አበደ
ለብሷል ማለቱ እንኳ ብዙ አያስደፍርም(2x)
ደረቱ ተጋልጦ ይታያል ለሁሉም
ዕብደትን መሰልጠን ብሎ እያደነቀ(2x)
ስንቱ ወርቅ በመዳብ ተለውጦ አለቀ
ምነው አልገባቸው የዕብደቱ መላ(2x)
እያሳሳቀ ነው ውሃም ሰው የሚበላ
በጠራራው ፀሐይ በቀን ጠርተናችሁ
ፀሐይ ወጥቶ እያለ በቀን ጠርተናችሁ
ምነው በጨለማው ከመሸ መጣችሁ
ባይሆን ከጨለማው ከውጭ እንዳትቀሩ(2x)
ከቤቱ እንድትገቡ አንኳኩ በበሩ
ያቺን ሴት አሟታል አካሏን በሙሉ(2x)
ነፍሷን ስለማታውቅ ባልጋ ሄደች አሉ
ምነው ሰዉ ሁሉ ሳይሰማ ያወራል
ምነው ሴቱ ሁሉ ሳይሰማ ያወራል
እውነተኛ ሳይሆን ሁሉ ባሉ ሆኗል
ባሏን ተለይታ ድንገት እራቅ ስትል(2x)
ቀለበቷን ጣለች የሌላት ልትመስል
ቀለበት ደብቀሽ ከምትቸገሪ(2x)
እሱ ይበቃሻል በዛው በአንዱ ኑሪ

ሲገፉኝ(ዘማሪ ታደለ)

ሲገፉገኝ ከእቅፍህ አረፍኩኝ ሲርበኝ በእጅህ አበላኸኝ
ሲጠማኝ አንተ ነህ ያጠጣኸኝ
ለመልካሙ ሁሉ ጌታዬ የሆንከኝ
የዘለዓለም ንጉስ አንተው ነው ያለኸኝ
የዘለዓለም አባት አንተው ነው ያለኸኝ
የደስታዬ ምንጭ ሰላሜ እውን የሆንከው ለሕልሜ
ስምህን ላንሳው ደግሜ ደግሜ
ያላንተ አልኖርኩምና የደቂቃን እድሜ
ተመስገንልኝ አልኩ በፊትህ ላይ ቆሜ
ተመስገን ልበልክ በፊትህ ላይ ቆሜ
የኑሮ ሐገሬ የእኔነቴ ፈዋሽ የዘመናት ክብሬ
የልቤ ውስጥ ፋኖስ እውነተኛ ምክሬ
አንተን ሀብቴ አድርጌ አለሁ እስከዛሬ
እነኳት ተቀበል የከንፈሬን ፍሬ (2x)
አዝ……
የደሃ ልጅ ደሃ የአድርቆ ለባሽ የአጥንተ ሰባራ የብረት ጠባሽ
ብሎ የሰደበኝ የሸማ ዘርጊ ልጅ ድሪቶ ለባሽ
ለጊዜው ቢመስልም የክብሬ አሳናሽ
ጌታዬ ባንተ ዘንድ አግኝቷል ምላሽ
ንጉሴ ባንተ ዘንድ አግኝቷል ምላሽ
ለድህነቴ መልስ እጄን ሞላህልኝ
ለሰባራው ስሜም ስምህን ሰጠኸኝ
ሊጦጥፍራን አልፈህ በመስቀል ጠራኸኝ
ጎዶሎ አይደለሁም ባንተ ዘንድ ሙሉ ነኝ (2x)
አዝ…..
በገናን ቃኝቼ በውል ብደረድር
በሰም እና በወርቅ ብሕር ባመሰጥር
በዘመኔ ሁሉ ስላንተ ብናገር
መጨረስ አልችልም ከመጀመር በቀር (2x)
በሰርክ ይሁን በቀን በድቅድቅ ጨለማ
እንደ ወፍ በያሬድ ላዚምልህ ስማ
ዛፍ ላይ እንዳለችው እንደዛች ወፍ ዜማ
ላንተ የምሰጥህ ምን አለኝ ሌላማ (2x)
አዝ……
የምሰክርልህ ሰማያዊው ወይኔ
የፍካት ፀዳል የዓይን ብርሀኔ
የምኮራብህ መመኪያ ወገኔ
ሌላ አምላክ የለኝም እንዳትለይ ከእኔ
ሌላ ረዳት የለኝም እንዳትለይ ከእኔ
ሌላ ንጉስ የለኝም እንዳትለይ ከእኔ
ሌላ አባት የለኝም እንዳትለይ ከእኔ
ሲገፉገኝ ከእቅፍህ አረፍኩኝ ሲርበኝ በእጅህ አበላኸኝ
ሲጠማኝ አንተ ነህ ያጠጣኸኝ
ለመልካሙ ሁሉ አባቴ የሆንከኝ
የዘለዓለም አምላክ አንተው ነው ያለኸኝ
የዘለዓለም አባት አንተው ነው ያለኸኝ
የደስታዬ ምንጭ ሰላሜ እውን የሆንከው ለሕልሜ
ስምህን ላንሳ ደግሜ ደግሜ
ያላንተ አልኖርኩምና የደቂቃን እድሜ
ተመስገንልኝ አልኩ በፊትህ ላይ ቆሜ
ተመስገን ልበልክ በፊትህ ላይ ቆሜ

ዘማሪ አቤል ተስፋዬ

በኪሩቤል ላይ ተቀመጠ (አቤል ተስፋዬ በገና)

ቅኝት -
በኪሩቤል ላይ ተቀመጠ
ምድርና ሠማይ ተናወጠ
ለዚህ ቅዱስ አምላክ ምስጋና
አስር አውታር ባለው በበገና
ክብርና ግርማን ለብሰህ
በላይ በአርያም ያለህ
እልፍኙን በውሃ የሠራህ
ሰውን በአርአያህ የፈጠርህ
ላንተ ቅዱስ ጌታ ምሥጋና
አስር አውታር ባለው በበገና
አዝ…
አቤቱ በጽዮን ከብረሃል
በእሳት መድረክ ላይ ተቀምጠሀል
ጠፈሩን በጥበብ ዘርግተሃል
ቀንና ሌሊቱን ለይተሀል
ላንተ ቅዱስ ጌታ ምሥጋና
አስር አውታር ባለው በበገና
አዝ…
በኃይል በሰማይ ታጥቀሀል
የባህሩን ጥልቀት ለክተሀል
የሞገዱን ጩኸት አናውፅህ
ጠላትን በፍቅር የገዛህ

ላንተ ቅዱስ ጌታ ምሥጋና
አስር አውታር ባለው በበገና
አዝ...
ሰማያት ጽድቅህን ተናገሩ
ያንተን ክብር ዝና መሠከሩ
ፍጥረትን አስውበህ የፈጠርክ
ሁሉን በችሎታህ ያደረግክ
ላንተ ቅዱስ ጌታ ምሥጋና
አስር አውታር ባለው በበገና
አዝ...

ስምሽ ጉልበት ሆኖኝ (አቤል ተስፋዬ በገና)

ቅኝት -

ስምሽ ጉልበት ሆኖኝ ወጣሁት ዳገቱን
ድንግል ባንቺ ምልጃ አለፍኩት ወጥመዱን
ድንግል ማርያም ባንቺ ምልጃ ሠበርኩት ወጥመዱን
አምላክ ቀድሶሻል ከሁሉም አብልጦ
ካንቺ ይወለድ ዘንድ በሥጋ ተገልጦ
ለዓለሙ መዳን ምክንያት የሆንሽው
ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም አንቺ ነሽ
አዝ...
ወጀቡን ልሻገር ባንቺ ተደግፌ
ድካሜ ይወገድ ከጥላሽ ሥር አርፌ
ያላንቺ መድኃኒት ከቶ የለምና
ባንቺ ተመገብኩት የሠማዩን መና
አዝ...
ይመስገን ፈጣሪ የነ ዳዊት አባት
ቤቴን ሞልቶልኛል ባንቺ አማላጅነት
አንቺን የተጠጋ በነፍስም በሥጋ
በልጅሽ ይወርሳል የሠማዩን ዋጋ
አዝ...
ዳግም እንዳልራብ ነፍሴ እንዳትጠማ
ከማይደርቀው ምንጭሽ አጠጪኝ እማማ
ከቤትሽ ገብቼ እረፍት አግኝቻለሁ
እድፌ ተወግዶ አዲስ ለብሻለሁ
አዝ...

ሞትን በሞት ገድለህ (አቤል ተስፋዬ በገና)

ቅኝት -

ሞትን በሞት ገድለህ እንዳልሞት ያረከኝ
ከመቃብር ውጣ ብለህ የጠራኸኝ
አራት ቀን ሞልቶታል ይሸታል ሰው ቢልህ
አልዓዛር ሆይ ብለህ ጠራኸኝ በቃልህ
ከሞቱት መካከል እኔን አስነስተህ
በፊትህ አቆምከኝ አይኖቼ እያዩህ
ተስፋ ቆርጠው ሳለ የዋህ ዘመዶቼ
አብሬያቸው በላሁ ከሞት ተነስቼ
ዕድሜዬን በሙሉ ከአልጋ ተጣብቄ
ሞቴን ስጠባበቅ ከወገን ርቄ
የናዝሬቱ ኢየሱስ የኔን መዳን ወደህ
አዲስ ሰው አረከኝ እድፌን አስወግደህ
ነፍሰ ገዳይ ሆኜ ብሰቀል ከጐንህ
በደምህ ምልክት ገባሁኝ ከቤትህ
ጌታዬ ብዙ ነው ያንተ ቸርነት
አለምን አዳንከው ዳግም እንዳይሞት
ጀርባህን በጅራፍ ስለኔ ተገረፍክ
እስከ ቀራንዮ ደምክን አንጠፈጠፍክ
እንዴት ይከፈላል ይህ ታላቅ ውለታ
ለእኔ ያደረከው በዚያች ጐልጐታ
ሞትን በሞት ሽረህ እንዳልሞት ያረከኝ
ከመቃብር ውጣ ብለህ የጠራኸኝ
አራት ቀን ሞልቶታል ይሸታል ሰው ቢልህ
አልዓዛር ሆይ ብለህ ጠራኸኝ በቃልህ

መች ይረሳል (አቤል ተስፋዬ በገና)

ቅኝት -

መች ይረሳል የዋለልን ውለታ
ቸርነቱ እፁብ ፍቅሩ የጌታ
የታተመው በልባችን ጽላት
ሞትን ገድሎ የሠጠንን ህይወት
በጥፋቱ ቢወጣ አዳም ከገነት
ቃል ገባለት ዳግም ሊሠጠው ህይወት
ህያው ጌታ አምላክ ፈጣሪ ሳለ
ስለ ቃሉ በእፀ መስቀል ላይ ዋለ
አዝ...
በአይሁድ እጅ በጽኑ ተንገላታ
የፍቅር አባት ክርስቶስ የእኛ ጌታ
ሥጋው ደክሞ ቅዱስ ደሙ ፈሰሰ
እዳችንን በሞቱ ደመሠሠ
አዝ...
ስንጠላው እርሱ አብዝቶ ወደደን
ስለ ፍቅሩ ሞትን ገድሎ አዳነን
ባርነትን ኃጢአትን ከኛ ጥሎ
ነፃ አወጣን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ
አዝ...
ሰላማችን የድንግል ማርያም ፍሬ
ይገባዋል ምስጋናና ዝማሬ
ስለ ፍቅሩ ስላረገልን ሁሉ
ተቀኙለት ፍጥረታት ዝም አትበሉ
አዝ...

የዛሬ ዘመን መኮንን (አቤል ተስፋዬ በገና)

ቅኝት -

የዛሬ ዘመን መኮንን
ይለማመጣል ሎሌውን
ዶሮ ካዘዙ በአንድ ውለታ
አባብሎ አያውቅም ጌታ
ጻድቁ አናፂ ለአንክሮ
መጥረቢያ የለው መብሻ መሮ
ይህን አዳራሽ ሠራልን
ዓለምን /5/

ቤት ስትሠራ ነፍስ ወይዘሮ
በጣሪያ ማገር ተሸጕርጉሮ
ብዙ እንኪን ነበር ሸንበቆው
ሥጋ ጨረሰችው
ለቀድሞ ሰዎች በህልማቸው
መጪውን ሁሉ ገልፆላቸው
ያላዩት የለም ከሆነው
ሁሉ እንዳለሙት ነው
ሞት ገበሬ ነው ለመሬት
እሰው ቤት ነዋሪ ሲዋትት
ያስደንቀኛል በተግባሩ
አፈራርሶ መኖሩ
እንግዳ አለብሽ አንቺ ነፍስ
ከሥጋ በቀር የማይቀምስ
አብረን እንፈልግ በማለዳ
እስኪ እዚያ ላይ ፍሪዳ
እንግዳው ድንገት ስትደርስ
ሳትሰናዳ ቆየች ነፍስ
ለእንጀራ ብቻ የለው መላ
ዓለምን /4/ አምን ብላ
የወልድ አምላክን እራቱን
ሳላሰናዳ ምናምን
በሥጋ አደረ ትላንትና
ጌታ ሰው ሆኗልና

በደም ሊታጠብ ኃጢአቴ (አቤል ተስፋዬ በገና)

ቅኝት -

በደም ሊታጠብ ኃጢአቴ /2/

በደም ሊታጠብ ኃጢአቴ
ተበጣጥሶ ሊወድቅ እስራቴ
ወጣህ ቀራንዮ ጎልጎታ
በእኔ ተገብተህ አንተ ጌታ
አዝ...
በወንበዴዎች መካከል
እንደወንጀለኛ ስትሰቀል
ከዋክብትም ረገፉ
ከመሬት ላይ ተነጠፉ
አዝ...
መቃብርን አፈራርሰህ
በስልጣንህ ሞትን ገድለህ
ሲኦልም ባንተ ተበርብራ
ነፍሳት ወጡ በየተራ
አዝ...
ጠላት ሞቷል ላይነሳ
ምርኮ ሆኗል በደም ካሳ
ምስጋና ብቻ የለም ሌላ
ለታደገን ከሞት ጥላ
አዝ...
ዳግም የለም በኛ ሞት
አንዴ ሞቷል ሞት ሊሞት
በክርስቶስ ክርስቲያን ነን
ሞት ከሞተ ህያዋን ነን አዝ...

ሠላምህ ይብዛላት (አቤል ተስፋዬ በገና)

ቅኝት -

ሠላምህ ይብዛላት ምድሪቱ
የሰው ልጅ እንዳይቀር በከንቱ /2/
የሌለንን ሰላም እንሰብካለን
በጎ ነገር ጠፍቶን እንጮሀለን
ጸሎት ልመናችን ከንቱ እንዳይቀር
ሰላምን ላክልን እግዚአብሔር
አዝ...
የካም ልጆች በዝተው በምድር ላይ
ገመናን ገለጡ በአደባባይ
ፍፁምነት ጠፍቶ ከልባቸው
በክፋት ተመላ ጉባኤያቸው
አዝ...
በሰላም ቤት ቆመን ሰላም ጠፍቷል
ታንኳችን በነፋስ ተጨናንቋል
አድነን ጌታ በሆይ እንዳንጠፋ
ገስፀው ማዕበሉን ሁነን ተስፋ
አዝ...
አለም ስለሰላም ቢዘምርም
ምድራችን ከሠላም አርፋ አታውቅም
ሰላማችን አንተን ስንይዝ ነው
እውነተኛ ሰላም የምናገኘው
አዝ...

ስሜ ዳዊት (አቤል ተስፋዬ በገና)

ቅኝት -
ስሜ ዳዊት የእሴይ ልጅ
እኖራለሁኝ በእግዚአብሔር ደጅ
ታዳጊ ነኝ የበጉን መንጋ
በመታገል በጌታ ጸጋ
እረኝነት ነው ግብሬ /2/
አምላክ የሰጠኝ ግብሬ
በጌታ ፊት ይዤ በገና
ስለ ስሙም ላቅርብ ምሥጋና
ጣቴ አያርፍም ሰልፍን ይሰራል
አንደበቴም ቅኔን ይቀኛል
እረኝነት ነው ግብሬ /2/
አምላክ የሰጠኝ ግብሬ
በሳኦል ፊት ቢልቅ ጎልያድ
ህዝበ እስራኤል ልቡ ቢሸፍት
አምላካችን ጌታ ሲከብር
ለጎልያድም በቅቶታል ጠጠር
እረኝነት ነው ግብሬ /2/
አምላክ የሰጠኝ ግብሬ
በአባቴ ፊት ፈልቷል ዘይቱ
ከብላቴናው ጸንቶ ጉልበቱ
ጸጋ እግዚአብሔር ፈሷል በላዬ
ከእረኝነት ጠርቶኝ ጌታዬ
እረኝነት ነው ግብሬ /2/
አምላክ የሰጠኝ ግብሬ

በፍርድ ወንበር አለ በገና
ለሰማይ ንጉስ ሞልቶ ምሥጋና
ከሳኦል ላይ መንፈሱ ይራቅ
ከፈጣሪው ጋር ነፍሱ ትታረቅ
እረኝነት ነው ግብሬ /2/
አምላክ የሰጠኝ ግብሬ

በደላችንን የተውክልን (አቤል ተስፋዬ በገና)

ቅኝት -

በደላችንን የተውክልን
በመስቀል ተሰቅለህ እራቁትህን
ጐንህን ተወግተህ የእኛ ጌታ
ሞትን ወጋህልን ወደማታ
ሞትን ወጋህልን በጐልጐታ
ጠላት ክንዱን ጭኖብን በላያችን
የእዳ ደብዳቤ በአንገታችን
አስሮ ቢጥለንም ከጉድጓዱ
በደምህ ፈታኸን ከወጥመዱ /2/
አዝ...
በስብራትህ የጠገንከን
አንተ ደክመህ ያድናናኸን
መስቀል ተሸክመህ ክንድህ ዛለ
ሞታችን በሞትህ ተገደለ /2/
አዝ...
ሲኦል ተበርብራ በሥልጣንህ
ነፍሳት ተመልሰው ወደቤትህ
ሞልቷል ከበረቱ በአንተው መንጋ
ደም ተከፍሎ ለሞት ዋጋ/2/
አዝ...
ከዋክብት ረገፉ ስለ ክብርህ
ብርሃናት ጨለሙ ላያሳዩህ
ሙታን ከመቃብር ተነሱና
ምስጋና አቀረቡ እንደገና /2/
አዝ...

ሥላሴ (አቤል ተስፋዬ በገና)

ቅኝት -
ሥላሴ አምላኬ ብዬ እዘምራለሁ
ሥላሴ አምባዬ ብዬ እቀኛለሁ
ሰማይና ምድር ደመና ሳይቀሩ
አዕዋፍ አዝርዕት በእርሱ ተፈጠሩ
ብርሃን ጨለማ እንዲሆን በተራ
በዓለሙ ሁሉ ፀሀይ እንዲያበራ
እንድትሰለጥን ጨረቃ በሌሊት
ሥላሴ አስውቦ ፈጠረ ከዋክብት
አዝ...
በእግር የሚሄዱ በክንፍ የሚበሩ
በምድር ላይ ያሉ በጥልቅ የሚኖሩ
በሥላሴ ዘንድ ሁላቸው ታውቀዋል
በከሀሊነቱ ፍጥረት ተፈጥረዋል
አዝ...
አስቀድሞ ያለ ዓለም ሳይፈጠር
ሥላሴ ነበረ ዘመን ሳይቆጠር
ዘመን አሳልፎ ዘመን የሚያመጣ
ለክፉ ለደጉ ፀሀይ የሚያወጣ
አዝ...

ጥሩልኝ ዳዊትን/አቤል ቁ2/

ቅኝት -
ጥሩልኝ ዳዊትን በገናውን ያምጣ
መንፈስ አስጨንቆት ሳኦል ስለመጣ (2)
ምድር ግብሯን ትታ ሕግ እያፈረሰች
የሳኦልን መንገድ ስለተከተለች
ከህልም ዓለም ቅዠት እንድትረጋ
ያን ዳዊትን ጥሩት ይደርድር በገና
አዝ ...
የርኩሰትን ሥራ ዓለም ስላበዛች
ያልተፈቀደውን ምርኮን ስለያዘች
በዝማሬው ጸጋ ፈውስን እንድታገኝ
ጥሩልኝ ዳዊትን በበገና ይቃኝ
አዝ ...
የአባቶቹን ትዕዛዝ መንገድ ስለሳተ
ጸያፍ የሆነውን እርሙን ስለሻተ
ለንስሃ ደርሶ መንግስቱ እንዲቀና
ጥሩልኝ ያን ዳዊት ይደርድር በገና
አዝ ...
መለያየት በዝቶ ፍቅር ስለራቃት
ስላቀረቀረች መከራው ጸንቶባት
በጥልቁ ዝማሬ እውነቱን እንድታይ
ዳዊት ይነሳና በበገና ይጸልይ
ዳዊት ይነሳና በበገና ይቃኝ
አዝ ...

ሦስትነት ባለው /አቤል ተስፋዬ በገና ቁ2/

ሦስትነት ባለው በእግዚአብሄር
ስሙን አምኜ ልዘምር
የመድኃኔአለም ህማሙን
እንባን በማፍሰስ በሀዘን
እንደርሱ ታጋሽ ማንም የለም
ቸሩ አምላካችን መድኃኔአለም
በጎልጎታ የዓለም ንጉስ ተንገላታ
አልበደለ እውነተኛው በግ ተሰቀለ ሰጊድ ስብሐት
ድህነት የሚሰጥ ለፍጥረቱ
የሚገዙለት መላእክቱ
ሁሉን በፍቅር የሚያድነው
ክፉዎች ያዙት ተረባርበው
የሚያዳፉ ውሾች በዙሪያው ተሰለፉ
ያለ እረፍት አጥንቱ እስኪታይ ገረፉት ሰጊድ ስብሐት
ትእግስቱ የበዛ ቸርነቱ
የሚመሰገን በፍጥረቱ
ከዓለም ሊያጠፋ የክፋት መርዝ
የአዳምን እዳ ለመሰረዝ
በፈወሰው በጥፊ መታው ያ ክፉ ሰው ሰጊድ ስብሐት

ድህነትን ሊሰጥ የፈቀደ
በፍቅር ተስቦ የወረደ
ዘላለማዊ የሚሰጥ ፀጋ
አዳምን ሊያድን ከአለንጋ
ግፍ ባልሰራ እየተነሱ በየተራ
ያለእረፍት አጥንቱ እስኪታይ ገረፉት ሰጊድ ስብሐት
የሁሉ ንጉስ የአለም ፈራጅ
በራሱ ፈቃድ ያለ ግዳጅ
ከነገሰበት ከዙፋኑ
ሰይጣንን ሊጥል በስልጣኑ
በፍቅር ነፍሱን ሰዋልን ሞት ሊሸር
ይቅር ባይ ተፈፀመ አለ ኤልሻዳይ ሰጊድ ስብሐት

የቃል ማደሪያ ነሽ/አቤል ተስፋዬ በገና ቁ2/

የቃል ማደሪያ ነሽ ለመለኮት አገር
ምክንያተ ድኅነት ያየንብሽ ምሥጢር
ስምሽን ሳነሳሳው ብሩህ ሆኗል መንገዴ
መዳኔ በአንቺ ነው ሰማያዊት ዘመዴ
እንደ ማር በምድር እንደ ያም በአርያም
ስምሽ ጥዑም ነው ለዘለአለም
በውሆች መካከል ጠፈር ሳይፈጠር
ብርሃንም ሳይታይ ባዶ ሆና ምድር
በአብ ህሊና ውስጥ ተስለሽ ነበረ
ትንቢቱ ሲፈፀም ቃሉ ባንቺ አደረ
እንደ ማር...
ድንግል ሆይ መአዛሽ በእግዚአብሔር ተወዷል
የልዑል ማደሪያው እንድትሆኝ መርጦሻል
ቤዛ የሚሆነን ለቆሸሸው ዓለም
ካንቺ ተገኘልን ሁለተኛው አዳም
እንደ ማር...
ከፀሀይ ሰባት እጅ ያበራል ገጽሽ
ትውልድን ያስምራል ብርቱ ጸሎትሽ
በምልጃሽ ያመነ በረከት አግኝቷል
ክብርሽን የናቀ ከእግርሽ ሥር ይወድቃል
እንደ ማር.../2/

በጾም /አቤል ተስፋዬ በገና ቁ2/

በጾም ትትፌውስ ቁስለ ነፍስ
ወበጸሎት ትትሐሠይ መንፈስ /2/
መአልትና ሌሊት በጾም ጸሎት ተግቶ
አሳይቷል ጌታ ስርዓትን ሰርቶ
አይቀርም ፈተናው ትጋት ከሌለበት
ስጋ ካልደከመች በጾምና ጸሎት
አዝ...
ሙሴ የተባለው ያ የእግዚአብሔር ሰው
ፊቱን የበራለት አርባ ቀን ጾሞ ነው
በሲና ተራራ ተቀብሎ ህግን
እርሙን እንድንተው አሳየን መንገድን
አዝ...
የጸሎት እናቷ ስለሆነች ጾም
ትህትናን ይዘን ደግሞም አንድ ሆነን
ብንተጋ በጸሎት ከንስሐ ጋራ
ጾም ታደርሰናለች ከጽዮን ተራራ
አዝ...
አንድበትም ይጹም ዓይንም ይረጋጋ
ጆሮም ክፉ ሰምቶ ነፍሱን እንዳይወጋ
ድህን ከመበደል ልብም ተመልሶ
መጾምስ እንዲህ ነው የበደለን ክሶ
አዝ...

ስለኔ ለሞተ /አቤል ተስፋዬ በገና ቁ፪/

ስለእኔ ለሞተ /4/
ለቤዛዬ ምን እከፍለዋለው
ለአምላኬ ምን እከፍለዋለው
ትዕዛዙን አፈረስኩ በምግባሬ ቆሸሽኩኝ
በምግባሬ ቆሸሽኩኝ
ህጉን ባለማክበሬ ተገፈፈብኝ ክብሬ
ተገፈፈብኝ ክብሬ
ጥፋቴን አይቶ አልተወኝ ከቶ
ቃል ገብቶልኛል ይደርስልኛል
ጥፋቴን አይቶ አልተወኝ ከቶ
ይደርስልኛል ይጠብቀኛል
አዝ...
ምንም እንኳን ብስትም ልጅነቴን ብክድም
ልጅነቴን ብክድም
በክቡር ደሙ አጠበኝ ዳግም ልጁ አደረገኝ
ዳግም ልጁ አደረገኝ
ክብሩን አዋርዶ ከአርያም ወርዶ
ዋለ መስቀል ላይ ሲሆን ኤልሻዳይ
ክብሩን አዋርዶ ከአርያም ወርዶ
ዋለ መስቀል ላይ ሲሆን ኤልሻዳይ
አዝ...
ግርፊያዬን ተገረፈ ሞቴን በሞቱ አለፈ
እዳዬን ከፈለልኝ ከባርነት አወጣኝ
እሳት ነው ቤቴ ባትደርስ አባቴ
አሁን የአንተ ነኝ ተመስገንልኝ
እሳት ነው ቤቴ ባትደርስ አባቴ
አሁን የአንተ ነኝ ተመስገንልኝ
አዝ...

ደጁ ሲመላለስ/አቤል ተስፋዬ በገና ቁ፪/

ደጁ ሲመላለስ ማን እንደኔ ይላል
የጸደቀ መስሎት ዘግቶ ይቀመጣል
ትዕዛዙን ሲፈጽም አንዱን ግን ዘንግቷል
ያለ ፍቅር ባዶ መሆኑን እረስቷል
ፍቅርን ስጠን ብለን እንለምናለን /2/
ፍቅር አንተ ነህና ፍቅርን አልብሰን
ልማዱን ነው እንጂ ያለ ፍቅር ደጁን መሳለሙን
ሰው መቼ አይቶታል ያለ ፍቅር የህይወት ጉድለቱን
በትንሽ ከፍታ ብዙ ይኮፈሳል
ወንድሙን ሳይወደው መጽደቅን ይመኛል
ፍቅርን ስጠን...

ተሸናፊ መስሎ ያለ ፍቅር በልቡ ያደባል
የወንድሙን ስኬት ያለ ፍቅር በቅናት ይመኛል
ሊጥለው ባሰበው በያዘው ወጥመድ
አንድ ቀን ይወድቃል እግዚአብሔር ሲፈርድ
ፍቅርን ስጠን...
ምን እምነት ቢኖርም ያለ ፍቅር ፍጹም በእግዚአብሔር
ምስጋናን ቢያበዛ ያለ ፍቅር በተስፋ ቢኖር
ከቶ እንዳይታበይ በያዘው ጎዳና
እምነት ያለ ፍቅር ጎዶሎ ነውና
ፍቅርን ስጠን...

በፈጣን ደመና/አቤል ተስፋዬ በገና ቁ፪/

በፈጣን ደመና መጣ እየበረረ
ኢሳይያስ በትንቢት እንደተናገረ
በእናቱ ጀርባ ላይ ሆኖ ተሰደደ
ከድንግል ማርያም ጋር ወደ ግብጽ ወረደ
ማርያም አዛኝቷ አሳዛኝ ስደቷ /2/
ሄሮድስ የተባለው የአገሬው ንጉስ
እጅግ ሰግቷልና ክብሩ እንዳይወረስ
የእስራኤል አምላክ ተወልዷል ቢሉት
የሞት አዋጅ አለ ያለ መራራት
ማርያም አዛኝቷ አሳዛኝ ስደቷ /2/
ድንግል ይህን ሰምታ የሞቱን አዋጅ
ልታድን ወደደች ከሀሊውን ልጅ
ይዛው ተሰደደች ወደ ግብጽ ምድር
ትንቢቱ እንዲፈጸም ዓለም እንዲማር
ማርያም አዛኝቷ አሳዛኝ ስደቷ /2/
እንዴት ይነገራል ረሀቡ ጥማቱ
ያ ሀሩር በረሀ ያሸዋው ግለቱ
በአምላክነቱ በቅድስናሽ
አለፈ ያ ዘመን ስቃይ መከራሽ
ማርያም አዛኝቷ አሳዛኝ ስደቷ /2/
ጻድቁን አይደለም ኃጥኡን አሳስቢ
ለንጹሐን አይደል ላደፉት አሳስቢ
በምልጃሽ አትርሺን በግብጽ ስደትሽ
በህይወት እንዲጽፈን ከሀሊውም ልጅሽ
በህይወት እንዲጽፈን የወደደን ልጅሽ
ማርያም አዛኝቷ አሳዛኝ ስደቷ /2/

እስከ መቼ ነው /አቤል ተስፋዬ በገና ቁ፪/

እስከመቼ ነው ጌታዬ
የሚፈሰው ይህ እንባዬ
ፊትህን መልስልኝ
በምህረትህ ጠል አርሰኝ
በባቢሎን መኖር ለእኔ ሰልችቶኛል
ከነዓን ለመድረስ እግሬ አጥሮብኛል
ጠላቴ አይደሰት አትስጠኝ ለሞት
በምናፍቃት ምድር ልኑር በህይወት
አዝ...
ወጥመዱን ሰባብሮ ትላንት የረዳኝ
ክንድህ ነው አምላኬ የሚያበረታኝ
ዛሬም አትተወኝ አባቴ ስልህ
እንባዬን አብሰው ልታደስ ልጅህ
አዝ...
ፈተና ቢበዛ በአንተ እታመናለሁ
እያነባው ፊትህ እርዳኝ እልሀለሁ
እኔ አላማርርም እጠብቅሀለሁ
ምን እንዳሰብክልኝ ከቶ መች አውቃለሁ
አዝ...
ሞገስ ይሁንልኝ ቅዱሱ ስምህ
ሀዘኔን ያስረሳኝ ጌታ ችሮታህ
በኃጢአት ጐዳና ቀርቶ መዋተቴ
ጽድቅን እንድሰራ እርዳኝ መድኃኒቴ
አዝ...

ቅዱስ/አቤል ተስፋዬ በገና ቁ፪/

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ
ኃያል ኃያል ኃያል አማኑኤል
አስቀድሞ የነበረ አሳልፎ የሚኖር
በስልጣኑ አጠፋልን ሙስና መቃብር
ከአባቱ ጋር ትክክል ነው በኃይል በጌትነት
በዓለም ሊፈርድ የሚመጣው በክብር በትስብዕት
አዝ...
የሰው ፍቅር አገብሮት ወደ ምድር የመጣ
ከሰማያት የወረደው ወደ ሰማይ የወጣ
ከምስጉኖች ይልቅ ምስጉን ከግሩማን ግሩም
የጠቢባን ጠቢብ ጌታ የሚመስልህ የለም
አዝ...
ብንዳስሰው ብንበላው ደግሞም ብንጠጣው
እረቂቁ የገዘፈው ሥጋን ተዋህዶ ነው
በደመናት መጋረጃ የተሰወረ እሳት
በግርግም ውስጥ አገኘነው በግዕዘ ህፃናት
አዝ...
ሰማያትን የዘረጋ ውሆችን የፈጠረ
የማይታይ የሚታየው እርሱ ተፈጠረ
ሁሉን በእጁ የጨበጠ አሸናፊው ልዑል
በቤተልሄም ተወለደ ከማርያም ድንግል
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር
ኃያል ኃያል ኃያል አማኑኤል

በርባን ነኝ/አቤል ተስፋዬ በገና ቁ፪/

በርባን ነኝ /3/
ባንተ መስቀል የዳንኩኝ

በኃጢአት በበደል የኖርኩኝ በክፋት
ወንበዴ ነበርኩኝ የሚገባኝ መሞት
ሁሉንም እረስተህ በፍቅር ያየኸኝ
ንገረኝ አምላኬ እንደ ምን ወደድከኝ
ጌታዬ በርባን ነኝ በሞትህ ያዳንከኝ
አምላኬ በርባን ነኝ በመስቀል ያዳንከኝ

ወንበዴው እኔ ነኝ ሀገር ያስቸገርኩኝ
እጆቼን በበደል በደም የታጠብኩኝ
አንተ ግን እራርተህ ተሰጠህ ስለእኔ
ዋጋ ከፈልክልኝ ክርስቶስ መድኅኔ
ጌታዬ በርባን ነኝ በሞትህ ያዳንከኝ
አምላኬ በርባን ነኝ በመስቀል ያዳንከኝ
ሞቴን ስጠባበቅ እኔ እንደ ሥራዬ
ትክክል ነውና የክፋት ዋጋዬ
አንተ ግን ንጹሁ እኔን የወደድክ
ለነፍስህ ሳትሳሳ እስከ ሞት ደረስክ
ጌታዬ በርባን ነኝ በሞትህ ያዳንከኝ
አምላኬ በርባን ነኝ በመስቀል ያዳንከኝ
በዋጋ ገዝተኸኝ ዳግመኛ እንዳልሞት
ብርታት ሁነኝና ልለይ ከኃጢአት
መልካምን እንዳስብ መልካም እንድሰራ
በጽድቅ ልመላለስ ልቦናዬን አብራ
ጌታዬ በርባን ነኝ በመስቀል ያዳንከኝ
አምላኬ በርባን ነኝ በመስቀል ያዳንከኝ

ሞት ሆይ/አቤል ተስፋዬ በገና ቁ፪/

ሞት ሆይ ዝም በል በሞት ተገለህል ሥልጣንህ ተሸሯል/2/

በመስቀል ተሰቅሎ አማኑኤል ጌታ
ሲኦልን በርብሮ ነፍሳትን ሲፈታ
ሞት ሆይ ወዴት ነበርክ
ነፃ ሲያወጣቸው የተማረኩትን
ሲሰበስባቸው የተበተኑትን
ሞት ሆይ ወዴት ነበርክ
አዝ...
መቃብርን ድል ነስቶ ሲነሳ በክብር
ለማርያም ሲታይ ሄዳ እንድትመሰክር
ሞት ሆይ ወዴት ነበርክ
ደቀመዛሙርቱ ሲያዝኑ ለብቻቸው
በዝግ ቤት እንዳሉ ገብቶ ሲያጽናናቸው
ሞት ሆይ ወዴት ነበርክ
አዝ...
ከነቀለዮጳ ጋር በኤማሁስ መንደር
አብሯቸው ሲወያይ ስለሆነው ነገር
ሞት ሆይ ወዴት ነበርክ
እነርሱ ጋር አብሮ ሲቀመጥ ለማዕድ
አለማስተዋል ከውስጣቸው ሲነድ
ሞት ሆይ ወዴት ነበርክ
አዝ...
ወደ ሰማይ ሲያርግ በአርባኛው ቀን
ምሥጢር ሲነግራቸው ሐዋርያቱን
ሞት ሆይ ወዴት ነበርክ
በክብሩ ሲቀመጥ በኃይል በሥልጣኑ
ደግሞ እንደሚመጣ ሲናገር በቃሉ
ሞት ሆይ ወዴት ነበርክ
አዝ...

ዘማሪ አለማየሁ ፈንታ

ከእንግዲህ አልደግምም /ዘማሪ አለማየሁ ፈንታ/

ቅኝት-

ከእንግዲህ አልደግምም ዳዊት ይበቃኛል/2/
ንግግሩ ሁሉ ፀፀት ሆኖብኛል
ፀፀት ሆኖብኛል ፀፀት ሆኖብኛል
ኖኅ አንድ ቀን ሰክሮ ገላው ቢራቆት
በስተኋላው ቀርበው ልብስ ቢያለብሱት
ቡራኬ አግኝተዋል ሴምና ያፌት
ሴምና ያፌት ሴምና ያፌት
ብልህ ነው ስትሉኝ እዩት ሞኝነቴን/2/
በራሴ ላይ ሆኖ አላውቀውን ሞቴን
አላውቀውን ሞቴን አላውቀውን ሞቴን
ብላጬው አያምር ብተወው በላኝ/2/
አንድ እራሴ እኮ ነው የሚያስቸግረኝ
የሚያስቸግረኝ የሚያስቸግረኝ
ኢትዮጵያ ናትና የወይን ዘለላ/2/
ከልምላሜ ስፍራ ፍሬዋን አብቅላ
ፍሬዋን ለመብላት ሁሉም ይጥራሉ
አጥሯ ፆም ፀሎት ነው በየት ይገባሉ
በየት ይገባሉ በየት ይገባሉ
ወንድሜ ፈረስህን እንዳወጣ ሽጠው/2/
ባስበው ከበደኝ እንኳን ልቀመጠው
እንኳን ልቀመጠው እንኳን ልቀመጠው
አዳራሹ ሰፊ በሩ አልጠበባችሁ/2/
በተራ በተራ ምነው መግባታችሁ
ምነው መግባታችሁ ምነው መግባታችሁ
መጫወቱን ትተህ ቆመህ ከመንገድ/2/
ተማር ይልቅ አንተ እንድወደድ
እንድወደድ እንድወደድ

እናት አባትሽ /ዘማሪ አለማየሁ ፈንታ/

ቅንት-

እናት አባትሽ ሳይድሩሽ በቤተ መቅደስ ተቀምጠሽ
ወልደሽ ተገኘሽ ልጅሽን አለምን አለምን/2/
ምድር ብትል ያለዘር እህል ላብቅል
ሴትም ልጅን ያለወንድ ልውለድ ብትል
ይቻላል ወይ መቼስ ተደርጎ ያውቃል
እኔ ድንግል ወንድ አጠገቤ አይደርስ
ይህን ነገር የት አገኘሽው አንተስ
መለሰላት እንዲህ እያለ ሳይዋሽ
ማርያም ሆይ አንቺስ አትፍሪ አይዞሽ
ያንቺማ ፅንስ እንደሴቶች ፅንስ መስሎሽ
ካንቺ ባህርይ ከአንዱ አካል ስጋን ሲለብስ
ያድርብሻል አንዱ አካል መንፈስቅዱስ
እናት አባትሽ ሳይድሩሽ በቤተ መቅደስ ተቀምጠሽ
ወልደሽ ተገኘሽ ልጅሽን አለምን አለምን አለምን አለምን
ያፀናሻል አንደኛው አካል አብም
በባህሪሽ እንዳያገኝሽ ድካም
እንዲህ አድርገሽ ሳትፈልጊ ወንድን
ትወልጃለሽ ከሦስቱ ቅዱስ አንዱን

እናት አባትሽ ሳይድሩሽ በቤተ መቅደስ ተቀምጠሽ
ወልደሽ ተገኘሽ ልጅሽን አለምን አለምን አለምን አለምን
እንኳን አንቺ ሙቀት ልምላሜ ያለሽ
ያረጀችው ኤልሳቤት እንኳን እህትሽ
በስተርጅና እግዚአብሄር ሰጥቷት ልጅን
ካረገዘች ስድስት ወር ሆኗት የለምን
እናት አባትሽ ሳይድሩሽ በቤተ መቅደስ ተቀምጠሽ
ወልደሽ ተገኘሽ ልጅሽን አለምን አለምን አለምን አለምን
ትፀንሻለሽ በድንግልና አንቺም
ለእግዚአብሄር አብ የሚሳን ነገር የለም
በዚህ ጊዜ ምክኒያት አድርጎ ቃሏን
በተከፍሎ ወይም በምትሃት ሳትሆን
ትንሽ ሆኖ እንደ ህፃናት መጠን
ተዋሐደ ፍፁም መለኮት ስጋን/2/
በቤተ መቅደስ ተቀምጠሽ እናት አባትሽ ሳይድሩሽ
ወልደሽ ተገኘሽ ልጅሽን አለምን አለምን

ዘማሪ ዘውዱ

ቅድመ ዓለም ንጉስ(ዘማሪ ዘውዱ)

ቅድመ ዓለም ንጉስ ዘለዓለም ሥላሴ
በአምሳልህ ሰርተህ ባከበርካት ነፍሴ
እሰዋልሃለሁ ምስጋና ውዳሴ

ቀንማ ሆነ ማታ ቀናት ተቆጠሩ
በሰማይ በምድር ፍጥረታት ሰፈሩ
በቃልህ የመጡ በእጅህ የተሰሩ
ሁሉም ፍፁም ናቸው በአንተ የሚኖሩ
ሁሉም ፍፁም ናቸው ስምህን የሚጠሩ
አዝ...
ፍጥረት መካተቻ እለተ አርብ ሆኖ
አዳምን ፈጠረው የክብር ዘውድ ከድኖ
አምሳሉን ቢረሳ ቢበድለው ቀድሞ
ልጁን ልኮ ገዛው በእለተ ዓርብ ደግሞ
የፈጠረው ዋጀው ቀራንዮ ደግሞ
አዝ...
እንከን የሌለብህ ፈጥረህ የምትገዛ
የምህረት አምላክ የፍጥረታት ቤዛ
የወደቀ ይነሳል በስምህ ሥላሴ
በአጸድህ ተገኝች ስደተኛ ነፍሴ
በቤትህ ተገኝች ስደተኛ ነፍሴ
አዝ...

ቤተ ስብሐት(ዘማሪ ዘውዱ)

ቤተ ስብሐት ድንግል መንበረ ልዑል
ሐረገወይን አንቲ ወልድኪ አስካል
የንጉስ አዳራሽ መዝገበ ዝማሬ
ሐረግ ነሽ ማርያም መድኃኔአለም ፍሬ
ንኢ ለባርኮ ንኢ ድንግል ምስለ ወልድኪ አማኑኤል/2/
ተስፋው እውን ሆኖ እንዲፅናና አዳም
ካንቺ ተወለደ አንበሳ ግሩም
ቤተልሄም ድንግል ማርያም ኤፍራታ
አለም ሁሉ ዳነ በወለድሽው ጌታ
ንኢ...
መላዕክት በሰማይ ለስምሽ ውዳሴ
ተፈሥሒ ይላሉ መትህተ ሥላሴ
የፅዮን ታቦት ነሽ የሰማይ ሰሌዳ
የምህረት ምልክት የምድር ፅጌረዳ
ንኢ...
ከኪሩቤል ሞገስ ከሱራፌል ግርማ
ድንግል ትበልጫለሽ የንጉስ ከተማ
ወላዲተ አምላክ ምልጃሽ መታመኛ
በረከት ሽተናል ነይልን ወደኛ
ንኢ...

ከሰገነት ወጥተህ(ዘማሪ ዘውዱ)

ከሰገነት ወጥተህ ለምን ትወርዳለህ
የጣልከው ነውርህን እንዴት ታየዋለህ
ግራ ቀኝ አትበል ውጣ ከተራራ
መኖሪያህን ቀይስ ከቅዱሳን ጋራ
የመቅረዙን መብራት አውጣው ከተራራ/2/
እንድታንጸባርቅ የአምላክህን ስራ/2/
ከጥልቁ የሚያወጣ እጁ ተዘርግቶ
ማን ጠርቶህ ተመለስክ አልገባህም ከቶ
የተጠራህበት ከዓለም ሁሉ ቀድሞ
በደሙ ማህተም ገፅህን አትሞ
የመቅረዙን...
ዓለም ሲንበረከክ ለእጆቹ ስራ
የወንጌሉ ነገር በኢትዮጵያ አበራ
በባኮስ ሰላማ ቅዱሳን ተሰዓቱ
በኩር የምትሆንበት አለህ አብነቱ
የመቅረዙን...
ቤትህ ያማረ ነው የለውም አምሳያ
ህይወትህን አክብር አትይ መታለያ
ሃይማኖት ጌጥህ ነው ጥሪ ተዋህዶ
ለፈቃዱ ለየህ አምላክ አንተን ወዶ
የመቅረዙን...
መክሊትህን ጠብቅ ጠላት ያይብሃል
ብኩርናህን ወስዶ ምርኮ ያደርግሃል
ላለፈው ተፀፀት በለቅሶ በእንባ
ተመለስ አንተ ሰው ወደ ቤትህ ግባ
የመቅረዙን...

በዘሩ የነበረች(ዘማሪ ዘውዱ)

በዘሩ የነበረች ድንግል የአዳም ተስፋ እንቁ ፀዓዳ
የፅድቃችን ፀሐይ ድንግል የወጣባት ብርክት ሰሌዳ
ድንግል እናታችን ድንግል ሶልያና
በፀዳልሽ ታየን ከበርን እንደገና
ልጅሽ ልጅ አደረገን ዳግም እንደገና

ባዝኖ የነበረ ድንግል የተጎሳቀለ ማርያም
በቀረችለት ዘር ድንግል አባቱን መሰለ ማርያም
እንደ ሰዶም በሆንን ልክ እንደ ገሞራ
ውሃው ባይለወጥ ድንግል ባንቺ ስራ
ድንግል እናታችን...
የሴቲቱ ልጅ ነው ድንግል በአውሬው ራስ የቆመው ማርያም
የጎደፈን ታሪክ ድንግል በደሙ ያረመ ማርያም
እርሱን ስሙት ያለች አድርጉት በሙሉ
ፈቃዷ ፈቃዱ እግዚአብሄር ኃያሉ
ድንግል እናታችን...
ሰማይ ዙፋኑ ነው ድንግል ምድርም መረገጫው ማርያም
የድንግል ማህጸን ድንግል ሆነው መናገሻ ማርያም
ሥርጉተ ንፅህና ጌታ አንቺን መረጠ
ጣዕም አልባነታችን በጨውሽ ጣፈጠ
ድንግል እናታችን...
ስለዚህ አርጋኖን ድንግል ስለዚህ በገና ማርያም
ልቦናዬ አወጣው ድንግል ከፍሬ ሀሊና ማርያም
የአንገታችን ማህተብ መዝገበ ልባችን
በጠበቀው ፍቅርሽ ለምኚ እናታችን
ድንግል እናታችን...

ሀዘን መከራ(ዘማሪ ዘውዱ)

ሀዘን መከራ ሰፍኖ በህይወቴ
መዛል ጀመረ ደክሞ ሰውነቴ
የቀደመውን በደሌን ረስቶ
ጌታ አበረታኝ ቸርነቱ በዝቶ
አንድ ቀን አይቀርም እነሳለሁ ከወደኩበት እቆማለሁ
ተስፋ ሳልቆርጥ በጌታዬ በእርሱ እኖራለሁ ከቤተመቅደሱ/2/
እንበረከካለሁ እንዲያነሳኝ ክንዱ
ይፈፀማልና ሁሉ በፈቃዱ
የንጋት ብርሃን የእውቀት መገኛ
አንተ ነህ የነፍሴ የስጋ መዳኛ
አንድ ቀን አይቀርም...
የማዳን ጥበብህ ኃያል ነው
ምግብ የሆነኝ ስጋህ ቅዱስ ነው
የሚለምኑህን ዘውትር የምትሰማ
የኔ ባርያህን ጩኸቴንም ስማ
አንድ ቀን አይቀርም...

የአባ ሕርያቆስ(ዘማሪ ዘውዱ)

የአባ ሕርያቆስ የኤፍሬም ውዳሴ
የያሬድ እመቤት ታመስግንሽ ነፍሴ
በብርሃኑ ምንጣፍ በመቅደሱ ፋና
ቅድስት ሆይ ልበል ዛሬም እንደገና
ሄዋን የሰጠችኝ ዕጸበለስ ቆርጣ
ሀጥያትና ሞትን በዓለም ላይ ሲያመጣ
ንፁሃ መሶቤ በአንቺ ህይወት ተገኘ
ትውልድ ሁሉ ላንቺ ቅኔ ፍቅር ተቀኘ/2/
አዝ...

የወርቁ መሰላል ከአርያም መድረሻ
ከጭንቀት ከችግር ከሀዘን መሸሻ
የአምላክ ስጦታ ድንግል በረከቴ
በምልጃሽ ልፅናና ነይልኝ እናቴ/2/
አዝ...
በእርሱ ሰላም ሆኗል ባንቺ ድኅነት
ብርሃን ከአንቺ ወጥቷል ተገፏል ፅልመት
ሰአሊ ለነ እያልኩኝ ከፊትሽ ቆሜአለሁ
በሰአታት በማሕሌት ዘምርልሻለሁ/2/
አዝ...

ሰላም ልበልሽ (ዘማሪ ዘውዱ)

ሰላም ልበልሽ/2/
አደግድጌ ቆሜ አገልጋይ ልጅሽ
ሰላም ለኪ ምልዕተ ውዳሴ ሰላም ለኪ ትልሻለች ነፍሴ/2/
ባንቺ ስለጠፋ የሰው ልጆች መርገም ሰላም ልበልሽ
ወደ ገነት ገባ ከነ ልጆቹ አዳም ሰላም ልበልሽ
መንገዱን አገኘ በራ ጨለማችን ሰላም ልበልሽ
ንዕድ ክብርት ነሽ ድንግል እናታችን ሰላም ልበልሽ
አዝ...
ከሞት ወደ ህይወት የተሻገርንብሽ ሰላም ልበልሽ
የጽድቅ መሰላል ዓለም የዳነብሽ ሰላም ልበልሽ
በልጅሽ መወለድ ዘመን ተከፈለ ሰላም ልበልሽ
ትውልድ ዘመረልሽ ብጽዕት እያለ ሰላም ልበልሽ
አዝ...
ለክህነታቸው ማዕረግ ስለሆንሽ ሰላም ልበልሽ
አባቶች ካህናት ከልብ ወደዱሽ ሰላም ልበልሽ
ለከፋበት ዓለም አዛኝ በመሆንሽ ሰላም ልበልሽ
ኃጥአን ይመጣሉ ሊማልዱ ፊትሽ ሰላም ልበልሽ
አዝ...
በገና ደርድሬ እኔ እንደ አባቶቼ ሰላም ልበልሽ
ክብርሽን ልመስክር ልናገር ተግቼ ሰላም ልበልሽ
ሰማያዊው ንጉስ ንፅህናሽን ወዶ ሰላም ልበልሽ
አለሙን አዳነው ከአንቺ ዘንድ ተወልዶ ሰላም ልበልሽ
አዝ...

አስተርዮ ኮነ (ዘማሪ ዘውዱ)

አስተርዮ ኮነ/4/

ሲጠበቅ የኖረው በትንቢት በተስፋ
መርገምን የሚሽር ሞትን የሚያጠፋ
ተገልጦ አየነው በበረት ተኝቶ
የእግዚአብሔር ልጅ ሳለ ግርግም ተጠግቶ
ተገልጦ አየነው በበረት ተኝቶ
የእግዚአብሔር ልጅ ሳለ ግርግም ተጠግቶ
አዝ...
በሔኖን በረሃ በዚያ ምድረበዳ
ምስጢረ ሥላሴ ለዓለም ሲረዳ
አብ በሰማይ ሆኖ ወልድ በዮርዳኖስ
መንፈስ ቅዱስ ሲወርድ አየ ዮሐንስ
አብ በሰማይ ሆኖ ወልድ በዮርዳኖስ
መንፈስ ቅዱስ ሲወርድ አየ ዮሐንስ

አዝ...
ከነ ጴጥሮስ ጋራ በታቦር ተራራ
ኢየሱስ ክርስቶስ በክብር ሲበራ
ልብሱ ተለወጠ ልክ እንደ በረድ
ለነ ሙሴም ታየ ወልደ አብ ዋሕድ
ልብሱ ተለወጠ ልክ እንደ በረድ
ለነ ሙሴም ታየ ወልደ አብ ዋሕድ
አዝ...
ተሰውሮ ነበር በዘመነ ፍዳ
ምስጢረ ሥላሴ ለዓለም ሳይረዳ
አንድ ልጁ መጥቶ ሁሉን ተረከልን
አስተርዮ ኮነ ክብሩን ገለጠልን
አንድ ልጁ መጥቶ ሁሉን ተረከልን
አስተርዮ ኮነ ክብሩን ገለጠልን
አዝ...

የንስሐ መዝሙር
ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ

ኑ እንቅረብ (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)

ቅኝት - ዋኔን
1-123-4 3-42 355 5
1-123-4 3-42 222 2
211 513-2 2 211 513 3 3
211 513 3-42 222 2

211 513 3-42 222 2(በበገና)

1-1-1-321 1 4-4-4 515 5
3-3-3 242-4 234222 2
ኑ እንቅረብ መጠራት ሳይመጣ /2/
ሥጋውን እንብላ ደሙንም እንጠጣ
በበገና...
የቀራንዮ በግ የአምላክ ሥጋው
ተሰውቶልናል እንመገበው
እድፋን ኃጢአታችንን በንስሓ አንፅተን
እንቀበል አምነን በልጅነታችን
መቅረብ ወደ ጌታ በእምነት የሚገባው
በስተርጅና አይደለም በወጣትነት ነው
አዝ...
ጨረቃና ፀሐይ ደም የለበሱለት
ከዋክብት ከሰማይ የተነጠፉለት
ይኸው ተፈተተ እሳተ መለኮት
አዝ...
ቅድስት እናታችን ቤተክርስቲያን
ትጋብዘናለች ሥጋና ደሙን
የአማኑኤል ሥጋ ይኸው ተዘጋጀ
ከግብዣው ተጠራን አዋጁም ታወጀ
አዝ...
መጥቁ ተደወለ እንቅረብ በእልልታ
በኋላ አይረባንም ዋይታና ጭጭታ
ይህችን እድል ፈጥነን እንጠቀምባት
ዓለምን አልያዝንም ብዙ ልንቆይባት
አዝ...
ካሁኑ ቅረቡ ታውጇል አዋጁ
የይለፍ ደብዳቤ ስንቅን አዘጋጁ
ይህ ዓለም ጠፊ ነው በሀብት አትመኩ
ብሏል አምላካችን ተስፋችሁን እንኩ
አዝ...

ድንግል (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)

ቅኝት -

ድንግል /2/ ወላዲተ ቃል /2/
አሚሚትሽ በጥር ነሐሴ መቃብር ድንግል
ያንቺ ለብቻ ነው ትንሳኤሽ ሲነገር "
ሥጋሽ በምድር ላይ የታለ እንደፍጡር "
ዐርጓል ወደ ሰማይ ከክርስቶስ መንበር "
አዝ...
ሥጋሽን ሲያሳርጉ መላእክተ ሰማይ ድንግል
ቶማስ በደመና ሲመጣ መንገድ ላይ "
መግነዝ ተረከበ ለሐዋርያት ሊያሳይ "
አዝ...
ትንሳኤሽን ሽተው ግራ ሲገባቸው ድንግል
ሐዋርያት ፆመው ተገለጽሽላቸው "
ተቀብራ አልቀረችም በምድር ከደጇ "
ወደ ላይ ዐረገች እሷም እንደልጇ "
አዝ...
ለማየት ሲጓጉ የድንግልን ትንሳኤ ድንግል
እርገቷን አወቁ በብዙ ሱባኤ "
እኛም እንፀልይ በራችንን እንዝጋ "
ከወላዲተ አምላክ እንድናገኝ ዋጋ "
አዝ...

የዓለም መድኃኒት (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)

ቅኝት -

የዓለም መድኃኒት የተወለደብሽ
አንቺ ቤተልሔም የተቀደስሽ ነሽ
የአማልክት አምላክ ንጉሠ ነገሥት
ኃያላን በሙሉ የሚሰግዱለት
በጨርቅ ተጠቅልሎ ተኛ ከበረት
አዝ...
አዋቂዎች ሁሉ በቅን አሳባቸው
ወዳንቺ ተጓዙ ኮከብ ሲመራቸው /2/
አዝ...
ለተከታይ ትውልድ ምሳሌ በመሆን
ሰግደው ገበሩለት ወርቅ እጣን ከርቤን/2/
አዝ...
የሚያድለው ጌታ እውቀት ለሕፃናት
የሚመሰገነው በአፈ መላእክት
ከእንስሳት ጋራ አደረ ከበረት
አዝ...
በስጋ ተገልጾ ረቂቅ ሚስጥሩ
ሰውና መላእክት በአንድ ላይ ዘመሩ/2/
አዝ...

እወርዳለሁ ቆላ (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)

ቅኝት -

እወርዳለሁ ቆላ እወጣለሁ ደጋ/2/
የጮንቅ አማላጄን ድንግልን ፍለጋ
ድንግልን/3/ ፍለጋ
አቀብ ቁልቁለቱን አይችልም ጉልበቴ /2/
ምርኩዜ ከሌለች ድንግል እመቤቴ
እመቤቴ /2/ ድንግል እመቤቴ
አንቺ የኖህ መርከብ የህይወት መገኛ/2/
መንግስተ ሰማያት መግቢያችን ነሽ ለኛ
መግቢያችን ነሽ /3/ ለኛ
እወርዳለሁ ቆላ እወጣለሁ ደጋ
የጮንቅ አማላጄን ድንግልን ፍለጋ
ድንግልን/3/ ፍለጋ
አልጫውን ዓለም የሚያጣፍው /2/
ስምሽ ማርያም ነው የዓለም ሁሉ ጨው
ማርያም ነው /2/ የዓለም ሁሉ ጨው
እንደበደላችን እንዳይሆን ቅጣቱ /2/
አማልጂን ከልጅሽ ድንግል አዛኝቱ
አዛኝቱ /2/ ድንግል አዛኚቱ
እወርዳለሁ ቆላ እወጣለሁ ደጋ
የጮንቅ አማላጄን ድንግልን ፍለጋ
ድንግልን/3/ ፍለጋ
የእናት አማላጅ የልጅ ተማላጅ /2/
ፊት አያስመልስም ይሁን ይሁን እንጅ
ይሁን ይሁን/3/ አንጅ

ይህ ቁርባን(ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)

ይህ ቁርባን ክቡር ነው ፍፁም ሰማያዊ /2/
እንዳይመስለን ተራ አይደለም ምድራዊ /2/
ዋ ምን አፍ ነው የሚቀበለው
ዋ ምን ጥርስ ነው የሚያላምጠው
ዋ ምን ሆድ ነው የሚሸከመው
ነበልባል ያለበት የሚያቃጥል ነው
በንጽህና ሆኖ ላልተቀበለው
የሚያፍገመግም የሚጐዳ ነው
አምላካችን ሆይ አንተ ይቅር ባይ
እንደ ቸርነትህ በደልን አትይ /2/
አሜን አሜን ብለን ተቀብለናል
በድፍረትም ሣይሆን በፍርሃት ቀርበናል /2/
አዝ...
ማክበር ይገባናል በንጽህና ሆነን
ደፍረን አናቅለው እንዳያቃጥለን /2/
እንደምታዩትም ይህ ቁርባን ፈራጅ ነው
እንደሌላው ሳይሆን የተቀደሰ ነው /2/
ሱራፌል ኪሩቤል ፀወርተ መንበር
ለመያዝ ያልቻሉት ፈርተውት በክብር /2/
እኛ ተመገብነው አገኘን ድኅነት
ለነፍስ ለሥጋችን ሆነልን ህይወት /2/
አዝ...

አልፋና ኦሜጋ(ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)

ቅኝት -

አልፋና ኦሜጋ ፈጣሪ የሆንክ
በከሀዲዎች እጅ ተይዘህ ቀረብክ /2/
ተገፋህ ተደፋህ በጥፊ ተመታህ
እየደበደቡህ ክርስቶስ ሆይ አሉህ
ጽድቅን ስለሰራህ በወንጀል ከሰሱህ
ለአዳም ቤዛ ብለህ ብዙ ተንገላታህ
አዝ...
ቅዱሳን እጆችህ የፊጥኝ ተስረው
እንደበግ ተጎተትክ ልትምራቸው
የትም ቦታ ያለህ ሁሉን የምታውቅ
ፊትህን ሸፈኑህ ለመመጻደቅ
አዝ...
በአውደ ምኩናን ከጲላጦስ ዘንድ
አሳልፈው ሰጡህ አጋልጠው ለፍርድ
ከሃና ቀያፋ ከመሳፍንቱ ደጅ
ከነሄሮድስ ዘንድ አቀረቡህ በአዋጅ
አዝ...
ግርፋት ህማሙ አልበቃ ብሎህ
በመስቀል ላይ ልትውል ተፈረደብህ
የሰላም ባለቤት ደረትህ ተወጋ
ሊያያዝ በችንካር እጅህ ተዘረጋ
አዝ...

ድንግል ሆይ ስለአንቺ(ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)

ቅኝት -

ድንግል ሆይ ስለአንቺ ነውና መሐሪ
አማልጂኝ ከአንድ ልጅሽ ከፈጣሪ
ስሙን እንዳልጠራ አንደበትም የለኝ
ፊቱንም እንዳላይ ስራዬ አስቸገረኝ
አዝ ...
ታውቆኛል ጥፋቴ ብዙ እንደበደልኩኝ
ትዕዛዙን እንደሻርኩ ሕጉን እንደጣስኩኝ
አዝ...
በፊቱ እንዳላፍር የተጠራሁ ለታ
እለምነዋለሁ ከአሁኑ ይቅርታ
አዝ...
አንተ ክቡር መልአክ ልደቱን አብሣሪ
አማልደኝ ከጌታዬ ከፈጣሪ
አዝ ...
ጻድቃን ሰማዕታት እናንተ ሁላችሁ
አማልዱኝ ከአምላኬ ከአምላካችሁ
አዝ...

እኔስ በምግባሬ (ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)

ቅኝት -

እኔስ በምግባሬ ደካማ ሆኛለሁ/2/
እዘኝልኝ ድንግል እለምንሻለሁ/2/
ያንን የእሳት ባህር እንዳላይ አደራ
ድረሺልኝ ድንግል ስምሽን ስጠራ
ስምሽን ስጠራ
አዝ...
የዳዊት መሠንቆ የኤልያስ መና
የናሆም መድኃኒት ንኢ በደመና
ንኢ በደመና
አዝ...
አንቺ ነሽ ጉልበቴ በደከመኝ ጊዜ
የልቤ መጽናኛ ረዳት ምርኩዜ
ረዳት ምርኩዜ
አዝ...
አፈሳለሁ እንባ በጣም ተጨንቄ
እማፀንሻለሁ በደሌን አውቄ
በደሌን አውቄ
አዝ...

እንደቸርነትህ(ሊቀ መዘምራን ኪነጥበብ)

ቅኝት -

እንደ ቸርነትህ አቤቱ ማረኝ አቤቱ ማረኝ
እንደ ምህረትህም ይቅርታ ስጠኝ ይቅርታ ስጠኝ
ከኃጢአቴም አንፃኝ ከክፉ በደሌ ከክፉ በደሌ
ለዚያች ክፉ ኃጢአት እንዳልሆናት ሎሌ እንዳልሆናት ሎሌ
እኔም አበሳዬን በደሌን ሳውቀው በደሌን ሳውቀው
ከቶም የሚያድነኝ ቸርነትህ ነው ቸርነትህ ነው
አንተን ብቻ በደልኩ ክፉም አደረግሁ ክፉም አደረግሁ
አሁን ይቅር በለኝ ከፊትህ ወደቅሁ ከፊትህ ወደቅሁ
ከፊትህ ወድቄ ስለምን አንተን ስለምን አንተን
መውደቄን ተመልከት አምላከ ብርሃን አምላከ ብርሃን
አሁን ትባርክ ዘንድ ማኅበራችንን ጸሎታችንን
ጌታ ሆይ ላክልን ቅዱስ ሚካኤልን ቅዱስ ገብርኤልን
አሁን ትጠብቅ ዘንድ ሀገራችንን ሀይማኖታችንን
ጌታ ሆይ ላክልን መንፈስ ቅዱስን ድንግል ማርያምን

ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ

ኖኅተ አንቲ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

ቅኝት

ኖኅተ አንቲ ለፀሀየ ጽድቅ ለፀሀየ ጽድቅ ምሥራቁ /2/
እንተ ባቲ ሰረቀ ለብርሃነ ዓለም ጽድቁ /2/
የተዘጋችው በር የምሥራቁ ደጃፍ
የታተመች ገነት የአዲስ ዘመን ምዕራፍ
ሌቱ ያለፈብሽ የተስፋ ማለዳ
በልጅሽ ተፋቀ መርገም እና ፍዳ /2/
አዝ...
ጨለማን የሻረ የጽድቅ ጐህ ፋና
የአዲስ ታሪክ ቀለም የዕረፍታችን ዜና
ሥጋሽ ሰውነቱ ነፍስሽ ነፍሱ ሆነ
ድል አድራጊው ልጅሽ ጠላትን በተነ /2/
አዝ...
የእምነት ምንጭ ነሽ የደስታ መፍሰሻ
የኃያሉ ንጉሥ መንበር መናገሻ
ንጽህና ተውበሽ በቀኙ ስትቆሚ
ባዶ የሚሞላ ድምፅሽን አሰሚ /2/
አዝ...
ማዘን መጨነቁ በምድር ሲበዛ
ከልጅሽ አሳስበሽ አድርጊልን ጤዛ
የተስፋ ወጋገን ምህረትን አሳይን
በብርሃንሽ ፀዳል ለምሥጋና አብቂን /2/
አዝ...

በባዕድ ሀገር (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

ቅኝት -

በባዕድ ሀገር አመልክሀለሁ
ፊቴን በምሥራቅ እመልሳለሁ
በምኞት ቤቴም አስብሃለሁ
ምትክ የለህም ይህን አውቃለሁ
ጠላት ቢነሳ በነፍሴ ላይ
የምታድነኝ ነህ በሰማይ
የአንበሳ ጉድጓድ ቢሆንም ቤቴ
ታዳጊዬ ነህ ቸር መድኃኒቴ
አዝ...
በምድር ጣኦታት አትረክስም ነፍሴ
አንተ አምላኬ ነህ ይሄ ነው መልሴ
የመርገም ሰዎች ቢነሱብኝ
አምናለሁ ባንተ በማትተወኝ
አዝ...
ማዳን የእግዚአብሔር ያንተ ብቻ ነው
ከእጅህ ሊነጥቀኝ የሚችል ማነው
አንበሳው ትራስ ምኞት ሆኖኛል
ሰላም አምሽቼ ያው ነግቶልኛል
አዝ...
ለሞት ብባልም አለሁ በሕይወት
በእርሱ በአምላኬ በእርሱ ቸርነት
አንተን ያመነ ማነው ያፈረ
ስምህ ቅዱስ ነው የተከበረ
አዝ...

ቢፈልግባትም (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

ቅኝት -

ቢፈልግባትም መልካሙ ገበሬ
አልተገኝባትም ከበለሷ ፍሬ
አዝ...
ለስልሶላት ነበር ሃይማኖት መሬቱ
ተቀጥሮላት ነበር አጥር ሥርዓቱ
ተለቅሞላት ነበር ድንጋይ ፈተናዋ
ፍሬ ግን ታጣባት በመጨረሻዋ
አዝ...

ፍሬ የሌለባት ቅጠል ስለሆነች
ተካይዋን በምግባር ስላላስደሰተች
መልካሙ ገበሬ ሊቆርጣት ተነሳ
ሌሎች እንዳይጠፉ በርሷ የተነሳ
አዝ...
ለንስሐ ሚሆን ዕድሜ እንዲሰጣት
ጠባቂ መልአክዋ ተማፅነላት
ምክርና ተግሳፅ ይጨመርላት
ታፈራ ከሆነ ለዓመት እንያት
አዝ...
ልመናውን ሰምቶ ጌታውም ፈቀደ
ጥቂት እድሜ ሊሰጥ ሊታገስ ወደደ
ዳግመኛ ሲመጣ ፍሬ ካላፈራች
ተቆርጣ ወደ እቶን እሳት ትጣላለች
አዝ...

ከካራን ስወጣ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

ቅኝት -

ከካራን ስወጣ ወደ አዲሱ መንገድ
አላውቅም ነበር ወዴት እንደምሄድ
ያንተ ቃል ነውና በማመን ወጣሁኝ
በረከት አግኝቼ ዘሬን አበዛሁኝ
ሲሰማኝ ምሬቱ የቀድሞ ኑሮዬ
ረገምኩ ታሪኬን ጨለመኝ ኋላዬ
ታራ ያስተማረኝ ተስፋ ቢስ ሕይወት ነው
ስትጠራኝ ያየሁት የነገ ክብሬን ነው
አዝ...
ከቶ ማን ሆኜ ነው እንዲህ ያከበርከኝ
ከአሕዛብ ለይተህ ከፍ ከፍ ያረከኝ
አብርሃም ሆይ አልከኝ የወደድከኝ አምላክ
ልግዛ ላምልክህ ለክብርህ ልንበርከክ
አዝ...
ህዝብህን ታደገው በረከት አይጥፋ
መሆንክን ይወቀው የዘለዓለም ተስፋ
አለማመን ይራቅ ጥርጥር ይወገድ
ልጆችህ ይጓዙ በአንዲቱ መንገድ
አዝ...

ሕሙም ስለአዳነ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

ሕሙም ስላዳነ በእጆቹ ዳስሶ
ሙትን ስላስነሳ በእጆቹ ዳስሶ
ይህ በደል ሆኖበት ለአምላክ ኖላዊ ሔር
በእጸ መስቀሉ ላይ ዘርግቶ በፍቅር
ቀኝ እጁን በሳዶር ግራውን በአላዶር
ተቸነከረልን ጌታ በሁለት ችንካር
አምንስቲቲ ሙኬርያ አንቲ ፋሲልያሱ
ቤተ ቤቅደስ ምኩራብ በተመላለሱ
ባህር ላይ በሄዱ ልክ እንደ በየብሱ
ለአምላክ ቤዛ ኩሉ ይህ ወንጀል ሆኖበት
በዕጸ መስቀሉ ላይ ተላልፎ ለመሞት
ሁለቱን በአንድ ላይ እግሮቹን በዳናት
ተቸነከረልን አምላክ የእኛ ህይወት
አምንስቲቲ ሙአግያ አንቲ ፋሲልያሱ
በልቡ አስቦ ድህነት የሚያመጣ
ከበጎ ልቦናው በጎ የሚወጣ
ይህ ወንጀል ሆኖበት ለአምላክ መድኅን ዓለም
በእጸ መስቀሉ ላይ ተዘርግቶ ለዓለም
ልቡን በአዴራ ደረቱን በሮዳስ
ተቸነከረልን ወልደ አምላክ ክርስቶስ
አምንስቲቲ ሙዳሱጣ አንቲ ፋሲልያሱ

ልቦና የሚመስጥ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

ቅኝት -

ልቦና የሚመስጥ አጥንት አለምላሚ
ምድራዊ አይደለም ምንጩ ሰማያዊ
ሄደህ የሰማኸው ከመላእክት ከተማ
ምንኛ ጥዑም ነው ያሬድ የአንተ ዜማ
ከትንሽ አንስቶ እስከ ግዙፎቹ
አምላክ እንደሰራው በስነ-ፍጥረቱ
ያልነገርከው የለም በዜማ ድርሰትህ
ከመንፈስ ቅዱስ ቃል ነውና እውቀትህ
አዝ...
ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ የሆነውን
መገረፍ መሰቀል መሞት መነሳቱን
እናስታውሰው ዘንድ አመልክተህ ጽፈህ
አበረከትክልን ከዜማው አስማምተህ
አዝ...
ለፀሐይ እናቱ ለብርሃን መውጫ
ለድንግል ማርያም ውዳሴ እንዲገባ
በምልዐት በስፋት በምሥጢር በአንክሮ
ያቀረብከው ዜማ ዛሬም አለ ከብሮ
አዝ...
ጸጋ በረከትህ ይደር በሁላችን
ሊቀ ተዋህዶ ያሬድ አባታችን
ጠፍተው እንዳንባክን የአንተን ዜማ አዋቂ
አምላክ ያስነሳልን ሊቃውንት ጠባቂ
አዝ...

ያቺን የተስፋ ምድር (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

ቅኝት -

ያቺን የተስፋ ምድር እናፍቃታለሁ
ኢየሩሳሌምን ሁሌም እመኛለሁ
በመሻቴ ብቻ እንዳይሆን አውቃለሁ
ሕግና ፍርድህን ከልቤ ጽፌያለሁ
መንገዷ ልዩ ነው ለሥጋ አይመችም
ያለብዙ ድካም በከንቱ አይገኝም
በሰፊው ያላችሁ ከዚህ ተመለሱ
የአባቶቼን ሀገር ከኔ ጋር ውረሱ ከኔ ጋር ውረሱ
አዝ...
የይሁዳ መንገድ የዴማስ ጎዳና
ከቤት አያደርስም አያዘልቅምና
ጴጥሮስ ዮሐንስን አሳዩኝ በልና
ወንድሜ ተመለስ ከኢየሩሳሌም ና ከኢየሩሳሌም ና
አዝ...

በግብፅ የምትኖሩ ወዲህ ተሰብሰቡ
በይሁዳ ያላችሁ ወደ ጽዮን ግቡ
ከባቢሎን ሽሹ መዝገቧንም ዝጉ
ኢየሩሳሌምን መጠጊያ አድርጉ መጠጊያ አድርጉ
አዝ...

ወንጌሉን ያመኑ (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

ይትበሃሉን እና ቃሉን አነበብነው
ሐተታውን እና ምሥጢሩን ተማርነው
በቅዱሳን ሕይወት ወንጌሉን አየነው
በቅዱሳን ሕይወት ወንጌሉን አየነው
አዝ
አጋንንትን ገዝተው በእሳት ውስጥ ሲያልፉ
ሞትን በሞታቸው ደግመው ሲያሸንፉ
እባቡን እረግጠው አንበሳውን ሲያዙ
ደመናውን ጠቅሰው በአየር ላይ ሲጓዙ 2x
አዝ
ወንጌል ትምህርት ብቻ አይደለችም ብለው
የተነገረውን በሕይወት ለውጠው
አምላክ ዘበጸጋ ሆነው አየናቸው
ወንጌሉን በገቢር ተማርን ከገድላቸው 2x
አዝ
የወንጌሉ ቅኔ ገድሉ ይፈታዋል
ፊደሉን ንባቡን ይተረጉመዋል
ይሆናል ተብሎ የተማርነውን
ቅዱሳን በገድል ሆነው አሳዩን 2x
አዝ
ፍልስፍና አይደለም የወንጌል ትምህርቱ
ዕውቀት ብቻ አይደለም ሕጉና ትንቢቱ
በሕይወት የሚታይ በእውነት የሚኖር
መሆኑን አሳዩን ቅዱሳን በግብር 2x

የመድኃኒት እናት (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

ቅኝት - ዋኔን

አዝማች
15 42 245-1 13 24-4 23 15-5 54 245-5
15 42 245-1 13 24-4 23 15-1 13 42 2
መሸጋገሪያ
23-1 454 23-3 231 454-42
ዘማች
15 4 51 44 33-3 33 15 13 24 45-5
15 4 51 44 33-3 33 15 13 24 242-2
22 31 32 4 45 13 3 35-4 33 23-3
22 31 32 4 45 13 3 35-4 33 22-2

የመድኃኒት እናት ሕመምተኛ ልጅሽ
ምህረትን ፍለጋ ቆሜአለሁ ከደጅሽ
ጸሎት ልመናሽን ታምኜአለሁና
ከቤትሽ መልሽኝ ዳግም እንደገና
የደካሞች ብርታት የምስኪናን ተስፋ
ለዓለም አልተውሽኝም በከንቱ እንድጠፋ
የህይወቴ ጥበብ እረፍቴ ሠላሜ
አማልጂኝ እላለሁ ከመቅደስሽ ቆሜ
አዝ...
በፍቅርሽ ብርሃን ነው ልጅሽን ያየሁት
ባዶ ማድጋዬን ጋኔን የሞላሁት
አልጫ ኑሮዬ ዛሬ ተለውጧል
በደልና ኃጢአቴ በምልጃሽ ተፍቋል
አዝ...
ብርሃን ወጥቶለታል ጨለማ ሕይወቴ
ዛሬም ጥላ ሁኚኝ እናቴ እመቤቴ
ፍቅር ውለታሽን ዘወትር አውጃለሁ
ከአእላፍ መካከል እቀኝልሻለሁ
አዝ...

በረከት ረድኤትሽ ....
ምስራቅ ቤተልሔም ...
መናን ያቀረብሽው...
ድንግል ዘለዓለም

በረከት ረድኤትሽ ይኑር ከእኔ ጋራ
ምሥራቅ ቤተልሔም የሲና ተራራ
መናን ያቀረብሽው ለተራበው ዓለም
ድንግል ዘለዓለም የሚመስልሽ የለም
አዝ...

በደለኞች ሳለን (ዘማሪ ዲ.ዳዊት ፋንታዬ)

በደለኞች ሳለን ምህረትን ሰጠኸን
ስለዚህ ስምህን እናወድሳለን
ዘለዓለማዊ ነህ አልፋና ኦሜጋ
ስምህን እንጠራለን በሰጠኸን ጸጋ
ለከ ሃይል ክብር ወስብሐት
ንዜምር ለከ አምላከ አማልክት (2x)
ሰማያትን ከፍተህ ብትወርድልን ምነው
አድነን ታደገን ብለን ያነባነው
የምህረት አባት ነህ ዛሬ አቅንተኸናል
ሊነገር የማይችል ክብርን ሰጥተኸናል
ቅዱስ አንተ ገባሬ ዓለማት
ንሴብሐከ አምላከ አማልክት (2x)
የጠፋውን ፈለግህ በመስቀል አዳንከው
ለምሥጋና በቃ በክብር ከለልከው
ቤዛና ተስፋችን መድኃኔዓለም
በምድር በሰማይ ሚመስልህ የለም
ለከ ሃይል ክብር ወስብሐት
እግዚአብሔር አምላከ አማልክት (2x)
በእሳትና ውሃ ረድተህ አሳለፍከን
ከድካም አድነህ እረፍትን ሰጠኸን
በመከራችን ቀን ረድተኸናልና
ከፊትህ ቆመናል ዛሬም ለምሥጋና
ለከ ሃይል ክብር ወስብሐት
ንዜምር ለከ አምላከ አማልክት (2x)

ዘማሪት ማርታ

ድንግል የዚያን ጊዜ(ዘማሪት ማርታ)

ቅኝት -

ድንግል የዚያን ጊዜ የዚያን ጊዜ ሀዘንሽ በረታ /2/
በመስቀል ላይ ሆኖ ልጅሽ ሲንገላታ /2/

የግፍ ግፍ ደርሶበት የዚያን ጊዜ ተጠማሁ ሲልሽ
ለውሻ ያጠጣሽ በወርቅ ጫማሽ /2/
አዝ...
ሴቶች ሲያባርሩት የዚያን ጊዜ እራርቶ ሆድሽ
ለፍጡር በማዘን ውሃ ያጠጣሽ /2/
አዝ...
ተጠማሁ እያለ የዚያን ጊዜ ሲናገር ልጅሽ
ታዲያ እንደምን ቻለ[redacted] አንጀትሽ /2/
አዝ...
አዛኝ
እንደዚያ ስታለቅሽ የዚያን ጊዜ ሀዘን ሲውጥሽ
እነማን ነበሩ ያስተዛዘኑሽ /2/
አዝ...
ስታለቅሽ በማየት የዚያን ጊዜ እራርቶ ልጅሽ
ዮሐንስን አድናኝ እንደ ልጅ ሰጠሽ /2/
አዝ...

ከፈጣሪ በታች(ዘማሪት ማርታ)

ቅኝት -

ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ /2/
ማን አለ እንደአንቺ ድንግል ንጹህ በዓለም ላይ /2/
ኦ ድንግል ማርያም ዘለዓለም መኩሪያዬ ነሽ መመኪያዬ /2/
አምላክ ለማደሪያው መርጦ ያዘጋጀሽ /2/
ጽዮን የተባለች ሀገር ድንግል ሆይ አንቺው ነሽ /2/
ኦ ድንግል ማርያም ዘለዓለም መኩሪያዬ ነሽ መመኪያዬ /2/
በሀሳብሽ ድንግል ድንግል በሥጋሽ /2/
ከፍጥረታት ሁሉ ላንቺ ምሳሌም የለሽ
ኦ ድንግል ማርያም ዘለዓለም መኩሪያዬ ነሽ መመኪያዬ /2/
ፍቅሩ ለዘለዓለም የማይጠገበው /2/
ከስም ሁሉ በላይ ጣፋጭ ድንግል ያንቺ ስም ነው /2/
ኦ ድንግል ማርያም ዘለዓለም መኩሪያዬ ነሽ መመኪያዬ /2/
በእዝራ መሠንቆ በዳዊት በገና /2/
ይገባሻል ላንቺ ድንግል ሁልጊዜ ምሥጋና
ኦ ድንግል ማርያም ዘለዓለም መኩሪያዬ ነሽ መመኪያዬ /2/
እስኪ ልያዝና ደጋፊ ምርኩዜን
እስኪ ልያዝና የረሃብ መድኃኒቴን
ወደ አምላኬ ቤት ልሂድ ልቀጥል ጉዞዬን /2/
ኦ ድንግል ማርያም ዘለዓለም መኩሪያዬ ነሽ መመኪያዬ /2/
ለፍርድ ስጠራ በደለኛዋ እኔ
ለፍርድ ስጠራ በደለኛው እኔ
የእኔ መማጸኛ ድንግል ቁሚልኝ ከጐኔ /2/
ኦ ድንግል ማርያም ዘለዓለም መኩሪያዬ ነሽ መመኪያዬ /3/
ዘለዓለም መኩሪያዬ ነሽ መመኪያዬ

ጥንታዊቷ (ዘማሪት ማርታ)

ቅኝት -

ጥንታዊቷ መጀመሪያይቷ ጥንታዊቷ ቀጥተኛይቷ
የነቢያት የሐዋርያት የጻድቃን የሰማዕታት
እምነታችን እንከን የሌላት
ተዋሕዶ ነሽ እምነቲቱ እንከን አልባይቱ
የተስፋው ቃል ኪዳን ዘመኑ ሲፈጸም
አምኖ የዳነብሽ ቀዳማዊው አዳም
እምነቲቷ እንከን አልባይቷ
በሊቃውንቶችሽ ችሎታና ሞያ
ድልን ተጎናጸፍሽ በቁስጥንጥንያ
እምነታችን እንከን የሌላት
እንደ ዲዮስቆሮስ እንደ አትናቴዎስ
ደጋግመሽ ውለጂ እናት ኦርቶዶክስ
እምነቲቷ እንከን አልባይቷ
ኃይልና ጥበቡን አምላክ ያሳየብሽ
የማዳን ሥልጣኑን በዓለም ያወጀብሽ
እምነቲቷ እንከን አልባይቷ
ጥንታዊቷ መጀመሪያይቷ ጥንታዊቷ ቀጥተኛይቷ
የነቢያት የሐዋርያት የጻድቃን የሰማዕታት
እምነታችን እንከን የሌላት
ተዋሕዶ ነሽ እምነቲቷ እንከን አልባይቷ
አዝ...
ጉባዔ ኒቂያ ጉባዔ ኤፌሶን
አወጁ በዓለም ላይ ተዋህዶ እምነትን
እምነቲቷ እንከን አልባይቷ
መጽሐፉ እንደሚለው ሀይማኖት አንዲት ናት
ዋጋን የምታሰጥ የቅዱሳን እናት
እምነቲቷ እንከን አልባይቷ
ጥንታዊቷ መጀመሪያይቷ ጥንታዊቷ ቀጥተኛይቷ
የነቢያት የሐዋርያት የጻድቃን የሰማዕታት
እምነታችን እንከን የሌላት
ተዋሕዶ ነሽ እምነቲቱ እንከን አልባይቱ
አዝ...

ይፍቱኝ አባቴ(ዘማሪት ማርታ)

ቅኝት -

የዓለም ወንጀለኛ በደለኛ ነኝ
ይፍቱኝ መምህሬ ይፍቱኝ ይባርኩኝ
ይፍቱኝ አባቴ ይፍቱኝ ይባርኩኝ
እናንተ ደካሞች ሸክም የከበዳችሁ
ኑ ብሎናል እና እንዳሳርፋችሁ እንዳሳርፋችሁ
አምላኬ ይቅር ባይ መሆኑን አውቃለሁ
አበስኩ ገበርኩ ብዬ ቀርቤአለሁ ብዬ ቀርቤአለሁ
አዝ...
ጴጥሮስ አስተምሯል ስለ ንስሐማ
ዮሐንስም ሰብኳል ስለ ንስሐማ
ልብ ያለው ልብ ያድርግ ጆሮ ያለው ይስማ ጆሮ ያለው ይስማ
ያለፈው ጥፋቴ በደሌ እንዲፋቅ
አምላኬን በእንባ ይቅርታ ልጠይቅ ይቅርታ ልጠይቅ
አዝ...
ስለ በደሌና ስለ ኃጢአቴ
ንስሐዬን ይስጡኝ የንስሐ አባቴ የንስሐ አባቴ
የማሰር የመፍታት ሥልጣን በሰጠዎ
ከኃጢአት ማሰሪያ ይፍቱኝ በአምላክዎ ይፍቱኝ በአምላክዎ
አዝ...
በምድር ያሰሩት ታስሯል በሰማይ
በምድር የፈቱት ተፈቷል በሰማይ ተፈቷል በሰማይ
አዝ...

ምስጋና ጀመረ(ዘማሪት ማርታ)

ቅኝት -

ምስጋና ጀመረ ብሎ ሃሌ ሉያ
ማኅሌታይ ያሬድ ዘኢትዮጵያ
ምስጋና ጀመረ ብሎ ሃሌ ሉያ
ይበል ይበል ኧኸ ይበል ሃሌ ሉያ
ጥዑመ ልሳን ያሬድ /4/ ዘኢትዮጵያ
ብሉይን ከሐዲስ ሐዲሱን ከብሉይ
አስተባብሮ ቃኘው ያሬድ ማኅሌታይ
ምሥጢር ተገልፆለት ከምድር እስከ ሰማይ
ይበል ይበል ኧኸ ይበል ሃሌ ሉያ
ጥዑመ ልሳን ያሬድ /4/ ዘኢትዮጵያ

በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ምሥጢር እያስማማ
ምስጋና ጀመረ በጽዮን ከተማ
ለቅድስት ሥላሴ በሦስት ዓይነት ዜማ
ይበል ይበል...
በወርቅ ጽናጽል በብር ከበሮ
ዜማው ሲንቆረቆር በሰው ልጆች ጆሮ
የያሬድ ዝማሬ ያድሳል አእምሮ
ይበል ይበል...
ተዋህዶ አቅርቢ ለአምላክ ምስጋና
በዕዝራ መሠንቆ በዳዊት በገና
ዜማውን ከያሬድ ተምረናልና
ተዋህዶ አቅርቢ ለአምላክ ምስጋና
በዕዝራ መሠንቆ በዳዊት በገና
ዜማውን ከያሬድ ተምረናልና
ይበል ይበል...

እንዲህ አለው ጴጥሮስ(ዘማሪት ማርታ)

ቅኝት -

እንዲህ አለው ጴጥሮስ ኢየሱስን
ምሥጢር ገሃድ ሲሆን በዚያ በተራራ
ባንድ ላይ እንኑር ሦስት ዳስ እንስራ
አንዱን ለአንተ አንዱንም ለሙሴ አንዱን ለኤልያስ
ተለወጠ ገጹ ከመ ጽጌረዳ
ወርዶ ከለላቸው ደመና ጸአዳ
አዝ...
ከሰማይ ቃል መጣ እንደዚህ የሚል
የምወደው ልጄ እርሱን ስሙት ሲል
አዝ .....
ኤልያስም ሄደ በሰረገላው
ሙሴም ከመቃብር ወደ መኖሪያው
አዝ...
ስላስደነቃቸው ግሩም ተዓምራቱ
ይህን ምሥጢር አይተው ተሰነባበቱ
ስላስደነቃቸው ግሩም ተዓምራቱ
ይህን ምሥጢር አይተው ተሰነባበቱ
አዝ...

ኦ ድንግል ደስ ይበልሽ(ዘማሪት ማርታ)

ቅኝት -

ኦ ድንግል ደስ ይበልሽ ኦ ቅድስት ደስ ይበልሽ
ገብርኤል በቃሉ ደስታን ያሰማሽ ኦ ንጽሕት ደስ ይበልሽ
ኦ ድንግል ደስ ይበልሽ ኦ ቅድስት ደስ ይበልሽ
የዘለዓለም አምላክ እናት ስለሆንሽ ኦ ንጽሕት ደስ ይበልሽ
ኦ ድንግል ደስ ይበልሽ ኦ ቅድስት ደስ ይበልሽ
ከፍጡራን ሁሉ በላይ ስለሆንሽ ኦ ንጽሕት ደስ ይበልሽ
ኦ ድንግል ደስ ይበልሽ ኦ ቅድስት ደስ ይበልሽ
የነገስታት ንጉሥ ዙፋን ስለሆንሽ ኦ ንጽሕት ደስ ይበልሽ
ኦ ድንግል ደስ ይበልሽ ኦ ቅድስት ደስ ይበልሽ
የድኅነቴ አርማ ልዩ ምልክቴ
ለኔም ነሽ እናቴ እመቤቴ /2/
የድኅነቴ አርማ ልዩ ምልክቴ
ልዩ ነሽ እናቴ እመቤቴ
ኦ ድንግል ደስ ይበልሽ ኦ ቅድስት ደስ ይበልሽ
የምታማልጂን ከቸሩ አባታችን
ለእኛም እናታችን እመቤታችን /2/
የምታማልጂን ከቸሩ አምላካችን
ለእኛም እናታችን አስታራቂያችን
.....
ኦ ድንግል ደስ ይበልሽ ኦ ቅድስት ደስ ይበልሽ
ስለ ውድ ሀገርሽ ስለ ኢትዮጵያ
ለልጅሽ አሳስቢ ብለሽ ሀሌ ሉያ
ድንግል ሆይ አሳስቢ ብለሽ ሀሌ ሉያ
ስለ ውድ ሀገርሽ ስለ ኢትዮጵያ
ለልጅሽ አሳስቢ ብለሽ ሃሌ ሉያ
ኦ ድንግል ደስ ይበልሽ ኦ ቅድስት ደስ ይበልሽ /2/

የሰው ልጅ በኃይልህ(ዘማሪት ማርታ)

ቅኝት -

የሰው ልጅ በኃይልህ ፈጽሞ አትመካ /2/
አንድ አምላክ አለና በኃይሉ ኃይልን የሚለካ /2/
ኃይል እንደ ሶምሶን ከአምላክ ሲሰጥ እንጂ /2/
በጉልበት መመካት ለማንም አይበጅ /2/
ሰናክሬም ቢነሳ በሕዝቅያስ ላይ /2/
የደረሰበትን አልሰማህም ወይ /2/
ጎልያድ በኃይሉ ዳዊትን ቢንቀው /2/
አዋረደው እንጂ ኃይሉ ምን ጠቀመው /2/
እንደ ዳታንና እንደ አቤሮን አይሆንም በግድ /2/
ተመርጦ ነው እንጂ ለክብር በአምላክ ፈቃድ /2/
አዝ...
ክህነትን ለአሮን ሕግንም ለሙሴ /4/
ከሰው ሁሉ መርጠው ሰጧቸው ሥላሴ
አዝ...

ለእኛ ብሎ(ዘማሪት ማርታ)

ቅኝት -

ለእኛ ብሎ ተንገላታ የሁላችን ጌታ /2/
አዳም ቅጠል በልቶ ባመጣው በሽታ /2/
አምላክ ዋለ ቀራንዮ ለብሶ ከለሜዳ /2/
አዳም ሕግ አፍርሶ በኅተተው እዳ /2/
ለመስቀሉ ተሰለፈ እየተገረፈ /2/
በእፅ ሊፈውሰው በእፅ ላይ አረፈ /2/
በመስቀል ላይ የዋለውን እናመስግነው /2/
በእፅ የሞተውን በእፅ አዳነው /2/
ምንም በደል ሳይኖርበት የዓለም መድኃኒት /2/
ፍዳን ተቀበለ ለሰው ልጆች ድኅነት /2/
በመሬት ላይ ተንገላታ እሩሀሩሁ ጌታ /2/
አዳም ህግ አፍርሶ ባመጣው በሽታ /2/
ለእኛ ብሎ ተንገላታ የሁላችን ጌታ /2/
አዳም ህግ አፍርሶ ባመጣው በሽታ /4/
አዳም ሕግ አፍርሶ በኅተተው እዳ /2/

አምላካችን (ዘማሪት ማርታ)

ቅኝት -

አምላካችን ቅዱስ ነህ
ፈጣሪያችን ብሩክ ነህ
የዘለዓለም አምላክ ነህ /2/
አዝ ...
የአዳም ልጅ ከትቢያ/2/ ወደነበረበት
መልሰን ከአፈር እንዲሆን ከመሬት
በተናገርከው ቃል ባዘዝከው መሠረት
እንደ ጐርፍ መጥተህ ትወስዳለህ ድንገት /2/
አዝ...
ከህልም የረዘመ/2/ ህይወት የለንም
ማለዳ እንደሚበቅል እንደ ጧት አረም
ጠውልጎ እንደሚደርቅ እንደዚህ ዓለም /2/
አዝ...
ህይወትህ ናትና/2/ እንደ ጠዋት ጤዛ
እረግፎ ለሚቀር ውበትና ለዛ
እባክህ የሰው ልጅ ታጢአትን አታብዛ /2/
አዝ...
ዕድሜያችን ሰባ ዓመት ቢበዛ ሰማንያ
በመከራ ያልቃል እሱም በዓለም ዙሪያ
እኛም እናልፋለን በጭራሽ ሳንሰራ
በራስ ተሸክመን የታጢአትን አዝመራ /2/
አዝ...
የመከራ ዓመታት አሳልፈናል
ፍርድህን በመፈራት ተሸብረናል
እባክህ ጌታ ሆይ በቸሮታህ ሥራ
ለአገልጋዮችህ አምላክ ሆይ እራራ /2/
አዝ...

ነፍሴ ሆይ (ዘማሪት ማርታ)

ቅኝት -

ነፍሴ ሆይ/2/ እግዚአብሔርን በቅን አገልግይ
እግዚአብሔርን በቅን አገልግይ
የተቀበለው በቀራንዮ
ያን ሁሉ መከራ በመስቀሉ ላይ
ለአንቺ ሲል ነውና ነፍሴ ሆይ
አዝ...
ተዘጋጅተሽ ኑሪ ሁልጊዜ
በነገ በዛሬ እንዳትታለይ
እንዳትታለይ ነፍሴ ሆይ
አዝ...
በንስህ ጥምቀት ታጠቢና
ክቡር ደሙን ጠጪ ሥጋውንም ብዪ
ሥጋውንም ብዪ ነፍሴ ሆይ
አዝ...
ዘለዓለም በደስታ እንድትኖሪ
ከዘለዓለም ቤትሽ መንግስተ ሰማይ
መንግስተ ሰማይ ነፍሴ ሆይ
አዝ.../3/

ዘማሪ ይልማ ታይሉ

ኪዳነ ምህረት እናቴ(ዘማሪ ይልማ ታይሉ)

ቅኝት -

ኪዳነ ምህረት እናቴ አማልጂኝ እኔን ከልጅሽ
የፍቅር እናት ነሽና አማልጅኝ እኔን ከልጅሽ/2/
የተገለጠው ብርሃን ከምሥራቅ የተወለደው
በፍቅር ሰንሰለት አስሮ ዓለምን ሁሉ አዳነው/2/
ኪዳነ ምህረት እናቴ አማልጂኝ እኔን ከልጅሽ
የፍቅር እናት ነሽና አስታርቂኝ እኔን ከልጅሽ
የሰላም እናት ነሽና አማልጅኝ እኔን ከልጅሽ
በረሃውን ባሰብኩት ጊዜ የግብጹን የአሸዋ ግለት
አንቺ ትንሽ ብላቴና ኧረ እንዴት ቻልሽው በእውነት/2/
ኪዳነ ምህረት እናቴ አማልጂኝ እኔን ከልጅሽ
የፍቅር እናት ነሽና አማልጅኝ እኔን ከልጅሽ
የሰላም እናት ነሽና አማልጅኝ እኔን ከልጅሽ
ዝም ብዬ ይደንቀኛል የአምላክን ሥራ ሳስበው
ምክንያት አንቺን አድርጎ ይህንን ዓለም አዳነው/2/
ኪዳነ ምህረት እናቴ አማልጂኝ እኔን ከልጅሽ
የፍቅር እናት ነሽና አማልጅኝ እኔን ከልጅሽ
የሰላም እናት ነሽና አማልጅኝ እኔን ከልጅሽ
የፍቅር እናት ነሽና አማልጅኝ እኔን ከልጅሽ
የሰላም እናት ነሽና አማልጅኝ እኔን ከልጅሽ

ለመዳኑ ህይወት(ዘማሪ ይልማ ታይሉ)

ቅኝት -

ለመዳኑ ህይወት ለጽድቁ ጠርቼህ
ከዓለም ለይቼ በፍቅሬ መርቼህ
በረከትና ፍቅር ሰላሜን ወርውረህ
ልጄ የምወድህ እባክህ ወዴት ነህ
ይልሀል እግዚአብሔር እባክህ ወዴት ነህ
አዝ .....
ከዓለም ጉያ ውስጥ ሸብር ከተሞላው
ከስንጥቅ አለት ውስጥ ጐድጓዳ ከሆነው
የአራዊቱ ግርማ የአንበሶቹ ግሳት
የዘንዶው ትርምስምስ የእባቦቹ ፉጨት
የጭለማው ክብደት የፍጥረት ማዛጋት
እንዲህ ያለው ስፍራ ተወርውረህ ነው ወይ
ቀናት ተቆጠሩ አይኖችህን ሳላይ
አዝ.....
ከቅዳሴው የወጣ ምስጋና ስቀበል
ጐላ ያለው ድምፅህ ተሰውሮብኛል
በቅድስቱ በኩል በምትቆምበት በቅዳሴ ጊዜ
ዓይኖቼ ስላጡህ ፈልገው ፈልገው ይዞኛል ትካዜ /2/
አዝ.....
ልጄ ምን በደልኩህ ምን አጐደልኩብህ
ትተኸኝ የሄድከው እንደዚያ ስወድህ
ዘወትር ፊትህን ሳየው ደስ እያለኝ
ደስታዬን በሀዘን ምነው ለወጥክብኝ /2/

ኦ ጌታ ሆይ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ኦ ጌታ ሆይ ተሰቀልክ ሆይ (2)
ምድር አለቀሰች እያለች ዋይ ዋይ
ኦ ጌታ ሆይ ተሰቀልክ ሆይ
ኮረብቶች ደንግጠው መድረሻ ጠፋቸው
ከዋክብትም ፈርተው ጨለማ ዋጣቸው
እጅግ አይደንቅም ወይ ጌታ መሰቀሉ
የጌቶቹ ጌታ ችንካር ላይ መዋሉ
ኦ ጌታ ሆይ ተሰቀልክ ሆይ...
ሰማይና ምድርን በፈጠረበት
ጨለማና ብርሃን ባደረገበት
ችንካር ተከሉበት መቱት በህብረት /2/
ኦ ጌታ ሆይ ተሰቀልክ ሆይ...
ድንግል አለቀሰች እንባዋ ፈሰሰ
ስደተኛ ልጇ መከራ ቀመሰ
ህማሙን ሳስበው አለቅሳለሁኝ
የስቃዩን ነገር አስባለሁኝ
ኦ ጌታ ሆይ ተሰቀልክ ሆይ...
እንባዬን ጠራርጒ ረሀቤን ተካፍሎ
ሞተልኝ ጌታዬ ስለሞቴ ብሎ
እኔ ልሙትልህ ሲለኝ ሰማሁት
እንዲህ የወደደኝ ምን አረኩለት
ኦ ጌታ ሆይ ተሰቀልክ ሆይ...

ስራህ ብዙ(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
ሥራህ ብዙ መድኃኔዓለም ሥራህ ብዙ
ቸርነትህ ፍቅርህ ብዙ የኔ ጌታ ሥራህ ብዙ
አዝ...
አዕዋፉ አናብርቱ ተሰብስበው
በማለዳ ከእንቅልፋቸው ተቀስቅሰው
ይጮኻሉ ወደሰማይ ያዜማሉ
ሥራህ ብዙ የእኛ ጌታ ተመስገን ሊሉ
አዝ...
የፍጥረትህ ምስጋናቸው ወደ ሰማይ እየወጣ
በረከትን ፍቅርን ስቦ እያመጣ
ስንባረክ በቸርነት ስንጐበኝ
ሥራህ ብዙ መድኃኔዓለም እላለሁኝ
አዝ...
ምሥጋና አለህ መድኃኔአለም ከደመነፍስ
ከግዑዛን ፍጥረታትህ ምሥጋና አለህ
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አምላክ ልዩ ሲሉህ
አዝ.../3/

በብርሃን ጸዳል (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
በብርሃን ፀዳል ተከባ እመቤቴ
በደመና ዙፋን ተቀምጣ ከፊቴ
የጽጌውን ዜማ ስንዘምር በደስታ
በምስጋናሽ መጠን ሲሰማኝ እርካታ
ሲሰማኝ እርካታ
እንባዬ ሲቀዳ ናፍቆትሽ መስጦኝ
ከደስታ በላይ አንቺን ስላየሁኝ
ምኞቴ ተሳክቶ ፊትሽን አይቼው
የሌሊቱ ህልሜ የቀን ምኞቴ ነው
የቀን ምኞቴ ነው
አዝ...
እሩህሩህ ነሽና ይህ ህልሜ ተሳክቶ
አመስግኜሽ ድንግል ህሊናዬ ረክቶ
ልጅሽ ልሁን ድንግል ከስርሽ አልጥፋ
አንቺን በማመስገን ህሊናዬ ይትፃ
ህሊናዬ ይትፃ
አዝ...
ልጅሽ ልሁን ድንግል ከስርሽ አልጥፋ
አንቺን በማመስገን ህሊናዬ ይርካ
የምስጋናሽ ብዕር ብራናሽ ብሆንም
ስምሽ ይጻፍልኝ በልዩ ህብር
በልዩ ህብር
አዝ...

የአብ ቃል አክብሮሽ(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
የአብ ቃል አክብሮሽ እናት ያደረገሽ
እግዚአብሔር በቃሉ ፍፁም ያከበረሽ
የምንመካብሽ መሰላል አንቺ ነሽ/2/
ቅድስና ላንቺ ጽድቅም ላንቺ ሆኖ
ዓለም የፈጠረ ባንቺ ተወስኖ
የገነት ፍሬ ነሽ ህይወት ያፈራሽ
አንቺን ለመረጠ አንቺን ላነጻሽ
ምስጋና ይድረሰው ለቸሩ አምላክሽ/2/
አዳም የኖረብሽ የኤዶም ገነት ነሽ
የኤፌሶን ወንዝ ወርቅ የሚፈልቅብሽ
የግዮን ማዕበል ኢትዮጵያን የከበብሽ
ዮርዳኖስ ሆነሽ አህዛብን ፈወስሽ
በልጇ ቃልነት አብም አከበረሽ /2/
አዝ...
መዓዛሽን ወዶ ወልድ ዋሕድ ዋጀሽ
አብም በሰማያት በኅሊናው ጻፈሽ
መንፈስ ቅዱስ መጥቶ አንቺን አከበረሽ
እመካብሻለሁ እመቤቴ ስልሽ /2/
ወልድ መወውደዱ ከአንቺ መወለዱን
ንጹህ ሆኖ አማኝቶት ቅዱሱን ሥጋሽን
ለቃሉ ማደሪያ ጽላትና ታቦት
በብሩህ ደመና ተመስለሽለት
ከሥጋሽ ተከፈሎ ከደምሽ ደም ወስዶ
ከነፍስሽም ነፍስ ፍጹም ተዋሕዶ
ፍጹም ተዋሕዶ/3/

እስራኤል ሠለቸው (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -

እስራኤል ሰለቸው የሰማዩ መና /2/
ዓለም አምሮት ሄደ ጸጋውን ተወና/2/
የእግዚአብሔር ስጦታ ጎብስቱ ሰልችቶት /2/
ዓለም አምሮት ሄደ ከተወው ባርነት /2/
አዝ ……
የፈርያን ጅራፍ አልታየው አለ
የዓለም አምሮቱን ውርደቱን ከለለ /2/
ግብፅ ልሂድ ብሎ አመጸ በእግዚአብሔር
መድረሱ አልገባውም ከከነዓን ሀገር /2/
አዝ ……
የኪዳኑ ታቦት የሙሴ ገጽታ
ዓለም ስላማረው አደረገው ተርታ
የአምላክን ካህናት የአሮንን ሥርዓት
በዓለም ለወጠው ትልቁን አምኃ /2/
አዝ ……
የጎብረቱን ጉዞ በፍቅር የሄደው
የማጎሌት ደስታ እስራኤል ታከተው
የእግዚአብሔርን ድንኳን ደመና ያጀባት
የኪዳኑን አርማ በበረሃ ተዋት /2/
አዝ ……
ዛሬም ይሄ ትውልድ እስራኤልን ሆኗል
ቤተክርስቲያኑን አምላኩን እረስቷል
ግብጽና ባቢሎን አጓጉተው ወስደውት
ወርቁን ከእጁ ጣለ መዳብ አስጎምጅቶት /2/

ተስፋ አለኝ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ተስፋ አለኝ በአምላኬ
ተስፋ አለኝ በእግዚአብሔር
ምናምንቴ ሆኜ በዚህች ምድር ብኖር
ተስፋ አለኝ በእግዚአብሔር
አዝ ……
ጥበብ የተሞሉ ታላላቅ ኃይለኞች
ሥልጣን የጨበጡ የምድር ብርቱዎች
ስላልተመረጡ በሀብታቸው ብዛት
ተስፋ አለኝ ለጽድቁ ለሰማያዊው ቤት /2/
አዝ ……
የአምላክ ዓይን ልዩ ነው አያዳላም ለሰው
ፍቅሩ ለፍጥረቱ ምንጊዜም እኩል ነው
ፀሐይን ለፍጥረት ያወጣል በእኩል
ጻድቅና ኃጥእ ክፉ ሰው ነው ሳይል /2/
አዝ ……
በኃጢአት ብወድቅም ሕይወቴ ቢጐድፍ
በንስሓ ዳንኩኝ እኔ ሳልቀሰፍ
አምላክ ቸርነቱ ምህረቱ አድኖኝ
አዲሲቷን ምድር እናፍቃለሁኝ /2/
አዝ ……
ያለፈው በደሌ ተደምስሷልና
ወደፊት ለፍቅሩ ለጽድቅ ሥራ ልቅና
በዓለም ከሚኖሩ ባለተስፋ ሁነው
ሰላም ያገኛሉ ክርስቶስን መርጠው /2/

ማነው እርሱ(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

___ ቅኝት -

ማነው እርሱ ማነው እርሱ /2/
ምድርን የሠራ በኃያል ቃሉ ማነው እርሱ
ሕይወት የሰጠ ለፍጥረት ሁሉ ማነው እርሱ
የባህርን ሞገድ የሚገስጸው ማነው እርሱ
የኃይላት ጌታ ጌታችን ማነው
ማነው እርሱ /2/
ከጥልቀት በታች ከምጥቀት በላይ
ማነው ጌታችን ሁሉንም የሚያይ
ማነው እርሱ ማነው እርሱ
ከፈሳሶች ውስጥ ወንዙን የሚያፈስ ማነው እርሱ
ምድርን ልምላሜ ፍጹም የሚያለብስ ማነው እርሱ
ጥቃቅን ነፍሳት የሚመግበው ማነው እርሱ
የሚመሰገን ጌታችን ማነው
ማነው እርሱ /2/
ከጥልቀት በታች ከምጥቀት በላይ
ማነው ጌታችን ሁሉንም የሚያይ
ማነው እርሱ ማነው እርሱ
የሰማይ መብረቅ የሚያንጐዳጉድ ማነው እርሱ
በፍትሕ በእውነት ለጽድቅ የሚፈርድ ማነው እርሱ
አምሳያ ለርሱ የሌለው ጌታ ማነው እርሱ
እግዚአብሔር ስሙ የሁሉ አለኝታ
ማነው እርሱ /2/
ከጥልቀት በታች ከምጥቀት በላይ
ማነው ጌታችን ሁሉንም የሚያይ
ማነው እርሱ ማነው እርሱ
ስብራትህን የሚጠግነው ማነው እርሱ
ትንሽነትህን የማይጸየፍ ማነው እርሱ
አድሎን የማያውቅ ለሰዎች ፊት ማነው እርሱ
ለሁሉ የሚሰጥ የጽድቅ ህይወት
ማነው እርሱ /2/
ከጥልቀት በታች ከምጥቀት በላይ
ማነው ጌታችን ሁሉንም የሚያይ
ማነው እርሱ ማነው እርሱ
እውነትና ምህረት የከበቡት ማነው እርሱ
ለሕዝብ የሚሰጥ ልዩ ሕይወት ማነው እርሱ
የሚፈሩትን የሚያከብራቸው ማነው እርሱ
የአማልክት አምላክ ስሙ ቅዱስ ነው
ማነው እርሱ /2/
ከጥልቀት በታች ከምጥቀት በላይ
ማነው ጌታችን ሁሉንም የሚያይ
ማነው እርሱ ማነው እርሱ
የሰማይ መብረቅ የሚያንጐዳጉድ ማነው እርሱ
በፍትሕ በእውነት ለጽድቅ የሚፈርድ ማነው እርሱ
አምሳያ ለርሱ የሌለው ጌታ ማነው እርሱ
እግዚአብሔር ስሙ የሁሉ አለኝታ /4/

ኢትዮጵያ ሆይ(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -

ኢትዮጵያ ሆይ እግዚአብሔርን አመስግኚ አመስግኚ
ከሕዝብሽ ጋር እልል በይ እልል በይ እልል በይ
አዝ...
እጆችሽን በበረከት ስለሞላ ስለሞላ
ስላዳነሽ በጭንቅ ቀን ከሞት ጥላ ከሞት ጥላ
እግዚአብሔር ብርሃንሽ ስለሆነ ስለሆነ
ከአስፈሪው ቀን ልጆችሽን ስላዳነ ስላዳነ
ኢትዮጵያ ሆይ እግዚአብሔርን አመስግኚ አመስግኚ
በሽብሸባ ጋር እልል በይ እልል በይ እልል በይ
በሽብሸባ ለአምላክሽ ዘምሪለት ዘምሪለት
ስብራትሽን ይጠግናል በምህረት በምህረት
ለሕዝብሽም እግዚአብሔር ኃይላቸው ነው ኃይላቸው ነው
በስቃይ የጎበኘህ መመኪያቸው መመኪያቸው
አዝ...
ሕዝብህን ባርክ ለዘላለም ጠብቃቸው ጠብቃቸው
በጽድቅህም ከፍ አድርጋቸው አድርጋቸው/2/
የምሥጋና ነጎድጓዱ ከአፍሽ ይውጣ ከአፍሽ ይውጣ
ድሮም ቢሆን እግዚአብሔር ነው ያንቺ ዕጣ ያንቺ ዕጣ
አዝ...

ከወገኔ ጋራ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -

ከወገኔ ጋራ አዘምራለሁኝ
በደስታ በሀሴት ስሙን እጠራለሁኝ
ምግብና መጠጡ አምላኬ ነውና
ሌሊት አቀርባለሁ ለጌታ ምስጋና/2/
ህዝቡ ተሰብስቦ በቤተ ክርስቲያን
ሲዘምር ደስ ይላል በአንድነት ሆነን
በረከት የሞላው ዝማሬ ይገርማል
ከእጣኑ ጋራ ወደ ላይ ይወጣል
አዝ ...
ቀሳውስቱ ሌሊት ማኅሌት ሲያቀርቡ
ከመላእክቱ ጋር ወረብ ሲወርቡ
ብርሃኑን ለብሰን በደስታ ስንዘምር
ትዝታው ልዩ ነው ሀሊና ሲሰውር/2/
አዝ...
ራዕይ ነውና ኑና ተመልከቱ
ሰዎች ሲዘምሩ እንደመላእክቱ
የፅጌው ዝማሬ የትንሣኤው ደስታ
ልዩ ዝማሬ ነው እንዳይመስለን ተርታ
የፅጌው ማኅሌት የትንሣኤው ደስታ
ልዩ ዝማሬ ነው እንዳይመስለን ተርታ
አዝ...
ራዕይ ነውና ኑና ተመልከቱ
ሰዎች ሲዘምሩ እንደመላእክቱ
የፅጌው ማኅሌት የትንሣኤው ደስታ
ልዩ ዝማሬ ነው እንዳይመስለን ተርታ
የፅጌው ማኅሌት የትንሣኤው ደስታ
ልዩ ዝማሬ ነው እንዳይመስለን ተርታ
አዝ...

በየገዳማቱ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -

በየገዳማቱ በየበረሀው ውስጥ
ስለተሰደዱት ፍቅርህን በመምረጥ
የዓለም ውዳቂ ምናምንቴ ሆነው
ስለፍቅርህ ሲሉ ክብራቸውን ትተው
እግዚአብሔር ሆይ ማረን /2/
የአለም ውዳቂ ጉድፍ በተባሉት
በምድር እየኖሩ በጽድቅ ህይወት ባሉት
ዓለምና አምሮቷን ትተው በመነኑት
ኢየሱስ ሆይ ማረን እግዚአብሔር ሆይ ማረን /2/
አዝ...
ህያዋን በሆኑት እስከዘለአለም
ከኢየሱስ ጋራ ሞተው በመስቀል ዓለም
ዓለም የናቃቸው እነርሱም በናቁት
አምላክ እራራልን አትጨክን በእውነት /2/
አዝ...

በርጠሜዎስ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -

በርጠሜዎስ ነኝ አይነ ስውር ምስኪን
ከሩቅ የሰማሁት የጌታዬ ድምፁን
ከብዙ ሁካታ ጉርምርምታ መሀል
የክርስቶስ ድምጹ በግልጽ ይሰማኛል /2/
የልቦናዬ አይን ፈጽሞ ታውሯል
ዓይኔን ፈውስልኝ በርጠሜዎስ ይላል
አብዝቼ እጮኻለሁ ጌታ ማረኝ ብዬ
በውስጤ እየታየኝ ሲምረኝ ጌታዬ /2/
አንተን አይሰማህም ይሉኛል ብዙዎች
በኃጢአት ሰንሰለት ታስረሀል እግር ከወርች
ስለዚህ አትልፋ ሲኦልን ጠብቃት
እንደዚህ ቢሉኝም ጮኻለሁ ሳልታክት/2/
አዝ...
የከበበውን ሰው ገለል በሉ እያለ
በደሌን በደሙ ዋጋ እየከፈለ
ስለእኔ የሞተው ኢየሱስ ይመጣል
የልቦናዬን አይን ገልጦ ያሳየኛል /2/
አብዝቼ እጮኻለሁ ጌታ ማረኝ ብዬ
በግልጽ እየታየኝ ሲምረኝ ጌታዬ
በውስጤ በደልስ ህይወቴ ዝላለች
በአምላኬ ቸርነት ህይወት ካላገኘች /2/
አዝ...

በእጸ መስቀሉ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -

በእጸ መስቀሉ የተከፈለልኝ
የኢየሱስ ፍቅር ምንኛ ማረከኝ
ከፍቅርም በላይ ሆነና መሰጠኝ
ከመስቀል ስር ሆኜ ፊቱን እያየሁኝ
ዓለምን በፍቅሩ ያሸነፈ ጌታ
የጸብን ማዕበል በፍቅሩ እየገታ
ህይወቴን ፀጥ አርጌ ይምራኝ በምልአቱ
እኔ ምን አለፋኝ አልደክምም በከንቱ

አዝ.....
ደሙ ከወዙ ጋር ተዋህዶ ሲወርድ
በእኔ በደል ጌታዬ ቀረበልኝ ለፍርድ
ታጢአቴን በጫንቃው ተሸክሞልኛል
በደሌን ደምስሶ ንጹህ አድርጐኛል
የቀራንዮ ግፍ በአንተ ላይ የሆነው
ሰይጣንን ጠርቆ ከመንገድ አወጣው
እሾህ አሜኬላው ተደምስሶልናል
የንጹሁ በግ ደም አዳምን ታድጓል
አዝ.....
ይህንን ሥጋዬን ብሉ ይላችኋል
ይህንን ደሜንም ጠጡ ይላችኋል
ከመስቀል ስር ሆነን ደሙን እንቀበል
ሥጋውን እንብላ ሰዎች ቸል አንበል
ሰአዝ.....

ደም ግባት የለውም (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
ደም ግባት የለውም ስለ እኛ ተገርፏል
ይህንን ህማሙን ማን ሰውኮ አምኗል
በእውነት ደዌያችንን እርሱ ተቀበለ
እርቃኑን ተሰቅሎ ቀራንዮ ዋለ
ተቅበዝብዘን ነበር ነፍሳችንን ቆዝማ
እንጠፋ ነበረ በሲኦል ጨለማ
ሁሉም አዘንብሎ ለጥፋት ሲቃረብ
አወጣን እየሱስ ከዲያብሎስ መረብ
ተጨነቀ ጌታ ተሰቃየ ጌታ
በመስቀል ሞት ሞትን ጠላትን ሊረታ
እንደሚታረድ በግ በሸላቾቹ ፊት
ዝምታን መረጠ እንዲያ ሲያንገላቱት
አዝ...
አፉን አልከፈተም ሲሰድቡት ሲከሱት
ሀሞትና ከርቤ ቀላቅለው ሲያጠጡት
ዓለም ጭካኔዋን ብታፈራርቀው
ከይቅርታ ሌላ አልመለሰላትም
ደዌ ማይስማማው በሥጋው ታመመ
የዓለምን ጠቢባን በዚህ አስገረመ
ሞቱ ግርፋቱ ሲያስቡት ይደንቃል
ዓለም የፈጠረው በፍጡራን ታስሯል
አዝ...
ምን አይነት መውደድ ነው ምን አይነት ትዕግሥት
ሰውን ያፈቀረው የፍጥረት አባት
ምን አይነት ርኅራሄ ምን አይነት ይቅርታ
በመስቀል ተሰዋ የፍጥረታት ጌታ
በመስቀል ተሰዋ በፍጥረታት ፋንታ
አዝ...

ነፍሴ ሆይ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
ነፍሴ ሆይ /3/ እግዚአብሔርን ባርኪ /2/
አጥንቶቼም ሁሉ /3/ የተቀደሰ ስሙን
በደስታ ዘምሪ በአዲስ ምሥጋና
ጸጥታና ሠላም አድሎሻልና
መሠንቆውን አንሺ ቅኔ ተቀኚለት
ለውጦሻልና በደስታ ዘይት
አዝ...
ሀሴትን አድርጊ ነፍሴ በእግዚአብሔር
ይሰጥሻልና በክብር ላይ ክብር
ደሴቶች ሲያወሩ በደስታ መንፈስ
እየተወያዩ ስለ ስሉስ ቅዱስ
አዝ...
ሰማያት ሲያወሩ ጽድቅን ሲወያዩ
ሲጠራው አድምጪ ቀላዩን ቀላዩ
ደመናው ጭጋጉ በዙሪያው ከበውት
ቅኔ ያቀርባሉ ለፍጥረታት አባት
አዝ...
መብረቅ ይሰማል ሰማዩን ሰንጥቆ
ምሥጋናውን ሊያቀርብ ጊዜውን ጠብቆ
በፊቱ ይነዳል እሳትም በግርማው
ምድር ተናወጠች ነጐድጓዱን ሰምታ
አዝ...

ክበር ተመስገን ጌታችን (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
ኧ... ክበር ተመስገን ጌታችን
ክበር ተመስገን ጌታችን /3/
ለዚህ ያደረስከን
ለጋሽ ጌታ ነው የተረፈው
ብሉ ጠጡ ሲል ስስት የለው
ሥጋውን ቆርሱ ሲያበላን
ፍቅሩን አወቅነው ጣዕሙን
ኧ... ክበር ተመስገን ጌታችን
ይሰጣል አሉኝ ሳይታክት
ለሚጠይቀው በእውነት
ይለምንሀል መላው ሀገር
ሰው ከሰው ተርታ እንዲቆጠር
ኧ... ወዳጅ ዘመዴ ምነው
ለደሀ ፍርዱ ተጣመመ
ሀብታም በእጥፍ ተጠቀመ
ምንም አልቀረው መመከቻ
በእጁ የሞላው እንባ ብቻ
ኧ... ወዳጅ ዘመዴ ምነው
ጌታ ተሰቅሎ በአደባባይ
ማን ሊዳኝን ነው አወይ አወይ
ዓለም የዳኘው በእውነት
እንዴት አቻኩለው ሰቀሉት
ኧ... ወዳጅ ዘመዴ ምነው

ነውሬን አጥርቼ እንድነግስ
መስታወት ገዛሁ የሚያድስ
ትኩር ብዬ ሳየው ገጼን
ያሳየኝ ጀመር ሰውነቴን
ኧ ... ወዳጅ ዘመዴ ምነው
ወዳጅ ዘመዴ ምነው /3/
መዋደዱንስ ምን ነካው
መፋቀሩንስ ምን ነካው
ይሉኝታውንስ ምን ነካው
ኧ... ወዳጅ ዘመዴ ምነው

ውለታው ብዙ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
ኧ... ውለታው ብዙ የእግዚአብሔር
ውለታው ብዙ የእግዚአብሔር አመስጋኝማ ቢኖር /2/
ኧ... ክበር ተመስገን ተመስገን
ክበር ተመስገን ተመስገን ጨለማን ወስዶ ብርሃን /2/
ኧ.... ክበር ተመስገን ተመስገን
ሰለሞን ነግሶ ጠቢቡ ሰው
ይህንን ዓለም እንዴት ናቀው
ቢከብር ቢያጌጥ ከሰው በላይ
ዙፋኑን ጣለው ከጭቃ ላይ
ኧ... ውለታው ብዙ የእግዚአብሔር
እቀና ነበር በንጉስ
ሞትን ሳላየው ሲያዳርስ
ሞገደኛ ነው ደፋር ዳኛ
ሁሉን አረገው መንገደኛ
ኧ... ተመስገንልን የእኛ ጌታ
ቆላ ወርጄ ጥጥ ልዘራ
አላበቅል አለኝ አላፈራ
የኋላ ልብሴን ይዞልኛል
አፈራለው ይለኛል
ኧ.... ውለታው ብዙ የእግዚአብሔር
ውለታው ብዙ የእግዚአብሔር
አስተዋይማ ቢኖር
ውለታው ብዙ የእግዚአብሔር
መርማሪ ሰውስ ቢገኝ
ኧ.... ተመስገንልን ተመስገን

እጅግ ብዙ ነው ቸርነቱ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
ኧ ... እጅግ ብዙ ነው ቸርነቱ
እጅግ ጥልቅ ነው ቸርነቱ
ጌታ ስጦታው ማስደሰቱ
ለጋሽ አምላክ ነው አያልቅበት
ለሚታመኑት በሀይማኖት
ኧ ... ለጋሽ አምላክ ነው አያልቅበት
ወይዛዝርት ሁሉ በጐዳና
ይሯሯጣሉ ያለ ጤና
የልኪንዳ ቤት ተበራክቷል
ስጋ በይፋ ይሸመታል
ኧ ... እጅግ ድንቅ ነው ቸርነቱ
ሻጭ ቢቸግራት ቢርባት
ስጋዋን ሸጠች ያለእፍረት
ገዢው ይገርማል ቅምጥሉ
እህቱን ይበላል ለአመሉ
ኧ ... ለጋሽ አምላክ ነው አያልቅበት
አስነሱት አሉ ደሀውን
ዓለምን ጠልቶ ቢመንን
አንድ ከስንዝር መሬቱን
ይነሱት ይሆን እርስቱን
ኧ ... እጅግ ድንቅ ነው ቸርነቱ
እፍረት የሚሏት የሰው ንዋይ
ተለወጠች ወይ በአባይ ሚዛን
ሰውን ቢንቀው ቢያፍር
ተደፈረ ወይ እግዚአብሔር
ኧ ... ለጋሽ አምላክ ነው አያልቅበት
መግረፊያው ብዙ የእግዚአብሔር
ምንም ከፍታ ብንኖር
ጤናው በእጁ ነው አርጩሜው
ግፈኛን አስሮ መግረፊያው
ኧ ... እጅግ ድንቅ ነው ቸርነቱ
ብቻዬን ሆኜ ሳስበው
አስደነገጠኝ የወጪው
እያጣቀሰ ግፍ የጠራው
ያባራ አይመስልም ከነአካቴው
ኧ ... ለጋሽ አምላክ ነው አያልቅበት
አፉ እስኪቀደድ የጐረሰው
አይጠረቃም ወይ ወየው ወየው
ትርጉም ለሌለው ለዚህ ዓለም
ለማይኖርበት እንዲህ መድከም
ኧ ... ለጋሽ አምላክ ነው አያልቅበት

አቤቱ እንማልዳለን (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

በአንድነት ጸንተን እንኖር ዘንድ
አቤቱ እንማልዳለን
በሀይማኖት ተግተን እንቆም ዘንድ
አቤቱ እንጸልያለን
በመከራ ትዕግስት ፍፃሜ እንዲሰጠን
ከቅዱሳን ጋራ በገነት ያኑረን
እርሱን ደስ ካሰኙ ከቅዱሳን ጋራ
በቅን አገልግሎት ምግባር እንድንሰራ
አቤቱ እንማልዳለን
አዝ...
ስለ ዲያቆናቱ ስለ ቀሳውስቱ
እንጸልያለን ስለ ጳጳሳቱ
ያለነውር ሆነው ፍጹም ንጽህና
ምግባር እንዲደረጅ እምነት እንዲጸና
አቤቱ እንማልዳለን
አዝ...
ኢትዮጵያን ጠብቃት ከረሀብ ጦርነት
ገበሬውም እንዲያርስ በብዙ በረከት
እረዳት የሚጦር ድጋፍ ለሌላቸው
እንማልዳለን ባልቴት ሽማግሌው
አቤቱ እንማልዳለን

አዝ...
የዕለት ምግባችንን አምላክ እንዲሰጠን
ስለረሀብተኞች እንጠራሀለን
በግፍ ለታሰሩ ለሚያዝኑ ምስኪናን
ዘወትር ሳንታክት እንማልድሀለን
አቤቱ እንጸልያለን
አዝ...
ስለተሰደዱ በባህር በረሀ
ከማይገኝበት ምግብና ውሃ
በምርኮ በስቃይ ለሚንገላቱቱ
እንማልድሀለን አምላክ ሆይ በብርቱ
አቤቱ እንጸልያለን
አዝ...
ስለ ድውያኑ ለታመሙ ሰዎች
ቤተክርስቲያንም ትማልድሃለች
ስለ ዝናብና ስለ ውሃ ሙላት
በልክ እንዲያደርገው ንፋሱን በእውነት
አቤቱ እንማልዳለን
አዝ...

የሚጠብቀኝ አይተኛም (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
የሚጠብቀኝ አይተኛም /2/ አያንቀላፋም /2/
ቤት ባይኖረኝም እደጅ ባድርም
ቀንና ሌሊት ከእኔ አይርቅም
ድምጸ አራዊት የሌሊት ግርማ
ወደእኔ አይቀርቡም ድምጽ ሲሰማ
አዝ...
መሰናከልን ለእግሮቼ አይሰጥም
ይሰውረኛል በቀኙ ሰላም
ፀሀይም በቀን አይተኩሰኝም
የአጋንንትም ኃይል አያስፈራኝም
አዝ...
ነፍሴን ጠበቃት ከጠላት ወጥመድ
ጌታዬ መራኝ በጽድቅ መንገድ
መውጣት መግባቴን እየጠበቀ
ለዚህ አበቃኝ እርሱ ባወቀ
አዝ...
የሰማዩን ጠል እታገሳለሁ
ሰው ከጨከነ ምን እሆናለሁ
ሌሊት በድብቅ ለሚጐበኙኝ
ለጻድቃኑ ግን አምላክ ይስጥልኝ
አዝ...
እንቅልፌን ባርከ የሰጠኝ ጌታ
በዓለም ሀሣብ ሳልንገላታ
የዕለት ምግቤንም ላልነሳኝ ፍፁም
ምሥጋና ላቅርብ እስከ ዘለአለም
አዝ...

ተወዳጅ ልጅሽን(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
ተወዳጅ ልጅሽን ሀማሙን ስታይ
ማሰብ ይሳነኛል የአንቺን ስቃይ
በእሾህ አክሊል ጉንጉን የቆሰለ ራሱን
በብዙ ግርፋት የታመመ አካሉን የታመመ አካሉን
በእጸ መስቀሉ የወረደ ደሙ
የቀራንዮ ግፍ እጅግ ማስገረሙ
ደጉ ልጅሽ ታስሮ የፍጥኝ ሲሰቃይ
ተሰክቶ ቀረ አይንሽ ወደ ሰማይ አይንሽ ወደ ሰማይ
ስለ መሰቀሉ አይሁድ ሲደሰቱ
ሲስቁ ሲያሾፉ ቁማር ሲጫወቱ
ሲዘባበቱበት አይንሽ በማየቱ
ሀሊናሽ ተገርፏል በሀዘን በብርቱ በሀዘን በብርቱ
ብላቴናይቱ የዳዊት ልጅ ማርያም
ስለደረሰብሽ ቢነገር አያልቅም
ተጠማሁ ቢላቸው መፃፃ አስጎነጩት
መርገም አስወግዶ ቢሰጣቸው ህይወት ቢሰጣቸው ህይወት
ለመጠጡ እንዲሆን መፃፃ ከሀሞት
ሰፍነግም ጨምረው በዘንግ አስጎነጩት
ዳዊት በትንቢቱ እንደተነበየው
በምግቤ መራራን ጨመሩ እንዳለው ጨመሩ እንዳለው
ይሄ ሁሉ ሲሆን ድንግል ተመልክታ
መጽናናት ተሰናት በሀዘን ተነክታ
ኤሎሄ ኤሎሄ ጌታ ባለም ጊዜ
እጅግ ኃያል ነበር የማርያም ትካዜ የማርያም ትካዜ
አዝ...

ያድነናል ብለው (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
ነገር ግን ያመነው ያድነናን ብለው /2/
ጸንተው ተሰለፉ ለሀይማኖታቸው
ሦስቱ ወጣቶችን ከእሳት ያወጣቸው
ሀይማኖት ነው እንጂ ሌላ ምን ሊሆን ነው
ናቡከደነፆር በዱራ ሜዳ ላይ
ጣኦቱን አቁሟል እንድንሰግድ እንድናይ
አዝ...
እንቢልታ ሲነፋ መለከት ሲሰማ
በአንድነት እንዲሰግድ ሰው ሁሉ ተስማማ
ነገር ግን ትዕዛዙን የማይቀበለው
ከሚነደው እሳት ይጨመራል ወዲያው
አዝ...
ሰው ሁሉ ይንበርከክ ለወርቁ ለብሩ
አምላክ ስለሆነ በአንድነት ያክብሩ
ለግዙፉ ሐውልት ያልሰገደ ቢኖር
ምህረት ሳያገኝ ወደ እሳት ይወርወር
አዝ...
ሲድራቅ ሚሳቅና አብድናጐም ሆነው
ሳይሰግዱ በድፍረት ቆመው አየናቸው
ንጉሱ ቢቆጣም አልተደናገጡም
አሉ እንጂ በድፍረት ለጣኦት አንሰግድም
አዝ...

በዚህ አንመስልህም አስፈላጊ አይደለም
አምላካችን አለ ከእቶን የሚያድነን
ከእጅህ ያድነናል ፍጹም እምነት አለን
ባያድነን እንኳን የእርሱ ፈቃድ ይሁን
አዝ...
ናቡከደነጾር እጅግ ተናደደ
እቶኑም ሰባት እጅ ከፍ ብሎ ነደደ
ከእሳት ቢከቷቸው ገብርኤል ተላከ
አህዛብን በድንቅ እግዚአብሔር ማረከ
አዝ...
በእሳት መካከል ሲመላለሱ አይቶ
ንጉሱ አደነቀ ከሥፍራው ተነስቶ
የአማልክትንም ልጅ አየዋለሁ አለ
እግዚአብሔር ይመስገን በክብር ያየለ
አዝ...

እግዚአብሔር ጽዮንን (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታል ለክብሩ
ማደሪያው እንድትሆን መኖሪያ ሀገሩ
እንዲህ ካደረገ ከወደደ እርሱ
ምን ያደርጋል ማመጽ አምላክን መክሰሱ /2/
ይህቺ ለዘላለም ማደሪያ ናትና
መረጥኳት እያለ አምላክ እንደገና
እርሶ አዛውንቱ ሲባረኩ እያየን
እንዴት ማማለዷን ክብሯን ትክዳለህ
አዝ...
ድሆችን እንጀራ ያጠግባል በእርሷ
ምድርም ታበራለች በጸጋ ታድሳ
የካህናት ሞገስ የደኅንነት ልብስ
በእመቤታችን ነው ሁሉ የሚታደስ
አዝ...
ቅዱሳን በድንግል ደስተኛ ናቸው
ድንቅ ስለሆነ የእግዚአብሔር ምርጫው
የዳዊት ቀንዲል እየሱስ ክርስቶስ
ከድንግል ተወልዶ ወገኑን ሊቀድስ
አዝ...

ለዚህ ለኃጢአት ህማ(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
ለዚህ ለኃጢአት ህማ ከተሰጠ
ከህይወት መርገምን ከመረጠ
ለሞት ከተሰጠ ከንቱ ኑሮ
ማነው የሚያድነኝ ሞትን ሰብሮ
አዝ...
ሥጋ በሥጋ ህማ ይስበኛል
መንፈስ በመንፈስ ሕማ ይጠራኛል
ለየትኛው ጌታ ተገዝቼ
የቱን እመርጣለሁ አንዱን ትቼ
ኃጢአት እሰራና ይጨንቀኛል
አምላኬ ሲለየኝ ይሰማኛል
ጌታዬ ሲለየኝ ይሰማኛል
አምላኬ ሲለየኝ ይሰማኛል
አዝ...
በኃጢአት ለመኖር በዚህ ዓለም
የአምላክን ትዕዛዝ በማጣመም
በስርቆት በዝሙት በስካር
በዲያብሎስ ፍቃድ ስንኖር
የኋላ የኋላ ውርደት ነው
አምላክ በክንዶቹ ያልያዘው
የጨለማ ጉዞ ምኑ ይጥማል
አይን እያሳወረ ያዋርዳል
አዝ...
መላዕክት ከሰማይ ያለቅሳሉ
የእግዚአብሔር ቅዱሳን ያነባሉ
በኃጢአት ተማርከን ስንወሰድ
ሰይጣን ድል አግኝቶ ስንዋረድ
አዝ...

ከዳዊት አብራክ ዘርን (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
ከዳዊት አብራክ ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ
አዳም በሲኦል በቀረ በውርደት አንገቱን ቀብሮ
ዝምታ በወረረን በወደቅን ማቅ ለብሰን
ቸርነቱ በዝቶ ግን እመቤታችንን ሰጠን
ፀሀይ ክርስቶስ ወጣ ከቤተልሔም ሀገር
የእንጀራ ቤት ነችና የእኛ የፍቅር ባህር
ተበልቶ አይጠገብም የማህፀንሽ ፍሬ
ህይወት ሆኖን በላነው የማህፀንሽን ፍሬ
አዝ...
ግርማዋ የሚያስፈራ የሙሴ ቤተ መቅደስ
ተገናኙብሽ በሰላም ሰውና ሥሉስ ቅዱስ
የወልድ መንበር ነሽና ደመና የከበበሽ
የሥላሴ ሙሽራ እጹብ እጹብ ድንቅ ነሽ
አዝ.../2/

እንተ በህሊና (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

_____ቅኝት -
እንተ በህሊና እግዚአብሔር ተገብረት /2/
መንፈሳዊት ይእቲ ማርያም
በእግዚአብሔር ሀሳብ የተሰራች /2/
እመቤታችን መንፈሳዊት
ምክንያተ ድህነት አንቺ በመሆንሽ
የሲኦል ደጆችን ታንቀጠቅጫለሽ
ባንቺ የተደረገው ይሄ ታላቅ ምሥጢር
አድርጎታልና ሰይጣንን እንዲያፍር
እንተ በህሊና እግዚአብሔር ተገብረት /2/
መንፈሳዊት ይእቲ ማርያም
ስለ ሰዎች ፍቅር ልቦናሽ ያስባል
ዓለምን ለማዳን እጅሽ ይዘረጋል
በሲኦል አንድ ሰው እንዳይቀር በስቃይ
ለምህረት ይዘርጋ እጅሽ ወደ ሰማይ
እንተ በህሊና እግዚአብሔር ተገብረት /2/
መንፈሳዊት ይእቲ ማርያም

የሲኦል እሳቱን ስቃዩን እያየሽ
ለፍጥረታት ሁሉ ድንግል ሆይ ታዝኛለሽ
በአይነ ምህረቱ እንዲያየን ክርስቶስ
ለምኚልን ማርያም ፍጥረት እንዲቀደስ
እንተ በህሊና እግዚአብሔር ተገብረት /2/
መንፈሳዊት ይእቲ ማርያም
እንደሚነገረው በአበው አንደበት
እኛም እንደምናይ ስንኖር በህይወት
ወላዲተ አምላክ እሩህሩህ ፍጥረት ናት
ምህረት የምትለምን ዘወትር ሳትታክት
በእግዚአብሔር ሀሳብ የተሰራች /2/
እመቤታችን መንፈሳዊት
አዝ...

ከንቱ ነኝ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
ከንቱ ነኝ የከንቱ ከንቱ ነኝ
ዋስትና መከታ እግዚአብሔር ካልሆነኝ
ተስፋ የሚሆነኝ ህይወት የሚሰጠኝ
እግዚብሔር ብቻ ነው የሚያስተማምነኝ
አምላኬ ብቻ ነው የሚያስተማምነኝ
እኔ ንጉስ ነበርኩ በክብር ያጌጥኩኝ
ሁሉን በምድር ላይ በጥበብ ፈፀምኩኝ
የዚህ ዓለም ደስታ ምንም አላዋጣኝ
በመጨረሻው ቀን በሞት ተወሰድኩኝ /2/
አዝ...
ከፀሀይቱ በታች አዲስ ነገር የለም
ሰዎች ይደክማሉ እስከ ዘለዓለም
ጥበብን ፍለጋ ደክሜ ነበረ
ሁሉም ከንቱ ሆኖ በመቃብር ቀረ /2/
አዝ...
ከእኔ አስቀድመው የከበሩ ሁሉ
አፈር ተጭኗቸው ከመቃብር አሉ
እብደትና እውቀት ሁሉን አወቅኪቸው
ምንም ቋሚ የለም ሁሉም ከንቱ ናቸው /2/
አዝ...
ልቤን የሰጠሁት ተስፋ የጣልኩበት
አልጨበጥ ብሎኝ አለሁኝ በጭንቀት
የጥበብም ብዛት ለትካዜ ሰጠኝ
እኔ በዚህ ምድር እጅግ ጎስቋላ ነኝ /2/
አዝ...
ልቤንም ፈተንኩት በደስታ ብዛት
የዚህን ዓለም ለውጥ ጣዕሙን አቀመስኩት
ሳቅም በልቤ ውስጥ ይፍለቀለቅ ነበር
ሁሉም ከንቱ ሆነ ገብቶ ከመቃብር /2/
አዝ...

ሕማሙን ልናገር (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
ሕማሙን ልናገር አንደበት ቢያጥረኝም አንደበት ቢያጥረኝም
መቼም ምንም ቋንቋ ለዚህ አይገኝም ለዚህ አይገኝም
ከረጅሙ በአጭር ከሰፊው በጠባብ ከሰፊው በጠባብ
ስላደረገልኝ ስለ ጌታ ላስብ ስለ ጌታ ላስብ
በጌቴ ሴማኔ በአትክልቱ ቦታ በአትክልቱ ቦታ
ምድሪቱ ተሞልታ በታለቅ ፀጥታ በታለቅ ፀጥታ
የአዳምን ልጅ ስቃይ በደሉን ሊሸከም በደሉን ሊሸከም
ጌታችን አዘነ ተጨነቀ በጣም ተጨነቀ በጣም
ሐዋርያት ደክመው ተኝተው ነበረ ተኝተው ነበረ
ይሁዳ ከአይሁድ እንደተማከረ እንደተማከረ
ጭፍሮች እየመራ ጌታውን ሊያስገድል ጌታውን ሊያስገድል
የተሰራለትን ቸርነት ሳይቆጥር ቸርነት ሳይቆጥር
ፋና እያበሩ ጭፍሮቹ ሲመጡ ጭፍሮቹ ሲመጡ
ጌታን ሊያንገላቱት እንደዚያ ሲቆጡ እንደዚያ ሲቆጡ
የአምላኩን ጠላቶች መንገድ እየመራ መንገድ እየመራ
ይሁዳ ብቅ አለ ከቀያፋ ጋራ ከቀያፋ ጋራ
ሕማሙን ልናገር...
ላቡ ከግንባሩ እንደውሃ ሲወርድ እንደውሃ ሲወርድ
በታላቅ ይቅርታ ጌታችን ሲራመድ ጌታችን ሲራመድ
ምስኪኖችን ሊያድን ድሆችን ሊታደግ ድሆችን ሊታደግ
ኢየሱስ ቀረበ እንደሚታረድ በግ እንደሚታረድ በግ
ይሁዳ ጉንጮቹን ሳመው በክህደት ሳመው በክህደት
የተማከረውን የማያውቅ መስሎት የማያውቅ መስሎት
የአይሁድም ጭፍሮችም ያዙት ተናጠቁት ያዙት ተናጠቁት
በታላቅ ጭካኔ በሰንሰለት መቱት በሰንሰለት መቱት
ሕማሙን ልናገር...
በጲላጦስ ችሎት አቁመው ከሰሱት አቁመው ከሰሱት
ንጹሁ ኢየሱስ ይሙት በቃ አሉት ይሙት በቃ አሉት
እጆቹን ቸንክረው በጠንካራ ብረት በጠንካራ ብረት
በእጸ መስቀሉ ቀራንዮ ዋለ ቀራንዮ ዋለ
ወልደ እጓለ ሀያው ተጠማሁ አያለ ተጠማሁ አያለ
ሀሞትና ከርቤ ቀላቅለው አጠጡት ቀላቅለው አጠጡት
ኧረ እንዴት ጨከኑ በምሬት ላይ ምሬት በምሬት ላይ ምሬት
ሕማሙን ልናገር...
ሕማሙን ልናገር አንደበት ቢያጥረኝም
መቼም ምንም ቋንቋ ለዚህ አይገኝም
ከረጅሙ በአጭር ከሰፊው በጠባብ
ስለከፈለልኝ ስለ ጌታ ላስብ
ፍጥረታት ተጨንቀው በአይሁድ ክፋት
በየተፈጥሯቸው እርቃኑን ሸፈኑት
ጨረቃ ደም ሆነች ፀሀይም ጨለመች
አልፋና ኦሜጋ ተሰቅሎ ስላየች
ከዋክብት ረግፈው ምድር ተናወጠች
መባርቅትም ታዩ ተቆጣ ባህሩ
መለሳቸው እንጂ ስለ ግሩም ፍቅሩ /2/
ከወንበዴ ጋራ ከመሀል አድርገው
ጌታን አንገላቱት በመስቀል ላይ ሰቅለው
በቀኝ የነበረ ወንበዴው ለመነው
በመንግስትህ ጌታ አስበኝ እያለው
ሕማሙን ልናገር...
ከመስቀሉ በታች ዮሐንስን አየው
እስከመስቀል ድረስ ስለተከተለው
ታላቋን ስጦታ እናቱንም ሰጠው
ተፈፀመ አለ ጌታ ነፍሱን ሰጠ
ሞትንም ከህዝቡ በፍፁም ቆረጠ
ሕማሙን ልናገር...

እንደተለመደው ዲያቢሎስ ቀረበ
ነፍሳትን ለመብላት እርሱ እንደተራበ
ፍጡር መስሎት ነበር በመስቀል ላይ ያለው
በአራቱም ማዕዘን በንፋስ ወጠረው
በሲኦል ወረደ በኃይሉ ብርሃን
ማረከ ጌታችን የአዳም ልጆችን
በሦስተኛውም ቀን ጌታችን ተነሳ
ሞትን ድል ያረገው የይሁዳ አንበሳ
በቃ ተወገደ የሰው ልጅ አበሳ /2/
በሦስተኛውም ቀን ጌታችን ተነሳ
ሞትን ድል ያረገው የይሁዳ አንበሳ
በቃ ተወገደ የሰው ልጅ አበሳ /2/
በሦስተኛውም ቀን ጌታችን ተነሳ
ሞትን ድል ያረገው የይሁዳ አንበሳ
በቃ ተወገደ የሰው ልጅ አበሳ /2/

አቤቱ ማረን (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
አቤቱ ማረን /4/
እንደበደላችን ጌታ አትክፈለን
አቤቱ ማረን /2/
እግዚአብሔር አዳምን ስቃዩን አስቦ
በታላቅ ቸርነት ወደ እርሱ ቀርቦ
ሐዘንህ ጸባኦት ከጸባኦት ደርሷል
አምላክህ ሊያድንህ እጆቹን ዘርግቷል
አቤቱ ማረን /2/
እንደቸርነትህ አምላክ ታደገን
ዲያብሎስ በክፋት እንደተሰወረ
በከይሲ እባብ ውስጥም እንደኖረ
በሥጋ ብዕሲ አድሬ እመጣለሁ
ከሲኦል እስራት እታደግሀለሁ
አቤቱ ማረን /2/
እንደበደላችን ጌታ አትክፈለን
አዳም በግዞት ውስጥ ተጥሎ በፍዳ
ይከፍል ነበረ የውርደትን ዕዳ
በእግረ አጋንንት ይጠቀጠቅ ነበር
ከነ ልጅ ልጆቹ በጨለማ ሲኖር
አቤቱ ማረን /2/
እንደቸርነትህ ጌታ አስበን
አቤቱ ማረን /2/
እንደበደላችን አታስብብን
አቤቱ ማረን /2/
በደላችንን ጌታ ተውልን
አቤቱ ማረን /2/
እንደበደላችን አታስብብን

እንዴት እንዲያጠፉት (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
እንዴት እንዲያጠፉት ካህናት መከሩ
ያመነቱ ነበር ህዝብን እየፈሩ
ሰይጣን በይሁዳ ገብቶ ነበርና
አሳልፎ እንዲሰጥ ልቦናውም ጸና
ከመቅደስ አዛዦች ከካህናት ጋራ
ስለ ጌታ መሞት ባንድ ላይ አወራ
ካህናት በደስታ ይሁዳን አቀፉት
አምላኩን እንዲያሲዝ ሰላሳ ብር ሰጡት
አዝ...
ህዝብ በሌለበት በአሳቻ ሥፍራ
ጌታን እንዲያሲዘው አደረገ ሴራ
ኧረ እንዴት ጨከነ ይሁዳ አንጀትህ
ጌታን ያስገደልከው እንደዚያ ሲወድህ
አዝ...
በረከቱን ከእጅህ ሥልጣኑን በራስህ
ሊሰጥህ አስቦ አየሱስ ሊያከብርህ
ሰማያዊ ሀብትን ሰማያዊ ጸጋ
አድሎህ ነበረ አልፋና ኦሜጋ
አዝ...
የቃኤል መስዋዕት የኤሳው ብኩርና
ጌታውን የሚሸጥ ከፍጡር ሆነና
በሰላሳ ዲናር በሚጠፋው ብዕል
እንዲህ ያለ ጌታ ኧረ እንዴት ይከዳል
አዝ...
የቃኤል መስዋዕት የኤሳው ብኩርና
ጌታውን የሚሸጥ ከፍጡር ሆነና
በሰላሳ ዲናር በሚጠፋው ብዕል
እንዲህ ያለ ጌታ ኧረ እንዴት ይከዳል
አዝ...

ዘመኑ ሲደርስ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
ዘመኑ ሲደርስ አዳምን አሰበው
ወደ ዓለም መጣ ከሲኦል ሊያድነው
ከድንግል ማርያም በግርግም ተወልዶ
ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ወስዶ
ቃሉን ከሥጋ ጋር ፍፁም አዋህዶ
በተለየ አካሉ ከሰማያት ወርዶ
ሰባ ሰገል መጡ በኮከብ ተመርተው
እረኞች ዘመሩ በደስታ ሆነው
መላዕክት በሰማይ ሽብሸባ ጀመሩ
አምላክ ስለጠራን ስለ ግሩም ፍቅሩ
ቃሉን ከሥጋ ጋር ...
ጌታችን አደገ በሰው መጠን ሆኖ
ከኃጢአት በስተቀር ሁሉን አከናውኖ
የጌታችን መንገድ አስተካክሉ እያለ
በኤልያስ መንፈስ የሚናገር አለ
ተብሎ በትንቢት የተነገረለት
መጥምቁ ዮሐንስ ተነሳ በድንገት
ቃሉን ከሥጋ ጋር ...
የውሃ ጥምቀት ያጠምቅም ነበረ
ስለ ጌታ መምጣት እየተናገረ
ያን ጊዜ ኢየሱስ በውሃ ሊጠመቅ
ከገሊላ መጣ እጅግ የሚያስደንቅ
ቃሉን ከሥጋ ጋር ...

ዮሐንስም ፈጥኖ በታላቅ ትህትና
ጌታችን ወደርሱ ሲመጣ አየና
እኔ በአንተ ጌታ ልጠመቅ ይገባል
ወደ እኔ ልትመጣ ኧረ እንዴት ይቻላል
ቃሉን ከሥጋ ጋር ...
ተጠምቆ ሲወጣ ሰማያት ተከፍተው
የአብ ድምጽ መጣ ምስክር የሆነው
የምወደው ልጄ ይሄ ነው እያለ
አብም ተናገረ በደመና እያለ
ቃሉን ከሥጋ ጋር ...
በርግብ ተመስሎ መንፈስ ቅዱስ መጣ
ከዚህም በኋላ ጌታም እንደወጣ
ገዳመ ቆሮንቶስ ከበረሃ ሄደ
አርባ ቀን ከሌሊት መጾምን ወደደ
በዲያብሎስ ያኔ ጌታ ተፈተነ
ሰይጣንም እንደጢስ እንደጉም በነነ

የአባቶች አለቃ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
የአባቶች አለቃ ያዕቆብም አለ
ለቅሶውም ታደሰ እንባውም አየለ /2/
ለምን አታለቅስ ድንግል ስለልጇ
ስላሳደገችው ታቅፋ በእጇ /2/
በስደት መከራ ስለተቀበለች
ከሀዘንም በላይ ድንግል አልቅሳለች ድንግል አልቅሳለች
ከልደቱ አንስቶ ስቅለቱንም ሳይቀር
ስቃይን ቀምሳለች በምድር ስትኖር በምድር ስትኖር
በተወዳጅ ልጇ እጅግ ለከበረው
ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ለተሸከመችው ለተሸከመችው
ወልዳ ላልሳመችው ራሄል ስታለቅስ
የድንግል ሀዘኗ እንዴት እጅግ አይብስ እንዴት እጅግ አይብስ
አዝ ...
ከሀገር ወደ ሀገር የተንከራተተች
ድንግል ስለ ልጇ እጅግ አልቅሳለች እጅግ አልቅሳለች
ልብሱን ሲያራቁቱት በአይኗ በማየቷ
በሐዘን ተላውሷል የእመቤቴ አንጀቷ የእመቤቴ አንጀቷ
በሰላሳ ዲናር ልጇን ሲሸጥባት
ይሁዳን በማየት አንብታለች በእውነት አንብታለች በእውነት
ጌታዋን ሊገድሉ አይሁድ ሲማከሩ
እንባዋ ወረደ ስለ ግሩም ፍቅሩ ስለ ግሩም ፍቅሩ
አዝ ...
በአይሁድ አደባባይ ጌታ ተከሰሰ
ምንም ቢጠይቁት ምንም አልመለሰ ምንም አልመለሰ
እኔ ልንገላታ እኔ ልከሰስ
አንተ ምን አጠፋህ አንተ ምን በደልክ አንተ ምን በደልክ
እሮብ መከሩበት ዓርብ ተሰቀለ
ድውይ ፈወሰ እንጂ ከቶ ምን በደለ ከቶ ምን በደለ
መቼም በዚህ ዓለም ንጹህ አይወደድ
ፍርድ ተንጋደደ በጲላጦስም ዘንድ በጲላጦስም ዘንድ
አዝ ...

ጻድቃን ስለጌታ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
ጻድቃን ስለጌታ እንዲህ ተወያዩ
የአምላክን መምጣት በርቀት እያዩ
በአምደ ደመና አየዋለው ያለው
ሙሴ መሬታዊው እንዴት ይመርምረው
ኢሳይያስ ልኡሉን ማየትማ አየው
አየለበት እንጂ እንዳይመረምረው
ኃይሉን ክህሎቱን ከሩቅ ተመልክቶ
አየዋለው አለ በመንፈስ ተሞልቶ
አዝ ...
ጌታውን ቢያጠምቅም ዮሐንስ በክብር
የአምላኩን ባህሪ አልቻለም መመርመር
ሰማዩ ሲከፈት ደመናው ሲናገር
ዮሐንስ በፍርሃት አልቻለም መናገር
አዝ ...
ማርያም ግን አምላኪን ስለወለደችው
በአይኗ አየችው ጡትም አጠባችው
በማህፀኗ እቅፍ ጌታን ወሰነችው
ለፍጥረታት ዓለምም መሰላል ሆነችው
አዝ ...
ባይመረመርም ባህሪው በሰዎች
በሥጋ ማርያም ታየ የምስራች
በሥጋ ማርያም ተገለጠ ለእኛ
በአባቱ ክብር መጣልን ወደእኛ
አዝ ...

እግዚአብሔር ምስክር (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
እግዚአብሔር ምስክር የሆነለት አቤል
በልጣ ነው እምነቱ ከወንድሙ ቃየል
እርሱ ጻድቅ ሰው ነው ተባለለትና
ከምድር አበራች የእምነቱ ፋና
ያለ ሀይማኖት ደስ ማሰኘት የታል
ያልጸና ያልተጋ እንዴት ይለወጣል
ኖህ እንኪን በሀይማኖት ትንቢት መናገሩ
ህዝቡን መምከሩ ነው መርከብ እንዲሰሩ
አዝ...
የታላቁ አባት አብርሃም በሀይማኖት
በሰማይና ምድር አንጸባራቂ ናት
ልጁን ይሰዋ ዘንድ ለእግዚአብሔር ታዘዘ
ሀዘንም አልገባው ምንም አልተከዘ
አዝ...
ሙሴ ምስፍናውን በሀይማኖት ለወጠ
የተስፋ ቃሉንም በእውነት አስበለጠ
በደረቅ መሬት ላይ በእምነት ተሻገሩ
ግድግዳ ሆነና ማዕበል ባህሩ
አዝ...
እነዚህ ሁሉ ግን በሀይማኖት ሞቱ
የተስፋውን መምጣት ሲያስሱ በብርቱ
ከሩቅ ተሳለሚት ምጽአተኞች ሆነው
እኛ ግን ተስፋውን አየነው ዳሰስነው
አዝ...

ስምህ ለዘለአለም (ዘማሪ ይልማ ታይሉ)

ቅኝት -

ስምህ ለዘለአለም ምስጉን ስለሆነ ምስጉን ስለሆነ (2)
ፍጥረት በአካቴት ስቡህ ብሎ ዳነ ስቡህ ብሎ ዳነ ስቡህ
ስምህ ለዘለአለም ምስጉን ነው ስቡህ
መኸርን ለሰው ልጅ ምግብን የሰጠህ
የተራበችው ነፍስ ከምድር በረከት
በመገብከት ጊዜ ታመሰግናለች ታመሰግናለች ስቡህ
ምስጉን ነህ /2/ ስቡህ በሰማያት ስቡህ በሰማያት
የምትመሰገን በፍጥረት አንደበት
በፍጥረት አንደበት ስቡህ
እንዳንተ ያለ ማነው ወቅት የሚያፈራርቅ
ምድርን በበረከት ሰማዩንም በጽድቅ
ተራሮች በአበባ ወንዞች የሚሞሉት
ስለጠገቡ ነው ከስጦታህ ብዛት
ከስጦታህ ብዛት ስቡህ
ስምህ ለዘለአለም...
የሚበራው ገጹ ፊቱ የሚያወዛው
ከአንተ በሚቀዳው ከቸርነትህ ነው
የምድር ልምላሜ የፍጥረታት ደስታ
ሲዘምር ይውላል ለለጋሹ ጌታ
ለለጋሹ ጌታ ስቡህ
ምስጉን ነህ /2/ ስቡህ በሰማያት ስቡህ በሰማያት (2)
የምትመሰገን በፍጥረት አንደበት
በፍጥረት አንደበት ስቡህ
እንዳንተ ያለ ማነው ወቅት የሚያፈራርቅ
ምድርን በበረከት ሰማዩንም በጽድቅ
ተራሮች በአበባ ወንዞች የሚሞሉት
ስለጠገቡ ነው ከስጦታህ ብዛት
ከስጦታህ ብዛት ስቡህ
ስምህ ለዘለአለም...
ምስጉን ነህ /2/ ስቡህ በሰማያት ስቡህ በሰማያት (2)
የምትመሰገን በፍጥረት አንደበት
በፍጥረት አንደበት ስቡህ

አልፈርድም እኔ (ዘማሪ ይልማ ታይሉ)

ቅኝት -

አልፈርድም እኔ በንም በደል በማንም ታጢአት
በፈርድኩበት እንዳልመዘን ጌታ ሲመጣ በታይል በስልጣን
በቸርነቱ አምላክ ባይተወው በደሌን ሁሉ
ውስጤ ቢፈተሽ በተሰጠኝ ሕግ በቅዱስ ቃሉ
በምን ምግባሬ በሰው እፈርዳለሁ አይኔን አቅንቼ
በደሌ በዝቶ ለራሴ ሳላውቅ በታጢአት ሞቼ
አዝ...
ይልቅ የአንዱን ሸክም ሌላው ሰው አዝሎ መጓዝ ይሻላል
መፍረድ ከመጣ አንድም ሰው አይድን ሁሉም በድሏል
ወንድም ወንድሙን እየከሰሰ ለፍርድ አቁሞ
አህዛብ ያያል በንትርኩ እጅግ ተገርሞ
አዝ...
ክርስቲያን ሆኖ ከወንድሙ ጋር እየተጣላ
ዓለም ዳኝችን በፀብ ፍርድ ቤት ታረቁ ብላ
ክርስቲያን ሆነን በአሕዛብ መሀል እየተካሰስን
አምላክ አዘነ የመስቀል ምስል ዓላማ ስተን
አዝ...
መቼ ከሰሰ የከሰሱትን የገረፉትን
አይተናል እንጂ ለጠላቶቹ ምህረት ሲለምን
ለጽድቅ ሥራ ለእውነት ብለን መጥተናል እንጂ
ማነው የሾመን በወንድሞች ላይ አድርጎ ፈራጅ
አዝ...
መቼ ከሰሰ የከሰሱትን የገረፉትን
አይተናል እንጂ ለጠላቶቹ ምህረት ሲለምን
ለጽድቅ ሥራ ለእውነት ብለን መጥተናል እንጂ
ማነው የሾመን በወንድሞች ላይ አድርጎ ፈራጅ
አዝ...

ማኔቴቄልፋሬስ (ዘማሪ ይልማ ታይሉ)

ቅኝት -

ማኔቴቄልፋሬስ /4/
የሰዎች መሰረት እዩት ሲገረሰስ
ማኔቴቄልፋሬስ /2/
በእውነት መስፈሪያ ተመዝነህ ነበር
የልብህ ትዕቢት ግን አዘቀጥክ እንዳፈር
ቆረጠው ዘመንህን ቅጥፈቱ አጀበህ
በለጋነት ዕድሜህ ወደሞት ተጠራህ
አዝ...
ዳንኤል የታለ አሁን የሚገስጽ
በመንፈሱ መብራት ወገንን የሚያንጽ
አብነት የታለ በጸሎት የተጋ
የህሊናን ወጀብ በፍቅር የሚያረጋ
አዝ...
አምላክ ያላነፀው የእንቧይ ካብ ተንዶ
የትናንቱ ትልቅ ማምሻውን ተዋርዶ
እንደ አበባ ፈክቶ ሲረግፍ እያየነው
ዛሬም ልቦናችን ለትዕቢት ጽኑ ነው
አዝ...
ቀይ ባህር ሲሰጥም ያለፈው ፈርኦን
ዛሬም የአምላክን ህዝብ አንለቅም ብለን
እንደጠጣር አለት ጠንክሮ ልባችን
ደግሞ ተፈጥረናል ፈርኦን ነን ብለን
አዝ...

ኢየሱስም አለ (ዘማሪ ይልማ ታይሉ)

ቅኝት -

ኢየሱስም አለ ሐዋርያትን ጠርቶ
ሥርዓት ሊያስተምራቸው ከሁሉ ለይቶ
ይህን የሀዲስ ኪዳን የፍቅር ስጦታ
ታላቅ ሰንሰለት ነው እጅግ የበረታ
ሥጋዬንም ብሉ ደሜንም ጠጡት
ስለሚሰጣችሁ የእውነት ህይወት
ሂዱና አዘጋጁ የፋሲካን መአድ
ይገባዋልና ንጹህ በግ ሊታረድ

ደቀ መዛሙርቱ ጴጥሮስና ዮሐንስ
በፍጥነት ተጓዙ እከተማው ድረስ
አዩና ማድጋ የተሸከመ ሰው
ከተማ ሲደርሱ ሄደው ተከትለው
እጅግ ተደሰተ የቤቱ ባለቤት
ጌታው በአዳራሹ ስለተገኘለት
አዝ...
ሰዓቱ ሲደርስ የተወሰነለት
ከማዕድ ሊቀመጥ ተገኘ ከዚያ ቤት
የቤቱ ባለቤት እጅግ የታደለው
ስምኦን ነበረ ጌታን የጋበዘው
እጅግ እመኝ ነበር ከመከራ በፊት
ከመአድ ልቀመጥ ከእናንተ ጋር በእውነት
የእግዚአብሔር መንግስት እስክትመጣ ድረስ
ከወይኑም አልጠጣም ከመአዱም አልቀምስ
አዝ...
ህብስቱንም ቆርሶ ባርኮ አደላቸው
ስለ እናንተ የሚሰጥ ሥጋዬ ይሄ ነው
ወይኑንም ባረከ አንስቶ ሰጣቸው
ስለ እናንተ የሚፈስ ደሜ ነው አላቸው
ይህን የሐዲስ ኪዳን የፍቅር ስጦታ
ታላቅ ሰንሰለት ነው እጅግ የበረታ
ሥጋዬንም ብሉ ደሜንም ጠጡት
ስለሚሰጣችሁ የእውነት ህይወት
መዝሙርም ዘመሩ እጅግ የተዋበ
ጌታም እግር ሊያጥብ ውሃን አቀረበ
ጴጥሮስ ግን ፈጽሞ አታጥበኝም አለ
ትሁት ነበርና እየተቻከለ
አዝ...
እግርህን ካላጠብኩ ዛሬ በዚህ ምሽት
ዕጣ ክፍል የለህም ከእኔ ጋራ በእውነት
እንዲህ ባለው ጊዜ ጴጥሮስ ደነገጠ
መላ ሰውነቱን ለመታጠብ ሰጠ
እኔ ጌታ ስሆን አምላክ የምከብር
እግራችሁን ሳጥብ ስኖር ከእናንተ ጋር
ይህንን ምሳሌ ተከተሉ በፍቅር
የእኔ ስጦታ ነው በትህትና መኖር
አዝ...

ኑ ተመልከቱልኝ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -

ኑ ተመልከቱልኝ የአምላክን ቸርነት
አንደበት የለኝም ስራውን ለማውራት
ሰላምና ፍቅር በልቤ ተሞልቷል
በምን ቋንቋ ላውራው ቃላቶች ያጥሩኛል /2/
ሰማይ ጉም ቢመስል ቀለያት ቢናጉ
የጥፋት አጋንንት እጅጉን ቢተጉ
እኔን የሚጠብቅ ኃይሉን አይሰውርም
እረኛዬ ከእኔ ዘወትር አይርቅም /2/
አዝ...
ፍርሃት ከኔ ራቅ ጨለማም ተወገድ
በጌታዬ ትምክህት እንደልቤ ልሂድ
የሞት አበጋዞች ተስፋችሁ ጨልሟል
እግዚአብሔር ሊያድነኝ ከአጠገቤ ቆሟል
አዝ...
ቅዱሳን በሙሉ ለእኔ ዘብ ቆመዋል
ወደእነርሱ ጎብረት ሊስቡኝ ጓጉተዋል
ዘወትር በመዓልት ድንግል ትመጣለች
በብርሃን እጆቿ ትባርከኛለች
አዝ...

ተዋህዶ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ተዋህዶ ተዋህዶ ሰማያዊት
የጸናች እምነት /2/ ሃሌ ሉያ
ተዋህዶ ተዋህዶ መንፈሳዊት
የመንፈስ መብራት /2/ ሃሌ ሉያ
ተዋህዶ ተዋህዶ መለኮት
ንጽሕት እምነት /2/ ሃሌ ሉያ
ባንቺ ቢያምኑ /2/ ቅዱሳን
ድል ነሱት ሰይጣንን /2/ ሃሌ ሉያ
ባንቺ ቢያምኑ /2/ ሰማዕታት
ተፈተኑ በእሳት /2/ ሃሌ ሉያ
እንደወርቅ /2/ ተፈትነው
አበራ ገድላቸው /2/ ሃሌ ሉያ
እንኑር /2/ በእምነታችን
በተዋህዶ መክበሪያችን /2/ ሃሌ ሉያ

የጴጥሮስን እንባ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት-

የጴጥሮስን እንባ ስጠኝ እልሀለሁ
ኃጢአቴን ልናዘዝ ፍቅርህን እያየሁ
በሞት ጥላ ውስጥ እንኳን ብሄድ ጌታ ሆይ /2/
ልቤን በፍቅር ውሃ እጠበው እባክህ
ቸርነትህ በዝቶ ምህረት ቢያሰጠኝ
እጆቼን ዘርግቼ እማፀናለሁኝ
ደምህ የፈሰሰው ለእኔ ስለሆነ /2/
በኃጢአት ልትወተኝ ልብህ አልጨከነ
አዝ...
ዓለማዊ ምግባር ልቤ ቢከተልም
ከዚህ ሁሉ ማዳን ጌታ አይሳንህም
ኃጢአት እየሰራሁኝ ባስቀይምህም /2/
በሂሶጵ እርጨኝ ጌታ እጠበኝ እባክህ
አዝ...
ዲያብሎስ ያመጣው ጸጸት የውድቀት ነው
የይሁዳ ምሬት የሞት ነው ፍጻሜው
ይህንን መማረር እኔ አልፈልግም /2/
የውድቀት ጉዞ እንጂ ትንሣኤ የለውም
ጴጥሮስ አባ ብሎ የተማፀነበት
ፍቅሩን በንስሐ ስቦ ያመጣበት
ፍጻሜው የሚያምር ንስሐ ስጠኝ /2/
የለቅሶ አምሀ የእንባ ህይወት ስጠኝ
አዝ...

ያ ድሀ ተጣራ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ያ ድሀ ተጣራ እግዚአብሔርም ሰማው
ደርሶ ስላንኪኪ ከፀባኦት እንባው
አምላክ በቸርነት በምህረት ጐበኘው
ባለቀሰ ጊዜ ግራ የገባው ሰው
መሻትህ ብቻ ነው የሚፈለግብህ
እግዚአብሔርን ጥራ እመን ትድናለህ
ንገረው ችግርክን የውስጥህን ብሶት
ይሸረዋልና አስፈሪውን ህይወት
ግራ የተጋባው የተከፋው ገጽህ
ይበራል በጸሎት አምላክህን ጠርተህ
መሻትህ ብቻ...
ለወገን ለዘመድ ያስቸገረው መላ
ሲቀል ታየዋለህ ካነባህ በኋላ
ሳግና ንዴትህ ይቀራል ይሻራል
በርሱ ፈንታ ሰላም ፍቅር ይከብሃል
መሻትህ ብቻ...
በከንቱ መጨነቅ እራስን መጥላቱ
ነውና የአጋንንት መግቢያ ምልክቱ
ሐዘን በህሊናህ በፈሰሰ ጊዜ
ንገረው ለአምላክህ የልብህን ትካዜ
መሻትህ ብቻ...
በከንቱ መጨነቅ እራስን መጥላቱ
ነውና የአጋንንት መግቢያ ምልክቱ
ሐዘን በህሊናህ በፈሰሰ ጊዜ
ንገረው ለአምላክህ የልብህን ትካዜ
መሻትህ ብቻ...

እውነት ስለሆነ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

እውነት ስለሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ
ዋለ በአደባባይ ሲሰደብ ሲከሰስ
የሐሰት ዳኝነት አምላክን ወቀሰው
ህይወት ሰጠን እንጂ ጥፋቱ ምንድነው
ከቃሉ እብለትን ባያገኙበትም
ዝምታውን አይተው አላዘኑለትም
ባላወቁት መጠን ጠሉት ካለበደል
ጥፋቱ ምን ይሆን የሚያደርስ ከመስቀል/2/
አዝ...
የልቡን ትህትና ፍቅሩን ሳያስተውሉ
ቸሩ ጌታችንን አቻኩለው ሰቀሉ
እሩሀሩሁን ጌታ ቸንክረው ሰቀሉት
ሞትን አስወግዶ ቢሰጣቸው ህይወት /2/
አዝ...
ስለቸርነቱ ስድብን ከፈሉት
ስለርህራሄው የእሾህ አክሊል ሰጡት
ሀሞትና ከርቤ ሆምጣጤ ደባልቀው
መራር አስጎነጩት ጨክኖ ልባቸው/2/
አዝ...
ፈውስን ለሰጣቸው ልባቸውን ሞልተው
አሉት ወንበዴ ነው ስቀለው ስቀለው
ከእጁ በረከትን የተሻሙ ሁሉ
ይጮሁ ነበረ ይገደል እያሉ /2/
አዝ...

በኃይልና ጥበብ (ይልማ ኃይሉ በገና)

በኃይልና ጥበብ ትልቆቹን ትቶ
ንጉሥ አደረገው ደሀውን ቀብቶ
በእረኝነት ሜዳ ልቡን መረመረው
እንደልቡ ሆኖ ዳዊትን ቢያገኘው/2/
ምንም ታናሽ ቢሆን አካሉ ቢኮስስ
የተገባ ነበር በእግዚአብሔር ፊት ሊነግስ
የሰው ዓይን ያልሞላው ትንሽ ብላቴና
አባት ሆኖ ነበር በእግዚአብሔር ህሊና/2/
አዝ...
የጌታችን እናት ታላላቅ ቅዱሳን
ይልቁን ጌታችን የሰው ልጆች መድኅን
በዓለም ሊወለድ ከዳዊት በሥጋ
ተስፋ ተሰጥቶታል እንዲሁ በጸጋ
እንዲሁ በጸጋ እንዲሁ በጸጋ
አዝ...
የዋህ ስለነበር ዳዊት በህይወቱ
ከበሩ ሲገባ ፈላለት ዘይቱ
ሳሙኤል አክብሮ በእግዚአብሔር ፊት ቀባው
አምላኩ ቢወደው ታላቅ አደረገው/2/
አዝ.....
የምሥጋና ሃብቱን ከንግሥና ጋራ
አጣምሮ ሰጥቶታል መልካም እንዲሠራ
ሌትና ቀን ሳይል ምሥጋና ሲመገብ
እየደረደረ መሠንቆ በገና /2/
አዝ...
ሌትና ቀን ሳይል ሲመገብ ምሥጋና
እየደረደረ መሠንቆ በገና
እራዕይ ተሰጥቶት ከላይ ከደመና
ድንግልን አሳየው አንገቱን ሲያቀና /2/
አዝ...

ወንበዴ የነበርኩኝ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -

ወንበዴ የነበርኩኝ ሀገር ያሰለቸሁ
በመስቀል ላይ ሆኖ ታሪኬን ለወጡው
አስበኝ ስላልኩት በኋላ ስትመጣ
ገነትን ለማየት የመጀመሪያው ሰው ሆንኩኝ ባለዕጣ
አቤት ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
ግሩም ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
አስበኝ ስላልኩት አሰበኝ ጌታዬ
ወንበዴ የነበርኩኝ ስርቆት ነው ሙያዬ
በመስቀል ላይ ሆኖ ህዝቡን ያስብ ነበር
እኔስ አላየሁም (2) እንዲህ ያለ ፍቅር
ግሩም ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
ኃያል ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
አልታይም ብዬ ኃጢአትን ስሰራ
ተመለስ ይለኛል ስሜን እየጠራ
እንዳልሞትበት ነው በኃጢአት ታስሬ
ፍቅሩን አልዘለቀውም (2) እንደዚህ ዘርዝሬ

አቤት ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
ግሩም ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
ታያል ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
ግሩም ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
መከራ ሲከበኝ መጥቶ ያጽናናኛል
በሐዘኔ ጊዜ እግዚአብሔርም ያዝናል
አይኑ ከእኔ አይርቅም ጥበቃው አይጠፋም
ስሙን እጠራለሁ (2) በጌታዬ አላፍርም
ግሩም ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
ታያል ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
ግሩም ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
አቤት ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
ታያል ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር
ግሩም ፍቅሩ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር

የተወደደ ስምሽ ማርያም (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
የተወደደ ስምሽ ማርያም
እንዳንቺ ንጹህ በዓለም የለም
አሳስቢልን እንዲምረን መድኃኔዓለም
በንጽህናሽ በመመረጥሽ
ድንግል በእውነት እፁብ ድንቅ ነሽ
አሳስቢልን እንዲምረን መድኃኔዓለም
አዝ...
ፍጥረታት አንቺን ይማፀኑሻል
ከሲዖል ዓለም አውጪን ይሉሻል
አሳስቢልን እንዲምረን መድኃኔዓለም
አዝ...
አስራትሽን ኢትዮጵያን
ጡብቂልን ድንግል ህዝቧን
አሳስቢልን እንዲምረን መድኃኔዓለም

ወዳንቺ የመጣው (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
ወዳንቺ የመጣው በብሩህ ደመና
ከሦስቱ አካል አንዱ ክርስቶስ ነውና
የጠፋ በግ አዳም ታደሰ በጌታ
ባንቺ ተፈፀመ የሰው ልጆች ደስታ
በደይን የተባለች ሄዋን ተደሰተች
የደስታ መፍለቂያ አንቺን ስላገኘች
የበረከት ፍሬ ካንቺ ተገኘልን
የወይን ቦታ ነሽ ድንግል እናታችን
አዝ...
ወልድም ባህሪሽን ባህሪ አድርጐት
ለፍጥረታት ጌታ መዓዛሽ ተስማምቶት
ካንቺ ይወለድ ዘንድ ፍፁም ሊላላክሽ
በጥቂቱ አደገ ተልኮና ታዘሽ
አዝ ...
ከድንግልና ጋር አንድ የሆነ ሀሊብ
በሩካቤ ሳይሆን በብስራት እንደ ንብ
ከሆድ መጥበብ ጋራ የመለኮት ስፋት
አንቺ ሆነሽ ሳለ ታናሿ ሙሽሪት
አዝ ...
በፍጡር ህሊና የማይመረመር
እፁብ ነው ድንቅ ነው የመፅነሷ ነገር
እሳተ ነበልባል በሆድሽ ውስጥ ሲያድር
ነደ ነበልባሉ አልፈጀሽም ነበር
አዝ ...

ልዑለ ባህርይ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
ልዑለ ባህርይ እግዚአብሔር ወደደሽ
በልዕልና ሆኖ ከአርያም አየሽ
አራቱን ማዕዘን ምድር ተመልክቶ
እንዳንች ንጽሕና አላገኘም ከቶ
መአዛሽ ደስ አለው ለአብ ቅድስናሽ
ስለዚህ እግዚአብሔር ከሰማይ ወደደሽ
ወዳንቺ ሰደደው አካላዊው ቃልን
ቅድመ ዓለም ያለ እናት የተወለደውን
አዝ...
እግዚአብሔር አብ አየ ምሥራቅና ምዕራብ
ፍለጋ አሻተተ ሰሜንና ደቡብ
እንዳንች ያለ ከቶ አላገኘምና
እንመስልሻለን በብሩህ ደመና
አዝ...
ስለተወደደ ልጇ ሆይ መአዛሽ
የወልድ ማደሪያ የቃል አዳራሽ ነሽ
የአባትሽን ቤት እርሺ ልጇ ተብለሻል
በአርያም ስምሽ ንጽሕናሽ ተወዷል
አዝ...
በነቢያት አድሮ በተስፋ ያጽናናው
ከድንግል በሥጋ የተወለደው ነው
መአቱን አርቆ ምህረቱን አብዝቶ
አዳምን ያዳነ ከሲኦል አውጥቶ
አዝ...

ስራህ ብዙ(ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
ሥራህ ብዙ መድኃኔዓለም ሥራህ ብዙ
ቸርነትህ ፍቅርህ ብዙ የኔ ጌታ ሥራህ ብዙ
አዝ...
አዕዋፉ አናብርቱ ተሰብስበው
በማለዳ ከእንቅልፋቸው ተቀስቅሰው
ይጮሀሉ ወደሰማይ ያዜማሉ
ሥራህ ብዙ የእኛ ጌታ ተመስገን ሊሉ
አዝ...
የፍጥረትህ ምስጋናቸው ወደ ሰማይ እየወጣ
በረከትን ፍቅርን ስቦ እያመጣ
ስንባረክ በቸርነት ስንጐበኝ
ሥራህ ብዙ መድኃኔዓለም እላለሁኝ
አዝ...
ምሥጋና አለህ መድኃኔዓለም ከደመነፍስ
ከግዑዛን ፍጥረታትህ ምሥጋና አለህ
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አምላክ ልዩ ሲሉህ
አዝ...

ኢትዮጵያ ሆይ ተነሽ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት - ዋኔን
213 24552 42421-11553 23
213 24552 42342 22-2 42
213 24552 42421-11553 23
213 24552 42342 22-2 42

213 24552 42342 22-2 42(በበገና)

15-113 42 42421-11553 23
15-113 42 42452-22-2 42
15-113 42 42421-11553 23
15-113 42 42452-22-2 42

ኢትዮጵያ ሆይ ተነሽ ክብርንም ልበሽ
በአዲስ ምሥጋና ይመላ ልብሽ
የተወደደ ነው በእግዚአብሔር ህዝብሽ/2/
በበገና...
ንብረቱ ጠፊ ነው ከንቱ የማይረባ
በግፍና ቅሚያ በአመፅ ሲገነባ
ሲሳይሽ ብዙ ነው ከአምላክ የተሰጠሽ
በረከት ለማግኘት መሥራት ነው ጠንክረሽ
አዝ...
የአህዛብ ብልጽግና አያስቀናሽ ፍፁም
ኃላፊ ጠፊ ነው ምኞቱም ዓለሙም
ደመና ነውና ይበናል በቅጽበት
በግፍ የተገኘ የተከማቸ ሀብት
አዝ...
ይልቅ በቅንነት በሰላም ለሰራ
ሲሳዩ ብዙ ነው ክብሩም አያባራ
ጉቦና ፍትህን ማጣመም እንዳንለምድ
ከወንጌሉ ጋራ አለብን መዛመድ
አዝ...
እግዚአብሔር ያለው ሰው በእርሱ የታመነ
ከግፍ ሥራ ሕመም አካላቱ ዳነ
ክርስቲያነኝ ብሎ ጉቦ የሚበላ
የሚያቃጥል እሳት ያገኘዋል ኋላ
አዝ...
በመታመን ፀጋ ይጠራ ስማችን
እውነተኛ እንሁን ለውድ ሀገራችን
የራሱን ሳይሻ ለሀገር የሚያስብ ሰው
በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ነው
አዝ...

ስለ ቸርነትህ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት - ስለቸርነትህ
231542-3 45-13-42 /2x/
231542-3 231515 /2x/

ስለ ቸርነትህ ጌታ ተመስገን
ስለ ፍፁም ፍቅርህ አምላክ ተመስገን
ማነው የገመተ ከዛሬ መድረስን
ልብሱ ሳይነካ በእሳቱ ወላፈን
ባህሩን አሻግሮ ማዕበል አቁሞ
እርሱ ያውቅልናል ለመጪው ቀን ደግሞ
ሃሌ ሃሌ ሉያ መስዋዕት እናቅርብ
ጌታ ይፈልጋል የተሰበረ ልብ
ክርስቶስ ከሌለው ፍቅር ላይኖረው
ሰላም ሰላም ይላል ፍጥረታዊው ሰው
ሰላም ሰላም ይላል የዘመኑ ሰው
የኢየሱስ ነገር ለሚጠፉት ሁሉ
የመስቀሉ ነገር ለሚጠፉት ሁሉ
ሞኝነት መስሏቸው ክህደት ተሞሉ
የስንፍና አመል እያናወዛቸው
መጸም መጸለዩ ይጎዳናል ብለው
አምላክን ቢክዱ ፍቅርን ነፈጋቸው

ለእኔስ ልዩ ነች (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት - ስለቸርነትህ
233-42 2-42423-15-13 31-31 (2x)
3-42 2-42423-15-13 31-31
233-42 2-42423-15-13 31-31
233-42233-42 2-42 (2x)

233-42 233-42 2-42(በበገና)

233-42 2-42423-15-13 31-31 (3x)
233-42233-42 2-42

ለእኔስ ልዩ ነች ድንግል ማርያም
ለእኔስ ልዩ ነች እመብርሃን
ፈልጌ /2/ ላንቺ ምሥጋና አላገኘሁም /2/
በበገና...
ልቤ ሲያበቅል የኃጢአት አረም
ውስጤ ሲሸፍት አልተወችኝም
ከቤተ መቅደስ እጇን ዘርግታ
ትጠራኛለች የእኔ መከታ
አዝ...
የሆዴን ሀዘን የልቤን ምሥጢር
እነግርሻለሁ አንድም ሳይቀር
የምትሸሸጊ የሕዝብን ኃጢአት
ለእኔስ ልዩ ነሽ ድንግል አዛኝት
አዝ...
ጣዕሙ ልዩ ነው ከእርሷ ጋር መኖር
ድንግልን ይዤ መቼም አላፍር
ወደ ጽድቅ ህይወት ትወስደኛለች
ድንግል ማርያም ለእኔ እናቴኮ ነች
አዝ...
በሀዘን ስሰበር ማንን እጠራለሁ
ውስጤ ሲደማ ለማን እነግራለሁ
ከኃጢአት እድፍ ንፁህ መሆኛዬ
አንቺ ነሽ ድንግል የኔስ መጽናኛዬ
አዝ...
የኃጢአት ቁስል ያለአንቺ አይጠግም
ልጅሽ ሳይፈቅድ በህይወት አልኖርም
ከልጅሽ ሌላ መድኅን የለኝም
ከጸሎት በቀር ፍፁም አልድንም
አዝ...

በህይወቴ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት - ስለቸርነትህ
23-42 2 14-15 5
15-11231 1 2223 42 2

2223 42 2 14-15-42 2
2223 42 2 2315-11 231 1

በህይወቴ በዘመኔ ደስ የሚለኝ ለኔ በወንጌል ማመኔ
ሕይወቴ ሲመራ ጌታ በቃልህ
ጣፋጭ ይሆን ነበር ሲያድሰኝ ፍቅርህ
ያንተ ጸጋ ጌታ ስለበዛልኝ
ጨለማው ተገፎ ብርሃንህ መራኝ
ወዴት እሄዳለሁ የእጅህ ጥበብ ሆኜ
ፍቅርህ እያደሰኝ ሞተህልኝ ድኜ
ምን አይነት መውደድ ነው ለኔ አንተ ያለህ
ምን ይከፈለዋል ለፍፁሙ ፍቅርህ
ምን አይነት መውደድ ነው አንተ ለኔ ያለህ
ምን ይከፈለዋል ለፍፁሙ ፍቅርህ
ደጅህ ላይ ተጥዬ ደጅህ ላይ ልሙት
ቃልህን ልጠብቅ በፍፁም ፍርሃት

እግዚአብሔር ሆይ (ዘማሪ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
እግዚአብሔር ሆይ እወድሃለሁ
ስለ ስምህ እቃጠላለሁ
ፍቅርህ እኔን ይመስጠኛል
እንደ እግዚአብሔር ከየት ይገኛል
ዓለም ሁሉ በጠላኝ ጊዜ
ስንገላታ ይዞኝ ትካዜ
አንተ ከእኔ አልተለየህም
እግዚአብሔር ሆይ ወደር የለህም
አዝ...
ሳኦል እኔን ሲያሳድደኝ
ጎልያድም ሲዝትብኝ
ግርማ ሆነህ ከፊቴ የቆምክ
እግዚአብሔር ሆይ ስምህ ይባረክ /2/
አዝ...
ሞቷል ብለው ቀብረውኝ ሰዎች
ምስኪን ሆኜ ሳይኖረኝ አንዳች
ከመቃብር ቆፍሮ አወጣኝ
አይዞህ ብሎ አምላኬ አጽናናኝ
አዝ...
ሀሳብህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል
ለዘለዓለም ያበራልሃል
ታማኝ ወዳጅ እርሱ ነውና
ሰላም ይሙላ ለእርሱ ተውና
አዝ...

የሰርግ መዝሙሮች

ሙሽራው ሙሽራ (የሠርግ)

ቅኝት- ስለቸርነትህ

ሙሽራው ሙሽራ /2/
እጹብ ነው ደስታው
ሙሽራው ሙሽራ
ሙሽራዋ ሙሽራ/2/
እጹብ ነው ደስታዋ
ሙሽራዋ ሙሽራ
እንደ አደይ አበባ ሙሽሮች ፈክታችሁ
በለምለም መስክ ያለ ፍሬ መሰላችሁ
ልክ እንደ ጨረቃ እንደ ሰማይ ፀሀይ
መልካሙ ሥራችሁ በራ በአደባባይ
አዝ.....
ካባዋን ደርባ በጥበቧ ላይ
የተዋህዶ ልጅ ደምቃ ስትታይ
በቤተክርስቲያን ሥርዓት በማደጓ
ይኸው መሠከረ የሙሽሪት ወጓ
አዝ.....
መልካም ሥነ ምግባር ፍቅር የከበበህ
የእመብርሃን ልጅ አቤት ማማርህ
ከመቼውም ይበልጥ ዛሬ ተውበሃል
የአማኑኤል ግርማ ዙሪያህን ከቦሀል
የእመቤቴ ፀዳል በእውነት አምሮብሀል
አዝ.....
መልካም ሥነ ምግባር ፍቅር የከበበሽ
የእመብርሃን ልጅ አቤት ማማርሽ
ከመቼውም በላይ ዛሬ ተውበሻል
የአማኑኤል ግርማ ዙሪያሽን ከቦሻል
የእመቤቴ ፀዳል በእውነት አምሮብሻል

የሀብከ ዮም (የሠርግ ይልማ ኃይሉ)

ቅኝት -
የሀብከ ዮም የሀብከ መድኃኔዓለም /2/
እድሜ ማቱሳላ ወአብርሃም /2/
ይስጣችሁ ዛሬ ይስጣችሁ መድኃኔዓለም/2/
እንደ ማቱሳላ እንደ አብርሃም /2/
አዝ.....
በቅዱስ ጋብቻ ሙሽሮች ተወሰናችሁ /2/
ክርስቶስ ተገኝቷል በመሀከላችሁ /2/
የድንጋዮቹን ጋን ወይኑን ወይኑን ሊመላበት/2/
ከድንግል ማርያም ጋር ተገኝቷል ከዚህ ቤት/2/
አዝ.....
ደስታውን አይቶ አምላክ ፍፁም ተደስቷል/2/
ሊባርካችሁም እጆቹን ዘርግቷል /2/
በህይወታችሁም ፍቅር ፍቅር ቅመም ሆኖ/2/
ትህትናን ይስጣችሁ እግዚአብሔር በቶሎ/2/
አዝ.....
ሠርጋችሁ እንዲሆን ደስታ ፍቅር የሞላበት
በህይወታችሁ ውስጥ ክርስቶስ ይግባበት
በህይወታችሁ ውስጥ አምላክ ይኑርበት
አዝ.....

የበረከት ፍሬ በጸጋው እንዲበዛላችሁ /2/
ዛሬ ተደሰቱ አምላክን ይዛችሁ /2/
እራስን በመግዛት እውቀት እውቀት ተሞልታችሁ
ዛሬ ተደሰቱ አምላክን ይዛችሁ /2/
አዝ.....
በሥጋ ወደሙ እግዚአብሔር ስለመረጣችሁ
የመንፈስ ቅዱስም ህፃናቶች ናችሁ /2/

እጹብ ድንቅ ስራ

እጹብ ድንቅ ስራ/2/
በእውነት የታደለ የእግዚአብሄር ሙሽራ
በእውነት የታደለች የእግዚአብሄር ሙሽራ
ነፍሳችሁ በሰማይ ርግብ ትመስላለች
ከመላእክት ጋራ ዛሬ ዘምራለች/2/
እልል እልል በሉ ክርስቲያኖች ሁሉ
ያበራ ጀመረ ሙሽራው ፀዳሉ
ታበራ ጀመረ ሙሽሪት ፀዳሏ
አዝ...
ከክርስቶስ ፍቅር እንዴት ይርቃል ሰው
ሥጋና ደሙን ሳይሳሳ ለሰጠው/2/
የመንፈስ ቅዱስ ሕፃናት በመሆን
በስጋወደሙ መቀደስ አለብን/2/
አዝ...
በእግዚአብሔር ተባርኮ የመኖር ምስጢር
የዘላለም ሕይወት ይሰጣል ፍቅር/2/
ሥጋውን ፍሪዳ ደሙን መጠጥ አድርጎ
ሰጥቶናል አማኑኤል ሕይወቱን ሰውቶ

ትዌድሶ

ትዌድሶ መርዓት ወትብሎ/2/
ወልድ እኁየ ቃልከ አዳም/4/